# መጽሐፈ ፡ ሄኖክ ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ ፤ ሕግ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የዘነጉ ፡ ሰዎችንና ፡
ክፉዎችን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለማራቅ ፡ መከራ ፡
በታዘዘበት ፡ ቀን ፡ ደጋግ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ያላ
ቸው ፡ ጻድቃንና ፡ የተመረጡ ፡ ሰዎችን ፡ እን
ዳመሰገነ ፡ ሄኖክ ፡ ያመነበት ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።
፪ ፤ ሄኖክ ፡ ተናገረ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ዓይኑ ፡ ልቡናየ ፡
ተገልጦ ፡ ሳለ ፡ እውነተኛ ፡ ሰው ፡ የምሆን ፡
ጽድቁ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተገኘልኝ ፡
እኔ ፡ ተናገርኩ ፡ በሰማይ ፡ ያሉ ፡ መላእክት ፡
ያሳዩኝ ፡ ዕኑዕ ፡ ራዕይን ፡ ከነሳቸው ፡ ዘንድ ፡ የሰ
ማሁትንም ፡ ሁሉ ፡ አየሁ ፡ እኔ ፡ ያየሁትም ፡
ራዕይ ፡ እንዳይቀር ፡ አወቅሁ ፡ አለ ።
፫ ፤ ይህም ፡ የሚደረገው ፡ በሥረኛው ፡ ትውልድ ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ በሰባተኛው ፡ ትውልድ ፡ አይደ
ለም ።
፬ ፤ የደናግልን ፡ ነገር ፡ የሕጋውያንንም ፡ ነገር ፡ ከማ
ደሪያው ፡ ከወጣ ፡ ገናናና ፡ ዕኑ ፡ ከሆነ ፡ ከፈጣሪ ፡
ጋራ ፡ ተናገርኩ ።
፭ ፤ አራቱን ፡ ማዕዘን ፡ ዓለም ፡ ከፈጠረ ፡ ከማደሪ
ያውም ፡ ወጥቶ ፡ ሕግ ፡ ለመሥራት ፡ በደብረ ፡
ሲና ፡ ከሚቆም ፡ ከሰማይም ፡ ወርዶ ፡ በእስራ
ኤል ፡ መከከል ፡ በከሃሊነቱ ፡ ከሚገለጥ ፤ ሁሉ ፡
ከሚፈራው ፡ ለምስጋና ፡ የሚተጉ ፡ መላእክ
ትም ፡ ከሚነዋወጡለት ፡ ከጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡

ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ከሚፈሩት ፡ ሰኑ ፡ መንቀጥ
ቀጥም ፡ ከሚንቀጠቀጡለት ፡ ረጃጅሞች ፡ ተራ
ሮች ፡ ከሚደነግጡለት ÷ የሙሴ ፡ አሮንን ፡ ረጃ
ጅሞች ፡ ከረብታዎችም ፡ ከሚዋረዱለት ፡ (ሰበ ፡
ሊቃናት ፡) ሰምም ፡ ከእሳት ፡ የተነሣ ፡ እንዲቀ
ልጥ ÷ እንደዚያ ፡ ከሚቀልጡለት ፡ ምድርም ፡
በማየ ፡ አይኅ ፡ ከምትሰጥምለት ፡ በምድርም ፡
ያለ ፡ ሁሉ ፡ ከሚጠፋለት ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ተነጋገ
ርሁ ።
፯፡ ፍርዱም ፡ በኃጥአን ፡ ሁሉ ፡ በጻድቃንም ፡ ላይ ፡
ሁሉ ፡ ይደረጋል ።
፰፡ ለወዳጆቹ ፡ ግን ፡ ፍቅር ፡ አንድነትን ፡ ያደርግላ
ቸዋል ፡ (ሒገውያን ፡) የተመረጡ ፡ ሰዎችንም ፡
ይጠብቃቸዋል ፡ ( ደናግል ፡ ) ለነሱም ፡ ይቅ
ርታ ፡ ይደረግላቸዋል ።
፱፡ ሁሉም ፡ የአምላክ ፡ ገንዘቦች ፡ ይሆናሉ ፡ በክብ
ርም ፡ ይከናወናሉ ፡ ይከብራሉ ፡ የአምላክ ፡ ብር
ሃንም ፡ ያበራላቸዋል ።
፲፡ ለወዳጆቹ ፡ ይፈርድላቸው ፡ ዘንድ ፡ እነሆ ፡
ከብዙ ፡ መላእክት ፡ ጋራ ፡ ይመጣል ፡ ሕገ ፡ እግ
ዚአብሔርንም ፡ የዘነጉ ፡ ሰዎች ፡ ያጠፋቸዋል ፤
ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የዘነጉ ፡ ሰዎችና ፡ ኃጥ
አን ፡ በሱ ፡ ፈጸመው ፡ ስለ ፡ አደረጉት ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ ሥጋዊ ፡ ደማዊን ፡ ሁሉ ፡ ይወቅሰል ።
፲፩፡ በሰማይ ፡ የሚኖሩ ፡ ፀሐይ ፡ ጨረቃ ፡ ሥራቸ
ውን ፡ እንዳይለወጡ ፡ ሁሉም ፡ እንዲወጣ ፡
እንዲገባ ፡ በየዘመኑ ፡ ሁሉም ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፡
ከዘዛቸውም ፡ ትእዛዛቸው ፡ እንዳይተላለፉ ፡
በሰማይ ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አወቅሁ ፡
ተረዳሁ ።
፲፪፡ ምድርን ፡ እይዋት ፡ ከመጀመሪያው ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ በሷ ፡ ላይ ፡ ከሚሠ
ራው ፡ ሥራ ፡ የተነሣ ፡ የሚታይ ፡ የአምላክ ፡
ሥራው ፡ ሁሉ ፡ እንዳይለወጥ ፡ ልብ ፡ አድርጉ ።
፲፫፡ በጋውን ፡ ክረምቱን ፡ እዩት ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡
ውሀን ፡ እንደ ፡ ተመላች ፡ ደመናውም ፡ ጤዛ
ውም ፡ ዝናቡም ፡ በሷ ፡ ላይ ፡ አርፈውባት ፡
እንዲኖሩ ፡ እዩ ።
፲፬፡ ከብሉይ ፡ ክረምት ፡ ጀምሮ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡
ክረምት ፡ በኋላ ፡ እስከሚመጣ ፡ እስከ ፡ አዲስ ፡
በጋ ፡ ድረስ ፡ ከሚቆዩ ፡ ቅጠላቸው ፡ ከማይረ
ግፍ ፡ ከሥራ ፡ አራት ፡ እንጨቶች ፡ በቀር ፡ እን
ጨቶች ፡ ሁሉ ፡ ምጥጥ ፡ ድርቅ ፡ ብለው ፡ እን
ዲታዩ ፡ ቅጠላቸውም ፡ ሁሉ ፡ እንዲረግፍ ፡
አወቅሁ ፡ ተረዳሁ ።
፲፭፡ አስቀድሞ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ፀሐይ ፡ እንዲጸና ፡
ዳግመኛም ፡ የበጋውን ፡ ወራት ፡ ተረዳሁ ።
፲፮፡ እናንተ ፡ ግን ፡ የፀሐይ ፡ ዋዕይ ፡ ስለ ፡ ጸና ፡ የድ
ንኳን ፡ ጥላና ፡ የዛፍ ፡ ጥላን ፡ ትፈልጋላችሁ ፡
ምድርም ፡ ከዋዕዩ ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ ትቃጠላ
ለች ።
፲፯፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ተቃጠለች ፡ ምድርን ፡ ድን
ጋይዋንም ፡ መርገጥ ፡ አትችሉም ።
፲፰፡ እንጨቶች ፡ ሁሉ ፡ በቅጠል ፡ ልምላሜ ፡ እንዲ
ሸፈኑ ፡ ኋላም ፡ እንዲያፈሩ ፡ አወቅሁ ።
፲፱፡ ለዘላለሙ ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ የሚኖር ፡ እሱ ፡ እነ
ዚህን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ፈጠረላችሁ ፡ የነዚህን ፡
ሁሉ ፡ ነገር ፡ ፈጽማችሁ ፡ እወቁ ።
፳፡ በያመቱ ፡ የሚሆነው ፡ ሥራውም ፡ በፊቱ ፡ ነው ፡
ፍጥረቱም ፤ ሁሉ ፡ ለሱ ፡ ይገዛሉ ፡ ፈጣሪ ፡ እንደ ፡
ሠራው ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ሲደረግ ፡ ይኖራል ፡
እንጂ ፡ ከወሰነላቸው ፡ አይነዋወጡም ።
፳፩፡ ፈሳሾችና ፡ ባሕሮችም ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ ሥራ
ቸውን ፡ እንዲጨርሱ ፡ እወቁ ።
፳፪፡ እናንተ ፡ ልበ ፡ ድንጋዮች ፡ ከሥራው ፡ ወጣ
ችሁ ፡ እንጂ ፡ በገናንነቱ ፡ ላይ ፡ በረከሰች ፡ በና
ንተ ፡ አፍ ፡ ታላላቅ ፡ ጽኑ ፡ ሐሜትንም ፡ አማች
ሁት ፡ እንጂ ፡ እናንተ ፡ በሕጉ ፡ አልጸናችሁም ፡
የጌታችሁንም ፡ ትእዛዝ ፡ አላደረጋችሁም ።
፳፫፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ አትደረግላችሁም ፡ ስለዚህ ፡
ነገር ፡ እናንተም ፡ ዘመናችሁን ፡ ትረግማላችሁ ፡
በሕይወት ፡ የምትኖሩባቸውንም ፡ ዘመኖች ፡
ታጣላችሁ ፤ በናንተም ፡ የዘላለም ፡ መርገም ፡
ይበዛባችኋል ፡ ይቅርታም ፡ አይደረግላችሁም ።
፳፬፡ በዘላለም ፡ መርገም ፡ ተይዛችሁ ፡ በዚያም ፡
ወራት ፡ የናንተን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ለጻድቃን ፡
ሁሉ ፡ ትሰጣላችሁ ፡ ኃጥአን ፡ ደቂ ፡ መዘሙር
ዩቻችሁ ፡ ዘወትር ፡ እናንተን ፡ ይረግማሉ ፡
ከኃጥአን ፡ ደቂ ፡ መዘሙርዩቻችሁም ፡ ጋራ ፡
እናንተን ፡ መከራው ፡ አንድነት ፡ ያገኛችኋል ።
፳፭፡ ለተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ፍቅር ፡
አንድነትና ፡ ተድላ ፡ ደስታውም ፡ ይደረግላቸ
ዋል ፡ (ደናግል) ።
፳፮፡ እነሱ ፡ ግን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ይወርሷ
ታል ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለዘነጋችሁ ፡ በና
ንተስ ፡ መርገም ፡ ይሆንባችኋል ።
፳፯፡ ለተመረጡም ፡ ሰዎች ፡ ጥበብ ፡ ቢሰጣቸው ፡
እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ይድናሉ ፡ ጥበብ ፡ ያላቸው ፡
እነሱም ፡ ለሱ ፡ ይገዛሉ ፡ እንጂ ፡ በመዘንጋ
ትም ፡ ሆኖ ፡ በትቢትም ፡ ሆኖ ፡ ዳግመኛም ፡
አይበድሉም ።
፳፰፡ ዳግመኛም ፡ አይበድሉም ፡ በሕይወት ፡ በሚኖ
ሩበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተው ፡
አይፈረድባቸውም ፡ በሕይወት ፡ የኖሩበትን ፡
ቍጥር ፡ ይጨርሳሉ ፡ እንጂ ፡ በመቅሠፍትና ፡
በመዓትም ፡ አይቀሠፉም ።
፳፱፡ በሕይወት ፡ የሚኖሩበት ፡ ወራት ፡ በፍቅር ፡
አንድነት ፡ ይበዛል ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ የሚኖ
ሩባቸውም ፡ ዘመኖች ፡ በሕይወታቸው ፡ በሚኖ
ሩበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ለዘላ
ለም ፡ በሚሆን ፡ ፍቅር ፡ አንድነትም ፡ ይበዛሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ከበዙ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ።
፪፡ በዚያ ፡ ወራትም ፡ መልክ ፡ መልካሞች ፡ ደመ
ግቡዎች ፡ ልጆች ፡ ተወለዱላቸው ፡ በደብር ፡
ቅዱስ ፡ ያሉ ፡ ደቂቀ ፡ ሴትም ፡ እነሱን ፡ አይ
ተው ፡ ወደዷቸው ።

፫፡ እስበሳቸውም ፡ ኑ ፡ ለኛ ፡ ከቃየል ፡ ልጆች ፡
ሴቶችን ፡ እንምረጥ ፡ ለኛ ፡ ልጆችን ፡ እንወ
ለድ ፡ አሉ ።
፬፡ አለቃቸው ፡ የሆነ ፡ ስማዝያ ፡ እኔስ ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡
ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ አትወዱም ፡ ብዬ ፡ እነሆ ፡ እፈ
ራለሁ ፡ የዚችም ፡ የዐናች ፡ ኃጢአት ፡ ፍዳ ፡
እምቀበል ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ እሆናለሁ ፡ አላቸው ።
፭፡ ይችን ፡ ምክር ፡ እንዳንለውጣት ፡ ይችንም ፡
ምክር ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ እንድናደርጋት ፡ ሁላችን ፡
ተለያይተን ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ ማላን ፡ እንማ
ማል ፡ ብለው ፡ ሁሉም ፡ መለሱለት ።
፮፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ ሁሉም ፡
እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተለያይተው ፡ ማሉበት ፡
ሁሉም ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሆኑ ።
፯፡ አርዲስ ፡ ወደሚባል ፡ በታም ፡ ወረዱ ፡ ይኸ
ውም ፡ የአርሞንኤም ፡ ተራራ ፡ ራስ ፡ ነው ፡
እርስበርሳቸው ፡ ተለያይተው ፡ ምለውበታልና ፡
የአርሞንኤምንም ፡ ተራራ ፡ በማላ ፡ ተራራ ፡
ብለው ፡ ጠሩት ።
፰፡ አለቆቻቸውም ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ መጀ
መሪያው ፡ አለቃቸው ፡ ስማዝያ ፡ ነው ፡ ሁለተ
ኛው ፡ ዑራኪብራምኤል ፡ ሦስተኛው ፡ አኪቢ
ኤል ፡ አራተኛው ፡ ጣምኤል ፡ አምስተኛው ፡
ራሙኤል ፡ ስድስተኛው ፡ ዳንኤል ፡ ሰባተ
ኛው ፡ ኢዜቃኤል ፡ ስምንተኛው ፡ ሱሩቃያል ፡
ዘጠኘኛው ፡ አስኤል ፡ አሥረኛው ፡ አርሞርስ ፡
አሥራ ፡ አንደኛው ፡ በጥርኤል ፡ አሥራ ፡ ሁለ
ተኛው ፡ አናንኤል ፡ አሥራ ፡ ሦስተኛው ፡
ዘቂቢ ፡ አሥራ ፡ አራተኛው ፡ ሳምሳፒኤል ፡
አሥራ ፡ አምስተኛው ፡ ስርትኤል ፡ አሥራ ፡ ስድ
ስተኛው ፡ ጡሩኤልዮም ፡ አሥራ ፡ ሰባተኛው ፡
ያኤል ፡ አሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ አራዝያል ፡ ነው፤
የሁለቱ ፡ መቶ ፡ አለቆች ፡ አለቆቻቸው ፡ እኒህ ፡
ናቸው ፡ ሌሎችም ፡ ሁሉ ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ አሉ ።
፱፡ ከነሳቸው ፡ ሚስት ፡ አገቡ ፡ ሁሉም ፡ ለየራሱ ፡
አንዳንዲቱን ፡ መረጠ ።
፲፡ ወደነሱም ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ ጀመሩ ፡ ከነሱም ፡
ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆኑ ፡ (ደረሱባቸው ።
፲፩፡ ሟርትን ፡ ምታት ፡ ማሳየትን ፡ አስተማሩዋቸው ፡
ሥር ፡ መማስን ፡ ቅጠል ፡ መበጠስንም ፡ አመለ
ከቷቸው ።
፲፪፡ እነሱም ፡ ፀንሰው ፡ረጃጅሞች ፡ አርበኞች ፡ ልጆ
ችን ፡ ወለዱ ፡ ቁመታቸውም ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡
ሺህ ፡ ክንድ ፡ ነው ።
፲፫፡ አባት ፡ እናቶቻቸው ፡ እነሱን ፡ መመገብ ፡ እስ
ኪሳናቸው ፡ ድረስ ፡ ደርሰው ፡ እነዚህ ፡ ሰው ፡
የደከመበትን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ በሉ ።
፲፬፡ ረጃጅሞቹም ፡ ልጆች ፡ አባት ፡ እናቶቻቸውን ፡
ይበሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መብላት ፡ ተመለሱ ።
፲፭፡ አውሬዎችንና ፡ ወፎችን ፡ ዓሣዎችንና ፡ ተሐዋ
ስያንንም ፡ እያመለኩ ፡ ይበድሉ ፡ ጀመር ።
፲፮፡ እርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ሥጋቸውን ፡ ተባሉ ፡
ከሷም ፡ ደምን ፡ ጠጡ ።
፲፯፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ ምድር ፡ በደለኞችን ፡ ከሰሰቻ
ቸው ፡ (ትሑታኑን ፡ ልዑላኑን) ።
አዛዝዔልም ፡ ለሰዎች ፡ ሾተልና ፡ ሰይፍ ፡ መሥ ፲፰፡
ራትን ፡ ጋሻ ፡ መሰጐድንም ፡ ጥሩር ፡ መሥራ
ትንም ፡ አስተማራቸው ።
ከነሱ ፡ በታች ፡ የሚሆኑ ፡ ሥራቸውንም ፡ ሌላ ፡ ፲፱፡
ጌጽና ፡ አምባሮችን ፡ ቅንድብ ፡ መሽለልንና ፡
ዓይን ፡ መኳልን ፡ ከተመረጠና ፡ ከከበረ ፡ ዕንቍ ፡
ሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ዕንቍንም ፡ እንሶስላ ፡ መሞ
ቅን ፡ ሁሉ ፡ የዓለምንም ፡ ለውጥ ፡ አሳይዋቸው ፡
(ፈረሱን ፡ በቅሎውን ፡ ሰው ፡ ማድረግ ) ።
ዕኑ ፡ በደል ፡ ብዙ ፡ ሰሰንም ፡ ተደረገ ፤ ሳቱ ፡ ፳፡
ሰሰኑ ፡ ሥራቸውም ፡ ሁሉ ፡ ጠፋ ።
አሚዛራክ ፡ ጋኔን ፡ መሳብን ፡ ምታት ፡ ማሳየ ፳፩፡
ትን ፡ ሥር ፡ መማስን ፡ ቅጠል ፡ መበጠስንም ፡
ሁሉ ፡ አስተማረ ፡ አርማሮስም ፡ ጋኔን ፡ መሳ
ብን ፡ አስተማረ ።
በረቅእልም ፡ ከከብ ፡ መቍጠርን ፡ አስተማረ ። ፳፪፡
ከከብኤልም ፡ ምልክት ፡ ማሳየትን ፡ አስተማረ ። ፳፫፡
ጥሞኤልም ፡ ከከብ ፡ መቍጠርን ፡ አስተማረ ። ፳፬፡
አስራድኤልም ፡ የጨረቃን ፡ አካሄድ ፡ አስተ ፳፭፡
ማረ ።
በሰዎችም ፡ ጥፋት ፡ ሰዎች ፡ ጮሁ ፡ ቃላቸውም ፡ ፳፮፡
ወደ ፡ ሰማይ ፡ ደረሰ ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ ሚካኤልና ፡ ገብርኤል ፡ ሱርኤልና ፡ ፳፯፡
ሱርያል ፡ በሰማይ ፡ ሆነው ፡ ጐበኙ ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ በግፍ ፡ የፈሰሰ ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ ፳፰፡
ደምን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚሠራ ፡ ግፉን ፡ ሁሉ ፡
አዩ ።
እስበሳቸውም ፡ የሰዎችን ፡ የጩኸታቸውን ፡ ፳፱፡
ቃል ፡ ተናገሩ ። ምድርም ፡ ብቻዋን ፡ ቀርታ ፡
(ትሑታኑ ፡ ) ጨኸቷ ፡ ከሰማይ ፡ በር ፡ እስከ
ደርስ ፡ ድረስ ፡ ጮኸች ።
አሁንም ፡ በሰማይ ፡ ያላችሁ ፡ መላእክት ፡ የሞቱ ፡ ፴፡
ሰዎችን ፡ ነፍሳት ፡ ልመናችንን ፡ ወደ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ አግቡልን ፡ እናንተን ፡ ይከሳሉ ፡ አሉ ።
ለነገሥ ፡ ንጉሣቸውን ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፡ የጌ ፴፩፡
ቶች ፡ ጌታ ፡ አንተ ፡ ነህና ፡ ከምላኮች ፡ በላይ ፡
ያለህ ፡ አምላክም ፡ አንተ ፡ ነህና ፡ ከነገሥታ
ትም ፡ በላይ ፡ ያለህ ፡ ንጉሥ ፡ አንተ ፡ ነህና ።
የጌትነትህም ፡ ዙፋን ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ ፴፪፡
ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ ስምህም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡
ዘመን ፡ ለዘላለሙ ፡ የከበረ ፡ የተመሰገነ ፡ ነውና ፡
የከበርህ ፡ የተመሰገንህ ፡ ነህና ።
ሁሉንም ፡ የፈጠርህ ፡ አንተ ፡ ፈጥረህ ፡ የሁ ፴፫፡
ሉም ፡ ሥልጣን ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፡ (በጅህ)
በፊትህም ፡ ሁሉ ፡ የተገለጠ ፡ ነውና ።
አንተም ፡ ሁሉን ፡ መርምረህ ፡ ታውቃለህና ፡ ፴፬፡
ካንተም ፡ ሊሰወር ፡ የሚቻለው ፡ የለምና ።
አዛዝኤል ፡ ያደረገውን ፡ እዩ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ፴፭፡
ግፉን ፡ ሁሉ ፡ እንዳስተማረ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
የተሰወሩትን ፡ ሁሉ ፡ በሰማያት ፡ የሚሠሩትን ፡
እንዳስተማረ ፡ እያ ፡ አሉት ።
ከሱ ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ ያሉትን ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ ፴፮፡
አንተ ፡ ሥልጣንን ፡ የሰጠኸው ፡ ስማዝያም ፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



ምታት ፡ ማሳየትን ፡ እንዳስተማረ ፡ እይ ።
፴፯፡ አንድ ፡ ሁነውም ፡ ወደ ፡ ቃየል ፡ ልጆች ፡ ሄዱ ፡
በለዚህም ፡ ሴቶች ፡ ጋራ ፡ ደረሱባቸው ፡ ረከሱ ፡
አሊህንም ፡ ኃጢአቶች ፡ ገለጡላቸው ።
፴፰፡ ሴቶችም ፡ ረዓጅም ፡ ልጆችን ፡ ወለዱ ፡ በዚ
ህም ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ግፍንና ፡ ደምን ፡ ተመ
ላች ።
፴፱፡ አሁንም ፡ ከሥጋቸው ፡ የተለዩ ፡ ነፍሳት ፡ እነሆ ፡
ይጮሃሉ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ እስኪደርስ ፡ ድርስ ፡
ይከሳሉ ።
፵፡ ጩኸታቸውም ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ደረሰ ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ የሚሠራው ፡ ግፍ ፡ ከመገለጡ ፡ የተነሣ ፡
መዳን ፡ አይችሉም ።
፵፩፡ ይህንንም ፡ ሳይደረግ ፡ አንተ ፡ ታውቀዋለህ ፡ ይህ
ንንም ፡ የባለጸጎችንና ፡ የድሆችንም ፡ ነገር ፡
አንተ ፡ ታውቀዋለህ ።
፵፪፡ የምትነግረንም ፡ ነገር ፡ የለም ፡ በዚህስ ፡ ነገር ፡
ምን ፡ እናደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ ልዑል ፡ ገናና ፡ የከበረ ፡ ፈጣሪ ፡
ተናገረ ፡ ወደ ፡ ላሜክ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኖኅም ፡
ሱርያልን ፡ ላከው ።
፪፡ በኔ ፡ ስም ፡ አምነህ ፡ ራስህን ፡ ከማየ ፡ አይህ ፡
ሰውር ፡ በለው ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ትጠፋለችና ፡
የሚመጣ ፡ የመከራውን ፡ መጨረሻ ፡ ግለጽለት ፡
አለው ።
፫፡ በዚችም ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የጥፋት ፡ ውሀ ፡
ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ አለው ፡ በውስጧም ፡ ያለው ፡
ሁሉ ፡ ይጠፋል ።
፬፡ አሁንም ፡ እሱ ፡ ይሸሽ ፡ ዘንድ ፡ ልጁም ፡ በዓ
ለሙ ፡ ሁሉ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ አስተምረው ፡
አለው ።
፭፡ ዳግመኛም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሩፋኤልን ፡ አዛዝ
ኤልን ፡ እጁን ፡ እግሩን ፡ አስረህ ፡ በጨለማ ፡
ውስጥ ፡ አግዘው ።
፮፡ በዱዳኤል ፡ ያለች ፡ ምድረ ፡ በዳዋንም ፡ ክፈ
ታት ፡ እሱንም ፡ በዚያ ፡ በጨለማው ፡ ውስጥ ፡
ጣለው ፡ በላዩም ፡ እንክብል ፡ እንክብል ፡ ሻሮ ፡
ሻሮ ፡ ድንጋዮችን ፡ ግጠምበት ።
፯፡ ጨለማንም ፡ አልብሰው ፡ በዚያ ፡ ለዘላለሙ ፡
ይኑር ፡ ብርሃንን ፡ እንዳያይ ፡ ፍርድ ፡ በሚደረ
ግበት ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ እንዲ
ሄድ ፡ ፊቱን ፡ በጨለማ ፡ ሸፍነው ፡ አለው ።
፰፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ያጠፏት ፡ ምድርንም ፡ እንዳድ
ናት ፡ ምድርን ፡ እንዳነፃት ፡ የምድርንም ፡ ንጽ
ሕና ፡ ተናገር ።
፱፡ ለኃጢአት ፡ የሚተጉ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ በገደሉ
በት ፡ ለልጆታቸውም ፡ በስተማሩት ፡ ኃጢአት ፡
ሁሉ ፡ ምሥጢር ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ አይ
ጠፉም ።
፲፡ በአዛዝኤል ፡ ሥራ ፡ ትምህርትም ፡ ምድር ፡
ሁሉ ፡ ጠፋች ፡ የሰውንም ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡
በሱ ፡ ጻፍበት ፡ አለው ።

ገብርኤልንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ተናቁ ፡ ፲፩፡
ሰዎችና ፡ ወዳመንዝራዎች ፡ ወደ ፡ ዘማም ፡
ልጆች ፡ ሂድ ፡ ያመንዝራይቱንም ፡ ልጆች ፡
ለኃጢአት ፡ የሚተጉ ፡ የሴትንም ፡ ልጆች ፡
ከሰው ፡ ለይተህ ፡ አጥፋቸው ፡ አለው ።
እስበሳቸው ፡ ተቀራደው ፡ ወደሚጠፉበት ፡ ፲፪፡
በታ ፡ አስወጥተህ ፡ ስደዳቸው ፡ የዘመን ፡ ርዝ
መት ፡ የላቸውምና ፡ እነሱ ፡ ራሳቸው ፡ በሰ
ይፍ ፡ ተቀራደው ፡ ያልቃሉ ።
የዘላለም ፡ ሕይወትን ፡ ሊኖሩ ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋ ፲፫፡
ሉና ፡ ከነሱ ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡
ዘመንን ፡ ሊኖር ፡ ይመስለኛልና ፡ ሁሉም ፡ ይለ
ምንሃል ፡ ላባቶቻቸው ፡ ለነሱም ፡ ፍቅር ፡ አን
ድነት ፡ አይደረግላቸውም ። ( አስታርቀን ፡
ብለው ፡ )
ሚካኤልንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሂደህ ፡ ለስም ፲፬፡
ያዛ ፡ ንገረው ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ላሉ ፡ በኃጢአታ
ቸው ፡ ሁሉ ፡ ከለሳቸው ፡ ጋራ ፡ ይጠፉ ፡ ዘንድ ፡
ከሴቶችም ፡ ጋራ ፡ ለተባበሩ ፡ ሰዎች ፡ ንገራ
ቸው ፡ አለው ።
ልጆቻቸውም ፡ ተቀራደው ፡ ካለቁ ፡ በኋላ ፡ እነ ፲፭፡
ሱም ፡ የሚወዷቸው ፡ የልጆቻቸውን ፡ ጥፋት ፡
ካዩ ፡ በኋላ ፡ የጥፋታቸው ፡ መጨረሻና ፡ ፍር
ዳቸው ፡ እስከሚደረግበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የዘ
ላለምም ፡ ፍርድ ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ሰባ
ውን ፡ ትውልድ ፡ በምድር ፡ ኮረብታ ፡ በታች ፡
አሥረህ ፡ አግዛቸው ፡ አለው ።
በዚያም ፡ ወራት ፡ በጭንቅ ፡ ሊኖሩ ፡ በእሳቱ ፡ ፲፮፡
በታች ፡ ወዳለው ፡ በታ ፡ ይወስዷቸዋል ፡ በግ
ዞት ፡ ቤትም ፡ ለዘላለሙ ፡ ተዘግቶባቸው ፡ ይኖ
ራሉ ።
ያን ፡ ጊዜም ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ፲፯፡
ድረስ ፡ መላከቻው ፡ አንድነት ፡ ይቃጠላል ፡
ይጠፋል ፡ እስከ ፡ ልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ መጨ
ረሻ ፡ ድረስም ፡ ይጋዛሉ ።
ሰዎችን ፡ በድለዋቸዋልና ፡ ዋዛ ፡ የሚወዱ ፡ ፲፰፡
ሰዎችን ፡ ሁሉ ፡ ለኃጢአት ፡ የሚተጉ ፡ የደቂቀ ፡
ሴት ፡ ልጆችንም ፡ አጠፋቸው ፡ ግፉንም ፡ ሁሉ ፡
ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አጥፋ ፡ ክፉ ፡ ሥራም ፡ ሁሉ ፡
ይጥፋ ፡ የቀና ፡ ሕግንና ፡ እውነት ፡ ሥራን ፡ የሚ
ሠራ ፡ ኖኅም ፡ ለዘላለሙ ፡ ይገለጥ ።
ሥራውም ፡ ሁሉ ፡ ለበረከት ፡ ይሆናል ፡ ሕጎጋ ፲፱፡
ቱም ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ይፀናሉ ።
አሁንም ፡ ደጋጎች ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብ ፳፡
ሔር ፡ ይገዛሉ ፡ ሺህ ፡ ልጆችንም ፡ እስኪወ
ልዱ ፡ ድረስ ፡ ደኅነኞችን ፡ ይሆናሉ ። (ፍጹም ፡
ልጅ ፡)
የሕፃንነታቸውን ፡ የሽምግልናቸውንም ፡ ወራት ፡ ፳፩፡
ሁሉ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ይጨርሳሉ ።
በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ በውነት ፡ ፳፪፡
ትታረሳለች ፡ በሁለመናዋም ፡ እንጨቶችን ፡
ትተክላለች ፡ በረከትንም ፡ ትመላለች ።
ተድላ ፡ ደስታ ፡ ያለባቸው ፡ እንጨቶችም ፡ ፳፫፡
ሁሉ ፡ በሷ ፡ ላይ ፡ ይተከላሉ ፡ ወይኖችም ፡ በሷ ፡

ይተክላሉ ፡ በሷም ፡ ላይ ፡ የሚተክለው ፡ ወይን ፡
ሊያጠግብ ፡ ያፈራል ፡ በሷም ፡ የሚዘራው ፡
ዘር ፡ ሊያጠግብ ፡ ያፈሪ ኋ ።
፳፩ አንዷቱም ፡ መስፈሪያ ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ ታፈራለች ፡
አንዷቱም ፡ መስፈሪያ ፡ ዘይት ፡ አሥር ፡ የዘይት ፡
ዓውድማን ፡ ትመላለች ።
፳፪ አንተ ፡ ግን ፡ ምድርን ፡ ከግፉ ፡ ሁሉ ፡ ከበደ
ሉም ፡ ሁሉ ፡ ከኃጢአቱም ፡ ሁሉ ፡ ከመበድ
ልም ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከሚሠራው ፡ ሁሉ ፡
ከሚያንድፈው ፡ ጣዖትም ፡ ሁሉ ፡ አንፃት ።
፳፫ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አጠፋቸው ፡ ከሰው ፡ የተወለዱ ፡
ልጆችም ፡ ሁሉ ፡ ደጋግ ፡ ሰዎችን ፡ ይሁኑ ፡
አሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ እኔን ፡ የሚያመልኩ ፡ እኔን ፡
የሚያመሰግኑ ፡ ይሁኑ ።
፳፬ ሁሉም ፡ ለኔ ፡ ይሰግዳሉ ፡ ምድርም ፡ ከጥፋት ፡
ሁሉ ፡ ከሚሠራውም ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ከተደ
ረገበትም ፡ መቅሠፍት ፡ ሁሉ ፡ ጭንቅ ፡ መከራ ፡
ሁሉ ፡ ትነፃለች ።
፳፭ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡
በሷ ፡ ጥፋት ፡ አመጣበት ፡ ዘንድ ፡ ዳግመኛ ፡
አላመጣበትም ።
፳፮ በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ በሰዎች ፡ ልጆች ፡ አዝ
መራቸው ፡ ላይና ፡ በትክልታቸው ፡ ላይ ወደ
ዚህ ፡ ዓለም ፡ ዝናሞችን ፡ አወርድላቸው ፡ ዘንድ ፡
በሰማዮች ፡ ያሉ ፡ በረከት ፡ የሚገኝባቸው ፡
ዳመናዎችን ፡ እከፍታለሁ ። (አዛለሁ ፡ )
፴ የቀና ፡ ነገርና ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
ወራት ፡ ሁሉ ፡ በልጅ ፡ ልጅም ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡
አንድ ፡ ሁነው ፡ ይኖራሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩ ከነገር ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ሄኖክ ፡ ተሠወረ ።
፪ ከሰውም ፡ ልጆች ፡ በተሠወረበት ፡ ቦታ ፡ ሳለ ፡
የሚያውቀው ፡ አልነበረም ፡ ይሞት ፡ ይድንም ፡
የሚያውቅ ፡ የለም ።
፫ ሥራውም ፡ ሁሉ ፡ በተሠወረበት ፡ ወራት ፡ በቅ
ዱሳኖቻቸው ፡ ከሚተጉ ፡ መላእክት ፡ ጋራና ፡
ከቅዱሳን ፡ ጋራ ፡ ነበር ።
፬ እኔም ፡ ሄኖክ ፡ ገናና ፡ ጌታን ፡ ባራቱ ፡ ማዕዘነ ፡
ዓለም ፡ የነገሠ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰግነው ፡
ጀመር ።
፭ ሕግን ፡ በሰው ፡ ልቡና ፡ የምጽፍ ፡ እኔን ፡ ሄኖ
ክንም ፡ ለቅዳሴያቸው ፡ የሚተጉ ፡ መላእክት ፡
እነሆ ፡ ይጠሩኛል ።
፮ ሕግን ፡ በልቡናህ ፡ የምትጽፍ ፡ ሄኖክ ፡ ለኃ
ጢአት ፡ ለሚተጉ ፡ ሰማያዊ ፡ ማዕርጋቸውን ፡
የከበረ ፡ ዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ መንግ
ሥተ ፡ ሰማይንም ፡ አተው ።
፯ ከሴቶችም ፡ ጋራ ፡ ለጠፉ ፡ የቃየል ፡ ልጆችም ፡
እንደሚያደርጉ ፡ ላደረጉ ፡ ለደቂቀ ፡ ሴት ፡
ሂደህ ፡ ንገር ፡ አሉኝ ።
፰ ራሳቸው ፡ ሚስት ፡ አገቡ ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡
ታላቅ ፡ ጥፋትን ፡ ጠፉ ።
፱ በዚህም ፡ ዓለም ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ የኃጢአ
ትም ፡ መሠረይ ፡ አይሆንላቸውም ።
በልጆቻቸው ፡ ደስ ፡ አይላቸውምና ፡ የሚወ ፲
ዳቸው ፡ የልጆቻቸውን ፡ ሞት ፡ ያያሉ ፡ በል
ጆቻቸውም ፡ ጥፋት ፡ ጩኸው ፡ ያለቅሳሉ ።
ለዘላለም ፡ ይለምናሉ ፡ ይቅርታም ፡ ፍቅርም ፡ ፲፩
አንድነትም ፡ አይደረግላቸው ።
እኔ ፡ ሄኖክም ፡ ሂጂ ፡ አዛዝኤልን ፡ ፍቅር ፡ አን ፲፪
ድነት ፡ አይደረግልህም ።
ሊያጠፋህ ፡ ፅኑዕ ፡ መቻያ ፡ ባንተ ፡ ታዘዘብህ ። ፲፫
ግፍን ፡ ስላስተማርህ ፡ የስድብንም ፡ ሥራ ፡ ፲፬
ሁሉ ፡ ስላስተማርህ ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ የኃጢአ
ትንና ፡ የግፍን ፡ ነገር ፡ ስላስተማርህ ፡ ዕረፍት ፡
ልመና ፡ ይቅርታ ፡ አይደረግልህም ፡ አልሁት ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ ሂጄ ፡ ለሁሉም ፡ አንድነት ፡ ነገርኋ ፲፭
ቸው ።
እነሱም ፡ ሁሉ ፡ ፈሩ ፡ ፍራት ፡ መንቀጥቀጥም ፡ ፲፮
ያዛቸው ።
ልጽፍላቸው ፡ ለነሱም ፡ የኃጢአታቸው ፡ መስ ፲፯
ተሥረያ ፡ ሊሆናቸው ፡ በሰማይ ፡ ወዳለ ፡ ወደ ፡
እግዚአብሔርም ፡ የልመናቸውን ፡ መታሰቢያ ፡
እኔ ፡ እንዳሳርግላቸው ፡ የልመናቸውን ፡ መታ
ሰቢያ ፡ ጻፍልን ፡ ብለው ፡ ለመኑኝ ።
እነሱ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምረው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ፲፰
መነጋገር ፡ አይችሉምና ፡ ከተፈረደባቸው ፡
በደል ፡ ኃፍረት ፡ የተነሣ ፡ ዓይናቸውን ፡ ወደ ፡
ሰማይ ፡ ቀና ፡ አድርገው ፡ ለማየት ፡ አይችሉ
ምና ።
የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ሰውነታቸው ፡ የፍጹም ፡ ፲፱
ልመናቸውን ፡ መታሰቢያ ፡ ጻፍሁ ፡ የኃጢአታ
ቸው ፡ መስተሥረያ ፡ የዘመንም ፡ ርዝመት ፡
ይሆንላቸው ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ለመኑኝ ፡ ያንዱ
ንም ፡ ያንዱንም ፡ ሥራቸውን ፡ ጻፍኩ ።
ሂጄም ፡ በውሀዎች ፡ ዳር ፡ ተቀመጥሁ ፡ ይቺ ፳
ውም ፡ በአርሞንኤም ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ያለች ፡
አገር ፡ ናት ።
እስካንጎላች ፡ ድረስ ፡ የልመናቸውን ፡ መታሰ ፳፩
ቢያ ፡ ተናገርሁ ።
እነሆ ፡ ሕልም ፡ መጣብኝ ፡ ራዕዮችም ፡ ተገለ ፳፪
ጡልኝ ።
በሰማያዊ ፡ ማዕርግ ፡ ለነበሩ ፡ ለደቂቀ ፡ ሴት ፡ ፳፫
ነግሬ ፡ እሰድባቸው ፡ ዘንድ ፡ መቅሠፍት ፡ ያለ
በት ፡ ራዕይን ፡ አየሁ ።
ነቅቼም ፡ ወደነሱ ፡ መጣሁ ፡ በሲኒሊርና ፡ በሊ ፳፬
ባኖስ ፡ መካከል ፡ ባለች ፡ በዑብልስያኢል ፡
ፊታቸውን ፡ ተከናንበው ፡ ሁሉም ፡ እያለቀሱ ፡
ተሰብስበው ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ።
እኔም ፡ ተኝቼ ፡ ያየሁትን ፡ ራእይ ፡ ሁሉ ፡ በፊታ ፳፭
ቸው ፡ ተናገርኩ ።
እውነት ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ይህነን ፡ ቃል ፡ እናገር ፡ ፳፮
ዘንድ ፡ በደብር ፡ ቅዱስም ፡ ለነበሩ ፡ ለኃጢአ
ታቸው ፡ ለሚተጉ ፡ ለደቂቀ ፡ ሴትም ፡ አስተ
ምር ፡ ዘንድ ፡ ጀመርሁ ።
የከበረ ፡ የገነነ ፡ ፈጣሪ ፡ በዚያች ፡ ራዕይ ፡ ንገ ፳፯
ራቸው ፡ ብሎ ፡ እንዳዘዘ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡

የነበሩ ፡ ለኃጢአታቸው ፡ የሚተጉ ፡ የደቂቀ ፡
ሴት ፡ ዘለፋና ፡ እውነት ፡ ነገር ፡ የተጻፈበት ፡
መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ።
፳፰፡ በሕሊና ፡ በሥጋዊ ፡ አንደበት ፡ እኔ ፡ ዛሬ ፡ የም
ናገረውን ፡ ነገር ፡ ተኝቼ ፡ አየሁ ፡ ይናገሩበት ፡
ዘንድ ፡ ለሰው ፡ አፍን ፡ የሰጠ ፡ የውቀትንም ፡
ነገር ፡ በልብ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ፈጥሮ ፡ ለሰው ፡
ልቡናን ፡ ሰጠ ።
፳፱፡ ገናና ፡ እግዚአብሔር ፡ በደብር ፡ ቅዱስ ፡ ያሉ ፡
ደቂቀ ፡ ሴትን ፡ አስተምራቸው ፡ ዘንድ ፡ ለኔም ፡
ፈጥሮ ፡ ልቡናን ፡ ሰጥቶኛልና ፡ የምናገረውን ፡
ነገር ፡ ተኝቼ ፡ አየሁ ።
፴፡ እኔ ፡ ልመናችሁን ፡ ጻፍኩላችሁ ።
፴፩፡ በሕልሜ ፡ እንዲህ ፡ አሳየኝ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ እን
ዲህ ፡ ፀንቶ ፡ በሚኖርበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ልመ
ናችሁ ፡ አትደረግላችሁምና ።
፴፪፡ የመከራም ፡ መጨረሻም ፡ በናንተ ፡ ታዘዘችብ
ችሁ ፡ የለመናችሁትም ፡ ልመና ፡ አይደረግላ
ችሁም ።
፴፫፡ ከዛሬም ፡ ጀምራችሁ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ እስ
ኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ከፍ ፡ ወዳለ ፡ ማሰርያችሁ ፡
አትወጡም ።
፴፬፡ ይህ ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖርበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ሊያ
ጠፋችሁ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ተናገረ ።
፴፭፡ ከዚህም ፡ አስቀድሞ ፡ የምትወዷቸው ፡ የልጆ
ቻችሁን ፡ ጥፋት ፡ አያችሁ ።
፴፮፡ በፊታችሁ ፡ በሰይፍ ፡ ተቀራደው ፡ ያልቃሉ ፡
እንጂ ፡ ጥሪትነታቸው ፡ የላችሁም ።
፴፯፡ ስለናንተ ፡ የለመናችሁት ፡ ስለነሳቸውም ፡ የለ
መናችሁት ፡ ልመና ፡ አይደረግላችሁም ።
፴፰፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ የተደረገባችሁ ፡ እናንተ ፡ የብስ
ጭት ፡ ኃዘን ፡ እያዘናችሁ ፡ ነው ፡ ከጻፍሁላች
ሁም ፡ መጽሐፍ ፡ ምንም ፡ ምንም ፡ እውነት ፡
ነገር ፡ አትናገሩም ።
፴፱፡ ለኔም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ራዕይ ፡ ታየኝ ።
፵፡ እነሆ ፡ ደመናዎች ፡ በራዕይ ፡ ይጠሩኛል ፡
ጉምም ፡ ይጠራኛል ።
፵፩፡ መብረቆችና ፡ ከከቦችም ፡ በሩጫ ፡ ያስቸኩሉ
ኛል ፡ ያስጨንቁኛል ።
፵፪፡ ነፋሶችም ፡ በሕልም ፡ ብር ፡ ብር ፡ ያደረጉኛል ፡
ያስቸኩሉኛል ፡ ( መላእክት ፡ ) ከምድር ፡ በላይ ፡
ወዳለ ፡ ሰማይም ፡ ይዘው ፡ አወጡኝ ።
፵፫፡ በበረድ ፡ ደንጊያ ፡ ወደ ፡ ተሠራች ፡ ማምብ ፡ እስ
ትቀርብ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ቅጥሩ ፡ ገባሁ ።
፵፬፡ የእሳትም ፡ ቅጥር ፡ ይከበታል ፡ እኔንም ፡ ያስፈ
ራኝ ፡ ጀመር ።
፵፭፡ ወደ ፡ እሳትም ፡ ቅጥር ፡ ገብቼ ፡ በበረድ ፡ ደን
ጊያ ፡ ወደ ፡ ተሠራ ፡ ታላቅ ፡ ቤት ፡ ቀረብሁ ።
፵፮፡ በበረድ ፡ ደንጊያዎች ፡ የተሠራ ፡ የዚያም ፡ ቤት ፡
ግድግዳ ፡ እንደ ፡ ሰንቃ ፡ ልገብ ፡ ነው ።
፵፯፡ ምድሩም ፡ በረድ ፡ ነው ፡ ጠፈሩም ፡ እንደ ፡
መብረቅና ፡ እንደ ፡ ከከብ ፡ ነው ። (ቀለም ፡ ሰጋ ፡ )
፵፰፡ በቅጥሩና ፡ በቤቱም ፡ መካከል ፡ ከእሳት ፡ የተፈ
ጠሩ ፡ ኪሩቤል ፡ አሉ ፡ ሰማያቸውም ፡ ውሀ ፡
ነው ።
በቅጽሩም ፡ ዙሪያ ፡ የሚነድ ፡ እሳት ፡ አለ ፡ ደጃ ፵፱፡
ፉም ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላል ።
ወደዚያም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ገባሁ ፡ እሳት ፡ እንደ ፡ ፶፡
መሆኑ ፡ ይሞቃል ፡ በረድ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ይቀ
ዘቅዛል ።
ምንም ፡ ምንም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ሕይወት ፡ ፶፩፡
በውስጡ ፡ የለም ፡ ፍራት ፡ ሸፈነኝ ፡ እንቅጥቀ
ጥም ፡ ያዘኝ ፡ ታውኬ ፡ እየተንቀጠቀጥሁ ፡ በግ
ምባሬ ፡ ወደቅሁ ፡ በሕልሜም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡
ራዕይ ፡ አየሁ ።
ከዚህ ፡ ቤትም ፡ የሚበልጥ ፡ ሌላ ፡ ቤት ፡ እነሆ ፡ ፶፪፡
አለ ።
በፊቱም ፡ ደጃፉ ፡ ሁሉ ፡ የተከፈተ ፡ ነው ፡ በእ ፶፫፡
ሳት ፡ ቅጽርም ፡ የተሠራ ፡ ነው ።
በሁሉም ፡ ይበልጣል ፡ በስብሐት ፡ በብርሃን ፡ ፶፬፡
በክብርም ፡ በወርድም ፡ በቁመትም ፡ የብርሃ
ኑም ፡ ነገር ፡ የወርዱም ፡ የቁመቱም ፡ ነገር ፡
ለናንተ ፡ መናገር ፡ የማይቻለኝ ፡ እስኪሆን ፡
ድረስ ፡ በሁሉ ፡ ይበልጣል ።
ወልወሉም ፡ እሳት ፡ ነው ፡ በላዩም ፡ መብረቅ ፡ ፶፭፡
የከከቦች ፡ መሮጫ ፡ አለበት ፡ ጠፈሩም ፡ የሚ
ነድ ፡ እሳት ፡ ነው ። (እንደ ፡ ቀለም ፡ ሰጋ ፡ )
በውስጡም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፶፮፡
ዙፋን ፡ ፈጽሜ ፡ አየሁ ።
መልኩም ፡ እንደ ፡ ውርጭ ፡ ነው ፡ አጎበሩም ፡ ፶፯፡
እንደሚያበራ ፡ ፀሐይ ፡ ነው ፡ የኪሩቤልም ፡
ቃል ፡ ይሰማል ።
ከታላቁ ፡ ዙፋንም ፡ በታች ፡ የሚነድ ፡ የእሳት ፡ ፶፰፡
ፈሳሾች ፡ ይወጣሉ ፡ ፊቱንም ፡ ማየት ፡ አይቻ
ላቸውም ።
የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታም ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ተቀም ፶፱፡
ጧል ፡ መጐናጸፊያውም ፡ ከፀሐይ ፡ ይልቅ ፡
ያበራል ፡ ከበረድም ፡ ሁሉ ፡ ይነጣል ።
ከመላእክትም ፡ ማንም ፡ ማን ፡ እሱ ፡ ወዳለበት ፡ ፷፡
መግባት ፡ አይችልም ፡ የከበረ ፡ የተመሰገነ ፡
ፊቱንም ፡ ማየት ፡ አይችልም ፡ ከሥጋዊ ፡ ከደ
ማዊ ፡ ሰው ፡ ያንን ፡ እሳት ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ማየት ፡
የሚቻለው ፡ ማነው ።
በዙሪያውም ፡ የሚነድ ፡ እሳት ፡ አለ ፡ በፊቱም ፡ ፷፩፡
ታላቅ ፡ እሳት ፡ ቆሟል ። (ደጆ ፡ ጠኒ ፡ መልአክ ፡
ነው ፡ )
በዙሪያው ፡ ካሉ ፡ መላእክትም ፡ ወደሱ ፡ የሚ ፷፪፡
ቀርብ ፡ የለም ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ መላእክትም ፡
በፊቱ ፡ አሉ ።
እሱ ፡ ግን ፡ ከባሕርዩ ፡ የተለየች ፡ ምክርን ፡ አይ ፷፫፡
ወድም ።
ወደሱ ፡ የሚቀርቡ ፡ መላእክትም ፡ በቀንም ፡ ፷፬፡
በሌሊትም ፡ ከሱ ፡ ፈጽመው ፡ አይርቁም ።
እኔም ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ እየተንቀጠቀጥሁ ፡ ፷፭፡
ፊቴን ፡ ተከናንቤ ፡ ነበርኩ ።
ጌታም ፡ ባንደበቱ ፡ ጠርቶ ፡ ሄኖክ ፡ ወደዚህ ፡ ፷፮፡
ቅረብ ፡ ለከበረ ፡ ቃሌም ፡ ታዘዝ ፡ አለኝ ።
አንሥቶም ፡ እስከ ፡ ደጃፉ ፡ ድረስ ፡ አቀረበኝ ፡ ፷፯፡

እኔ ፡ ግን ፡ ፈቱን ፡ ደፍቼ ፡ ወደታች ፡ እመለከት ፡
ነበር ።
፴፰ ደግ ፡ ሰው ፡ የምትሆን ፡ ሕግንም ፡ በሰው ፡
ልቡና ፡ የምትጽፍ ፡ ሄኖክ ፡ በቃሉ ፡ ስማ ፡ አት
ፍራም ፡ አለኝ ።
፴፱ ወደዚህ ፡ ቅረብ ፡ ቃሌንም ፡ ስማ ፡ ለነሱ ፡ ልት
ለምንላቸው ፡ ለላኩህ ፡ ለኃጢአት ፡ ለሚተጉ ፡
ለደቂቀ ፡ ሴትም ፡ ሂደህ ፡ ንገራቸው ፡ አለኝ ።
፵ እናንተ ፡ ለሰው ፡ ልትለምኑ ፡ ይገባችሁ ፡ ነበር ፡
ሰው ፡ ግን ፡ ለናንተ ፡ ሊለምንላችሁ ፡ አይገበ
ውም ፡ ነበር ።
፵፩ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደብር ፡ ቅዱስን ፡ ዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡
የሚኖር ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ስለምን ፡
ተዋችሁት ፡ በላቸው ።
፵፪ ከሴቶችም ፡ ደረሳችሁ ፡ ከቃየልም ፡ ልጆች ፡
ጋራ ፡ ረከሳችሁ ።
፵፫ ለናንተ ፡ ሚስት ፡ አገባችሁ ፡ የቃየልም ፡ ልጆች ፡
እንደሚያደርጉት ፡ አደረጋችሁ ፡ ረጃጅም ፡ ልጆ
ችንም ፡ ወለዳችሁ ።
፵፬ ረቂቃን ፡ የምትሆኑ ፡ የከበራችሁ ፡ ዘለዓለም ፡
ጸንቶ ፡ በሚኖር ፡ ሕይወት ፡ (መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡)
ደኅነኞች ፡ የምትሆኑ ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ በሴቶች ፡
ረከሳችሁ ።
፵፭ በደማዊ ፡ በሥጋዊ ፡ ሥራም ፡ እንደ ፡ ወለዱ ፡
አደረጋችኋቸው ፡ እናንተም ፡ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡
ሥራን ፡ ወደዳችሁ ፡ እነሱ ፡ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡
ሥራን ፡ እንዲሠሩ ፡ እናንተም ፡ እንደነሱ ፡ ሠራ
ችሁ ።
፵፮ እነዚህም ፡ የሚሞቱ ፡ የሚጠፉ ፡ ናቸው ፡ የሚ
ሞቱ ፡ ስለሆነ ፡ ዘራቸውን ፡ በነሱ ፡ ይዘሩ ፡ ዘንድ ፡
ልጆችም ፡ ከነሱ ፡ ይወልዱ ፡ ዘንደ ' ሴቶችን ፡
ሰጠኋቸው ።
፵፯ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደዚህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡
ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ ይኖራል ።
፵፰ እናንተ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ረቂቃንን ፡
ዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖር ፡ በልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመ
ንም ፡ በማያልፍ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ሕያ
ዋን ፡ ሁናችሁ ፡ ነበር ።
፵፱ የረቂቃን ፡ መላእክት ፡ ማደሪያቸው ፡ በሰማይ ፡
ነውና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ሴቶችን ፡ ለናንተ ፡
ሚስቶች ፡ አላደረግኋቸውም ።
፶ አሁንም ፡ ወገኖቻቸው ፡ ከሚሆኑ ፡ ከደቂቀ ፡
ሴት ፡ የተወለዱ ፡ ረጃጅሞች ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ ክፉ ፡ ልጆችን ፡ ይበላሉ ።
፶፩ ማዳሪያቸውም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይሆናል ።
፶፪ አባቶቻቸው ፡ ከደብር ፡ ቅዱስ ፡ ከወረዱ ፡ ከደ
ቂቀ ፡ ሴት ፡ ተወልደው ፡ ነበርና ፡ ወገኖቻቸው ፡
ከሚሆኑ ፡ ከደቂቀ ፡ ሴት ፡ ክፉ ፡ ልጆች ፡ ተወ
ለዱ ።
፶፫ ቀድሞ ፡ የንጽሕና ፡ መሠረት ፡ የነበሩ ፡ እነዚ
ህም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ክፉ ፡ ልጆች ፡ ይሆናሉ ፡
ክፉ ፡ ልጆችም ፡ ይባላሉ ።
፶፬ በሰማይ ፡ የሚኖሩ ፡ ረቂቃን ፡ መላእክት ፡ ማደ
ሪያቸው ፡ በሰማይ ፡ ይሆናል ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
የተወለዱ ፡ በምድር ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎችም ፡ ማደ
ሪያቸው ፡ በምድር ፡ ይሆናል ።
ከደመና ፡ የሚደርሱ ፡ ረጃጅሞች ፡ ሰዎችም ፡ ፶፭
ፈጽመው ፡ ይጠፋሉ ፡ እስበሳቸውም ፡ ይጣላሉ ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሰውን ፡ ያጠፋሉ ።
በሰውም ፡ ኃዘንን ፡ ያደርጋሉ ፡ እነሳቸውም ፡ ፶፮
የሚበሉትን ፡ እህል ፡ ምንምን ፡ አያገኙም ።
ማየ ፡ አይህን ፡ ይጨልጣሉ ፡ እንጂ ፡ አይጠ ፶፯
ሙም ፡ በመኖርም ፡ አይታወቁም ።
ጥፋትና ፡ ሰልፍ ፡ በታዘዘበት ፡ ወራት ፡ ተወል ፶፰
ደዋልና ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ኑረው ፡ በሴቶችና ፡
በወንዶች ፡ ላይ ፡ በጠላትነት ፡ አይነሱም ፡ አለ ።

ምዕራፍ ፡ ፳ ።

ወገኖቻቸው ፡ ከሚሆኑ ፡ ከደቂቀ ፡ ሴት ፡ ፩
የተወለዱ ፡ የረዓይት ፡ ሞታቸው ፡ በወጡበት ፡
በታ ፡ ነው ።
ሞታቸውም ፡ ሙሉን ፡ ሞት ፡ ይሁን ። ፪
ፍርድ ፡ ሳይደረግ ፡ የመከራ ፡ ፍጻሜ ፡ እስከሚ ፫
ደረግበት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡
እንደዚሁ ፡ ይጠፋሉ ፡ የከበረ ፡ መንግሥተ ፡
ሰማይ ፡ ከመሰጠቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ሕግን ፡ በዘ
ነጉ ፡ ሰዎችና ፡ በደቂቀ ፡ ሴት ፡ ፍርድ ፡ ይጀመ
ራል ።
አሁንም ፡ ለነሱ ፡ ልትለምንላቸው ፡ የላኩህን ፡ ፬
ከዚያ ፡ አስቀድሞ ፡ በደብር ፡ ቅዱስ ፡ የነበሩ ፡
ለኃጢአት ፡ የሚተጉ ፡ ደቂቀ ፡ ሴትን ፡ እንዲህ ፡
በላቸው ።
ዛሬም ፡ በደብር ፡ ቅዱስ ፡ ነበራችሁ ፡ የተሠወ ፭
ሩም ፡ ኃጢአቶች ፡ ገና ፡ አልተገለጡላችሁም ፡
ነበር ።
የተናቀ ፡ ምሥጢርንም ፡ አወቃችሁ ፡ በልቡ ፮
ናችሁም ፡ ዕናት ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ ለሴቶች ፡ ነገ
ራችሁ ።
ከዚህም ፡ ምሥጢር ፡ በወንዶችና ፡ በሴቶች ፡ ፯
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ክፋትን ፡ ያበዛሉ ፡ እንግዲህስ ፡
ፍቅር ፡ አንድነት ፡ የላችሁም ፡ በላቸው ፡ አለኝ ።
እንደ ፡ ቋያ ፡ የሚቃጠሉ ፡ ሰዎች ፡ ወዳሉበት ፡ ፰
ወደዚያ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ መላእክት ፡ ወሰ
ዱኝ ፡ ሊታዩም ፡ በወደዱ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ሆነው ፡
ይታያሉ ።
ጥቅል ፡ ነፋስ ፡ ወዳለበት ፡ ቦታ ፡ ራሱም ፡ እስከ ፡ ፱
ሰማይ ፡ ወደሚደርስ ፡ ተራራ ፡ ወሰዱኝ ። (ስነ ፡
ፍጥረት ፡)
የሚያበሩ ፡ አራት ፡ ቦታዎችን ፡ አየሁ ፡ በጥል ፲
ቁም ፡ ዳርቻ ፡ ነጐድጓድ ፡ አለ ፡ የእሳት ፡ ቀስት ፡
የእሳት ፡ ፍላፃ ፡ ጐረጐሪያቸውም ፡ የእሳት ፡
ሰይፍ ፡ መብረቆችም ፡ ሁሉ ፡ አሉ ።
የሚናገር ፡ የመጣያ ፡ ወሀ ፡ እስከ ፡ አለበት ፡ ፲፩
ድረስ ፡ የምዕራብም ፡ እሳት ፡ እስካለበት ፡ ድረስ ፡
ወሰዱኝ ፡ ይኸውም ፡ የፀሐይን ፡ መግቢያ ፡
ሁሉ ፡ የሚይዝ ፡ ነው ።
እሳቱ ፡ እንደ ፡ ወሀ ፡ እስከሚፈስ ፡ እስከ ፡ እሳት ፡ ፲፪
ፈሳሽ ፡ ድረስ ፡ መጣሁ ፡ በምዕራብ ፡ ወዳለ ፡

ወደ ፡ ታላቁም ፡ ባሕር ፡ ያፈሳል ።

፲፫ ታላላቅ ፡ ወንዞችንም ፡ ሁሉ ፡ አየሁ ፡ እስከ ፡
ታላቁ ፡ (በርበሮስ ፡) ጨለማም ፡ ድረስ ፡ ደረ
ስኩ ፡ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ሁሉም ፡ ወደሚመላለ
ስበት ፡ ሄድኩ ።

፲፬ የክረምት ፡ ጭጋጎች ፡ ያሉባቸው ፡ ተራሮች
ንም ፡ የወንዙንም ፡ ሁሉ ፡ ውሀ ፡ የሚፈስበትን ፡
አየሁ ፡ (ውቅያኖስንም ፡) ።

፲፭ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚፈሱ ፡ የወንዞችንም ፡ ሁሉ ፡
አፋቸውን ፡ የውቅያኖስንም ፡ አፍ ፡ አየሁ ።

፲፮ የነፋሶችን ፡ ሁሉ ፡ በታዎችንም ፡ ሁሉ ፡ አየሁ ፡
ፍጥረቱን ፡ የምድሩንም ፡ ሁሉ ፡ መሠረቶች ፡
በነሳቸው ፡ እንዳስጌጠ ፡ አየሁ ፡ (አጸና) ።

፲፯ ባራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ያለ ፡ አድማስንም ፡ አየሁ ፡
ምድርን ፡ ያጸኗት ፡ የጸናች ፡ ሰማይንም ፡ የሚ
ሸከሟት ፡ አራቱን ፡ ነፋሶች ፡ አየሁ ።

፲፰ የከበረች ፡ ሰማይንም ፡ ነፋሶች ፡ እንደ ፡ ዘረጓት ፡
አየሁ ።

፲፱ እነሳቸውም ፡ በምድርና ፡ በሰማይ ፡ መካከል ፡
ቁመው ፡ ይኖራሉ ፡ እነሳቸውም ፡ የሰማይ ፡
ምሰሶዎች ፡ ናቸው ።

፳ ሰማይን ፡ ዘርግተው ፡ የያዙ ፡ የፀሐይንም ፡
ክበብ ፡ የሚያገቡ ፡ ከዋክብትንም ፡ ሁሉ ፡ የሚ
ያገቡ ፡ ነፋሶችንም ፡ አየሁ ።

፳፩ ደመናዎችን ፡ የሚሸከሙ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡
ነፋሶችንም ፡ አየሁ ።

፳፪ የመላእክትንም ፡ ቍጥር ፡ አየሁ ፡ በላይ ፡ ያለ ፡
ጠፈርን ፡ የሚያፀና ፡ በምድር ፡ ዳርቻ ፡ ያለ ፡
አድማሱን ፡ አየሁ ።

፳፫ ወደ ፡ አዜብም ፡ ሄድኩ ፡ በቀንም ፡ በሌሊትም ፡
ወደሚያበሩ ፡ ከከበረ ፡ ደንጊያ ፡ ወደሚበልጡ ፡
ወደ ፡ ሰበት ፡ ተራሮችም ፡ ሄድኩ ። (ዕንቍ ፡)

፳፬ ሦስቱ ፡ በምሥራቅ ፡ ሦስቱም ፡ በዓዜብ ፡ ናቸው ፡
በምሥራቅ ፡ ያለ ፡ ዕንቍ ፡ ግን ፡ አንዱ ፡ ቅጥ
ልጣል ፡ የሚባል ፡ ዕንቍ ፡ አንዱም ፡ ባሕር ፡
የሚባል ፡ ዕንቍ ፡ ነው ። አንዱ ፡ ደምርዕ ፡ የሚ
ባል ፡ ዕንቍ ፡ ነው ፡ በዓዜብ ፡ ያለ ፡ ቀይ ፡ ዕንቍ ፡
ነው ።

፳፭ መካከለኛው ፡ ግን ፡ ፒካ ፡ ከሚባል ፡ ዕንቍ ፡
እንደ ፡ ተሠራ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መቀ
መጫ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ይደርሳል ።

፳፮ የመቀመጫው ፡ አነበሩ ፡ በሰንፒር ፡ ከሚባል ፡
ዕንቍ ፡ የተሠራ ፡ ነው ፡ በተራራው ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡
የሚቃጠል ፡ እሳትንም ፡ አየሁ ።

፳፯ በታላቅ ፡ ምድር ፡ መጨረሻ ፡ የሚሆን ፡ በታን ፡
በዚያ ፡ አየሁ ፡ ውሀዎች ፡ በዚያ ፡ ይሰበሰባሉ ።

፳፰ በሰማይ ፡ እሳት ፡ የሚቃጠሉ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡
የተጋዙበት ፡ ጥልቅ ፡ የሚሆን ፡ በዘ ሀ ፡ ዓለም ፡
ያለ ፡ ገሃነምንም ፡ አየሁ ።

፳፱ በእሳት ፡ የሚቃጠሉ ፡ ወደ ፡ ጥልቅም ፡ የሚወ
ርዱ ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸው ፡ የሰማይ ፡
ደቂቀ ፡ ሴትን ፡ በውስጣቸው ፡ አየሁ ፡ በዚያም ፡
በታ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ርቀት ፡ ወደ ፡ ታችም ፡ ጥልቅ
ነት ፡ የለውም ።

በዚያም ፡ በገሃነም ፡ ላይ ፡ በታ ፡ አየሁ ፡ ለዚ
ያም ፡ በታ ፡ በላይ ፡ ጠፈር ፡ በታችም ፡ መሠ
ረት ፡ የለውም ። ፴

የምድረ ፡ በዳ ፡ በታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በላዩ ፡
ውሀ ፡ የለም ፡ ወፎችም ፡ የሉም ። ፴፩

በዚያም ፡ የሚያስፈራ ፡ በታን ፡ አየሁ ፡ እንደ
ሚቃጠሉ ፡ እንደ ፡ ታላላቅ ፡ ተራሮች ፡ የሚቃ
ጠሉ ፡ ሰበት ፡ ከከቦችንም ፡ አየሁ ። ፴፪

የሚጠይቀኝ ፡ ረቂቅ ፡ ባልደረበዬም ፡ እንደመ
ሆኑ ፡ መልአኩ ፡ ይህ ፡ በታ ፡ የምድርና ፡ የሰ
ማይ ፡ መጨረሻ ፡ በታ ፡ ነው ። ፴፫

ለሰማይ ፡ ከከቦች ፡ ለደቂቀ ፡ ሴት ፡ ለሰማይም ፡
ሠራዊት ፡ በእሳት ፡ ላይ ፡ ለሚገለባበጡ ፡ ከከበ
ችም ፡ ይህ ፡ የግዞት ፡ ቤት ፡ ሆናቸው ፡ አለኝ ። ፴፬

በጊዜያቸው ፡ አልመጡምና ፡ በአእምሮ ፡
ፍጹም ፡ ከመሆናቸው ፡ አስቀድሞ ፡ የእግዚአ
ብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ያፈረሱ ፡ እኒህ ፡ ናቸው ። ፴፭

የተሠወረ ፡ ፍዳቸውን ፡ በሚቀበሉበት ፡ ዘመን ፡
እስከ ፡ ኃጢአታቸው ፡ መጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡
ተቈጥቶ ፡ አጋዛቸው ። ፴፮

ሁርኤልም ፡ በዚህ ፡ በነገሩ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ከሴ
ቶች ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ ሰውነቶቻቸው ፡
በፍዳ ፡ ተይዘው ፡ ይኖራሉ ። ፴፯

በብዙ ፡ ወገንም ፡ አብነት ፡ ሁነዋቸው ፡ ሰዎችን ፡
አረከሷቸው ፡ ታላቅ ፡ በሆነ ፡ ጨርሰው ፡ እስኪ
ያጠፏቸው ፡ ድረስ ፡ በሚፈረድባቸው ፡ ገንዘብ ፡
ጽኑ ፡ ፍርድ ፡ በሚፈረድበት ፡ በዕለተ ፡ ምጽ
አት ፡ ይፈረድባቸዋልና ፡ ምዕመናን ፡ ለሥላሴ ፡
እንዲሠዉ ፡ እነሱም ፡ ለአጋንንት ፡ ይሠዉ ፡
ዘንድ ፡ ሰዎችን ፡ ያስቷቸዋል ። ፴፰

ሚስቶቻቸውም ፡ ክፉ ፡ ባለ ፡ ማዕርግ ፡ የነበሩ ፡
የሴትን ፡ ልጆች ፡ አስተው ፡ ደኀና ፡ ሴቶችን ፡
ይሆናሉ ። ( ይመስላሉ ፡ ሊ ፡ ነ ፡) ፴፱

እኔ ፡ ሄኖክ ፡ በሁሉ ፡ ዳርቻ ፡ በአድማስ ፡ ሁኜ ፡
የኔን ፡ ብቻ ፡ ሥራ ፡ አየሁ ፡ ከሰዎችም ፡ እኔ ፡
እንዳየሁ ፡ ያየ ፡ የለም ። ፵

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

ለምስጋና ፡ የሚተጉ ፡ የከበሩ ፡ የመላእክት ፡
ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ። ፩

ከከበሩ ፡ ከመላእክት ፡ አንዱ ፡ ሁርኤል ፡ በመ
ብረቅ ፡ በነጐድጓድ ፡ የተሾመ ፡ ነው ። ፪

በሰው ፡ ቍስል ፡ የተሾመ ፡ ከከበሩ ፡ ከመላእ
ክት ፡ አንዱ ፡ ሩፋኤል ፡ ነው ። ፫

ዲያብሎስን ፡ የሚበቀለው ፡ አጋንንትንም ፡ የሚ
በቀላቸው ፡ ከከበሩ ፡ ከመላእክት ፡ አንዱ ፡ ራጉ
ኤል ፡ ነው ። ፬

ለሰው ፡ በደረገው ፡ በጎነት ፡ ላይ ፡ ለሕዝቡ ፡
ታዛዥ ፡ ነውና ፡ ከከበሩ ፡ ከመላእክት ፡ አንዱ ፡
ሚካኤል ፡ ነው ። ፭

አእምሯቸውን ፡ ባጡ ፡ ሰዎችም ፡ ላይ ፡ የተ
ሾመ ፡ ከከበሩ ፡ ከመላእክት ፡ አንዱ ፡ ሠረቃ
ኤል ፡ ነው ። ፮

በበቦች ፡ ላይ ፡ በገነትም ፡ ባሉ ፡ ጻድቃን ፡ ላይ ፡ ፯

በኪሩቤልም ፡ ላይ ፡ የተሾመ ፡ ከክበሩ ፡ ከመላ
እክት ፡ አንዱ ፡ ገብርኤል ፡ ነው ።
፰፡ የሚሠራበት ፡ ሥራ ፡ እስከሌለበት ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡
ዞርኩ ፡ በዚያም ፡ የሚያስፈራ ፡ ሥራን ፡ አየሁ ።
የተዘጋጀ ፡ የሚያስፈራ ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ ቦታ ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ በላይ ፡ ጠፈር ፡ በታችም ፡ መሠ
ረት ፡ የለውም ።
፱፡ በዚያም ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ተላላቅ ፡ ተራሮች ፡ እንደ ፡
ቋያም ፡ ሲቃጠሉ ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ በሱ ፡ የተ
ጋዙ ፡ ሰባት ፡ የሰማይ ፡ ከክቦች ፡ አየሁ ። (ደቂቀ ፡
ሴት ፡ ናቸው ፡)
፲፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ በምን ፡ ኃጢአታቸው ፡ ታሰረው ፡
ተግዘዋል ፡ በምንስ ፡ ኃጢአታቸው ፡ በዚህ ፡
ወድቀዋል ፡ አልሁ ።
፲፩፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ ወደ ፡ ወደደውም ፡ ሥራ ፡ የሚ
መራኝ ፡ ከክበሩ ፡ ከመላእክት ፡ አንዱ ፡ ዑር
ኤልም ፡ ሄኖክ ፡ ስለምን ፡ ትጠይቃለህ ፡ የማን
ነስ ፡ ነገር ፡ ልትረዳ ፡ ትፈልጋለህ ፡ አለኝ ፡ አለ ።
፲፪፡ እኒህ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡
ያፈረሱ ፡ የሴት ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡
ዘመን ፡ ቍጥር ፡ ኃጢአታቸውም ፡ የሚሠራ
በት ፡ ወራት ፡ ቍጥር ፡ እስቲጨረስ ፡ ድረስ ፡
በዚህ ፡ ተግዘዋል ፡ አለኝ ።
፲፫፡ ከዚያም ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ ወደሚያስፈራ ፡ ወደ ፡
ሌላ ፡ ቦታ ፡ ሄድኩ ።
፲፬፡ በዚያም ፡ ቦታ ፡ የሚያስፈራ ፡ ሥራን ፡ አየሁ ፡
በዚያም ፡ ቦታ ፡ ፈጽሞ ፡ የሚቃጠል ፡ ታላቅ ፡
ቋያ ፡ አለ ፡ መጋዛም ፡ አለበት ፡ ድምበሩም ፡
በመምላት ፡ ፍጹም ፡ እስከ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ውቅያ
ኖስ ፡ ደርሷል ።
፲፭፡ ወደዚያው ፡ የሚያወርዷቸው ፡ ታላላቅ ፡ የእ
ሳት ፡ ምሰሶዎችም ፡ አሉ ፡ (ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ና ፡)
ቁመቱን ፡ ወርዱን ፡ ማየት ፡ አልቻልሁም ፡ መል
ኩንም ፡ ማየት ፡ ተሳነኝ ።
፲፮፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ ይህ ፡ ቦታ ፡ እንዴት ፡ የሚያስ
ፈራ ፡ ነው ፡ ሊያውትም ፡ ደዌ ፡ ነው ፡ አልኩ ።
፲፯፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ ከክበሩ ፡ ከመላ
እክት ፡ አንዱ ፡ ዑርኤል ፡ መለሰልኝ ።
፲፰፡ ሄኖክ ፡ እንደዚህ ፡ አድርገህ ፡ መፍራትህ ፡ ምን
ድን ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ ስለሚያስፈራ ፡ ቦታ ፡ መደ
ንገጥህ ፡ በዚህስ ፡ መከራ ፡ ገጸ ፡ መዓት ፡ መፍ
ራትህ ፡ ስለምነው ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ።
፲፱፡ ይህም ፡ ቦታ ፡ ለደቂቀ ፡ ሴት ፡ የግዞት ፡ ቤታ
ቸው ፡ ነው ፡ በዚያም ፡ ቦታ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡
ድረስ ፡ ይጋዛሉ ።
፳፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ሄድሁ ፡ በምዕራ
ብም ፡ ረጅምና ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ ተራራን ፡ የጸና ፡
አለትንም ፡ አሳየኝ ። (አሕዛብን ፡)
፳፩፡ በጠገቡም ፡ ያማሩ ፡ አራት ፡ ቦታዎች ፡ አሉ ፡
በውስጡም ፡ ጥልቅነት ፡ ሰፊነት ፡ አለት ፡ እንደ ፡
መሆኑ ፡ ፈጽሞ ፡ የሚያድጥ ፡ አለት ፡ ነው ፡ ሊያ
ዩትም ፡ ጥልቅ ፡ ነው ፡ ጨለማም ፡ ነው ።
፳፪፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ ከክበሩ ፡ መላእክት ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡
ያለ ፡ አንዱ ፡ ሩፋኤል ፡ መለሰልኝ ።
፳፫፡ እኒህ ፡ መልካም ፡ መልካም ፡ ቦታዎች ፡ የሞቱ ፡
ሰዎች ፡ ነፍሶች ፡ በነሱ ፡ ሊሰበሰቡባቸው ፡ እነ
ዚህ ፡ ለነሱ ፡ ተፈጠሩላቸው ፡ መላእክትም ፡
የደጋግ ፡ ሰዎች ፡ ልጆች ፡ ነፍሶችን ፡ ሁሉ ፡
በዚያ ፡ ይሰበስባሉ ።
፳፬፡ ፍጹም ፡ መቻያቸውን ፡ እስተሚቀበሉበት ፡ ቀን ፡
ድረስ ፡ እስከ ፡ ጊዜያቸውም ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እነ
ሱን ፡ የሚያኖሩባቸው ፡ እነዚህን ፡ ቦታዎች ፡
ሥላሴ ፡ ፈጠሩ ።
፳፭፡ ይኸውም ፡ በነሱ ፡ ታላቅ ፡ መከራ ፡ እስኪደረግ
ባቸው ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ነው ።
፳፮፡ የደጋግ ፡ ሰዎች ፡ ልጆች ፡ ነፍሶችንም ፡ አየሁ ፡
እነሱ ፡ ሙተው ፡ ሳሉ ፡ ቃላቸው ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡
ይደርሳል ፡ ወንድሞቻቸውንም ፡ ይከሳሉ ፡ ይጣ
ላሉ ።
፳፯፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ ሩፋኤል ፡ ቃሉ ፡
እስከ ፡ ሰማይ ፡ ድረስ ፡ የሚደርስ ፡ የሚከስ ፡
ይኸ ፡ ነፍስ ፡ የማነው ፡ ነፍስ ፡ ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።
፳፰፡ ይህ ፡ ነፍስ ፡ ወንድሙ ፡ ቃየል ፡ በግፍ ፡ ከገደ
ለው ፡ ከአቤል ፡ የተለየ ፡ ነፍስ ፡ ነው ፡ ልጁ ፡
ከዚህ ፡ ዓለም ፡ እስኪጠፋ ፡ ድረስ ፡ የልጅ ፡
ልጁም ፡ ከሰው ፡ ልጅ ፡ ተለይቶ ፡ እስኪጠፋ ፡
ቃየልን ፡ ይከሳል ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ።
፳፱፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ የጻድቃንን ፡ ነገር ፡ የኃጥአንንም ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጠየቅሁ ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ስለምን ፡
ተለየ ፡ አልኩ ።
፴፡ የሞቱ ፡ ሰዎችን ፡ ነፍስ ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ፡ እነዚህ ፡
ሦስት ፡ ቦታዎች ፡ ተፈጠሩ ፡ የጻድቃንም ፡ ነፍስ ፡
እንደዚህ ፡ ተለየ ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ፡ ይህ ፡ ቦታ ፡
ብርሃን ፡ ያለበት ፡ የውሀ ፡ ምንጭ ፡ ነው ።
፴፩፡ አሁን ፡ እንደ ፡ ተገናርሁት ፡ ለጻድቃን ፡ ቦታ ፡
እንደ ፡ ተፈጠረ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሞተው ፡ በተቀ
በሩ ፡ ጊዜ ፡ ሊኖሩበት ፡ ለኃጥአን ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡
ተፈጠረላቸው ።
፴፪፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳሉ ፡ በነሱ ፡ መከራ ፡ አል
ተደረገባቸውም ።
፴፫፡ መቻያ ፡ እስከሚቀበሉበት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽ
ዓት ፡ ድረስ ፡ በዚች ፡ ታላቅ ፡ ጭንቅ ፡ ተይዘው ፡
ሊኖሩ ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ ነፍሶቻቸው ፡ ከጻድቃን ፡
ነፍሳት ፡ ይለያሉ ፡ ለሚሳደቡም ፡ ሰዎች ፡ እስከ ፡
ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ መከራና ፡ መቅሠፍት ፡ ይደረ
ጉባቸዋል ፡ በሰውነታቸውም ፡ በቀል ፡ ትደረግ
ባቸዋለች ።
፴፬፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ዓሥሮ ፡ ያግዛቸ
ዋል ፤ ምንም ፡ ከዕለተ ፡ ምጽዓት ፡ አስቀድሞ ፡
ቢሆን ፡ በዚያ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ ዓሥሮ ፡
ያግዛቸዋል ።
፴፭፡ የኃጥአን ፡ ነፍስ ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ተለየ ፡ ወንድ
ሞቻቸውን ፡ ለሚከሰሱ ፡ በኃጥአንም ፡ ወራት ፡
በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ የጥፋታቸውን ፡ ነገር ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ ለሚያሳዩ ፡ ለጻድቃንም ፡ ነፍስ ፡ ቦታ ፡
ተለየ ።
፴፮፡ ለጻድቃንም ፡ ነፍስ ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ተፈጠረ ፡
በደልን ፡ የጨረሱ ፡ ኃጥአንን ፡ ሆኑ ፡ እንጂ ፡

ጻድቃንን ፡ ላልሆኑ ፡ ለክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ ነፍ
ስም ፡ ቦታ ፡ ተፈጠረ ፡ ከበደለኞችም ፡ ጋራ ፡
እንደነሱ ፡ በደለኞች ፡ ይሆናሉ ።
፴፯፡ መከራ ፡ በሚቀበሉበት ፡ በዕለተ ፡ ምጽአትም ፡
ነፍሳቸው ፡ አትሞትም ፡ ከፍዳም ፡ አይድኑም ።
፴፰፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታን ፡ አመሰ
ገንሁት ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ ሁሉን ፡ የሚ
ገዛ ፡ የቸርነትና ፡ የጌትነት ፡ ባለቤት ፡ ጌታዬም ፡
የተመሰገነ ፡ ነው ፡ አልሁ ።
፴፱፡ ከዚያም ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ በም
ዕራብ ፡ ወዳለ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ሄድሁ ።
፵፡ ሳያርፍ ፡ እየሮጠ ፡ የሚነድን ፡ እሳትንም ፡ አየሁ ፡
(ፀሐይ ፡ ነው) እኔ ፡ እንዳየሁት ፡ ፈጽሞ ፡ ሲሮጥ ፡
ይኖራል ፡ እንጂ ፡ በሌትና ፡ በቀን ፡ ከሩጫው ፡
አይገታም ፡ (አያርፍም ፡ ሲል ፡ ነው ፡)
፵፩፡ ይህ ፡ ዕረፍት ፡ የሌለው ፡ ምንድነው ፡ ብዬ ፡
ጠየቅሁ ።
፵፪፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ ከከበሩ ፡ ከመላእ
ክት ፡ አንዱ ፡ ራጉኤል ፡ መለሰልኝ ፡ ወደ ፡ ምዕ
ራብ ፡ ሊሮጥ ፡ ሩጫውን ፡ ያየኸው ፡ ይህ ፡ የሚ
ነድ ፡ እሳት ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ በሰማይ ፡ የሚ
ያበራ ፡ ፀሐይ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩፡ ከዚያም ፡ ቦታ ፡ በምድር ፡ ወዳለ ፡ ወደሌላ ፡
ቦታ ፡ ሄድሁ ፡ በሌትና ፡ በቀን ፡ የሚቃጠል ፡
ቋያ ፡ ያለበት ፡ ተራራንም ፡ አሳየኝ ።
፪፡ ወደሱም ፡ ደጅ ፡ የከበሩ ፡ ሰባት ፡ ተራሮችን ፡
አየሁ ።
፫፡ ያየሁትም ፡ ሁሉ ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ልውጥ ፡
ነው ፡ ያማሩና ፡ የከበሩ ፡ ድንጋዮችንም ፡ አየሁ ፡
ሁሉም ፡ የከበረ ፡ ነው ።
፬፡ መልካቸው ፡ የበራ ፡ ነው ፡ ፊታቸውም ፡ ያማረ ፡
ነው ፡ ሦስቱ ፡ በምሥራቅ ፡ ናቸው ፡ አንዱ ፡
ባንዱ ፡ ላይ ፡ የጸኑ ፡ ናቸው ።
፭፡ ሦስቱም ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ናቸው ፡ አንዱ ፡
ባንዱ ፡ ላይ ፡ የጸኑ ፡ ናቸው ። ጥልቆች ፡ ቆላ
ዎች ፡ አሉ ፡ ጠማሞችም ፡ ናቸው ፡ አንዲቱ ፡
አንዲቱን ፡ አትቀርባትም ።
፮፡ ሰባተኛውም ፡ ተራራ ፡ በነዚህ ፡ መካከል ፡ ነው ፡
ቁመታቸው ፡ እንደ ፡ አፍርንጊ ፡ ወምበር ፡
ሁሉም ፡ ይመሳሰላሉ ።
፯፡ መዓዛ ፡ ያላቸውም ፡ እንጨቶች ፡ ይከቡታል ፡
በመካከላቸውም ፡ አንድ ፡ እንጨት ፡ አለ ፡ በሸ
ተተኝም ፡ ጊዜ ፡ ከነሳቸው ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡
እንደነሱ ፡ የሸተተኝ ፡ የለም ።
፰፡ ሌሎችም ፡ እንጨቶች ፡ ከሽቱው ፡ ሁሉ ፡ የሚ
ሸት ፡ እንደሱ ፡ የሚሸት ፡ አልሆነም ።
፱፡ ቅጠሉ ፡ አበባው ፡ እንጨቱም ፡ ለዘላለም ፡ አይ
ጠወልግም ።
፲፡ ፍሬውም ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ እንደዘምባባም ፡ ፍሬ ፡
ንብብር ፡ ነው ።
፲፩፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ ይህ ፡ እንጨት ፡ እነሆ ፡ ያማረ ፡
ነው ፡ ሊያውትም ፡ ፈጽሞ ፡ የተወደደ ፡ ነው ፡
ቅጠሉ ፡ ጽፍቅ ፡ ነው ፡ ፍሬው ፡ ንብብር ፡ ሊያ
ውትም ፡ ፈጽሞ ፡ የተወደደ ፡ ነው ፡ አልሁ ።
የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ በላያቸው ፡ ፲፪፡
የተሾመ ፡ ፈጽመው ፡ ከከበሩ ፡ ከመላእክት ፡
አንዱ ፡ ሚካኤል ፡ መለሰልኝ ።
ሄኖክ ፡ የዚህን ፡ እንጨት ፡ ሽታ ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ፲፫፡
ትጠይቃለህ ፡ ልታውቅስ ፡ ምን ፡ ትመረምራ
ለህ ፡ አለኝ ።
ያን ፡ ጊዜም ፡ እኔ ፡ ሄኖክ ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ መለ ፲፬፡
ስሁለት ፡ የእንጨቶችን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ላውቅ ፡
እወዳለሁ ፡ ይልቁንም ፡ የዚህን ፡ እንጨት ፡
ነገር ፡ ላውቅ ፡ እወዳለሁ ፡ አልሁት ።
እሱም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ፡ረጅም ፡ ፲፭፡
ሆኖ ፡ የምታየው ፡ ራሱ ፡ የጌታን ፡ መቀመጫ ፡
መስሎ ፡ ያየኸው ፡ ይህ ፡ ተራራ ፡ የተመሰገነ ፡
የገነነ ፡ የዘለዓለም ፡ ንጉሥ ፡ የሚሆን ፡ የክብር ፡
ባለቤት ፡ ይህችን ፡ ዓለም ፡ በበጎ ፡ ሊጎበኛት ፡
በወረደ ፡ ጊዜ ፡ የሚቀመጥበት ፡ ዙፋኑ ፡ ደብረ ፡
ሲና ፡ ነው ።
ይህም ፡ መዓዛ ፡ ያለው ፡ የተወደደ ፡ እንጨት ፡ ፲፮፡
ጌታ ፡ ሁሉን ፡ በተቀበለ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ዘለዓ
ለም ፡ የሚሆን ፡ መከራም ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡
ጽኑ ፡ መከራ ፡ እስከሚደረግበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡
ከሥጋዊ ፡ ከደማዊ ፡ አንዱስ ፡ ስንኳ ፡ ሊነካው ፡
ሥልጣን ፡ የለውም ።
ለደጋጎች ፡ ለተዋረዱም ፡ ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ እን ፲፯፡
ጨት ፡ ፍሬ ፡ ይሰጣቸዋል ፡ ለተመረጡም ፡ ሰዎች ፡
ደኅንነት ፡ ይሰጣል ።
የዘለዓለም ፡ ንጉሥ ፡ ወደሚሆን ፡ በደጊቱ ፡ ፲፰፡
ማደሪያ ፡ አንጻር ፡ በመስዕ ፡ በኩል ፡ በከበረ ፡
ቦታ ፡ ይተከላል ።
ያን ፡ ጊዜም ፡ ፈጽመው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። ፲፱፡
በየወገናቸው ፡ ወደ ፡ ከበረ ፡ ቦታ ፡ ሽቱን ፡ ያቀ ፳፡
ርቡለታል ፡ አባቶችህ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ እንደኖሩ ፡
እነሱም ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ይኖ
ራሉ ።
በዘመናቸውም ፡ መከራና ፡ አዘን ፡ መቅሠፍ ፳፩፡
ትና ፡ ድካምም ፡ አይዳስሳቸውም ፡ (አያገኛቸ
ውም) ።
እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ ወዳጆቹ ፡ ለሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ፳፪፡
አዘጋጅቷልና ፡ እንደዚህም ፡ አድርጎ ፡ ፈጥሮ ፡
ይሰጧቸው ፡ ብሏልና ፡ የዘላለም ፡ ንጉሥ ፡ የሚ
ሆን ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታን ፡ አመሰገንሁት ፡
አለ ።
ከዚያ ፡ ተነሥቼ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ መካከል ፡ ፳፫፡
ሄድሁ ፡ የከበረ ፡ የለመለመም ፡ እንጨት ፡ የተ
ቈረጠ ፡ ለምለሞ ፡ የሚኖር ፡ ጫፍ ፡ ያለበት ፡
ቦታንም ፡ አየሁ ። (ከነቢያት ፡ የተወለዱ ፡ ሐዋ
ርያት ፡ ናቸው ። )
በዚያም ፡ ቦታ ፡ የከበረ ፡ ተራራን ፡ አየሁ ፡ በተ ፳፬፡
ራራውም ፡ በታች ፡ በምሥራቁ ፡ አንጻር ፡ ውሀ ፡
አለ ፡ የሚፈሰውም ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ነው ። (ትእ
ምርት ፡ ነው ። )
በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ከዚህ ፡ የሚበልጥ ፡ ፳፭፡

ሌላ ፡ ተራራንም ፡ አየሁ ።
፳፮፤ በመካከላቸውም ፡ ጥልቅ ፡ ቈላ ፡ አለ ። (አሕ
ዛብ ፡ ናቸው ፡ ) ስፋት ፡ የለውም ፡ ( ስፉሕ ፡
አእምሮ ፡ የላቸውም ፡ ) ውሀውም ፡ ለቧ ፡
እንደ ፡ ፈሰሰ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ይፈሳል ።
(ትእምርቱ ፡ ለእስራኤል ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፡ ለአ
ሕዛብም ፡ ይነገራል ። )
፳፯፤ በዚህም ፡ በሁለተኛው ፡ ተራራ ፡ ምዕራብ ፡ አጠ
ገብ ፡ ከሱ ፡ የሚያንስ ፡ ተራራ ፡ አለ ። (አርሞን
ዔም ፡ ነው ፡ ) ርዝመት ፡ የለውም ፡ በመካከላቸ
ውም ፡ በበታቹ ፡ ቆላ ፡ አለ ።
፳፰፤ በሦስቱ ፡ ተራሮች ፡ ዳርቻ ፡ አጠገብ ፡ ጥልቅ ፡
የሆኑ ፡ የደረቁ ፡ ሌሎች ፡ ቈላዎች ፡ አሉ ።
፳፱፤ ቈላዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ጥልቆች ፡ ናቸው ፡ ስፋት ፡ የለ
ውም ፡ ከጽኑ ፡ ደንጊያ ፡ የተገኘ ፡ ጽኑ ፡ አለት ፡
ደንጊያ ፡ አለ ። ( ከአሕዛብ ፡ የተወለዱ ፡ አሕ
ዛብ ፡ )
፴፤ በነሱ ፡ ላይ ፡ እንጨት ፡ ይተከላል ፡ (ሕግ ፡ ነው ፡ )
የአሕዛብን ፡ ነገር ፡ አደነቅሁ ፡ የሌላውንም ፡
ነገር ፡ አደነቅሁ ፡ ( እስራኤል ፡ ) ይልቁንም ፡
የአሕዛብን ፡ ነገር ፡ አደነቅሁ ።
፴፩፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ይች ፡ የተባረከች ፡ ሁለመናዋ ፡
እንጨቶችን ፡ የተመላች ፡ ይቺ ፡ ምድር ፡ ለምን ፡
ተፈጠረች ። ( መንግሥት ፡ )
፴፪፤ ይችስ ፡ የተረገመች ፡ ቈላ ፡ በመካከላቸው ፡
ለምን ፡ ተፈጠረች ።
፴፫፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ ከከበሩ ፡ ከመላ
እክት ፡ አንዱ ፡ ኡራኤል ፡ መለሰልኝ ፡ ይች ፡
የተረገመች ፡ ቈላ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ሊኖሩበት ፡
ለተረገሙ ፡ ሰዎች ፡ ተፈጠረች ፡ አለኝ ።
፴፬፤ ( ገሃነም ፡ ) በቃላቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡
የማይገባ ፡ ነገርን ፡ የሚናገሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
በዚያ ፡ በታ ፡ ይሰበሰባሉ ።
፴፭፤ በጌትነቱ ፡ ጭንቅ ፡ ነገርን ፡ ስለ ፡ ተናገሩ ፡ በዚያ ፡
መላእክት ፡ ይሰበስቧቸዋል ፡ በታቸውም ፡
ይህ ፡ ነው ።
፴፮፤ በፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ለዘላለሙ ፡ በጻድቃን ፡ ፊት ፡
በውነት ፡ የሚቀበሉት ፡ የመከራቸው ፡ ምሳሌ ፡
በነሱ ፡ ይሆንባቸዋል ።
፴፯፤ ለሰው ፡ የሚያዝኑ ፡ የሚራሩ ፡ ጻድቃንም ፡ ለዘ
ላለም ፡ የሚነግሥ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታን ፡
በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በዚያ ፡ በታ ፡ አመሰገንሁት ።
፴፰፤ በተፈረደባቸውም ፡ ወራት ፡ እንዳደላቸው ፡
በቸርነቱ ፡ ያመሰግኑታል ።
፴፱፤ እኔም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታን ፡
አመሰገንሁት ፡ ጌትነቱንም ፡ ተናገርሁለት ፡ ለገ
ናናነቱም ፡ እንደሚገባ ፡ መጠን ፡ ስሙን ፡
ጠራሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

፩፤ ከዚያ ፡ በመድበራ ፡ ተራራ ፡ መካከል ፡ ወደ ፡
ምሥራቅ ፡ ሄድሁ ።
፪፤ ምድረ ፡ በዳውንም ፡ ብቻ ፡ አየሁ ። (እንደ ፡ አብ
ረንታንት ፡ )
ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ እንጨት ፡ ፍሬ ፡ የተገኙ ፡ ፫፤
እንጨቶችን ፡ ተመልቷል ።
ውሀም ፡ ከወደላይ ፡ ይመነጫል ፡ ሻሻቴውም ፡ ፬፤
በገዞቶ ፡ ይታያል ።
በመስዕ ፡ በኩል ፡ እንደ ፡ ፈሰሰ ፡ ወደ ፡ ምዕራ ፭፤
ብም ፡ ይፈሳል ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ አራቱ ፡ ማዕ
ዘን ፡ ይሄዳል ፡ ከዚያም ፡ ውሀና ፡ ጠል ፡ ይገ
ኛል ። (ትእምርት ፡ ነው ፡ )
ከመድበራ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ በታ ፡ ሄጀ ፡ ወደዚህ ፡ ፮፤
ተራራ ፡ ምሥራቅ ፡ ቀረብሁ ።
በዚያም ፡ ሕግ ፡ የሚጠበቅባቸው ፡ እንጨቶ ፯፤
ችን ፡ አየሁ ፡ ይልቁንም ፡ የከርቤና ፡ የነጭ ፡
ዕጣን ፡ መዓዛ ፡ ያለባቸው ፡ የቅመም ፡ እንጨቶ
ችን ፡ አየሁ ፡ እንጨቶችም ፡ አይመሳሰሉም ።
እነሱንም ፡ ካየሁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ፰፤
ተራራ ፡ ሄድሁ ፡ ፈጽሚም ፡ የራቅሁ ፡ አይደለ
ሁም ።
የማይገታ ፡ ውሀ ፡ ያለባቸው ፡ ሌላ ፡ የቈላዎች ፡ ፱፤
በታን ፡ አየሁ ።
ያማረ ፡ እንጨትንም ፡ አየሁ ፡ ሽታውም ፡ እንደ ፡ ፲፤
ለውዝ ፡ ሽታ ፡ ነው ።
በነዚህ ፡ ቈላዎች ፡ አጠገብም ፡ መዓዛ ፡ ያለው ፡ ፲፩፤
ሽታ ፡ አየሁ ።
እኒህን ፡ ካየሁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ቀረ ፲፪፤
ብሁ ፡ በውስጡ ፡ እንጨቶች ፡ ያሉበት ፡ ሌላ ፡
ተራራንም ፡ አየሁ ።
ግሬራ ፡ ከልበኔም ፡ እንደሚባል ፡ እንደ ፡ ነቂጥሮ ፡ ፲፫፤
ያለ ፡ ውሀ ፡ ይፈሳል ።
በዚያው ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ሆኜ ፡ ሌላ ፡ ተራራ ፡ ፲፬፤
አየሁ ፡ በውስጡም ፡ ዋግራ ፡ የሚባሉ ፡ እንጨ
ቶች ፡ አሉበት ።
እኛም ፡ እንጨቶች ፡ ከርካዕ ፡ የሚባል ፡ ሽቱ ፡ ፲፭፤
የተመሉ ፡ ጽናትንም ፡ ያገኙ ፡ ናቸው ፡ ይህን
ንም ፡ ሽቱ ፡ በቈረጡት ፡ ጊዜ ፡ ከሽቱ ፡ ሁሉ ፡
ይበልጣል ።
እነዚህን ፡ ሽቶች ፡ ካየሁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ መስዕ ፡ ፲፮፤
እየተመለከትሁ ፡ ወደ ፡ ተራሮች ፡ ሄድሁ ።
ያማረ ፡ ሽቱን ፡ መዓዛ ፡ ያላቸው ፡ እንጨቶች ፲፯፤
ንም ፡ ቀናንሞስ ፡ የሚባል ፡ ሽቱን ፡ ፕፕሬ ፡
የሚባል ፡ ሽቱን ፡ የተመሉ ፡ ሰባቱን ፡ ተራራ
ዎች ፡ ሄድሁ ።
ከዚያም ፡ በነዚያ ፡ ተራሮች ፡ ላይ ፡ ርቄ ፡ ወደ ፡ ፲፰፤
ምሥራቅ ፡ ሄድሁ ።
ወደ ፡ ኤርትራ ፡ ባሕርም ፡ ሄድሁ ፡ ከዚያም ፡ ፲፱፤
በታ ፡ የራቅሁ ፡ ሆንሁ ።
ዙጡኤል ፡ በሚባል ፡ መልአክ ፡ (ዓቃቤ ፡ ገነት ፡ ፳፤
ነው ፡ ) በላይ ፡ አልፌ ፡ ሄድሁ ፡ በቸርነቱም ፡
ወደምትወረስ ፡ ገነት ፡ መጣሁ ።
ከኒህ ፡ እንጨቶች ፡ ወዲያ ፡ ብዙዎች ፡ ታላላ ፳፩፤
ቆች ፡ እንጨቶችን ፡ በዚያ ፡ በቅለው ፡ አየሁ ።
ሽታቸውም ፡ ያማረ ፡ ሲሆን ፡ ታላላቆች ፡ ናቸው ፡ ፳፪፤
ብርሃናቸውም ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ እነሱም ፡ ያበራሉ ።
ከሱ ፡ በልተው ፡ ታላቅ ፡ ጥበብን ፡ የሚያውቁ ፡ ፳፫፤
በት ፡ የጥበብ ፡ እንጨትን ፡ አየሁ ፡ ተረርቃ

ሞም ፡ ይመስላል ።
፳፬፤ ፍሬውም ፡ እንደ ፡ ወይን ፡ ዘለላ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡
ነው ፡ የዚያም ፡ እንጨት ፡ ሽታው ፡ ሄዶ ፡ ከሩቅ ፡
ይደርሳል ።
፳፭፤ ያማረ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ሊያውትም ፡ ደስ ፡ እንደ
ማሰኘቱ ፡ ይህ ፡ እንጨት ፡ ያማረ ፡ ነው ፡ አልሁ ።
፳፮፤ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ የከበረ ፡ መልአኩ ፡ ሩፋኤ
ልም ፡ መለሰልኝ ።
፳፯፤ ካንተ ፡ አስቀድመው ፡ የተፈጠሩ ፡ ባልቴት ፡
እናትህና ፡ ሽማግሌ ፡ አባትህ ፡ ( አዳምና ፡
ሔዋን ፡ ) ከሱ ፡ የበሉለት ፡ ጥበብን ፡ የሚገልጥ ፡
ዕፀ ፡ በለስ ፡ ይህ ፡ ነው ።
፳፰፤ ከሱም ፡ በልተው ፡ ክፉን ፡ ጥበብን ፡ አወቁት ፡
ዓይኖቻቸውም ፡ ተገለጡ ፡ ዕራቁታቸውንም ፡
እንዳለ ፡ አወቁ ፡ ከገነትም ፡ ተሰደዱ ፡ አለኝ ።
፳፱፤ ከዚያ ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ሄድሁ ፡
በዚያም ፡ ቦታ ፡ ታላላቅ ፡ አውሬዎችን ፡ አየሁ ።
፴፤ አንዱ ፡ ካንዱም ፡ ልውጥ ፡ ነው ፡ የወፎችም ፡
ፊታቸው ፡ ይለዋወጣል ፡ ጠጕራቸው ፡ ቃላቸ
ውም ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ይለዋወጣል ።
፴፩፤ በነዚህ ፡ አውሬዎችም ፡ አጠገብ ፡ በምድር ፡ ዳርቻ ፡
ሰማይ ፡ በላዩ ፡ ያረፈበት ፡ አድማስን ፡ የተከፈቱ ፡
ደጃፎችንም ፡ አየሁ ።
፴፪፤ የሰማይ ፡ ከከቦችንም ፡ እንዲወጡ ፡ አየሁ ፡ ከዋ
ክብት ፡ የሚወጡባቸው ፡ ደጃፎችንም ፡ ቈጠ
ርሁ ።
፴፫፤ የየአንድ ፡ አንዳንዱን ፡ መውጫ ፡ ሁሉ ፡ በየቍ
ጥራቸው ፡ ጻፍሁ ፡ ስማቸውን ፡ አናኗራቸውን ፡
ጊዜያቸውን ፡ ወራታቸውን ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡
መልአኩ ፡ ዑራኤል ፡ እንዳሳየኝ ፡ በንድነት ፡
ጻፍኩ ።
፴፬፤ ሁሉንም ፡ ለኔ ፡ አሳየኝ ፡ ጻፈው ፡ ዳግመኛ ፡
ስማቸውን ፡ ሥራታቸውንም ፡ ጻፈልኝ ።
፴፭፤ ከዚያ ፡ ተነሥቼ ፡ በምድር ፡ ዳርቻ ፡ ወደ ፡ መስዕ ፡
ሄድኩ ፡ በዚያም ፡ ሳለሁ ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡
ዳርቻ ፡ የሚያበሩና ፡ ታላቅ ፡ ተአምራትን ፡
አየሁ ።
፴፮፤ ከዚያም ፡ ቦታ ፡ ሳለሁ ፡ የተከፈቱ ፡ የሰማይ ፡
ደጃፎችን ፡ አየሁ ፡ ሦስቱም ፡ ገጹ ፡ በሰማይ ፡
ናቸው ፡ ከነዚያም ፡ ነበያ ፡ አንዳንዱ ፡ ነፍሶች ፡
ይወጣሉ ።
፴፯፤ በመስዕ ፡ በክረምት ፡ ነፋስ ፡ በነፈሰ ፡ ጊዜ ፡ ቀቅ ፡
በረዶ ፡ ውርጭም ፡ ቀማም ፡ ጤዛም ፡ ዝናምም ፡
ይፈሳል ፡ ከሦስቱ ፡ በንዲቱ ፡ መስኮት ፡ በበጎ ፡
ይነፍሳል ።
፴፰፤ በሁለቱ ፡ ሁሉ ፡ መስኮቶች ፡ ግን ፡ በነፈሱ ፡
ጊዜ ፡ በኃይል ፡ ይነፍሳሉ ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡
ጭንቅ ፡ መከራ ፡ ይሆናል ፡ እነሱም ፡ በኃይል ፡
ይነፍሳሉ ።
፴፱፤ ከዚያም ፡ ቦታ ፡ በምድር ፡ ዳርቻ ፡ ወደ ፡ ፀሐይ ፡
መግቢያ ፡ ሄድሁ ፡ በመስኮቶቹ ፡ ልክ ፡ በመው
ጫውም ፡ ልክ ፡ በምሥራቅ ፡ እንዳየሁ ፡ በዚ
ያም ፡ ቦታ ፡ የተከፈቱ ፡ ሦስት ፡ መስኮቶችን ፡
አየሁ ።

ከዚያም ፡ ቦታ ፡ በምድር ፡ ዳርቻ ፡ ወደ ፡ ዓዜብ ፡ ፵፤
ሄድሁ ።
በዚያም ፡ ቦታ ፡ የተከፈቱ ፡ ሦስት ፡ የሰማይ ፡ ፵፩፤
መስኮቶችን ፡ አየሁ ፡ ከዚያም ፡ ቦታ ፡ ዋዕይ ፡
ጤዛ ፡ ዝናም ፡ ነፋስም ፡ ይነፍሳል ።
ከዚያም ፡ ቦታ ፡ ተነሥቼ ፡ በሰማይ ፡ ዳርቻ ፡ ወደ ፡ ፵፪፤
ፀሐይ ፡ መውጫ ፡ ሄድሁ ።
በዚያም ፡ ቦታ ፡ ሳለሁ ፡ በፀሐይ ፡ መውጫ ፡ ፵፫፤
በክረምት ፡ የተከፈቱ ፡ ሦስት ፡ የሰማይ ፡ ደጃፎችን ፡
አየሁ ።
በተናናሽ ፡ ደጃፎችም ፡ ላይ ፡ ከነዚህ ፡ ደጃፎች ፡ ፵፬፤
በያንዳንዱ ፡ ተናናሾች ፡ የሰማይ ፡ ከከቦች ፡ ይገ
ቡበታል ።
በታየችላቸውም ፡ ጎዳና ፡ ወደ ፡ ፀሐይ ፡ መግ ፵፭፤
ቢያ ፡ ይሄዳሉ ።
ይህነንም ፡ በየሁ ፡ ጊዜ ፡ ፈጣሪን ፡ አመሰገንሁ ፡ ፵፮፤
የፍጥረቱን ፡ ገናንነት ፡ ለሰዎች ፡ ሰውነቶችና ፡
ለመላእክት ፡ ሲገልጥ ፡ የሚያበሩና ፡ ታላላቅ ፡
ተአምራቶችን ፡ ያደረገ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታ
ንም ፡ በየጊዜው ፡ አመሰግነዋለሁ ።
ፍጥረቱን ፡ ያመሰግኑ ፡ ዘንድ ፡ ፍጥረቱም ፡ ፵፯፤
ሁሉ ፡ የኃይሉን ፡ ሥራ ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡
የሆነ ፡ የቃሉንም ፡ ሥራ ፡ ያመሰግኑ ፡ ዘንድ ፡
እሱንም ፡ ለዘላለሙ ፡ ያመሰግኑት ፡ ዘንድ ፡ ይኸ
ንን ፡ አደረገ ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

የያሬድ ፡ ልጅ ፡ ሄኖክ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ያየው ፡ ፩፤
ጥበብ ፡ ያለበት ፡ ራዕይ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ያሬድን ፡
የመላልኤል ፡ ልጅ ፡ አለው ፡ መላልኤልን ፡ የቃ
ይናን ፡ ልጅ ፡ አለው ፡ ቃይናንን ፡ የሄኖስ ፡ ልጅ ፡
አለው ፡ ሄኖስን ፡ የሴት ፡ ልጅ ፡ አለው ፡ ሴትን ፡
የአዳም ፡ ልጅ ፡ አለው ።
በዚህም ፡ ዓለም ፡ ላሉ ፡ ሰዎች ፡ እናገረው ፡ ፪፤
ዘንድ ፡ የጀመርሁት ፡ የዘጠኙ ፡ ሕገጋት ፡ አበ
ጋዝ ፡ ይህ ፡ ኢታምልክ ፡ ነው ።
የቀድሞ ፡ ሰዎች ፡ ይኸንን ፡ ነገር ፡ ሰሙ ፡ በኋ ፫፤
ላም ፡ የተነሣችሁ ፡ ሰዎች ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡
ፊት ፡ የምናገረው ፡ የከበረ ፡ የኢታምልክን ፡
ነገር ፡ አስተውሉ ።
የለዚህ ፡ የአበው ፡ ነገራቸው ፡ ከዘጠኙ ፡ ሕገ ፬፤
ጋት ፡ ኢታምልክ ፡ ይበልጣል ፡ ማለት ፡ ነው ፤
እኛም ፡ በኋላ ፡ የተነሣን ፡ ሰዎች ፡ ከዘጠኙ ፡
ሕገጋት ፡ ኢታምልክ ፡ ትበልጣለች ፡ ማለትን ፡
አንከለክልም ።
እኔ ፡ እንዳሰብሁት ፡ ዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ፭፤
የሕይወት ፡ እድል ፡ ከሱ ፡ የተሰጠኝ ፡ የመላእ
ክት ፡ ጌታ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ዛሬ ፡ የያዝሁት ፡
ጥበብ ፡ ከመላእክት ፡ ፊት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡
አልተሰጠኝም ፡ ነበር ።
ሦስት ፡ ነገሮችም ፡ ተገለጡልኝ ። ፮፤
እኔም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ እነግ ፯፤
ራቸው ፡ ጀመር ።
መጀመሪያው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የደጋጎቹ ፡ ፰፤

ማደሪያ ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ፡ ኃዋአንም ፡ በኃጢ
አታቸው ፡ በተፈረደባቸው ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡
ዓለም ፡ ይጠፋሉ ።
፱፤ ከመላእክት ፡ ጌታ ፡ ዘንድ ፡ ሥራቸው ፡ በጸናላ
ቸው ፡ በተመረጡ ፡ ጻድቃን ፡ ፊት ፡ ጻድቅ ፡
ባሕርይ ፡ ክርስቶስ ፡ በተገለጠም ፡ ጊዜ ።
፲፤ በዚህም ፡ ዓለም ፡ ለሚኖሩ ፡ ለደናግልና ፡ ለሕ
ጋውያን ፡ ብርሃን ፡ መለኮቱ ፡ በተገለጠበት ፡
ጊዜ ።
፲፩፤ የኃጢአተኞች ፡ ማደሪያ ፡ ወዴትስ ፡ ነው ፡ የነ
ፍሳት ፡ ጌታን ፡ የከዱት ፡ ሰዎችስ ፡ ቦታቸው ፡
የት ፡ ነው ፡ አለ ።
፲፪፤ ጥንቱን ፡ ባልተወለዱ ፡ በተሻላቸው ፡ ነበር ።
(በይፈጠሩ ፡ ) የጻድቃን ፡ የተሠወሩ ፡ ክብሮቻ
ቸውም ፡ በተገለጡ ፡ ጊዜ ፡ በኃጠአተኞች ፡
ይፈረድባቸዋል ፡ ደናግልና ፡ ሕጋውያንን ፡ ከመ
በደላቸው ፡ የተነሣ ፡ ሕግን ፡ የዘነጉ ፡ ሰዎች ፡
ይታወከሉ ።
፲፫፤ ይህን ፡ ዓለም ፡ የሚገዟት ፡ ሰዎች ፡ እንግዲህ ፡
ወዲህ ፡ የሚይዙ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ አይሆኑም ።
፲፬፤ ለደናግልና ፡ ለከበሩ ፡ ሕጋውያን ፡ የመላእክት ፡
ጌታ ፡ የባሕርይ ፡ ክብሩ ፡ ተገልጧልና ፡ የቅዱ
ሳንን ፡ ፊት ፡ ማየት ፡ አይችሉም ።
፲፭፤ የጸኑ ፡ ነገሥታቱም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ይጠፋሉ ፡
በከበሩና ፡ በደጋጎች ፡ ሰዎች ፡ እጅም ፡ ይወድ
ቃሉ ።
፲፮፤ የነሱ ፡ የሚሆን ፡ ደኅንነታቸው ፡ ጨርሶ ፡ ጠፍ
ቷልና ፡ ከዚያ ፡ ከመከራው ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡
ዘንድ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ለነሱ ፡ የሚያማ
ልድ ፡ የለም ።
፲፯፤ በዚህ ፡ ወራት ፡ እንዲህ ፡ ይሆናል ፡ የከበሩና ፡
የተመረጡ ፡ የሴት ፡ ልጆች ፡ ከደብር ፡ ቅዱስ ፡
ይወርዳሉ ፡ ልጆቻቸውም ፡ ከቃየል ፡ ልጆች ፡
ጋር ፡ አንድ ፡ ይሆናሉ ።
፲፰፤ በዚያ ፡ ወራት ፡ ሄኖክ ፡ ቍጣና ፡ ቅናት ፡ የተጻፈ
ባቸው ፡ መጻፎችን ፡ ሁከትና ፡ ችኩላም ፡ የተጻ
ፈባቸው ፡ መጽሐፎችን ፡ ያዘ ።
፲፱፤ የመላእክትም ፡ ጌታ ፡ ይቅርታ ፡ አይደረግላቸ
ውም ፡ አለ ።
፳፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ጥቅል ፡ ነፋስና ፡ ደመና ፡ ከዚህ ፡
ዓለም ፡ ወስዶ ፡ በሰማይ ፡ ዳርቻ ፡ በአድማስ ፡
አኖረኝ ።
፳፩፤ በዚያም ፡ ቦታ ፡ ሌላ ፡ ራዕይ ፡ አየሁ ፡ የጻድቃንን ፡
ማደሪያቸውን ፡ የቅዱሳንን ፡ ቦታቸውን ፡
አየሁ ።
፳፪፤ ከዚያም ፡ ቦታ ፡ ዓይኖቼ ፡ ከመላእክት ፡ ጋራ ፡
የሚኖሩበት ፡ ማደሪያቸውን ፡ ከቅዱሳንም ፡
ጋራ ፡ የሚኖሩበት ፡ ቦታቸውን ፡ አዩ ።
፳፫፤ ስለ ፡ ሰውም ፡ ልጆች ፡ ፈጽመው ፡ ይለምናሉ ፡
ይጸልያሉ ።
፳፬፤ ቸርነት ፡ በፊታቸው ፡ እንደ ፡ ውኃ ፡ በዝቶ ፡
ይፈሳል ፡ (ይሰጣል ፡ ) ይቅርታም ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ እንደ ፡ ጠል ፡ ይሆናል ። (በዝቶ ፡ ይሰ
ጣል ፡) በመካከላቸው ፡ ለዘላለሙ ፡ እንዲህ ፡
ይሆናል ።
በዚያም ፡ ወራት ፡ ሃይማኖትንና ፡ ምግባርን ፡ ፳፭፤
የያዙ ፡ የደናግልን ፡ ቦታ ፡ ዓይኖቼ ፡ አዩ ።
በዘመናቸውም ፡ ቸርነቱ ፡ ይደረግላቸዋል ፡ ለደ ፳፮፤
ናግልና ፡ ለሕጋውያንም ፡ ለዘላለሙ ፡ በሱ ፡
ፊት ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የላቸውም ።
በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ሥልጣን ፡ የተያዘ ፡ ማደሪ ፳፯፤
ያቸውን ፡ አየሁ ።
ደናግልና ፡ ሕጋውያንም ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ እንደ ፡ ፳፰፤
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብርሃን ፡ ያበራሉ ።
አፋቸውም ፡ ምስጋናን ፡ ይመላል ፡ ከንፈሮቻቸ ፳፱፤
ውም ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ስምን ፡ ያመሰግናሉ ።
በፊቱ ፡ የሚሰጥ ፡ ቸርነት ፡ አያልቅም ፡ በፊ ፴፤
ቱም ፡ የሚሠራ ፡ ቅንነት ፡ አይፈጸምም ።
በዚያም ፡ ቦታ ፡ እኖር ፡ ዘንድ ፡ ወደድሁ ፡ ያን ፴፩፤
ንም ፡ ቦታ ፡ ልቡናዬ ፡ ወደደችው ።
በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፈቃድ ፡ ስለኔ ፡ ጸንቶአልና ፡ ፴፪፤
ጥንቱንም ፡ እድል ፡ ፈንታዬ ፡ በዚያ ፡ ሆነ ።
በዚያም ፡ ወራት ፡ የመላእክት ፡ ጌታን ፡ ስም ፡ ፴፫፤
አክብሬ ፡ አመሰገንሁ ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ እን
ደወደደ ፡ በፍጹም ፡ ምስጋና ፡ እሱ ፡ አጽንቶኛ
ልና ፡ ፍጹም ፡ ምስጋና ፡ አቀረብሁ ።
በዚያም ፡ ቦታ ፡ ዓይኖቼ ፡ ትዝ ፡ ብለው ፡ አዩ ። ፴፬፤
የተመሰገነ ፡ ነው ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላ ፴፭፤
ለሙ ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡ እያልሁ ፡ ፈጽሜ ፡
አመሰገንሁት ።
በፊቱም ፡ በሚደረገው ፡ ቸርነት ፡ ፍጻሜ ፡ የለ ፴፮፤
ውም ።
ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ምንም ፡ እን ፴፯፤
ደሆነ ፡ እሱ ፡ ያውቃል ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡
የሚሆነውንም ፡ ነገር ፡ ያውቃል ።
የማያርፉ ፡ በጌትነትህም ፡ ፊት ፡ የሚቆሙ ፡ ፴፰፤
መላእክት ፡ ያመሰግኑሃል ።
ፈጽመው ፡ ያመሰግናሉ ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፴፱፤
ንጹሕ ፡ ክቡር ፡ ልዩ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ የፈጠርኸ
ውም ፡ ፍጥረት ፡ ምድርን ፡ ይመላል ፡ እያሉ ፡
እሱን ፡ ያከብራሉ ።
በዚያም ፡ ቦታ ፡ የማያርፉ ፡ መላእክትን ፡ ሁሉ ፡ ፵፤
በፊቱ ፡ ቁመው ፡ ሲያመሰግኑ ፡ ዓይኖቼ ፡ አዩ ።
አንተ ፡ የከበርህ ፡ ነህ ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፵፩፤
ስሙም ፡ ለዘላለም ፡ የከበረ ፡ ነው ፡ ይላሉ ።
ቀና ፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ እስቲሳነኝም ፡ ድረስ ፡ ፊቴ ፡ ፵፪፤
ተለወጠ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ፈጽመው ፡ የበዙ ፡ የብዙ ፡ ፩፤
ብዙ ፡ የሚሆኑ ፡ መላእክትን ፡ አየሁ ፡ በመላእ
ክት ፡ ጌታ ፡ ጌትነት ፡ ፊት ፡ የሚቆሙ ፡ መላ
እክትም ፡ ቍጥር ፡ ስፍር ፡ የላቸውም ።
በነፋሳት ፡ ጌታ ፡ ሥልጣን ፡ በተጠበቁ ፡ ባራቱ ፡ ፪፤
ማዕዘን ፡ በፊቱ ፡ ለሚቆሙ ፡ መላእክት ፡ ተለ
ይተው ፡ ሌሎች ፡ አራቱ ፡ መላእክትን ፡ አየሁ ።
ስማቸውንም ፡ አወቅሁ ፡ ስማቸውንም ፡ የነገ ፫፤
ረኝ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ የመጣ ፡ መልአኩ ፡ ነው ።

፬፤ የተሠወረውንም ፡ ሁሉ ፡ ገለጠልኝ ፡ በክብር ፡
ባለቤት ፡ ጌታም ፡ ፊት ፡ ሲያመሰግኑ ፡ የነዚያን ፡
የአራቱን ፡ መላእክት ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ፡ አለ ።
፭፤ መጀመሪያውም ፡ ቃል ፡ የነፍሳት ፡ ጌታን ፡ ለዘ
ላለሙ ፡ ያመሰግነዋል ። (ሚካኤል ፡ ነው ፡)
፮፤ ክርስቶስን ፡ ሲያመሰግነው ፡ ለመላእክት ፡ ጌታ ፡
ያመኑ ፡ ደናግልንም ፡ ሲያመሰግናቸው ፡ ሁለተ
ኛውን ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ። (ሩፋኤል ፡ ነው ፡)
፯፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ስለሚኖሩ ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡
ስምም ፡ አምነው ፡ ስለሚለምኑ ፡ ሰዎች ፡ ፈጽ
መው ፡ ሲለምኑ ፡ ሦስተኛውን ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ።
(ገብርኤል ፡ ነው ፡)
፰፤ ሰይጣናትን ፡ አስወጥቶ ፡ ሲሰዳቸው ፡ አራተኛ
ውንም ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ። (ፋኑኤል ፡ ነው ፡)
፱፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎችን ፡ ያጣሏቸው ፡
ዘንድ ፡ ወደ ፡ መላእክት ፡ ጌታ ፡ እንዲገቡ ፡
አይተዋቸውም ።
፲፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ የሚኖር ፡ ፍቅር ፡
አንድነት ፡ ያለው ፡ መላኩን ፡ ጠየቅሁት ፡ የተ
ሠወረውንም ፡ ሁሉ ፡ የገለጠልኝ ፡ እሱ ፡ ነው ።
፲፩፤ ፊታቸውን ፡ ያየሁት ፡ ቃላቸውንም ፡ የሰማኋ
ቸው ፡ እኔም ፡ የቈጠርኋቸው ፡ እነሀ ፡ አራቱ ፡
እነማናቸው ፡ ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።
፲፪፤ እሱም ፡ መጀመርያው ፡ ቃል ፡ ይቅር ፡ የሚል ፡
ከመዓትም ፡ የራቀ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ነው ፡
አለኝ ።
፲፫፤ ሁለተኛውም ፡ በበሽታው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በሰው ፡
ልጆችም ፡ ቍስል ፡ ላይ ፡ የተሾመ ፡ ቅዱስ ፡
ሩፋኤል ፡ ነው ፡ አለኝ ።
፲፬፤ ሦስተኛውም ፡ በመላእክት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የተ
ሾመ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ነው ፡ አለኝ ።
፲፭፤ አራተኛውም ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ የሚወርሱ ፡
ሰዎች ፡ ተስፋ ፡ ሊሆን ፡ ንስሐ ፡ በሚገቡ ፡ ሰዎች ፡
ላይ ፡ የተሾመ ፡ ፋኑኤል ፡ ነው ፡ አለኝ ።
፲፮፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አራቱ ፡ መላክተ
ኞች ፡ እነሀ ፡ ናቸው ፡ በዚያም ፡ ወራት ፡ አራ
ቱን ፡ ቃሎች ፡ ሰማሁ ፡ አለ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

፩፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በሰማይ ፡ የተሠወሩ ፡ ምሥ
ጢሮችን ፡ ሁሉ ፡ አየሁ ።
፪፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ እየተከፈለች ፡ እንድትሰጥ ፡
ጻድቃንም ፡ በሠሩት ፡ ሥራቸው ፡ ዋጋቸው ፡
እየተመጠነ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ አየሁ ።
፫፤ በዚያም ፡ በታ ፡ የደናግልን ፡ ማደሪያቸውን ፡
የሕጋውያንንም ፡ ማደሪያቸውን ፡ አየሁ ።
፬፤ የመላእክት ፡ ጌታን ፡ ስም ፡ የካዱ ፡ ኃጥአንም ፡
ሁሉ ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ወጥተው ፡ ሲሰ
ደዱ ፡ ዓይኖቼ ፡ አዩ ።
፭፤ መላእክት ፡ ስበው ፡ ያወጧቸዋል ፡ በመላእክት ፡
ጌታ ፡ በወጣች ፡ መቅሠፍትም ፡ ተይዘው ፡
ቁመው ፡ መቅረት ፡ የላቸውም ።
፮፤ በዚያም ፡ በታ ፡ የነጐድጓድንና ፡ የመብረቆችን ፡
በታ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሊነፍሱ ፡ ተመጥነው ፡
እንዲወጡ ፡ የነፋሶችንም ፡ በታ ፡ የጠልና ፡ የደ
መናዎችንም ፡ በታ ፡ ዓይኖቼ ፡ አዩ ።
በዚያም ፡ በታ ፡ የሚወጡበትን ፡ አየሁ ፡ ከደ ፯፤
መናውም ፡ የምድር ፡ ትቢያዎች ፡ ዝናሙን ፡
ይጠግባሉ ።
በዚያ ፡ በታ ፡ የተዘጉ ፡ በታዎችን ፡ አየሁ ፡ ከነ ፰፤
ዚያም ፡ ነፋሳት ፡ እየተመጠኑ ፡ ይወጣሉ ።
የበረድን ፡ በታ ፡ የጉምንም ፡ በታ ፡ አየሁ ፡ የደ ፱፤
መናዎችንም ፡ በታ ፡ አየሁ ፡ ደመናውም ፡ ከጥ
ንት ፡ጀምሮ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።
ከየትም ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡ ወዴትም ፡ እንዲገቡ ፡ ፲፤
የጨረቃንና ፡ የፀሐይን ፡ በታ ፡ አየሁ ፡ መመለ
ሻቸውም ፡ የበራ ፡ ነው ።
አንዱም ፡ ከንዱ ፡ እንዲከብር ፡ አወቅሁ ፡ አካሄ ፲፩፤
ዳቸውም ፡ በብርሃን ፡ የከበረ ፡ ነው ፡ ቀን ፡ አያ
ተርፉ ፡ አይጨምሩም ፡ ከመሄዳቸውም ፡ አያ
ጕሉም ።
ጸንተው ፡ በሚኖሩበትም ፡ ሥርዓት ፡ አንዱ ፡ ፲፪፤
ከንዱ ፡ ጋራ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ይጠብቃሉ ።
ፀሐይ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ይወጣል ፡ በነፋ ፲፫፤
ሳት ፡ ጌታ ፡ ትእዛዝም ፡ ጕዳናውን ፡ ያደርጋል ፡
(ይፈጽማል ፡) ስሙም ፡ ለዘላለሙ ፡ ጸንቶ ፡
ይኖራል ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የተሠወረ ፡ የተገለጠ ፡ የጨረ ፲፬፤
ቃን ፡ ጎዳና ፡ አየሁ ፡ የጎዳናውንም ፡ መሄጃ ፡
በዚያ ፡ በታ ፡ በሌትና ፡ በቀን ፡ ይጨርሳል ።
በነፋሳት ፡ ጌታም ፡ ትእዛዝ ፡ አንዱ ፡ ሁለተኛ ፲፭፤
ውን ፡ ያየዋል ። (ጨረቃና ፡ ፀሐይ ፡)
ለነሱ ፡ ዕረፍታቸው ፡ ምስጋናቸው ፡ ነውና ፡ ፲፮፤
ፈጽመው ፡ ያመሰግናሉ ፡ ከምስጋናውም ፡ አያ
ርፉም ፡ ለሚያበራ ፡ ፀሐይም ፡ ብዙ ፡ መለዋ
ወጥ ፡ አለውና ፡ ለበጎዎች ፡ በረከት ፡ ነው ፡ ለክ
ፉዎችም ፡ መርገም ፡ ነው ።
የጻድቃን ፡ ብርሃን ፡ ነው ፡ የጨረቃም ፡ ጎዳና ፡ ፲፯፤
መመላለሻ ፡ በጨለማና ፡ በብርሃን ፡ መከከል ፡
ድንበር ፡ በጠፈር ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ስም ፡
ላላመኑ ፡ ኃጥአን ፡ ግን ፡ ጨለማ ፡ ነው ፡ አለ ።
ለሰውም ፡ ዕውቀትን ፡ አደለ ፡ በቸርነቱ ፡ ስም ፡ ፲፰፤
ያመኑ ፡ የጻድቃንን ፡ ዕውቀትንም ፡ አጠና ።
ሁሉን ፡ መርምሮ ፡ የሚያውቅ ፡ ገገር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ፲፱፤
አለቃው ፡ አይከለክልምና ፡ ንጉሡም ፡ መከል
ከል ፡ አይችልምና ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ እሱ ፡ በፈ
ቃዱ ፡ ይገዛል ፡ አለ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

ጥበብ ፡ የምታድርበት ፡ በታን ፡ አላገኘችም ፡ ፩፤
(ሕግ ፡) ማደሪያዋም ፡ በሰማይ ፡ አለ ። (መላእ
ክት ፡)
ሕግም ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ ቀጥላ ፡ ቀጥላ ፡ ልታ ፪፤
ድር ፡ ወጣች ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ማደሪያ ፡ አላገኘ
ችም ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ማደሪያዋ ፡ ወደ ፡ መላእክት ፡
ልቡና ፡ ተመለሰች ፡ በመላእክትም ፡ መከከል ፡
አደረች ።
ኃጢአት ፡ ከማደሪያዎቿ ፡ ከአጋንንት ፡ ተገኘች ፡ ፫፤

ያልወደደችው ፡ የሔዋንና ፡ የአዳምን ፡ ልቡ
ናን፡ አገኘች ፡ ገነናም፡ በምድረ፡ በዳ፡ ጠል፡ በተ
ጠማች ፡ ምድር ፡ እንዲያድር ፡ እሷም ፡ በነሱ ፡
አደረች ።
፬፡ ሌሎች ፡ መብረቆችን ፡ የሰማይ ፡ ከከቦችንም ፡
አየሁ ። (መምህራንን ፡ ደቀ ፡ መዝሙሮችን ፡)
፭፡ ሁሉንም ፡ በየስማቸው ፡ ሲጠራቸው ፡ እነሱም ፡
ሲሰሙት ፡ አየሁ ።
፮፡ በአእምሮ ፡ በሰፋ ፡ ልቡናቸው ፡ በሥሩትም ፡
ምግባር ፡ ትሩፋታቸው ፡ የሥራቸው ፡ ዋጋ ፡
እየተመጠነ ፡ ሲሰጣቸው ፡ አየሁ ።
፯፡ መምህራን ፡ የሆኑበትን ፡ ከጨዋነት ፡ ወደ ፡ ነቢ
ይነት ፡ የተመለሱበትንም ፡ ቀን ፡ አየሁ ፡ መብ
ረቅ ፡ መብረቅን ፡ ይወልዳል ። (መምህር ፡ መም
ህርን ፡ ያስገኛል ፡) ከጨዋነት ፡ ወደ ፡ ነቢይነት ፡
መመለሳቸው ፡ በመላከ ፡ ውቃቢያቸው ፡ ቍጥር ፡
ነው ፡ ሃይማኖታቸውንም ፡ እስበሳቸው ፡ ይጠ
ብቃሉ ።
፰፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ የሚኖረውን ፡ የተሠወረውንም ፡
የገለጠልኝ ፡ መላኩን ፡ እኒህ ፡ ምንድናቸው ፡
ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።
፱፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ የመምራን ፡ ምሳሌ ፡ የሚ
ሆኑ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትን ፡ አሳየህ ፡ አለኝ ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ በመላእክትም ፡ ጌታም ፡ ስም ፡
ለዘላለሙ ፡ የሚያምኑ ፡ የጻድቃንም ፡ ስማቸው ፡
ይህ ፡ ነው ፡ አለኝ ።
፲፡ ስለ ፡ መብረቅ ፡ ሌሎች ፡ ራዕዮችን ፡ አየሁ ፡ ከከ
በችም ፡ መብረቅን ፡ እንዲሆኑ ፡ አየሁ ፡ (ከደቀ ፡
መዛሙርቱ ፡ መምህራን ፡ እንዲሆኑ ፡) ከነሱ ፡
ጋራ ፡ መኖር ፡ መተውን ፡ አይችሉም ።
፲፩፡ ከቅዱሳን ፡ ማደሪያ ፡ የመላእክትንም ፡ ጌታ ፡
ስም ፡ በሚክዱ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የተነገረ ፡ ሁለ
ተኛው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ።
፲፪፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አይወጡም ፡ ወደ ፡ ምድርም ፡
አይወርዱም ፡ የመላእክትን ፡ ጌታ ፡ ስም ፡ የሚ
ክዱ ፡ ፍጹም ፡ መከራ ፡ ለሚደረግበት ፡ ቀን ፡
እንደዚህ ፡ የሚጠብቁ ፡ የኃጢአተኞች ፡ እድል ፡
እንዲህ ፡ ይሆናል ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ ክርስቶስ ፡
በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ ይቀመጣል ።
፲፫፡ ሥራቸውን ፡ በታቸውንም ፡ ይመረምራል ፡
ቍጥር ፡ የላቸውም ።
፲፬፡ ልጁ ፡ ክርስቶስን ፡ በዩት ፡ ጊዜ ፡ የከበረ ፡ የተ
መሰገነ ፡ ስሙን ፡ የሚለምኑ ፡ ወዳጆቹንም ፡
ባይዋቸው ፡ ጊዜ ፡ በልቡናቸው ፡ መከከል ፡
ያለች ፡ እውቀታቸው ፡ ትጸናለች ።
፲፭፡ በዚያችም ፡ ቀን ፡ የመረጥሁት ፡ ክርስቶስን ፡
በመከከላቸው ፡ አኖረዋለሁ ፡ አለ ።
፲፮፡ ሰማይን ፡ አሳልፋታለሁ ፡ የምትመጣ ፡ መንግ
ሥተ ፡ ሰማይን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አደርጋታለሁ ፡ ዘላ
ለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ዕውቀት ፡ ይሰጣቸዋል ፡
ይችን ፡ ዓለም ፡ አሳልፋታለሁ ፡ የምትመጣይ
ቱን ፡ ዓለም ፡ ግን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አደርጋታለሁ ።
፲፯፡ ወዳጆቼን ፡ በውስጧ ፡ አኖራቸዋለሁ ። በደል
ንና ፡ ኃጢአትን ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች • ግን ፡
ወደሷ ፡ አይገቡም ፡ እኔ ፡ ባይኑ ፡ ምሕረት ፡ አይ
ቻቸዋለሁና ፡ ለወዳጆቼ ፡ ተድላውን ፡ ደስታ
ውን ፡ አጥግቤያቸዋለሁና ፡ በፊቴም ፡ በባለሟ
ልነት ፡ አኖርኋቸው ።
ሁሉንም ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ አርቃቸው ፡ ፲፰፡
ዘንድ ፡ በኃጥአን ፡ የምፈርድባት ፡ ፍርድ ፡
ወደኔ ፡ ቀረበች ።
በዚያም ፡ በታ ፡ ብሉየ ፡ መዋዕልነት ፡ ገንዘቡ ፡ ፲፱፡
የሚሆን ፡ ጌታን ፡ አየሁ ፡ ራሱም ፡ ብዝት ፡
ነጭ ፡ ነው ።
መልኩ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ መልክ ፡ የሆነ ፡ ሌላ ፡ ፳፡
ከሱ ፡ ጋራ ፡ አለ ። ( ክርስቶስ ፡ ነው ) ፡ የባሕ
ርይ ፡ ክብር ፡ የተመላ ፡ ነው ፡ ፊቱም ፡ ከከ
በሩ ፡ ከመላእክት ፡ እንዳንዱ ፡ ነው ።
ከኔ ፡ ጋራ ፡ የሚኖር ፡ የተሠወረንም ፡ ሁሉ ፡ የገ ፳፩፡
ለጠልኝ ፡ ከከበሩ ፡ ከመላእክት ፡ አንዱን ፡ ከሰው ፡
የተወለደ ፡ የዚህን ፡ የክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ጠየ
ቅሁት ።
ይህ ፡ ማነው ፡ ከወዴትስ ፡ ተገኘ ፡ ከብሉየ ፡ መዋ ፳፪፡
ዕል ፡ ከአብስ ፡ ጋራ ፡ ስለምን ፡ ተቀመጠ ፡ ብዬ ፡
ጠየቅሁት ።
ይህ ፡ ትንቢት ፡ የተነገረለት ፡ ትንቢት ፡ የተፈጸ ፳፫፡
መለት ፡ ከሰው ፡ የተወለደ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡
ብሎ ፡ መለሰልኝ ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ አብ ፡
እርሱን ፡ መርጧልና ፡ እሱ ፡ የተሠወረውን ፡ ይገ
ልጣል ።
እድሉ ፡ ሥጋ ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ በአብ ፡ ፊት ፡ ፳፬፡
ሁሉን ፡ ድል ፡ የነሣ ፡ ለዘላለሙ ፡ በሚገባ ፡ ነው ።
ይህ ፡ ያየኸው ፡ ከሰው ፡ የተወለደ ፡ ክርስቶስ ፡ ፳፭፡
ነገሥታቱን ፡ ኃያላኑን ፡ ከመቃብር ፡ ያነሣቸ
ዋል ፡ ፅኑዓኑንም ፡ ከዙፋናቸው ፡ እየገለበጠ ፡
ይጥላቸዋል ።
የፅኑዓኑንም ፡ ሥልጣን ፡ ያጠፋል ፡ የኃጥአን ፳፮፡
ንም ፡ ጥርሶች ፡ ይሰብራል ፡ ( ሥልጣን ፡ ) አክ
ብረው ፡ አላመሰገኑትምና ፡ ለሱም ፡ አልተገዙ
ለትምና ፡ ነገሥታቱንም ፡ ከዙፋናቸው ፡ እየገ
ለበጠ ፡ ይጥላቸዋል ፡ ከመንግሥታቸውም ፡
ይለያቸዋል ፡ እሱን ፡ አለማመስገናቸው ፡ መን
ግሥት ፡ ከወዴት ፡ ተሰጠችን ፡ ብለው ፡ ነው ።
የፀኑ ፡ ሰዎች ፡ ሰውነትን ፡ ያጠፋል ፡ ኃፍረት ፳፯፡
ንም ፡ ይመላቸዋል ፡ ማደሪያቸውም ፡ ጨለ
ማን ፡ ይሆንባቸዋል ።
ትሎችም ፡ ምንጣፍ ፡ ይሆኗቸዋል ፡ የመላእክ ፳፰፡
ትን ፡ ጌታ ፡ ስም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አላደረጉምና ፡
ከመቃብርም ፡ ይነሡ ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ አላደረ
ጉም ።
እነሱም ፡ የሰማይ ፡ ከከቦችን ፡ (ጻድቃን ፡) ፳፱፡
የሚገዙ ፡ ሆነዋልና ፡ ቃላቸውንም ፡ ወደ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ያደርሳሉና ፡ ይችን ፡ ዓለም ፡ ይገ
ዛሉና ፡ በዚችም ፡ ዓለም ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡
ጸንተው ፡ ይኖራሉና ።
በደል ፡ የሆነ ፡ ሥራቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ይገልጣ ፴፡
ሉና ፡ ሥራቸውም ፡ ሁሉ ፡ በደል ፡ ነውና ፡
ኃይላቸውም ፡ በባለጸግነታቸው ፡ ላይ ፡ ነውና ።

፴፩፤ ሃይማኖታቸውም ፡ በጃቸው ፡ ለሠሯቸው ፡ ለጣ
ዖታቱ ፡ ሆኗልና ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ስሙ
ንም ፡ ክደዋልና ፡፡
፴፪፤ ከሱ ፡ ማደሪያ ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ስም ፡ ካመኑ ፡
ከጻድቃንም ፡ ማደሪያ ፡ ከመንግሥት ፡ ሰማ
ያት ፡ ተሰደው ፡ ይሄዳሉ ፡፡
፴፫፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ የወዳጆቼ ፡ የጻድቃን ፡ ልመ
ናቸው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወጣች ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡
በግፍ ፡ የፈሰሰ ፡ የጻድቁም ፡ ደም ፡ በመላእክት ፡
ጌታ ፡ ፊት ፡ ተወደደ ፡፡
፴፬፤ በነዚህ ፡ ወራቶች ፡ በሰማይ ፡ የሚኖሩ ፡ ጻድ
ቃን ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ሁነው ፡ ተባብረው ፡ ያመ
ሰግናሉ ፡ ለሰው ፡ ፈጽመው ፡ ይለምናሉ ፡ ፈጣሪ
ያቸውንም ፡ ያመሰግናሉ ፡፡
፴፭፤ በግፍ ፡ የፈሰሰ ፡ የጻድቃን ፡ ደም ፡ ዋጋ ፡ ስለ
ሰጠ ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ስም ፡ አምነው ፡ ፈጽ
መው ፡ ያመሰግናሉ ፡፡
፴፮፤ የጻድቃንም ፡ ልመናቸው ፡ ለዘላለም ፡ ፍርድ ፡
ይደረግላቸው ፡ ዘንድ ፡ ትዕግሥትም ፡ ለዘላ
ለሙ ፡ ይደረግላቸው ፡ ዘንድ ፡ በመላእክት ፡
ጌታ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ ከማሰጠት ፡ የተከለከለች ፡
እንዳትሆን ፡ ነው ፡፡
፴፯፤ በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ ብሉየ ፡ መዋዕልነት ፡
ገንዘቡ ፡ የሆነ ፡ ጌታን ፡ በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ ተቀ
ምጦ ፡ አየሁት ፡ የጻድቃን ፡ ደብዳቤዎቻቸውም ፡
በፊቱ ፡ ተገለጡ ፡፡
፴፰፤ በሰማይ ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ መላእክትም ፡ ሁሉ ፡
በዙሪያው ፡ ሁነው ፡ በፊቱ ፡ ይቆማሉ ፡፡
፴፱፤ የኢታምልክ ፡ ቍጥሯ ፡ ደርሷልና ፡ የጻድቃንም ፡
ልመናቸው ፡ ተሰምቷል ፡ ተድላ ፡ ደስታን ፡
ትመላለች ፡፡
፵፤ የጻድቅ ፡ በሕርይ ፡ ክርስቶስም ፡ ደም ፡ በመላ
እክት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ ተወደደ ፡፡

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ፡፡

፩፤ በዚያም ፡ በታ ፡ የማይቈጠር ፡ እውነተኛ ፡
ምንጭን ፡ አየሁ ፡፡ (አሪት ፡ ወንጌል ፡ ናቸው ፡)
፪፤ በዙሪያውም ፡ ብዙ ፡ የጥበብ ፡ ምንጮች ፡ ይከ
ቡታል ፡፡ (መጻሕፍት ፡) የተጠሙ ፡ ሰዎችም ፡
ሁሉ ፡ ከሱ ፡ ይጠጣሉ ፡ (ይማራሉ ፡) ጥበብንም ፡
ይመላሉ ፡፡
፫፤ ማደሪያቸውም ፡ ከደናግልና ፡ ከሕጋውያን ፡
ከቅዱሳንም ፡ ጋር ፡ ነው ፡፡
፬፤ በዚያችም ፡ ሰዓት ፡ በነፋሳቱ ፡ ጌታ ፡ ዘንድ ፡
ከሰው ፡ የተወለደ ፡ ይህ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡
ተባለ ፡፡
፭፤ ስሙም ፡ ከስድስቱ ፡ ዕለታት ፡ ከምትበልጥ ፡
ከዕለተ ፡ እሑድ ፡ የቀደመ ፡ ተባለ ፡፡
፮፤ ፀሐይ ፡ ሳይፈጠር ፡ ጨረቃም ፡ ሳይፈጠር ፡
በሰማይ ፡ ያሉ ፡ ከዋክብትም ፡ ሳይፈጠሩ ፡ በመ
ላእክት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ ስሙ ፡ ብሉየ ፡ መዋዕል ፡
ተባለ ፡፡
፯፤ እንዳይወድቁ ፡ እሱን ፡ ይመረኰዙ ፡ ዘንድ ፡ ለቅ
ዱሳንና ፡ ለጻድቃን ፡ በትር ፡ ይሆናቸዋል ፡
(ጽንዕ ፡) እሱም ፡ የአሕዛብ ፡ ብርሃን ፡ ነው ፡
(መምር ፡) በልቡናቸው ፡ ላዘኑ ፡ ሰዎችም ፡ እሱ ፡
አለኝታቸው ፡ ይሆናል ፡፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ ፰፤
ወድቀው ፡ ይሰግዳሉ ፡ ፈጽመውም ፡ ያመሰግኑ
ታል ፡ ለመላእክት ፡ ጌታ ፡ ስም ፡ ምስጋናን ፡ ያቀ
ርቡለታል ፡፡
ለዚህም ፡ ነገር ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ ከጥ ፱፤
ንት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ አስታ
ራቂ ፡ ሆነን ፡ የተሠወርንም ፡ ሆነ ፡፡
የጻድቃንን ፡ እድል ፡ ፈንታ ፡ አጽንቶላቸዋልና ፡ ፲፤
የመላእክት ፡ ጌታ ፡ አብ ፡ የባሕርይ ፡ ጥበቡ ፡
ለደናግልና ፡ ለሕጋውያን ፡ በሥጋ ፡ ገለጠው ፡፡
ግፍ ፡ የሚሠራበት ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ንቀው ፡ ፲፩፤
ጠልተውታልና ፡ ሹመቱ ፡ ሽልማቱን ፡ ሁሉ ፡
በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ ስም ፡ አምነው ፡ ሥራ
ውንም ፡ ጠልተውታልና ፡፡
በስሙ ፡ አምነው ፡ ይድናሉና ፡ ድኅነታቸውንም ፡ ፲፪፤
ወደደ ፡፡
ፈጽመው ፡ በተጨነቁበት ፡ ቀን ፡ ሰውነታቸ ፲፫፤
ውን ፡ አላዳኑምና ፡ ይችን ፡ ዓለም ፡ የሚገዟት ፡
አርበኞች ፡ ሰዎችና ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ነገሥታት ፡
በጃቸው ፡ ስለ ፡ ሠሩት ፡ ክፉ ፡ ሥራቸው ፡
በዚያ ፡ ወራት ፡ አንገታቸውን ፡ የደፉ ፡ ሆኑ ፡፡
በመረጥኋቸው ፡ በጻድቃንም ፡ እጅ ፡ ሥላሴ ፡ ፲፬፤
ይጥሏቸዋል ፡፡
ሣር ፡ በእሳት ፡ እንዲቃጠል ፡ እርሳስም ፡ ፲፭፤
በውሀ ፡ ውስጥ ፡ እንዲሠጥም ፡ አሁን ፡ እንደተ
ናገርሁት ፡ ጻድቃንን ፡ ከመበደላቸው ፡ የተነሣ ፡
በገሃነም ፡ ይቃጠላሉ ፡ ቅዱሳንንም ፡ ከመበደላ
ቸው ፡ የተነሣ ፡ በባሕረ ፡ ገሃነም ፡ ይሠጠማሉ ፡፡
በተጨነቁበትም ፡ ቀን ፡ ፍሊጋቸው ፡ አይገኝም ፡ ፲፮፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሠሩት ፡ ኃጢአታቸው ፡ ፍር
ሃት ፡ ትደረጋለች ፡፡
በፊቱም ፡ ይወድቃሉ ፡ አይነሡም ፡ የመላእክት ፡ ፲፯፤
ጌታን ፡ አብ ፡ ክደውታልና ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ
ንም ፡ ክደዋልና ፡ የመላእክት ፡ ጌታም ፡ ስሙ ፡
ይመስገናልና ፡ ከወደቁበት ፡ በታ ፡ እጁን ፡ ሰጥቶ ፡
የሚያነሣቸው ፡ የለም ፡፡
የተሠወረውን ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በመ ፲፰፤
ግለጥ ፡ አዋቂ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ዕውቀት ፡ እንደ ፡ ውሀ ፡
በገዛ ፡ ተሰጥቷልና ፡ በፊቱም ፡ የምትሠጥ ፡
ክብር ፡ ለዘላለም ፡ አትፈጸምምና ፡ የመላእክት ፡
ጌታ ፡ ስም ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡፡
አስታራቂ ፡ ክርስቶስ ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ ፲፱፤
ቈሟልና ፡ አሰት ፡ ነገርም ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ያል
ፋል ፡ ቆሞ ፡ የሚሠወሩበት ፡ በታ ፡ የለም ፡፡
ጌትነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ነው ፡ ኃይሉም ፡ ለልጅ ፡ ፳፤
ልጅ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡፡
ጥበብን ፡ የሚገልጥ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ለሰው ፡ ፳፩፤
ጥበብን ፡ የሚገልጥ ፡ ትምርትንም ፡ የሚገልጥ ፡
ኃይልንም ፡ የሚያደርግ ፡ የሞቱትንም ፡ ሰዎች ፡
በውነት ፡ የሚያስነሣቸው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡
በሱ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡፡ (ሕልውና ፡ ነው ፡)

፳፪፤ አስታራቂ ፡ ክርስቶስ ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ አብ ፡
ፊት ፡ እሱ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ነውና ፡ የተሰወሩ
ትን ፡ ነገሮች ፡ ገልጦ ፡ የሚፈርድ ፡ እሱ ፡ ነው ፡
በሱም ፡ ፊት ፡ ዋዛ ፡ ነገርን ፡ ተናግሮ ፡ መዳን ፡
የሚችል ፡ የለም ።
፳፫፤ በዚያ ፡ ወራት ፡ ለደናግልና ፡ ለሐጋውያን ፡ መመ
ለስ ፡ (ግዛት ፡) ትደረግላቸዋለች ፡ ዘበናይ ፡ ብር
ሃንም ፡ በነሱ ፡ ያድራል ፡ ፍጹም ፡ ጌትነትም ፡
ለቅዱሳን ፡ ይመለስላቸዋል ።
፳፬፤ ጭንቅ ፡ መከራም ፡ የምትደረግበት ፡ ቀን ፡ ለኃ
ጥአን ፡ መከራ ፡ ትደልብላቸዋለች ፡ በመላእ
ክት ፡ ጌታ ፡ ስም ፡ ያመኑ ፡ ጻድቃንም ፡ ድል ፡
ይነሣሉ ።
፳፭፤ ንስሐ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ የጃቸውንም ፡ ሥራ ፡
ይተዉ ፡ ዘንድ ፡ ለሌሎች ፡ ነስሐ ፡ ብሎ ፡ ያስተ
ምራል ።
፳፮፤ በነፍሳት ፡ ጌታ ፡ ፊትም ፡ ክብር ፡ ይደረግላቸ
ዋል ፡ በስሙም ፡ አምነው ፡ ይድናሉ ።
፳፯፤ ቸርነቱ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ በፍርዱም ፡ በጌትነቱም ፡
እውነተኛ ፡ ነውና ፡ የነፍሳት ፡ ጌታ ፡ ይቅር ፡ ይላ
ቸዋል ፡ አለ ።
፳፰፤ አሰት ፡ ነገርም ፡ በፍርዱ ፡ ጊዜ ፡ አትጸናም ፡
ንስሐም ፡ ያልገባ ፡ ሰው ፡ በሱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይጠ
ፋሉ ፡ የመላእክት ፡ ጌታም ፡ ንስሐ ፡ ያልገቡ
ትን ፡ ሰዎች ፡ እንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ይቅር ፡ አልላ
ቸውም ፡ አለ ።
፳፱፤ በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ ምድር ፡ አደራዋን ፡ ትመ
ልሳለች ፡ መቃብርም ፡ የተቀበለችውን ፡ አደራ ፡
ትመልሳለች ።
፴፤ ሞትም ፡ የሚከፍለውን ፡ ይመልሳል ፡ (አይገ
ልም ፡) እነሱ ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ፡ የሚድኑበት ፡
ቀን ፡ ቀርባለችና ፡ ደናግልና ፡ ሐጋውያንን ፡ ከኃ
ጥአን ፡ ይመርጣል ።
፴፩፤ አስታራቂ ፡ ክርስቶስም ፡ በነዚያ ፡ ወራት ፡ በዙ
ፋኑ ፡ ይቀመጣል ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ሰጥቶ ፡
አክብሮታልና ፡ የተሠወረ ፡ የጥበብን ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ አስቦ ፡ ከሚናገርበት ፡ ከአንደበቱ ፡ ያወ
ጣል ።
፴፪፤ በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ ተራሮች ፡ እንደ ፡ ጊደ
ሮች ፡ ይዘፍናሉ ፡ ኮረብቶችም ፡ ወተት ፡ እንደ ፡
ጠገቡ ፡ ጠቦቶች ፡ ይዘላሉ ።
፴፫፤ በነዚያ ፡ ወራቶች ፡ አስታራቂ ፡ ክርስቶስ ፡ ተነ
ሥቷልና ፡ ሁሉም ፡ በሰማይ ፡ መላእክትን ፡ ይሆ
ናሉ ። (የግብር ፡ ነው ፡) ፊታቸውም ፡ በደስታ ፡
ያበራል ።
፴፬፤ መንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ ደስ ፡ ይላታል ፡ ጻድ
ቃንም ፡ በሷ ፡ ይኖራሉ ፡ ደናግልም ፡ በሷ ፡ እየ
ተመላለሱ ፡ ይኖራሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

፩፤ ከነዚያም ፡ ወራቶች ፡ በኋላ ፡ በነፋስ ፡ ሠረገላ ፡
ተነጥቄ ፡ ነበርና ፡ መላእክትም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡
ወስደውኝ ፡ ነበርና ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ የተሠወሩ
ትን ፡ ራእዮች ፡ ሁሉ ፡ አየሁ ።
በዚያም ፡ ቦታ ፡ በሰማይ ፡ የተሠወሩትን ፡ በዚህ ፡ ፪፤
ዓለምም ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ዓይ
ኖቼ ፡ አዩ ።
የብረት ፡ ተራራን ፡ የናስ ፡ ተራራን ፡ የብር ፡ ተራ ፫፤
ራን ፡ የወርቅ ፡ ተራራን ፡ የዕይር ፡ ተራራን ፡
የርሳስ ፡ ተራራን ፡ አዩ ።
ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ በልደረበዬ ፡ መላኩንም ፡ ተሠ ፬፤
ውረው ፡ የማያቸው ፡ እነሂ ፡ ምንድናቸው ፡
ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።
እኒህ ፡ ያየሃቸው ፡ ሁሉ ፡ ያገዛ ፡ ዘንድ ፡ በዚ ፭፤
ህም ፡ ዓለም ፡ ይበረታባቸው ፡ ዘንድ ፡ ልጁ ፡ በሥ
ልጣኑ ፡ የሚፈርድባቸው ፡ ይሆናሉ ፡ አለኝ ።
ፍቅር ፡ ያለው ፡ ያም ፡ መልአኩ ፡ ጥቂት ፡ ቆይ ፡ ፮፤
ታያለህ ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ያጸናው ፡ የተሠወ
ረው ፡ ሁሉ ፡ ይገለጥልሃል ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ።
ያየሃቸው ፡ እነዚህም ፡ ተራሮች ፡ የብረቱ ፡ ፯፤
ተራራ ፡ የናሱም ፡ ተራራ ፡ የብሩም ፡ ተራራ ፡
የወርቁም ፡ ተራራ ፡ የዕይሩም ፡ ተራራ ፡ የርሳ
ሱም ፡ ተራራ ፡ እኒህ ፡ ሁሉ ፡ በአስታራቂ ፡ ክር
ስቶስ ፡ ፊት ፡ በእሳት ፡ ፊት ፡ እንዳለ ፡ አደሮማር ፡
ይሆናሉ ፡ አለ ።
ከላይ ፡ የወረደ ፡ ውሀ ፡ ቀጥሎ ፡ ቀጥሎ ፡ እንዲ ፰፤
ወርድ ፡ በነዚያ ፡ ነገሥታትም ፡ ላይ ፡ ቀጥሎ ፡
ቀጥሎ ፡ መከራው ፡ መጥቶባቸው ፡ በእግሩ ፡
በታች ፡ የወደቁ ፡ ይሆናሉ ።
በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ እንደዚህ ፡ ይሆናል ፡ በወ ፱፤
ርቅም ፡ ቢሆን ፡ በብርም ፡ ቢሆን ፡ አይድኑም ፡
ሸሽቶ ፡ መዳንም ፡ አይቻላቸውም ።
ብረትም ፡ ለጠብ ፡ አይሆንም ፡ ልብስም ፡ ለደ ፲፤
ረት ፡ ጥሩር ፡ አይሆንም ፡ ብርትም ፡ አይረባም ፡
ቅልቅሉም ፡ አይጠቅምም ፡ ካለ ፡ ከሌለ ፡ አይቈ
ጠርም ፡ ሁሉም ፡ ይከዳሉ ፡ እንጂ ፡ እርሳስም ፡
አይወደድም ።
አስታራቂ ፡ ክርስቶስ ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ በአብ ፡ ፲፩፤
ፊት ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ፡ ጠላቶቹ ፡ ኃጥአን ፡ ከመ
ንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ይጠፉ ፡ ዘንድ ፡ አላቸው ።
በዚያም ፡ ቦታ ፡ ዓይኖቼ ፡ ጥልቅ ፡ ቈላን ፡ አዩ ፡ ፲፪፤
አፉም ፡ የተከፈተ ፡ ነው ። (መቃብር ፡)
በዚህ ፡ ዓለም ፡ በደሴትና ፡ በባሕርም ፡ የሚኖሩ ፡ ፲፫፤
ሁሉ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ገጸ ፡ በረከቱን ፡ ግብሩን ፡
ያመጡለታል ፡ ይህም ፡ ጥልቅ ፡ ቈላ ፡ አይመ
ላም ።
እጆቻቸው ፡ ክፉ ፡ ሥራን ፡ ይሠራሉ ፡ ዕዳ ፡ ፲፬፤
ሊሆንባቸው ፡ ኃጥአን ፡ የደከሙበትን ፡ ጻድ
ቃን ፡ ይበላሉታል ።
ከነፍሳት ፡ ጌታ ፡ ገጸ ፡ መዓትም ፡ የተነሣ ፡ ኃጥ ፲፭፤
አን ፡ ይጠፋሉ ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ ይከ
ለከላሉ ።
መቅሠፍት ፡ የሚያመጡ ፡ መላእክትን ፡ ሄደው ፡ ፲፮፤
ለሰይጣን ፡ ዙሀውን ፡ ሁሉ ፡ (መቅሠፍት ፡) ሲያ
ዘጋጁ ፡ አይቻቸዋለሁና ፡ ለዘላለሙ ፡ ፈርሰው ፡
በስብሰው ፡ አይቀሩም ።
ፍቅር ፡ ያለው ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ የሚኖር ፡ መላኩን ፡ ፲፯፤
እነዚህን ፡ ዘሀወች ፡ ለማን ፡ ያዘጋጃቸዋል ፡

ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።
፲፰፡ በሱ ፡ ይጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ለዚህ ፡ ዓለም ፡ አርበኞ
ችና ፡ ለነገሥታቱ ፡ ያዘጋጃሉ ፡ አለኝ ።
፲፱፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እውነተኛ ፡ አስታራቂ ፡ ክርስ
ቶስ ፡ ጻድቃንን ፡ በሚሰበስብበት ፡ በመንግ
ሥተ ፡ ሰማይ ፡ ይገለጣል ።
፳፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ስም ፡ ያመኑ ፡ ጻድቃን ፡ እን
ግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይከለከሉም ።
፳፩፡ እኒህ ፡ ነገሥታት ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡
ይሆናሉ ፡ መኳንንቱም ፡ እንደ ፡ ውሀ ፡ ምንጭ ፡
ይሆናሉ ፡ ጻድቃንም ፡ ኃጥአን ፡ ከሚያመጡብ
ቸው ፡ መከራ ፡ ያርፋሉ ።
፳፪፡ ተመልሼም ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ አየሁ ፡ በዚያም ፡ እሳት ፡
ሲነድ ፡ ጥልቅ ፡ ቦታን ፡ አየሁ ። ( ገሃነም ፡ ነው ፡ )
፳፫፡ አርበኞቹንና ፡ ነገሥታቱን ፡ አምጥተው ፡ በዚያ ፡
በጥልቅ ፡ ቦታ ፡ ጣሏቸው ።
፳፬፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ ዓይኖቼ ፡ ዙሀዎችን ፡ ቍጥር ፡ የሌ
ላቸው ፡ የብረት ፡ ማሠሪያዎችን ፡ አድርገው ፡
ሲያሥሯቸው ፡ አዩ ።
፳፭፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ የሚኖር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡
አንድነት ፡ ያለው ፡ መልአኩንም ፡ እነዚህ ፡ የዙ
ሀዎች ፡ ማሠሪያዎችን ፡ ለማን ፡ ያዘጋጃሉ ፡ ብየ ፡
ጠየቅሁት ።
፳፮፡ ተቀብለዋቸው ፡ በገሃነም ፡ በታች ፡ ይጥሏቸው ፡
ዘንድ ፡ እነዚህ ፡ ለአዛዝኤል ፡ ሠራዊት ፡ ይዘጋ
ጃሉ ፡ አለኝ ።
፳፯፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ እንዳዘዘ ፡ በፊታቸውም ፡
እንክብል ፡ እንክብል ፡ ደንጊያዎችን ፡ ይገጥሙ
ባቸዋል ።
፳፰፡ ገብርኤልና ፡ ሚካኤል ፡ ፋኑኤልና ፡ ሩፋኤልም ፡
እነሱ ፡ ታላቅ ፡ በሆነች ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ አጽን
ተው ፡ ይጥሏቸዋል ።
፳፱፡ የሰይጣን ፡ መልክተኛ ፡ ስለሆኑ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
የሚኖሩትንም ፡ ሰዎች ፡ ስላሳቷቸው ፡ በኃጢ
አታቸው ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ከነሱ ፡ በቀልን ፡
ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ መላእክት ፡
እሳት ፡ ወደሚነድበት ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ይጥሏ
ቸዋል ።
፴፡ በዚያም ፡ ወራት ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ብዙ ፡
የሚያጠርደው ፡ መቅሠፍት ፡ ይመጣል ። ( ማየ ፡
አይህ ፡ ነው ፡ )
፴፩፡ ከሰማዮች ፡ በላይ ፡ ያሉ ፡ የውሀዎች ፡ በታዎች ፡
ሁሉ ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ከምድር ፡ በላይም ፡ ያሉ ፡
የምንጮች ፡ በታዎችም ፡ ሁሉ ፡ ይከፈታሉ ።
፴፪፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ ውሆችም ፡ ሁሉ ፡ ከሰማ
ዮች ፡ በላይ ፡ ካሉ ፡ ውሀዎች ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡
ይሆናሉ ።
፴፫፡ በሰማዮች ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ውሀ ፡ ግን ፡ ሬስ ፡ የሚ
ቀጠቅጥ ፡ ነው ፡ በምድር ፡ በታች ፡ ያለች ፡
ውሀም ፡ ፍፍ ፡ የምትል ፡ ናት ።
፴፬፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ በሰማይም ፡ ዳርቻ ፡
በታች ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋሉ ።
፴፭፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሠሩት ፡ ኃጢአታቸው ፡ በገ
ቢር ፡ ስላወቁት ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ይጠፋሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፩፡
ትን ፡ ሰዎች ፡ በከንቱ ፡ ኃጢአታቸው ፡ አጠፋኋ
ቸው ፡ ብሎ ፡ ብሉየ ፡ መዋዕልነት ፡ ገንዘቡ ፡ የሚ
ሆን ፡ ጌታ ፡ አዘነ ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እንግ ፪፡
ዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንዲህ ፡ እንዳያደርግ ፡ በከበረ ፡
ስሙ ፡ ማለ ።
በሰማይ ፡ ቀስተ ፡ ደመናውንም ፡ ምልክት ፡ አደ ፫፡
ርጋለሁ ፡ ይህም ፡ በነሱና ፡ በኔ ፡ መካከል ፡ ጠፈር ፡
በአድማስ ፡ ላይ ፡ ጸንቶ ፡ የኖረውን ፡ ያህል ፡
እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ መተማመኛ ፡ ይሆናል ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በመላእክት ፡ እጅ ፡ አጽንቼ ፡ ፬፡
እጣላቸው ፡ ዘንድ ፡ ብወድ ፡ በትእዛዜ ፡ ነው ።
ፍጹም ፡ መከራ ፡ በሚቀበሉበት ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ፭፡
አስቀድሞ ፡ መዓቱ ፡ መቅሠፍቱ ፡ ይመጣባቸ
ዋል ።
የመላእክት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በዚህ ፡ ፮፡
ዓለም ፡ የምትኖሩ ፡ ኃይለኞች ፡ ነገሥታት ፡ የመ
ረጥሁት ፡ ልጄን ፡ በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ በተቀመጠ ፡
ጊዜ ፡ ታዩት ፡ ዘንድ ፡ አላችሁ ፡ አለ ።
በአዛዝኤል ፡ ይፈርድበታል ፡ በወገኖቹም ፡ ፯፡
ሁሉ ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ስም ፡ ባላመኑ ፡ በሠ
ራዊትም ፡ ሁሉ ፡ ይፈርድባቸዋል ።
በዚያም ፡ ቦታ ፡ ለመቅሠፍት ፡ የታዘዙ ፡ የመላ ፰፡
እክትን ፡ ሠራዊት ፡ ታዘው ፡ ሲሄዱ ፡ የብርትና ፡
የብረት ፡ ማሠሪያንም ፡ ይዘው ፡ አየሁ ፡ አለ ።
ከኔ ፡ ጋር ፡ የሚኖር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ፱፡
አንድነት ፡ ያለው ፡ መልአኩን ፡ እግር ፡ ብረቱን ፡
ሰንሰለቱን ፡ የያዙ ፡ እነዚህ ፡ ማንን ፡ ሊያሥሩ ፡
ይሄዳሉ ፡ ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።
በቈላው ፡ ጥልቅ ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ( ገሃነም ፡ ) ይወ ፲፡
ድቁ ፡ ዘንድ ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ አጋንንት ፡ የወ
ደዷቸውንና ፡ የመረጧቸውን ፡ ኃጥአንን ፡ ሊያ
ሥሯቸው ፡ ይሄዳሉ ፡ አለኝ ።
የዚያን ፡ ጊዜ ፡ አጋንንት ፡ ከመረጧቸው ፡ ከወ ፲፩፡
ደዷቸው ፡ ከኃጥአን ፡ የተነሣ ፡ ያ ፡ ጥልቅ ፡ ገሃ
ነም ፡ ይመላል ።
በሕይወት ፡ የሚኖሩበት ፡ ቀን ፡ ያልቃል ፡ የሚ ፲፪፡
ያስቱበትም ፡ ቀን ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይቈ
ጠርም ።
በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ አለቆች ፡ ተሰብስበው ፡ ፲፫፡
የሚድንና ፡ የጻድቱን ፡ ሰዎች ፡ ለመጥራት ፡ ራሳ
ቸውን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመልሳሉ ። ( ፊታቸ
ውን ፡ )
ነገሥታቱንም ፡ ያነቃቁቸዋል ፡ ሁከት ፡ ያደረ ፲፬፡
በት ፡ ልቡናም ፡ ያድርባቸዋል ፡ ከዙፋናቸውም ፡
እየገለበጡ ፡ ይጥሏቸዋል ።
ከከተማቸውም ፡ እንዳንበሶች ፡ በማስፈራራት ፡ ፲፭፡
ይወጣሉ ፡ እንደ ፡ ተራቡ ፡ በመንጋዎቻቸው ፡
መካከል ፡ እንዳሉ ፡ ጅቦች ፡ ይበሳጫሉ ።
ይዘምታሉ ፡ ለጥፋት ፡ የመረጧቸው ፡ የእስራኤ ፲፮፡
ልንም ፡ አገር ፡ ያጠፏታል ፡ ለጥፋት ፡ የመረጣ

ቸው፡ የእስራኤልም፡ አገር፡ በፊታቸው፡ መመ
ላለሻ፡ መገሥገሻ፡ ትሆናለች ። (፲ሩ፡ ነገድ፡)
፲፯፡ የወዳጆቼ፡ የሁለቱ፡ ነገድ፡ አገር፡ ግን፡ ለፈረ
ሶቻቸው፡ መሰናክል፡ ትሆናለች ።
፲፰፡ እስበሳቸው፡ ጠብን፡ ያነሣሉ፡ ሥልጣናቸውም፡
በወንድሞቻቸው፡ ላይ፡ ትጸናለች፡ ባልንጀራ፡
ባልንጀራውን፡ ወንድም፡ ወንድሙንም፡ አያ
ውቀውም ።
፲፱፡ ከመቅሠፍታቸውና፡ ከሞታቸው፡ የተነሣ፡
የራሳቸው፡ ቍጥር፡ ብላሽ፡ የማይሆን፡ እስኪ
ሆን፡ ድረስ፡ ልጅም፡ እናቱንና፡ አባቱን፡ አያ
ውቅም ።
፳፡ በነዚያም፡ ወራቶች፡ መቃብር፡ አፏን፡ ትከ
ፍታለች ።
፳፩፡ በውስጧም፡ ይቀበራሉ፡ ሁለቱን፡ ነገድ፡ ከመ
በደላቸው፡ የተነሣ፡ አሥሩን፡ ነገድ፡ የምታጠ
ፋቸው፡ መቃብር፡ ትውጣቸዋለች ።
፳፪፡ ከዚህ፡ በኋላ፡ እንዲህ፡ ሆነ፡ ሰዎች፡ ተቀምጠ
ውባቸው፡ ሌሎች፡ ብዙዎች፡ ሠረገላዎችን፡
አየሁ ።
፳፫፡ በነፋሶችም፡ ላይ፡ ሁነው፡ ከምዕራብና፡ ከም
ሥራቅ፡ እስተ፡ ቀን፡ እኩል፡ ይመጣሉ ። (ፈጥ
ነው፡ ሲል፡ ነው፡)
፳፬፡ የሠረገሎቻቸው፡ ድምፅ፡ ቃልም፡ ከሩቅ፡
ተሰማ፡ ይህም፡ ሁከት፡ በተደረገ፡ ጊዜ፡ መላ
እክት፡ በሰማይ፡ ሁነው፡ አወቁ ።
፳፭፡ የምድር፡ ምሰሶም፡ ከቦታው፡ ተናወጠ ። (ሰና
ክሬም፡)
፳፮፡ ጥፋቱም፡ ከሰማይ፡ ዳርቻ፡ ጀምሮ፡ እስከ፡
ምድር፡ ዳርቻ፡ ድረስ፡ ባንዲት፡ ቀን፡ ተሰማ ።
፳፯፡ ሁሉም፡ ወድቀው፡ ለመላእክት፡ ጌታ፡ ይሰግ
ዳሉ ።
፳፰፡ የሁለተኛውም፡ ነገር፡ መጨረሻ፡ ይህ፡ ነው ።
፳፱፡ ስለ፡ ደናግልና፡ ስለ፡ ሕጋውያንም፡ ሦስተኛ
ውን፡ ነገር፡ እናገር፡ ጀመርኩ ።
፴፡ እድላችሁ፡ መንግሥተ፡ ሰማይ፡ የበራ፡ ነውና፡
ደናግልና፡ ሕጋውያን፡ እናንተ፡ የተደነቃችሁ፡
ናችሁ ።
፴፩፡ ጻድቃን፡ እንደ፡ ፀሐይ፡ ያበራሉ፡ (ሕጋውያን፡)
ደናግልም፡ ዘላለም፡ ጸንቶ፡ በሚኖር፡ በመን
ፈስ፡ ቅዱስ፡ ብርሃን፡ ያበራሉ ።
፴፪፡ በሕይወት፡ ለሚኖሩትም፡ ዘመን፡ ፍጻሜ፡ የለ
ውም፡ በቅዱሳንም፡ የተቈጠረ፡ ዘመን፡ የላቸ
ውም ።
፴፫፡ ክብርንም፡ ይፈልጉታል፡ በመላእክት፡ ጌታም፡
ዘንድ፡ ቸርነቱን፡ ያገኛሉ ።
፴፬፡ በመላእክት፡ ጌታም፡ ዘንድ፡ ለጻድቃን፡ ፍቅር፡
አንድነት፡ ይደረጋል ።
፴፭፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ የሃይማኖት፡ እድል፡ የሚሆን፡
የተሠወረው፡ እውነተኛውን፡ ነገር፡ በሰማይ፡
ይፈልጉ፡ ዘንድ፡ ለጻድቃን፡ ክብር፡ ይሰጣል፡
ይባላል ።
፴፮፡ ፀሐይ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ እንዲያበራ፡ ብርሃነ፡
መለኮቱ፡ ያበራልና፡ ድንቍርናም፡ ጠፍቷልና፡
የማይቈጠር፡ ጸጋ፡ ክብር፡ ይሰጣል ።
አስቀድሞ፡ ድንቍርና፡ ጠፍቷልና፡ ጻድቃን፡ ፴፯፡
በዘመን፡ ቍጥር፡ ወደ፡ መንግሥተ፡ ሰማያት፡
አይገቡም ።
ዕውቀትም፡ በመላእክት፡ ጌታ፡ ፊት፡ ይጸናል፡ ፴፰፡
በቅንነት፡ የሠሯት፡ ሥራቸውም፡ በመላእክት፡
ጌታ፡ ፊት፡ ለዘላለሙ፡ ትጸናለች ።
በነዚያም፡ ወራቶች፡ ዓይኖቼ፡ የብርሃኖችንና፡ ፴፱፡
የመብረቆችን፡ ቦታዎች፡ አዩ፡ መቻያነታቸው
ንም፡ አዩ ።
የመላእክት፡ ጌታ፡ እንደ፡ ወደደ፡ ለጥፋትና፡ ፵፡
ለበረከት፡ ያበራሉ ።
በዚያም፡ ቦታ፡ የነጐድጓድን፡ ቦታዎችን፡ ፵፩፡
አየሁ፡ በሰማይ፡ ላይም፡ ብልጭ፡ ባለ፡ ጊዜ፡
የመብረቅና፡ የነጐድጓድ፡ ቃል፡ ይሰማል ።
የየብሱንም፡ ቦታዎች፡ አሳየኝ ። ፵፪፡
የነጐድጓድም፡ ቃል፡ ለበረከትና፡ ለፍቅር፡ ፵፫፡
ለጥፋትም፡ ቢሆን፡ ለመላእክት፡ ጌታ፡ ቃል፡
ይሰማል ።
ከዚህም፡ በኋላ፡ የመብረቆችና፡ የብርሃኖች፡ ፵፬፡
ቦታ፡ ሁሉ፡ ተገለጠልኝ ።
ለጥጋብና፡ ለበረከት፡ ሊሆኑ፡ ያበራሉ ። ፵፭፡

## ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

ሄኖክ፡ የዚህን፡ ዓለም፡ አነዋወር፡ ትቶ፡ ፩፡
ከተሠወረ፡ በኋላ፡ በምስት፡ መቶ፡ ዘመን፡ በሰበ
ተኛው፡ ወር፡ በሥራ፡ አራተኛ፡ ቀን፡ ከሰማ
ዮች፡ በላይ፡ ያለች፡ ሰማይ፡ ታላቅ፡ ንውጥው
ጥታ፡ ስትነዋወጥ፡ የእግዚአብሔርም፡ ሠራ
ዊት፡ መላእክት፡ ሲነዋወጡ፡ በሱ፡ አምሳል፡
አየሁ ።
ብዙ፡ የብዙ፡ ብዙ፡ የሚሆኑ፡ መላእክትም፡ ፪፡
በሰው፡ ጥፋት፡ ብዙ፡ ሁከትን፡ ታወኩ ።
ያን፡ ጊዜም፡ ዕለተ፡ እኍድ፡ ገንዘቡ፡ የሆነች፡ ፫፡
ጌታን፡ በጌትነቱ፡ ዙፋን፡ ተቀምጦ፡ አየሁ ።
ጻድቃንና፡ መላእክትም፡ በዙሪያው፡ ቁመው፡ ፬፡
አየሁ፡ እኔንም፡ ጽኑ፡ እንቅጥቅጥታ፡ ያዘኝ ።
ፍራትም፡ ያዘኝ፡ ወገቤም፡ ጐበጠ፡ ተለያየ፡ ፭፡
ሁለመናየም፡ እንደ፡ ሰም፡ ቀለጠ፡ በግምባ
ሬም፡ ፍግም፡ ብዬ፡ ወደቅሁ ።
ቅዱስ፡ ሚካኤልም፡ ከክበሩ፡ መላእክት፡ አን ፮፡
ዱን፡ ሌላ፡ መልአክ፡ ልኮ፡ አነሣኝ ።
ያንን፡ ተአምራት፡ ያንንም፡ ሁከት፡ የሰማይ ፯፡
ንም፡ መነዋወጥ፡ ከማየቴ፡ የተነሣ፡ መታገ
ሥን፡ አልቻልሁምና፡ ባነሣኝ፡ ጊዜ፡ አእም
ሮዬ፡ ተመለሰች፡ አለ ።
ቅዱስ፡ ሚካኤልም፡ ምን፡ ራዕይ፡ ስላየህ፡ ፰፡
እንደዚህ፡ ታወክህ፡ አለኝ ።
ይህች፡ ዓለም፡ አለፈች፡ መስሎህ፡ ቸርነቱ፡ ፱፡
የሚደረግበት፡ ቀን፡ እስከ፡ ዛሬ፡ አለች፡ ይቅር፡
ባይ፡ ከመዓትም፡ የራቀ፡ ጌታ፡ በዚህ፡ ዓለም፡
የሚኖሩ፡ ሰዎችን፡ በመታገሥ፡ አለ ።
መፍራትስ፡ መቅሠፍትና፡ ኃይል፡ የሚደረግ ፲፡
ባት፡ የመላእክት፡ ጌታ፡ ለእውነተኛ፡ ሕጉ፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org

ለሚሰግዱ ፡ ለጻድቃን ፡ እውነተኛ ፡ ሕጉንም ፡
በካዱ ፡ ስሙንም ፡ በከንቱ ፡ ለሚጠሩ ፡ በኃጥ
አን ፡ ፍርድን ፡ የሚገልጥበት ፡ ቀን ፡ በመጣች ፡
ጊዜ ፡ ፍራ ።
፲፩፡ ያችም ፡ ቀን ፡ ለደናግል ፡ ክብር ፡ ለኃጥአንም ፡
ምርመራ ፡ ሁና ፡ ተዘጋጀች ።
፲፪፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ሁለቱ ፡ አውሬዎች ፡ ከደማዊት ፡
ነፍስ ፡ ይለያሉ ፡ ስሟ ፡ ሌዋታን ፡ የሚባል ፡
ሴቲቱ ፡ አውሬ ፡ በውሆች ፡ ምንጮች ፡ ላይ ፡
በባሕሩ ፡ ጥልቅ ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፡ ተፈጠረች ።
፲፫፡ የማይታየውን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በደረቱ ፡ የሚ
ይዝ ፡ ስሙ ፡ ብሔሞት ፡ የሚባል ፡ የወንዱም ፡
አውሬ ፡ቦታው ፡ በየብስ ፡ ነው ።
፲፬፡ ደናግልና ፡ ሕጋውያን ፡ በሚኖሩበት ፡ የመላእ
ክት ፡ ጌታ ፡ ለፈጠራቸው ፡ ሰዎች ፡ መጀመሪያ
ቸው ፡ ከሚሆን ፡ ከአዳም ፡ ሰባተኛ ፡ የሚሆን ፡
አያቴ ፡ ሄኖክ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በተቀበለበት ፡
በገነት ፡ ምሥራቅ ፡ ያለ ፡ የቦታውም ፡ ስም ፡
ዶንዳይን ፡ ይባላል ።
፲፭፡ በንዳት ፡ ቀን ፡ ተፈጥረው ፡ አንዱ ፡ በባሕር ፡
ዳር ፡ አንዱ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ቦታ ፡ ሊኖሩ ፡
እንደ ፡ ተለያዩ ፡ የነዚያን ፡ አውሬዎችንም ፡ ሥራ
ቸውን ፡ ይገልጥልኝ ፡ ዘንድ ፡ ያንን ፡ ሁለተኛ
ውን ፡ መልአክ ፡ ጠየቅሁት ።
፲፮፡ አንተ ፡ የበለአእምሮ ፡ ልጅ ፡ የተሠወረን ፡ ነገር ፡
በዚህ ፡ ልታውቅ ፡ ትወዳለህ ፡ አለኝ ።
፲፯፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ የሚኖር ፡ የተሠወረውን ፡ የፊቱንም ፡
የኋላውንም ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ ባለ ፡ በሰማይ ፡
ከሰማይ ፡ በታች ፡ ባለ ፡ በየብስ ፡ በጥልቁ ፡ በሰ
ማይም ፡ ዳርቻ ፡ በሰማይም ፡ መሠረት ፡ በነፋ
ሶችም ፡ ቦታ ፡ ያለውን ፡ የገለጠልኝ ፡ ሁለተ
ኛው ፡ መልአክ ፡ ነገረኝ ።
፲፰፡ ነፋሳት ፡ ተመጥነው ፡ ተመጥነው ፡ እንደ ፡ ነፈሱ ፡
ምንጮችም ፡ ተመጥነው ፡ ተመጥነው ፡ እንዲ
ፈሱ ፡ ነፋሶችም ፡ በረቂቅነቱ ፡ ኃይል ፡ እንዲከ
ፈሉ ፡ የሀሊዩ ፡ የጨረቃም ፡ ብርሃን ፡ ሥራ ፡
የውነት ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዋክብትም ፡ በየ
ስማቸው ፡ እንዲከፈሉ ፡ ነገረኝ ።
፲፱፡ ሥራውም ፡ ሁሉ ፡ ይከፈላል ፡ መብረቅና ፡ ነጐ
ድጓድም ፡ በቦታዎቻቸው ፡ ይሰማሉ ፡ ለሚሠ
ራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ መመጠን ፡ አለው ።
፳፡ መብረቁ ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፡ የመብረቅና ፡ የነጐ
ድጓድ ፡ ሠራዊትም ፡ ፈጥነው ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡
ለነጐድጓድ ፡ ማረፊያ ፡ አለውና ፡ ታግሦ ፡ ታግሦ ፡
ሊያመጣው ፡ ለቃሉ ፡ ጊዜ ፡ ተሰጠው ።
፳፩፡ መብረቅና ፡ ነጐድጓድም ፡ አይለያዩም ፡ አን
ዱም ፡ አንዱም ፡ ሁለቱ ፡ ሁሉ ፡ በነፋስ ፡ ይሄ
ዳሉ ።
፳፪፡ መብረቅ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ነጐድጓድ ፡ ቃሉን ፡
ይሰጣልና ፡ አይለያዩም ፡ ነፋሱም ፡ በጊዜዋ ፡
ጊዜ ፡ ያርፋል ።
፳፫፡ በሚወጡበት ፡ ጊዜ ፡ በታቸው ፡ በሸዋና ፡
በድኝ ፡ መካከል ፡ ነውና ፡ መልአኩ ፡ በመከከላ
ቸው ፡ አስተካክሎ ፡ ይከፍላል ፡ አለ ።

ከነሳቸው ፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ፳፬፡
በልጓም ፡ ይገታሉ ። ( በሥልጣን ፡ )
በነፋስም ፡ ኃይል ፡ ይመላለሳሉ ፡ እንደ ፡ ምድር ፡ ፳፭፡
አውራጃ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ እንዲሁ ፡ ይነዳል ።
ባሕርን ፡ የሚጠብቀው ፡ መልአክ ፡ ብርቱ ፡ ነው ፡ ፳፮፡
እንደ ፡ ዕናቷም ፡ ኃይል ፡ መጠን ፡ በልጓም ፡
ይገታታል ። ( ሥልጣን ፡ )
እንዲሁ ፡ ትነዳለች ፡ በምድር ፡ ተራሮችም ፡ ፳፯፡
ሁሉ ፡ ትበተናለች ።
ለውርጭም ፡ ጠባቂ ፡ አለው ፡ ይኸውም ፡ መል ፳፰፡
አኩ ፡ ነው ፡ በረዱንም ፡ የሚጠብቀው ፡ መል
አክ ፡ ደግ ፡ መልአክ ፡ ነው ።
ዋግንም ፡ የሚጠብቅ ፡ መልአክ ፡ ክፉ ፡ ስለ ፡ ፳፱፡
ሆነ ፡ ለብቻው ፡ ጠባቂ ፡ አለው ።
ከሱም ፡ የሚወጣ ፡ እንደ ፡ ጢስ ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ፴፡
ስሙም ፡ ደደክ ፡ ይባላል ።
አከሄዱ ፡ በጌትነት ፡ በጨለማና ፡ በብርሃን ፡ በበ ፴፩፡
ጋና ፡ በክረምት ፡ ነውና ፡ ለብቻው ፡ ቦታ ፡
አለው ፡ እንጂ ፡ የጉሙ ፡ ጠባቂ ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡
በቦታቸው ፡ አንድ ፡ አይሆንም ።
የሷም ፡ ቦታ ፡ ብርሃን ፡ ነው ፡ ጠባቂዋም ፡ መል ፴፪፡
አክ ፡ ነው ፡ የጠልም ፡ ጠባቂ ፡ ቦታው ፡ በሰ
ማይ ፡ ዳርቻ ፡ ነው ።
ከዝናም ፡ ቦታዎች ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ሹመ ፴፫፡
ቱም ፡ በበጋና ፡ በክረምት ፡ ነው ።
የጉም ፡ ደመና ፡ የገዝናም ፡ ደመና ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ፴፬፡
አንዱ ፡ መግበ ፡ ሹመቱን ፡ ላንዱ ፡ ይሰጣል ።
ዝናሙን ፡ የሚያመጣውም ፡ ነፋስ ፡ ከቦታው ፡ ፴፭፡
በተናወጠ ፡ ጊዜ ፡ መላእክት ፡ ይመጣሉ ፡ ቦታ
ውንም ፡ ከፍተው ፡ ያወጡታል ።
በዚህም ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ገዝናሙ ፡ በተበተነ ፡ ጊዜ ፡ ፴፮፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ ሁሉ ፡ ውሀ ፡ ጋራ ፡
አንድ ፡ ይሆናል ።
በየጊዜው ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ ፴፯፡
ውሀ ፡ ጋር ፡ በሚተባበርበት ፡ ጊዜ ፡ ውሀዎች ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ምግብ ፡ ሁነ
ዋልና ፡ በሰማይ ፡ ካለ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
ታዘ ፡ ለየብስም ፡ ምግቢ ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡
ለገዝናሙ ፡ መመጠን ፡ አለውና ፡ መላእክት ፡
ይቀበሉታል ።
ጻድቃን ፡ እስከሚወርሷት ፡ ገነት ፡ ድረስም ፡ ፴፰፡
ሄጄ ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ አየሁ ።
ከኔ ፡ ጋር ፡ የሚኖር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ ፴፱፡
አንድነት ፡ ያለው ፡ መልአኩም ፡ እኒህ ፡ ሁለቱ ፡
አውሬዎች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ገናንነት ፡ ተጠ
ብቀው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅሠፍቱ ፡ በከ ፡
እንዳታደርጋቸው ፡ ይመገቡ ፡ ዘንድ ፡ የተዘጋጁ ፡
ናቸው ፡ አለኝ ።
ቢያዩዋቸውስ ፡ ልጆች ፡ ከናቶቻቸው ፡ ከባቶ ፵፡
ቻቸውም ፡ ጋራ ፡ በሞቱ ፡ ነበር ፡ የመላእክት ፡
ጌታ ፡ የሚያዘት ፡ መቅሠፍቱ ፡ በመጣች ፡ ጊዜ ፡
ለነሳቸው ፡ ትመጣባቸዋለች ።
የመላእክት ፡ ጌታ ፡ መቅሠፍቱ ፡ ብላሽ ፡ ልታ ፵፩፡
ደርጋቸው ፡ እንዳትመጣ ፡ በቸርነቱ ፡ ታግሦ ፡

ታግሦ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ኋላ ፡ ትመጣበቻዋለች ፡
አለኝ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

፩፤ በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ ለነዚያ ፡ መላእክት ፡
ረጃጅሞች ፡ ገመዶች ፡ ተሰጡ ። ( ሥልጣን ፡ )
፪፤ ገመዱን ፡ ተቀብለው ፡ ፈጥነው ፡ ወደ ፡ መስዕ ፡
ሄዱ ። ( ሥልጣን ፡ )
፫፤ እነዚህን ፡ ረጃጅሞች ፡ ገመዶችን ፡ ይዘው ፡
ለምን ፡ ሄዱ ፡ ብዬ ፡ መልአኩን ፡ ጠየቅሁት ።
፬፤ እሱም ፡ ይለኩ ፡ ዘንድ ፡ ሄዱ ፡ አለኝ ።
፭፤ ከኔ ፡ ጋር ፡ የሚኖር ፡ ባልደረባዬ ፡ መልአኩም ፡
እኒህ ፡ ሥልጣናት ፡ ለዘላለሙ ፡ በመላእክት ፡
ጌታ ፡ ስም ፡ ይጸኑ ፡ ዘንድ ፡ የጻድቃንን ፡ አንድ
ነት ፡ ያመጣሉ ።
፮፤ የፈጣሪያቸውን ፡ ፍቅር ፡ ይጀምራል ፡ ደናግልም ፡
ከደናግል ፡ ጋራ ፡ ይኖራሉ ።
፯፤ እኒህም ፡ ቦታዎች ፡ በሃይማኖታቸው ፡ ጸንተው ፡
ለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ይሰጣሉ ፡ እውነተኛውንም ፡
ቃል ፡ ያጸናሉ ።
፰፤ እሊህም ፡ ሥልጣኖች ፡ በመቃብር ፡ ጥልቅነት ፡
የተሠወሩ ፡ ሰዎችን ፡ ሁሉ ።
፱፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሙተው ፡ ያልተቀበሩትን ፡
ዓሣዎች ፡ አውሬዎች ፡ የበሏቸውንም ፡ ያስነሣሉ ፡
በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ የሚጠፋ ፡ የለምና ፡
ፈርሶ ፡ በስብሶ ፡ የሚቀር ፡ የለምና ፡ አስታራቂ ፡
ክርስቶስ ፡ በሚመጣበት ፡ ቀን ፡ ተነሥተው ፡
ወደ ፡ ሕይወታቸው ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ያስነ
ሣሉ ።
፲፤ በሰማይ ፡ ያሉ ፡ ጻድቃን ፡ ሁሉ ፡ በመላእክትም ፡
ትእዛዝን ፡ ተቀበሉ ፡ ቃላቸው ፡ አንድ ፡ ነው ፡
ዕውቀታቸውም ፡ አንድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ነጡ ።
፲፩፤ ያንን ፡ ቀዳማዊ ፡ ቃልን ፡ ያመሰግኑታል ፡ ያከ
ብሩታል ፡ በዕውቀት ፡ ጸንተው ።
፲፪፤ በነገር ፡ እየተራቀቁ ፡ ሕይወት ፡ በሚሆን ፡ በመ
ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እየተቃኙ ፡ ያመሰግኑታል ፡
የመላእክት ፡ አብ ፡ አስታራቂ ፡ ክርስቶስን ፡
በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ አስቀመጠው ።
፲፫፤ ከጠፈር ፡ በላይ ፡ ባለ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡
የቅዱሳንን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ይመረምራል ፡ ሥራ
ቸውም ፡ በፍርዱ ፡ ይመረመራል ።
፲፬፤ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ስም ፡ አምነው ፡ በተናገር
ዋት ፡ በተሠወረች ፡ ሥራቸው ፡ ልዑል ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ በሠራት ፡ በእውነተኛ ፡ ሕግ ፡ አም
ነው ፡ የሠሯት ፡ ሥራቸውንም ፡ አውቆ ፡ ይፈ
ርድላቸው ፡ ዘንድ ፡ ፊቱን ፡ ቀና ፡ በደረገ ፡ ጊዜ ።
፲፭፤ ሁሉም ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ይናገራሉ ፡ ፈጽመው ፡
ያመሰግናሉ ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ስምንም ፡ ያከ
ብራሉ ፡ ያመሰግናሉ ።
፲፮፤ እሱም ፡ በሰማያት ፡ ያሉ ፡ መላእክትን ፡ ሁሉ ፡
በልዕልና ፡ ያሉ ፡ ቅዱሳንንም ፡ ሁሉ ፡ ይጠራል ።
(አመስግኑኝ ፡ ይላል ፡)
፲፯፤ የእግዚአብሔር ፡ ሠራዊት ፡ ኪሩቤል ፡ ሱራ
ፌል ፡ አፍኒን ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ መላእ
ክትም ፡ ሁሉ ፡ ሥላሴ ፡ የፈጠሯቸው ፡ መላእ
ክት ፡ ሁሉ ፡ ያመሰግናሉ ፡ ሌላ ፡ ዕውቀትም ፡
ይሰጣል ።
በደሴትና ፡ በየብስ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ለዚያች ፡ ፲፰፤
ቀን ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ተቀብለው ፡ ያመሰግናሉ ፡
ሃይማኖትን ፡ እንዲያጸኑ ፡ በሚያደርግ ፡ በመን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጥበብንም ፡ በሚገልጥ ፡ እንዲታ
ገሡም ፡ በሚያደርግ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ።
ለሰው ፡ እንዲራሩ ፡ በሚያደርግ ፡ እውነት ፡ ፲፱፤
እንዲፈርዱ ፡ ፍቅር ፡ አንድነትም ፡ እንዲያደ
ርጉ ፡ ለሰውም ፡ ቸርነት ፡ እንዲያደርጉ ፡ በሚ
ያደርግ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እየተቃኙ ፡ ይህን ፡
ሁሉ ፡ ያመሰግናሉ ፡ ያከብራሉ ።
ሁሉም ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ የከበረ ፡ ነው ፡ የመላእ ፳፤
ክት ፡ ጌታ ፡ ስምም ፡ ለዘላለም ፡ ይክበር ፡ ይመ
ስገን ፡ ይላሉ ።
የማያርፉ ፡ በሰማይ ፡ ያሉ ፡ መላእክትም ፡ ሁሉ ፡ ፳፩፤
እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ ያመሰግኑታል ፡ በልዕ
ልና ፡ ያሉ ፡ ሕጋውያን ፡ ሁሉ ፡ ድኅነት ፡ በሚገ
ኝበት ፡ በገነት ፡ የሚኖሩ ፡ ደናግልም ፡ ሁሉ ፡
ያመሰግኑታል ፡ አለ ።
ፈጽማ ፡ ማመስገን ፡ የከበረ ፡ ስምህንም ፡ ፈጽማ ፡ ፳፪፤
ማክበርን ፡ የሚችል ፡ ዕውቀት ፡ ያላት ፡ ሰው
ነት ፡ ሁሉ ፡ ናት ።
የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ቸርነቱ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ ከቀኑ ፳፫፤
ጣም ፡ የራቀ ፡ ነውና ፡ ሥጋዊት ፡ ደማዊት ፡
ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ከዕውቀት ፡ የወጣ ፡ ምስጋናን ፡
ለስምህ ፡ ለዘላለሙ ፡ ፈጽማ ፡ ታቀርባለች ።
ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ ያደረገውንም ፡ ኃይል ፡ ሁሉ ፡ ፳፬፤
በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ስም ፡ ላመኑ ፡ ለደናግልና ፡
ለሕጋውያን ፡ ገለጠ ።
ገዢ ፡ የሚሆን ፡ ጌታም ፡ ነገሥታቱን ፡ ጽኑዓን ፡ ፳፭፤
የከበሩ ፡ ሰዎችም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩት
ንም ፡ ሰዎች ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ አዘዘ ።
አስታራቂ ፡ ክርስቶስንም ፡ ማወቅ ፡ ትችሉ ፡ ፳፮፤
እንደ ፡ ሆነ ፡ ዓይኖቻችሁን ፡ ግለጡ ፡ ሥልጣና
ችሁንም ፡ አንሡ ፡ አለ ።
የሀብታት ፡ ጌታ ፡ ክርስቶስም ፡ በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ ፳፯፤
ተቀመጠ ፡ እውነተኛ ፡ የበሕርይ ፡ ክብሩም ፡
በሱ ፡ ተገለጠ ።
ከፉ ፡ የወጣውም ፡ ነገር ፡ ኃጥአንን ፡ ሁሉ ፡ በደ ፳፰፤
ለኞችንም ፡ ሁሉ ፡ ይገድላል ። ( ሐሩ ፡ ይላል ፡ )
እነሱም ፡ ከፊቱ ፡ ይጠፋሉ ።
በዚያችም ፡ ቀን ፡ ንጉሦቹ ፡ ሁሉ ፡ የከበሩ ፡ ሰዎ ፳፱፤
ችና ፡ የጸኑ ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ ይችንም ፡ ዓለም ፡
የሚገዟት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይቆማሉ ።
በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጦ ፡ ያዩታል ፡ ያውቁ ፴፤
ታል ፡ ጻድቃንም ፡ ሁሉ ፡ በውነት ፡ በፊቱ ፡
ይገዛሉ ።
በፊቱም ፡ ዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ የሚናገር ፡ የለም ። ፴፩፤
በምጥ ፡ እንደ ፡ ተያዘች ፡ ሴት ፡ ልጅዋ ፡ በማኅ ፴፪፤
ፀኗ ፡ ሊወጣ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ መውለዱ ፡ እንዲ
ያስጨንቃት ፡ ለመውለድም ፡ እንድትጨነቅ ፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



መከራውም ፡ እነሱን ፡ ያስጨንቃቸዋል ።
፴፫፡ እኩሌቶቹ ፡ ኃጥአን ፡ እኩሌቶቹ ፡ ኃጥአንን ፡ አይተው ፡ ይደነግጣሉ ፡ አንገታቸውን ፡ ይደፋሉ ።
፴፬፡ ከድንግል ፡ የተወለደ ፡ ያንንም ፡ ክርስቶስን ፡ በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጦ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ መከራው ፡ አስጨንቆ ፡ ይይዛቸዋል ።
፴፭፡ የአዳም ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡ ከዚያ ፡ አስቀድሞ ፡ በሥጋ ፡ አልተገለጠም ፡ ነበርና ፡ የጸኑ ፡ ነገሥታቱ ፡ ይችንም ፡ ዓለም ፡ የሚገዙት ፡ መኳንንትም ፡ ሁሉ ፡ የተሠወረውን ፡ የሚገዛ ፡ ክርስቶስን ፡ ፈጽመው ፡ ያመሰግኑታል ፡ ያከብሩታል ።
፴፮፡ የአዳም ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የተሠወረ ፡ ሆኖ ፡ ነበርና ፡ አብ ፡ በሠራዊቱ ፡ በመላእክት ፡ ፊት ፡ ለልብሰተ ፡ ሥጋ ፡ አዘጋጀው ፡ ለወዳጆቹም ፡ ገለጠው ፡ የደናግልና ፡ የሕጋውያን ፡ ጉባኤያቸው ፡ ይሰፋል ።
፴፯፡ ወዳጆቹ ፡ ጻድቃንም ፡ ሁሉ ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ በፊቱ ፡ ይቆማሉ ።
፴፰፡ የጸኑ ፡ ነገሥታቱም ፡ የከበሩ ፡ ሹማምትም ፡ ያችን ፡ ዓለም ፡ የሚገዝዋትም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በፊቱ ፡ በግምባራቸው ፡ ወድቀው ፡ በፊቱ ፡ ይሰግዳሉ ።
፴፱፡ ያን ፡ የአዳም ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስንም ፡ ተስፋ ፡ ያደርጉታል ፡ ይማለዱታል ፡ ከሱም ፡ ዘንድ ፡ ይቅርታውን ፡ ይለምናሉ ።
፵፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ከፊቱ ፡ ፈጥነው ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ ያስቸኩላቸዋል ።
፵፩፡ ፊታቸውም ፡ ኃፍረትን ፡ ይመላል ፡ ፊታቸውም ፡ በጥቁረት ፡ ላይ ፡ ጥቁረት ፡ ይጨምራል ።
፵፪፡ ልጆቹ ፡ ሕጋውያንን ፡ የመረጣቸው ፡ ደናግልንም ፡ በበደሏቸው ፡ ሰዎች ፡ ፍዳ ፡ ያመጣባቸው ፡ ዘንድ ፡ ለመቅሠፍት ፡ የታዘዙ ፡ መላእክት ፡ ይቀበሏቸዋል ።
፵፫፡ ለወደዳቸው ፡ አርአያ ፡ ይሆናሉ ።
፵፬፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ቍጣው ፡ በነሱ ፡ ትጸናለችና ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ሾተሉም ፡ ከደማቸው ፡ የተነሣ ፡ ትሰክራለችና ፡ ( ትገለጻለች ፡ ) ወዳጆቹ ፡ በነሱ ፡ ጥፋት ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ አለ ።
፵፭፡ ደናግልና ፡ ሕጋውያንም ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ ይድናሉ ።
፵፮፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የበደለኞችና ፡ የኃጥአንን ፡ ፊት ፡ አያዩም ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ በጻድቃን ፡ ላይ ፡ ያድርባቸዋል ።
፵፯፡ ከዚያ ፡ ከአዳም ፡ ልጅ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ይኖራሉ ፡ ፈጽመው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ ከመከራውም ፡ ያርፋሉ ፡ ለዘላለሙም ፡ ይከብራሉ ።
፵፰፡ ደናግልና ፡ ሕጋውያንም ፡ ከመቃብር ፡ ተነሡ ፡ አንገታቸውንም ፡ መድፋት ፡ ተዉ ።
፵፱፡ ሕይወት ፡ ልብስንም ፡ ለበሱ ፡ (ሕይወትን ፡ አገኙ ፡) እሱም ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ዘንድ ፡ ሕይወትነት ፡ ያለው ፡ ልብስ ፡ ይሆናቸዋል ።
፶፡ ልብሶቻችሁም ፡ አላረጁም ፡ (ክብራቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡) ክብራችሁም ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ አይፈጸምም ።
በነዚያ ፡ ወራቶች ፡ የጸኑ ፡ ይችን ፡ ዓለም ፡ የሚገዙት ፡ ነገሥታቱ ፡ ተይዘው ፡ ባሉበት ፡ በታ ፡ ጥቂት ፡ ዕረፍት ፡ ይሰጡቸው ፡ ዘንድ ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ እነሱም ፡ ወድቀው ፡ ይሰግዱ ፡ ዘንድ ፡ ለመቅሠፍት ፡ ከታዘዙ ፡ መላእክት ፡ ይለምናሉ ። ፶፩፡
ኃጢአታቸውንም ፡ በፊቱ ፡ አምነው ፡ የመላእክት ፡ ጌታን ፡ ፈጽመው ፡ ያመሰግኑታል ። ፶፪፡
ገዥ ፡ የሚሆን ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ የነገሥታት ፡ ጌታ ፡ የጽኑ ፡ ሰዎችም ፡ ጌታ ፡ የባለጸጋውም ፡ ጌታ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ የዕውቀትም ፡ ባለቤት ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ የተሠወረውም ፡ ሁሉ ፡ በሱ ፡ ዘንድ ፡ ይገለጣል ። ፶፫፡
ኃይልህም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ጌትነትህም ፡ ለዘላለም ፡ ነው ። ፶፬፡
ምሥጢርህም ፡ ሁሉ ፡ የረቀቀ ፡ ነው ፡ ቍጥርም ፡ የለው ፡ ለቸርነትህም ፡ ቍጥር ፡ የለውም ። (አይመረመርም ፡) ፶፭፡
አሁንም ፡ ነገሥታቱን ፡ የሚገዛ ፡ በነገሥታቱም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የሚነግሥ ፡ ጌታን ፡ ፈጽመን ፡ እናመሰግን ፡ ዘንድ ፡ ወደድን ፡ አሉ ። ፶፮፡
ፈጽመን ፡ እናመሰግነው ፡ ዘንድ ፡ እናከብረውም ፡ ዘንድ ፡ ጌትነቱንም ፡ እናምን ፡ ዘንድ ፡ ዕረፍትን ፡ ማን ፡ በሰጠን ፡ አሉ ። ፶፯፡
አሁንም ፡ ጥቂት ፡ ዕረፍት ፡ እንመኛለን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አናገኝም ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወጥተን ፡ እንሄዳለን ፡ ጥግ ፡ ይዘን ፡ አንቀርም ። ፶፰፡
በፊቱ ፡ አላመንምና ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ስሙንም ፡ አላመሰገንምና ፡ ብርሃን ፡ ከኛ ፡ ጠፋ ፡ ለዘላለሙም ፡ መኖሪያችን ፡ ጨለማ ፡ ነው ። ፶፱፡
ጌታችን ፡ እግዚአብሔርንም ፡ በሠራው ፡ ሁሉ ፡ አላመሰገነውም ፡ አለኝታችንም ፡ በመንግሥታችን ፡ ዙፋን ፡ ሥልጣን ፡ ሆነ ። ፷፡
ጌትነታችንም ፡ በደከምንበት ፡ መከራም ፡ በተቀበልንበት ፡ ቀን ፡ አላዳነንም ። ፷፩፡
ጌታችን ፡ እግዚአብሔር ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ በቸርነቱና ፡ በፍርዱም ፡ ሁሉ ፡ የታመነ ፡ ነውና ፡ የበደልነውን ፡ ኃጢአት ፡ እናምን ፡ ዘንድ ፡ ዕረፍትን ፡ አናገኝም ፡ ይላሉ ። ፷፪፡
እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ ገጸ ፡ ፍትሑን ፡ አያገኙም ፡ ስለ ፡ ክፉም ፡ ሥራችን ፡ ከፊቱም ፡ ተፈርዶብን ፡ እንሄዳለን ፡ ኃጢአታችንም ፡ ሁሉ ፡ በውነት ፡ ተቈጠረ ፡ ይላሉ ፡ አለ ። ፷፫፡
አለመብላታችን ፡ አለመጠጣታችን ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ከመውረድ ፡ አትከለክልምና ፡ አሁንም ፡ ሠርቀን ፡ ቀምተን ፡ ከጠራቀምነው ፡ ገንዘብ ፡ ሰውነታችን ፡ ትጥገብ ፡ ይሏቸዋል ። ፷፬፡
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዚያ ፡ በአዳም ፡ ልጅ ፡ በክርስቶስ ፡ ፊት ፡ ፊታቸው ፡ ኃፍረትንና ፡ ጨለማን ፡ ይመላል ። ፷፭፡
ከፊቱም ፡ ተሰደው ፡ ይሄዳሉ ፡ በነሱና ፡ በመከ ፷፮፡

ከላቸውም ፡ ሰይፍ ፡ ያድራል ። (ሥልጣን ፡ ያጸናል ፡)
፷፯፡ የመላእክትም ፡ ጌታ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ የነገሥታ
ቱና ፡ የጸኑ ፡ ሰዎች ፡ ይችን ፡ ዓለም ፡ ለሚገዙ ፡
ሰዎችና ፡ ለከበሩ ፡ ሹማምት ፡ በመላእክት ፡
ጌታ ፡ በአብ ፡ ፊት ፡ ሥራቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለ ።
፷፰፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ የትሠወሩ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎችን ፡
አየሁ ።
፷፱፡ ከደብር ፡ ቅዱስ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ የወረዱ ፡
በመሠወር ፡ ያለውንም ፡ ሁሉ ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡
የገለጡ ፡ ኃጢአትንም ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ የቃየ
ልን ፡ ልጆች ፡ ያሳቷቸው ፡ መላእክት ፡ እኒህ ፡
ናቸው ፡ ሲል ፡ የመልአኩን ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ፡
አለ ። (ደቂቀ ፡ ሴት ፡)

ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

፩፡ በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ ኖኅ ፡ ለጥፋት ፡ እንደ ፡
ቀረበች ፡ ጥፋቷም ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ምድርን ፡ አየ ።
፪፡ ከዚያ ፡ እግሩን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ምድር ፡
ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ሄደ ።
፫፡ ሄዶ ፡ ላያቱ ፡ ለሄኖክ ፡ ጮኸ ፡ ኖኅም ፡ በሚያሳ
ዝን ፡ ቃል ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ስማኝ ፡ ስማኝ ፡
ስማኝ ፡ አለ ።
፬፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ምንም ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ንገረኝ ፡ አለው ።
፭፡ እንዲህ ፡ ለጥፋት ፡ ቀርባለችና ፡ ተነዋውጣለ
ችና ፡ ወይስ ፡ እነሆ ፡ ከሷ ፡ ጋር ፡ እኔ ፡ እጠፋ ፡
ይሆን ፡ አለው ።
፮፡ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ታላቅ ፡ ሁከት ፡
ሆነ ፡ ከሰማይም ፡ ቃል ፡ ተሰማ ።
፯፡ በግምባሬ ፡ ፍግም ፡ ብዬ ፡ ወደቅሁ ፡ አያቴ ፡
ሄኖክም ፡ ወደኔ ፡ መጥቶ ፡ ባጠገቤ ፡ ቆመ ፡ እን
ዲህ ፡ የሚያሳዝን ፡ ፍጹም ፡ ልቅሶን ፡ ታለቅሳ
ለህ ፡ አለኝ ።
፰፡ እሱ ፡ ጥፋታቸው ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ከመላእክት ፡ ጌታ ፡
ፊት ፡ ትእዛዝ ፡ ወጣ ፡ አለኝ ።
፱፡ የመላእክትን ፡ ምሥጢር ፡ ሁሉ ፡ ሰይጣናት ፡
የሚሠሩትንም ፡ ግፍ ፡ ሁሉ ፡ የተሠወረ ፡ ሥራ
ቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ሟርት ፡ የሚያሟርቱ ፡ የሰዎ
ችን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የቀለማትንም ፡ ምሥጢር ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ጣዖት ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ሥራን ፡
አስተምረዋልና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ትእ
ዛዝ ፡ ወጣ ፡ አለኝ ።
፲፡ እነሱ ፡ ባያስተምሩ ፡ ከመሬቱ ፡ ትቢያ ፡ ብር ፡
እስኪ ፡ እንዴት ፡ ይገኝ ፡ ነበር ።
፲፩፡ እነሱን ፡ የሚያስገኛቸው ፡ መሬት ፡ ቀድሞ ፡
እንደ ፡ ተገኘ ፡ በሷም ፡ የተሾመው ፡ ስማዝያ ፡
ከመሬት ፡ እንደ ፡ ተገኘ ፡ እነሳቸው ፡ ባያስተ
ምሩ ፡ እርሳስ ፡ ቅልቅልም ፡ ከመሬት ፡ አይገ
ኝም ፡ ነበርና ፡ እይርስ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እስኪ ፡
እንዴት ፡ ይገኝ ፡ ነበር ።
፲፪፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አያቴ ፡ ሄኖክ ፡ በጄ ፡ ይዞ ፡ አነ
ሣኝ ።

ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ስለ ፡ ታዘዘው ፡ ሁከት ፡ ፲፫፡
የመላእክትን ፡ ጌታ ፡ ጠይቄዋለሁና ፡ ሂድ ፡
አለኝ ።
ስለ ፡ ሠሩት ፡ በደላቸው ፡ መቻያቸው ፡ ተፈጸ ፲፬፡
መችባቸው ፡ ስለ ፡ ፈለጓቸውም ፡ ወራቶች ፡
በፊቴ ፡ አይቈጠርላቸውም ፡ አለኝ ።
ምድር ፡ እንድትጠፋ ፡ በሷም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ፲፭፡
እንዲጠፉ ፡ እወቁ ፡ የተሠወረውን ፡ ኃጢአት ፡
ለሰዎች ፡ አስተምረዋልና ፡ እነሱም ፡ የተፈረደ
ባቸው ፡ ናቸውና ፡ እነሱ ፡ ለዘላለም ፡ መመለስ ፡
የላቸውም ።
ከተሠወረው ፡ ከዚህ ፡ ነቀፋ ፡ አንተ ፡ ንጹሕ ፡ ፲፮፡
እንደ ፡ ሆንክ ፡ ቸርም ፡ እንደ ፡ ሆንክ ፡ የመላእ
ክት ፡ ጌታ ፡ አውቋልና ፡ አንተ ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡
መከራው ፡ ላንተ ፡ አይደለም ።
በቅዱሳን ፡ መካከልም ፡ ስምህን ፡ አጽናው ፡ ፲፯፡
በዚህ ፡ ዓለምም ፡ ካሉ ፡ ሰዎች ፡ ለይተው ፡ መላ
እክት ፡ ይጠብቁሃል ።
ለመንግሥት ፡ ለብዙ ፡ ምስጋናም ፡ ሊሆን ፡ ልጅ ፲፰፡
ህን ፡ በውነት ፡ አጽናው ፡ ከልጅህም ፡ የቅዱሳ
ንና ፡ የጻድቃን ፡ መገኛ ፡ አብርሃም ፡ ይወለዳል ፡
ለዘላለሙም ፡ ቍጥር ፡ የላቸውም ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ እንዲመጡ ፡ ፲፱፡
በዚህም ፡ ዓለም ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
መቻያ ፡ ጥፋት ፡ ሊሆን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ያለ ፡
የውሀውንም ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ይከፍቱ ፡ ዘንድ ፡
የተዘጋጀ ፡ ለመቅሠፍት ፡ የታዘዙ ፡ መላእክ
ትን ፡ አሳየኝ ።
የመላእክት ፡ ጌታም ፡ እነዚያ ፡ መላእክት ፡ በው ፳፡
ሀው ፡ ሥራ ፡ ተሾመው ፡ አሉና ፡ ለትእዛዝ ፡
የወጡ ፡ መላእክትን ፡ እጃቸውን ፡ እንዳያነሱ ፡
ያዘዛቸውን ፡ እንዲጠብቁ ፡ አዘዘ ።
ከሄኖክም ፡ ፊት ፡ ወጣሁ ። ፳፩፡
በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃሉ ፡ ፳፪፡
ወደኔ ፡ ወጣ ።
ኖኅ ፡ እድል ፡ ፋንታህ ፡ እነሆ ፡ ወደኔ ፡ ደረሰ ፡ ፳፫፡
ይኸውም ፡ ነውር ፡ ነቀፋ ፡ የሌለበት ፡ እድል ፡
የቀና ፡ ነገርና ፡ ፍቅር ፡ ያለበት ፡ እድል ፡ ነው ፡
አለኝ ።
አሁንም ፡ መላእክት ፡ እንጨቶችን ፡ ያምጡ ፳፬፡
ልህ ፡ መላእክት ፡ ለዚያ ፡ ሥራ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡
እጄን ፡ ጭኜ ፡ መርከብን ፡ እጠብቃታለሁ ።
ከመርከብ ፡ ወጥተህ ፡ ሕይወት ፡ ያለው ፡ ዘር ፡ ፳፭፡
ትሆናለህ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ባዶውን ፡ እንዳይቀር ፡
በሞተው ፡ ለውጥ ፡ ይግባ ።
ልጅህንም ፡ ለዘላለም ፡ በፊቱ ፡ አጸናዋለሁ ፡ ፳፮፡
ካንተ ፡ ጋራ ፡ የሚኖሩ ፡ ልጆችህንም ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ አበዛቸዋለሁ ።
በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ስም ፡ ያመነ ፡ ሰውም ፡ ፳፯፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይበዛል ፡ ይከብራል ።
ግፍን ፡ ያስተማሩት ፡ እነዚያን ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፳፰፡
ንም ፡ መላእክት ፡ የብርና ፡ የወርቅ ፡ የይርና ፡
የብረት ፡ የናስም ፡ ተራሮች ፡ ባሉበት ፡ በምዕ
ራብ ፡ አያቴ ፡ ሄኖክ ፡ ቀድሞ ፡ ባሳየኝ ፡ በምት

ነድ ፡ በዚያች ፡ በገሃነም ፡ ያግዟቸዋል ።
፴፱፡ ታላቅ ፡ መከራ ፡ ያለበት ፡ የውሀዎችም ፡ መታ
ወክ ፡ ያለበት ፡ ያችን ፡ ገሃነም ፡ አየኋት ።
፵፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ከእሳቱ ፡
ነጠብጣብ ፡ የተነሣ ፡ ከሚያውኳቸውም ፡ ሁከት ፡
የተነሣ ፡ በዚያ ፡ በታ ፡ የድኝ ፡ ሽታ ፡ ተወለደ ፡
( ተገኘ ፡ ) ከነዚያም ፡ ውሀዎች ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡
ሆነ ፡ አለኝ ፡ አለ ።
፵፩፡ ሰውን ፡ ያሳቱ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ያሉበት ፡ ያችም ፡
ገሃነም ፡ በዚያች ፡ ምድር ፡ በታች ፡ ትነዳለች ።
፵፪፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ ሰዎችን ፡ ያሳቷቸው ፡
እነዚያ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ በሚኰነኑበት ፡ በታ ፡
ወደ ፡ ቈላዎች ፡ የእሳት ፡ ፈሳሾች ፡ ይፈሳሉ ።
፵፫፡ እነዚያም ፡ ውሀዎች ፡ በነዚያ ፡ ወራት ፡ ለነገሥ
ታቱ ፡ ለፀኑም ፡ ሰዎች ፡ ለከበሩም ፡ ሰዎች ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለሚኖሩም ፡ ሰዎች ፡ ለሥጋና ፡
ለነፍስ ፡ ድኅነት ፡ ለሰውነታቸውም ፡ መቻያ ፡
ይሆናሉ ።
፵፬፡ የመላእክት ፡ ጌታን ፡ ክደውታልና ፡ በሥጋቸው ፡
ይፈርድባቸው ፡ ዘንድ ፡ ልቡናቸው ፡ ዋዛ ፡ ነገ
ርን ፡ ይመላል ።
፵፭፡ በቀኑ ፡ ሁሉ ፡ የሚደረግባቸው ፡ መከራቸውን ፡
ያያሉ ፡ በስሙም ፡ አያምኑም ።
፵፮፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ ዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ የሚና
ገር ፡ የለምና ፡ ሥጋቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡
ተቃጠለ ፡ መጠን ፡ ለዘለዓለሙ ፡ በነፍሳቸው ፡
እንደዚህ ፡ ይለወጡባቸዋል ።
፵፯፡ በነሱ ፡ መቻያ ፡ ትመጣለችና ፡ በሥጋቸው ፡ በሚ
ሠሩት ፡ ዋዛ ፡ ነገር ፡ ያምናሉና ፡ የእግዚአብሔ
ርንም ፡ ባሕርይ ፡ ሕይወቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡
ይክዳሉና ፡ በነፍሳቸው ፡ ይለወጥባቸዋል ።
፵፰፡ እሊያ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ በተፈረደባቸው ፡ ጊዜ ፡
የነህ ፡ ውሀዎች ፡ ማቃጠል ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡
ይለወጣልና ፡ እነዚያ ፡ ውሀዎች ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡
መለወጥ ፡ አላቸው ።
፵፱፡ መላእክት ፡ ማየ ፡ አይህን ፡ አውርደው ፡ ካወጡ ፡
በኋላ ፡ የምንጮች ፡ ውሀ ፡ ተለውጦ ፡ ይቀዘቅ
ዛል ።
፶፡ እነዚያ ፡ መቻያ ፡ የሚሆኑ ፡ ውሀዎች ፡ ቢመ
ለሱ ፡ ለደቂቀ ፡ ሴት ፡ ሰውነት ፡ ድኅነት ፡ በይመ
ለሱ ፡ ለሥጋቸው ፡ ሞት ፡ ናቸውና ፡ ደቂቀ ፡
ሴት ፡ የሚኰነኑበት ፡ ይች ፡ መከራ ፡ ለነገሥ
ታቱ ፡ ይችን ፡ ዓለም ፡ ለሚገዙትም ፡ ዕሩዓን ፡
ሁሉ ፡ የኃጢአታቸው ፡ ምስክር ፡ ናት ፡ ብሎ ፡
ቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ ሲናገር ፡ ሰማሁት ።
፶፩፡ እኒያ ፡ ውሀዎች ፡ ተለውጠው ፡ ለዘላለሙ ፡ የሚ
ነድ ፡ እሳት ፡ እንዲሆኑባቸው ፡ አይተው ፡ አያ
ምኑም ።
፶፪፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አያቴ ፡ ሄኖክ ፡ የተሰጡትን ፡ ነገ
ሮች ፡ ሁሉ ፡ ምልክት ፡ በመጽሐፍ ፡ ጽፎ ፡
ሰጠኝ ፡ ለሱም ፡ የተሰጡትን ፡ ነገሮች ፡ የኔ ፡
ነገር ፡ በተጻፈበት ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፎ ፡ አንድ ፡
አድርጎ ፡ ሰጠኝ ፡ አለ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

በዚያችም ፡ ቀን ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ የመን ፩፡
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዕውቀቱ ፡ ወደ ፡ ኃዘን ፡ ይወስደ
ኛል ፡ ያበሳጨኛል ፡ ብሎ ፡ ለቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡
መለሰለት ።
ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ስለሚቀበሏት ፡ ስለ ፡ ተሠወረች ፪፡
ውም ፡ መከራ ፡ ስለ ፡ መጨነቅስ ።
ስትሠራ ፡ የኖረች ፡ እነሱም ፡ በፊቷ ፡ እንደ ፡ ፫፡
ሰም ፡ የሚቀልጡበት ፡ የመከራይቱን ፡ ጭንቅ ፡
መታገሥ ፡ የሚቻለው ፡ ማነው ፡ ብሎ ፡ መለሰ
ለት ።
ዳግመኛ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሩፋኤልን ፡ በዚች ፡ ፬፡
ነገር ፡ ልቡናውን ፡ የሚያራራ ፡ ከዚችም ፡ ቃል ፡
የተነሣ ፡ ዡላሊቱ ፡ የማይተዋወክበት ፡ ማነው ፡
ብሎ ፡ መለሰለት ።
መከራም ፡ መጣባቸው ፡ መከራዎችንም ፡ እንደ ፭፡
ዚህ ፡ ያመጧቸው ፡ በኃጢአታቸው ፡ ነው ።
ለመማለድም ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ በቆመ ፡ ፮፡
ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሩፋኤ
ልን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ተቈ
ጥቷቸዋልና ፡ በጌታ ፡ ፊት ፡ ይቅርታ ፡ አይደረ
ግላቸውም ፡ አለው ።
በጌታ ፡ አምሳል ፡ ጣዖቱን ፡ ይሠራሉና ፡ ስለ ፯፡
ዚህ ፡ ነገር ፡ ለዘላለሙ ፡ የተሠወረ ፡ መከራ ፡
ይመጣባቸዋል ።
እነሱ ፡ ብቻ ፡ መቻያቸውን ፡ ለዘላለሙ ፡ ተቀበ ፰፡
ሉት ፡ እንጂ ፡ አለቃም ፡ ቢሆን ፡ ጭፍራም ፡
ቢሆን ፡ ያንዱን ፡ መከራ ፡ አንዱ ፡ አይቀበለው
ምና ፡ ስለዚህ ፡ መከራ ፡ ትመጣባቸዋለች ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ይችን ፡ ኃጢ ፱፡
አት ፡ ገልጠው ፡ አስተምረዋልና ፡ ከዚህ ፡ መከ
ራቸው ፡ በኋላ ፡ አጋንንት ፡ ያስደነግጧቸዋል ፡
ያሳገቧቸዋል ።
የነዚያም ፡ የአጋንንት ፡ ስማቸው ፡ እነሆ ፡ እን ፲፡
ዲህ ፡ ነው ፡ የደቂቀ ፡ ሴትም ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡
ነው ።
አለቃቸው ፡ ስማዝያ ፡ ነው ፡ ሁለተኛውም ፡ አር ፲፩፡
ስጢኪፉ ፡ ነው ፡ ሦስተኛውም ፡ አርሚን ፡ ነው ፡
አራተኛውም ፡ ከከብኤል ፡ ነው ።
አምስተኛውም ፡ ጡርኤል ፡ ነው ፡ ስድስተኛ ፲፪፡
ውም ፡ ሩምያል ፡ ነው ፡ ሰባተኛውም ፡ ዳንኤል ፡
ስምንተኛውም ፡ ምቃኤል ፡ ነው ፡ ዘጠኝኛ
ውም ፡ በራቃኤል ፡ ነው ፡ አሥረኛው ፡ አዛዝ
ኤል ፡ ነው ፡ አሥራ ፡ አንደኛውም ፡ አርማሮስ ፡
ነው ፡ አሥራ ፡ ሁለተኛውም ፡ በጠርያል ፡ ነው ።
አሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ በስላኤል ፡ ነው ፡ አሥራ ፡ ፲፫፡
አራተኛውም ፡ አናንያል ፡ ነው ፡ አሥራ ፡ አም
ስተኛውም ፡ ጡርያል ፡ ነው ፡ አሥራ ፡ ስድስተ
ኛውም ፡ ሲምሳፒኤል ፡ ነው ።
አሥራ ፡ ሰባተኛውም ፡ ይታርኤል ፡ ነው ፡ ፲፬፡
አሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ቱማኤል ፡ ነው ፡ አሥራ ፡
ዘጠኝኛውም ፡ ጥራኤል ፡ ነው ፡ ሀያኛውም ፡

ራሙኤል ፡ ነው ፡ ሀያ ፡ አንደኛውም ፡ አዛዝ
ኤል ፡ ነው ።
፲፭፤ ያለቆቻቸው ፡ አለቆች ፡ እሊህ ፡ ናቸው ።
፲፮፤ የመቶው ፡ አጋንንት ፡ አዝማች ፡ ያምሳ ፡ አለቃ ፡
ያሥር ፡ አለቃ ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የመጀ
መሪያው ፡ ስሙ ፡ ይቆን ፡ ነው ።
፲፯፤ ደቂቀ ፡ ሴትንም ፡ ሁሉ ፡ ያሳተ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለ
ምም ፡ ያወረዳቸው ፡ በቃየልም ፡ ልጆች ፡ ያሳ
ታቸው ፡ ይህ ፡ ነው ።
፲፰፤ ሁለተኛውም ፡ ስሙ ፡ አስብኤል ፡ ነው ፡ ይህ ፡
ንጹሐን ፡ ለሆኑ ፡ ለደቂቀ ፡ ሴት ፡ ክፉ ፡ ምክርን ፡
አስተማራቸው ፡ ሰውነታቸውንም ፡ በቃየል ፡
ልጆች ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ አሳታቸው ።
፲፱፤ ሦስተኛውም ፡ ስሙ ፡ ጋድርኤል ፡ ነው ፡ መትቶ ፡
መግደልን ፡ ሁሉ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ያስተማረ ፡
ይህ ፡ ነው ።
፳፤ ሔዋንንም ፡ ያሳታት ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ለሰው ፡ ልጆ
ችም ፡ የሞት ፡ መሣርያን ፡ ጋሻን ፡ ጥሩርን ፡
ለሰልፍም ፡ ሰይፍን ፡ ያስተማረ ፡ እሱ ፡ ነው ።
፳፩፤ ለሰውም ፡ ልጆች ፡ የሚጋደሉበት ፡ የሚዳ ፡
ዕብቱን ፡ ሁሉ ፡ አስተማረ ፡ ከዚያች ፡ ቀን ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከሱ ፡ ቃል ፡
ወጣባቸው ፡ አለ ።
፳፪፤ አራተኛውም ፡ ስሙ ፡ ፔንሙዕ ፡ ይባላል ፡
ለሰው ፡ ልጆችም ፡ የጣፈጠውንና ፡ የመረረ
ውን ፡ ያስተማረ ፡ ይህ ፡ ነው ።
፳፫፤ የተሠወረ ፡ ጥበባቸውን ፡ ሁሉ ፡ አስተማራ
ቸው ፡ ለሰዎችም ፡ በጥቍር ፡ ቀለም ፡ በወረቀት ፡
ቀይ ፡ መጽሐፍ ፡ መጻፍን ፡ አስተማራቸው ።
፳፬፤ እንደ ፡ መላእክት ፡ ንጹሐን ፡ ጻድቃን ፡ ሁነው ፡
ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ በእንዲህ ፡
ያለ ፡ ሥራ ፡ አልተፈጠረም ፡ በጥቍር ፡ ቀለምና ፡
በቀይ ፡ ቀለም ፡ ጽፈው ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ሊያ
ጸኑ ፡ ሰው ፡ ለእንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ አልተፈጠ
ረም ፡ ነበርና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ እስከዚያችም ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡
ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይስታሉ ፡ አለ ።
፳፭፤ ይህን ፡ በማወቃቸው ፡ ይጠፋሉ ፡ እንጂ ፡ ሁሉን ፡
የሚያጠፋ ፡ ባላገኛቸውም ፡ ነበር ።
፳፮፤ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ እውቀት ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ይበ
ላኛል ።
፳፯፤ ያምስተኛውም ፡ ስሙ ፡ ካዕድያዕ ፡ ይባላል ፡
ግዙፋኑና ፡ ረቂቃኑን ፡ አጋንንት ፡ ያመጡትን ፡
ክፉ ፡ መቀራደድን ፡ ሁሉ ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡
ያስተማረ ፡ እሱ ፡ ነው ።
፳፰፤ በናቱ ፡ ማኅፀን ፡ ያለ ፡ ዕንስ ፡ ወጥቶ ፡ ይወድቅ ፡
ዘንድ ፡ ዕንስ ፡ ማስወረድን ፡ ነፍስ ፡ መግደል
ንም ፡ አስተማረ ።
፳፱፤ ያውሬ ፡ መንከስን ፡ ስሙ ፡ ጨከኝ ፡ የሚባል ፡
ያውሬ ፡ ልጅ ፡ እሱ ፡ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ የሚደረጉ ፡
ሥራዎችን ፡ ሁሉ ፡ አስተማረ ፡ አለ ።

ምዕራፍ ፡ ፳ ።

እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በጌትነት ፡ ፩፤
በኖረ ፡ ጊዜ ፡ ለቅዱሳን ፡ የገለጠው ፡ የመሐላ ፡
ፍጻሜ ፡ የክስብኤል ፡ የስሙ ፡ ቍጥር ፡ ይህ ፡
ነው ።
ሁለተኛውም ፡ ስሙ ፡ ቤቃ ፡ ይባላል ፡ ይኸውም ፡ ፪፤
አጋንንት ፡ ያንን ፡ የተሠወረ ፡ ስሙን ፡ ይሰሙት ፡
ዘንድ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ የተሠወረ ፡ ስሙን ፡
ግለጥላቸው ፡ አለው ።
የተሠወረውን ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ፫፤
ያስተማሩ ፡ አጋንንት ፡ ከዚያ ፡ መሐላና ፡ ከዚያ ፡
ስም ፡ የተነሣ ፡ ይንቀጠቀጡ ፡ ዘንድ ፡ በመሐ
ላም ፡ ጊዜ ፡ ይጠሩት ፡ ዘንድ ፡ ያንን ፡ የተሠ
ወረ ፡ ስሙን ፡ ግለጥላቸው ፡ አለው ።
ኃይለኛ ፡ ነውና ፡ የጸናም ፡ ነውና ፡ የዚህ ፡ የመ ፬፤
ሐላ ፡ ምሥጢሩ ፡ ይህ ፡ ነው ።
ይኸንንም ፡ ስም ፡ ከሃሊ ፡ የሚሆን ፡ አምላክ ፡ ፭፤
በቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ እጅ ፡ አኖረው ፡ የዚህም ፡
ስም ፡ የተሠወሩ ፡ ምሥጢሮቹ ፡ እነህ ፡ ናቸው ፡
ፍጥረታቱም ፡ ሁሉ ፡ በመሐላው ፡ ጸና ።
በዚህም ፡ ስም ፡ ሰማይ ፡ ፀና ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ፮፤
ነበር ፡ እስከ ፡ ዘላለሙም ፡ ይኖራል ፡ ምድርም ፡
በሱ ፡ በውሀው ፡ ላይ ፡ ተፈጠረች ።
ከተራሮችም ፡ ውስጥ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፯፤
ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ የጣፈጡ ፡ ውሀዎች ፡ ይመነ
ጫሉ ።
በዚያም ፡ ስም ፡ ባሕር ፡ ተፈጠረች ፡ መሠረ ፰፤
ቷም ፡ ተፈጠረ ፡ በተቈጣችም ፡ ጊዜ ፡ እንዳት
ወጣ ፡ በሸዋ ፡ ገደባት ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ ከድምበሯ ፡ አታልፍም ።
በዚያም ፡ ስም ፡ ጥልቅ ፡ ውሀዎች ፡ ሁሉ ፡ ጸን ፱፤
ተው ፡ ኖሩ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡
ድረስ ፡ ከቦታቸው ፡ አይወጡም ።
በዚያም ፡ ስም ፡ ጨረቃና ፡ ፀሐይ ፡ ጎዳናቸ ፲፤
ውን ፡ ይጨርሳሉ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮም ፡ እስከ ፡
ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ ካዘዛቸው ፡ ትእዛዝ ፡ አልወ
ጡም ።
በዚያም ፡ ስም ፡ ከከቦች ፡ ጎዳናቸውን ፡ ይጨር ፲፩፤
ሳሉ ፡ ስማቸውንም ፡ ይጠራል ፡ እነሱም ፡ ከጥ
ንት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ ይሰሙ
ታል ።
እንደዚሁ ፡ ነፍሳት ፡ ሕይወት ፡ የሚሆናቸው ፡ ፲፪፤
የውሀዎች ፡ አካሎች ፡ የነፋሶችም ፡ ሁሉ ፡ አካ
ሎች ፡ ከነፋሶች ፡ ቅመምነት ፡ ሁሉ ፡ የተገኙ ፡
ሥራዎቻቸውም ፡ ተፈጠሩ ።
በዚያም ፡ ቦታ ፡ የነጐድጓድ ፡ የቃሉ ፡ በታዎች ፡ ፲፫፤
ይጠበቃሉ ፡ የመብረቅም ፡ ብርሃን ፡ ይጠበቃል ።
በዚያም ፡ ቦታ ፡ የውርጭና ፡ የበረድ ፡ በታዎች ፡ ፲፬፤
የጉምም ፡ በታዎች ፡ የጤዛና ፡ የዝናም ፡ በታ
ዎች ፡ ይጠበቃሉ ።
በነዚያም ፡ ሁሉ ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ ፲፭፤

አምነው ፡ ያመሰግናሉ ፡ በፍጹም ፡ አእምሮዋ
ቸው ፡ ያመሰግናሉ ።
፲፮ በሥራቸውም ፡ ሁሉ ፡ ምግባቸው ፡ ምስጋና ፡
ናት ፡ ፈጽመው ፡ ያመሰግናሉ ፡ ለዘላለሙ ፡
የሚኖር ፡ የነፍሳት ፡ ጌታ ፡ ስሙንም ፡ ያከብ
ራሉ ።
፲፯ ይህም ፡ ስም ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ጸና ፡ በሱም ፡ ይጠ
በቃሉ ፡ ሥራዎቻቸውም ፡ ይጠበቃሉ ፡ ጎዳና
ቸውም ፡ አይጠፋም ።
፲፰ ይኸውም ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ሆነላቸው ፡ ፈጽመ
ውም ፡ አመሰገኑ ፡ ከአዳም ፡ የተወለደ ፡ የክር
ስቶስ ፡ ስሙ ፡ ስለ ፡ ተገለጠላቸውም ፡ እሱን ፡
አከበሩ ።
፲፱ በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ ላይም ፡ ተቀመጠ ፡ ለአዳም ፡
ልጅ ፡ ለክርስቶስም ፡ የፍርድ ፡ ፍጻሜ ፡ ተሰ
ጠው ።
፳ ከመንግሥት ፡ ሰማያትም ፡ በታ ፡ ኃጥአንን ፡
ፈጽሞ ፡ ያጠፋል ፡ ሰውን ፡ ያሳቱ ፡ ደቂቀ ፡ ሴትም ፡
በሰንሰለት ፡ ይታሠራሉ ፡ አለ ። (በፍዳ ፡ ነው ፡)
፳፩ ጥፋተኛ ፡ ወገናቸውም ፡ በሲኦል ፡ ይጋዛል ፡
ሥራቸውም ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ይጠፋል ።
፳፪ ከሰው ፡ የተወለደ ፡ ክርስቶስ ፡ ተገልጦ ፡ በጌት
ነቱ ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጧልና ፡ ክፉ ፡ ነገርም ፡
ሁሉ ፡ ከፊቱ ፡ ይጠፋልና ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡
ፈርሶ ፡ በስብሶ ፡ የሚቀር ፡ የለም ።
፳፫ ሄደውም ፡ ከሰው ፡ ለተወለደ ፡ ክርስቶስ ፡ በደ
ላቸውን ፡ ይነግሩታል ፡ በነፍሳት ፡ ጌታ ፡ ፊትም ፡
ፍርዱ ፡ ይጸናል ፡ የሄኖክ ፡ ሦስተኛ ፡ ነገሩ ፡
ይህ ፡ ነው ።
፳፬ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡
በአብ ፡ ዘንድ ፡ የአዳም ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡
ሕያው ፡ የሚሆን ፡ ስሙ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከሚ
ኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ይልቅ ፡ ከበረ ፡ ገነነ ።
፳፭ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ባደረበቸው ፡ በሐዋርያትም ፡
ልሰልናውን ፡ ገለጠ ፡ በመከከላቸውም ፡ ስም ፡
ወጣለት ፡ አለ ፡ ቀዳማዊ ፡ አምላክ ፡ ተባለ ።
፳፮ ከዚያች ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በመከከላቸው ፡ አልኖር
ኩም ፡ አለ ። (ሄኖክ ፡)
፳፯ ለሕጋውያንና ፡ ለደናግል ፡ ቦታን ፡ ይሰፍሩልኝ ፡
ዘንድ ፡ መላእክት ፡ ገመዶችን ፡ በተቀበሉበት ፡
በሁለቱ ፡ ማዕዘን ፡ በምዕራብና ፡ በሰሜን ፡ መከ
ከል ፡ አኖረኝ ።
፳፰ ከዚያም ፡ የቀድሞ ፡ አባቶችን ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡
በዚያ ፡ ቦታ ፡ የሚኖሩ ፡ ሕጋውያንንም ፡ አየሁ ።
፳፱ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፡ ልቡናዬ ፡ ትራ
ቀቅ ፡ ጀመር ፡ ከሰማዮች ፡ በላይ ፡ ወጻለች ፡
ወደ ፡ ጽርሐ ፡ አርያምም ፡ ትወጣ ፡ ጀመር ።
፴ ከቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ በግብር ፡ የተወለዱ ፡
ጻድቃንንም ፡ በእሳት ፡ ዋዕይ ፡ ላይ ፡ ቁመው ፡
አየኋቸው ። (መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡) ቀሚሳቸው ፡
መጐናጸፊያቸውም ፡ ነጭ ፡ ነው ፡ (ጸጋ ፡ ክብር ፡)
የፊታቸውም ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ነው ፡
አለ ።
፴፩ ሁለት ፡ የእሳት ፡ ፈሳሾችንም ፡ አየሁ ፡ የዚያም ፡
የእሳት ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ ዕንቍ ፡ ያበራል ፡ በሀ
ብታት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ በፊቴ ፡ ፍግም ፡ ብዬ ፡ ወደ
ቅሁ ።
የመላእክት ፡ አለቆች ፡ አንዱ ፡ መልአክ ፡ ሚካ ፴፪
ኤል ፡ ቀኝ ፡ እጄን ፡ ይዞ ፡ አነሣኝ ይቅርታው ፡
ወደ ፡ ተሠወረበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ቸርነቱም ፡
ወደ ፡ ተሠወረበት ፡ ቦታ ፡ አወጣኝ ።
በሰማይ ፡ ዳርቻ ፡ የተሠወሩትንም ፡ ሁሉ ፡ የከ ፴፫
ዋክብትንም ፡ ቦታዎች ፡ ሁሉ ፡ ለሰው ፡ ሊያበሩ ፡
የሚወጡ ፡ የብርሃኖችንም ፡ ሁሉ ፡ ቦታ ፡ አሳየኝ ።
መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ሄኖክን ፡ በሰማዮች ፡ በላይ ፡ ፴፬
ባለ ፡ ሰማይ ፡ ሠወረው ። (አራቀቀው ፡)
በዚያም ፡ ብርሃን ፡ መከከል ፡ በዕንቍ ፡ የተሠራ ፡ ፴፭
ቤትን ፡ አየሁ ።
በነዚያም ፡ ድንጋዮች ፡ መከከል ፡ ደኅነኛ ፡ የሚ ፴፮
ሆን ፡ የእሳት ፡ (መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡) አንደበቶች ፡
(መምህራን ፡) አሉ ፡ አለ ።
ሰውነቴም ፡ እሳት ፡ የሚከበው ፡ የዚያን ፡ ቤት ፡ ፴፯
ዙሪያ ፡ አየች ፡ በዚያም ፡ ወንዝ ፡ ባራቱ ፡ ማዕ
ዘን ፡ ሕያው ፡ የሚሆን ፡ የጌታን ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡
የተመሉ ፡ መምራን ፡ አሉበት ።
ኪሩቤልና ፡ ሱራፌል ፡ አፍኒንም ፡ የዚህን ፡ ፴፰
ቤት ፡ ዙሪያውን ፡ ከበውታል ፡ እነዚህም ፡ የማ
ያርፉ ፡ ናቸው ፡ የጌትነቱንም ፡ ዙፋን ፡ ይጠብ
ቃሉ ።
የማይቈጠሩ ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ የሚሆኑ ፡ መላእ ፴፱
ክትን ፡ አየሁ ።
ገብርኤልና ፡ ሚካኤል ፡ ፋኑኤል ፡ ሩፋኤል ፡ ፵
ያንን ፡ ቤት ፡ ይከቡታል ፡ በሰማይ ፡ ያሉ ፡ የከ
በሩ ፡ መላእክትም ፡ በዚያ ፡ ቤት ፡ ይወጡ ፡
ይገቡ ፡ ነበር ።
ከዚያም ፡ ቤት ፡ ገብርኤልና ፡ ሚካኤል ፡ ፋኑኤ ፵፩
ልና ፡ ሩፋኤልም ፡ ብዙ ፡ የሆኑ ፡ ቍጥር ፡ የሌላ
ቸው ፡ ሌሎች ፡ መላእክት ፡ የከበሩ ፡ ወጡ ።
ብሉየ ፡ መዋዕልነት ፡ ገንዘቡ ፡ የሚሆን ፡ ጌታም ፡ ፵፪
ከነሱ ፡ ጋራ ፡ አለ ፡ ራሱም ፡ እንደ ፡ ብዝት ፡
ነጭ ፡ ነው ፡ ንጹሕም ፡ ነው ፡ ልብሱም ፡ የማይ
ተረጐም ፡ ነው ።
እኔም ፡ በግምባሬ ፡ ፍግም ፡ ብዬ ፡ ወደቅሁ ፡ ፵፫
ሥጋዬም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሰም ፡ ቀለጠ ፡ አእም
ሮዬም ፡ ተለወጠ ።
በታላቅ ፡ ቃል ፡ እውቀት ፡ ባለበት ፡ ልቡና ፡ ፵፬
አሰምቼ ፡ ጮኹ ፡ ፈጽሜም ፡ እሱን ፡ አመሰገ
ንሁ ፡ ስሙንም ፡ አከበርኩ ።
ከፊ ፡ የወጡ ፡ እኒህ ፡ ምስጋናዎች ፡ ዕለተ ፡ ፵፭
እሑድ ፡ ገንዘቡ ፡ በሆንችለት ፡ በዚያ ፡ በጌታ ፡
ፊት ፡ የተወደዱ ፡ ሆኑ ፡ አለ ።
ብሉየ ፡ መዋዕልነት ፡ ገንዘቡ ፡ የሚሆን ፡ ያም ፡ ፵፮
ጌታ ፡ ከገብርኤልና ፡ ከሚካኤል ፡ ከፋኑኤልና ፡
ከሩፋኤልም ፡ ቍጥር ፡ ከሌላቸው ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡
ከሚሆኑ ፡ መላእክትም ፡ ጋራ ፡ ወደኔ ፡ መጣ ።
ያም ፡ መልአክ ፡ ወደኔ ፡ መጣ ፡ ቢቃሉም ፡ ተና ፵፯
ገረኝ ፡ አለ ።
ለበጎ ፡ ሥራ ፡ የተወለደ ፡ የባለ ፡ አእምሮ ፡ ልጅ ፡ ፵፰

አንተ ፡ ነህ ፡ ረድኤቱም ፡ በንተ ፡ አደረ ፡ ዕለተ ፡
እኁድ ፡ ገንዘቡ ፡ የሆነች ፡ የጌታ ፡ ቸርነቱም ፡
አይለይህም ፡ አለኝ ።
፵፱፤ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ከሱ ፡ ተገ
ኝቷልና ፡ ለዘላለሙ ፡ የሚሆን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡
በስሙ ፡ ይደረግልሃል ፡ አለኝ ።
፶፤ እንደዚሁም ፡ ለዘላለሙ ፡ ሁሉም ፡ ይደረግል
ሃል ፡ ለዘላለሙ ፡ ረድኤቱ ፡ ሳይለይህ ፡ ደጋጎች ፡
ሰዎች ፡ በሥራህ ፡ ፀንተው ፡ ይኖራሉ ።
፶፩፤ ማደሪያቸው ፡ እድል ፡ ፈንታቸውም ፡ ካንተ ፡
ጋር ፡ ይሆናል ፡ ለዘላለሙም ፡ ካንተ ፡ አይለዩም ።
፶፪፤ ከዚያም ፡ ልጅ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ እንዲህ ፡
ብዙ ፡ ዘመን ፡ ይሰጣቸዋል ።
፶፫፤ ለወዳጆቹም ፡ ለጻድቃን ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡
ይደረግላቸዋል ፡ ሕጉም ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡
ስም ፡ ላመኑ ፡ ለሕጋውያን ፡ ለዘላለሙ ፡ የቀና ፡
ነው ፡ አለኝ ፡ አለ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

፩፤ በሰማይ ፡ የሚመላለሱ ፡ የብርሃናት ፡ ነገር ፡
የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ።
፪፤ አንዱም ፡ አንዱም ፡ በየወገናቸው ፡ እንዳሉ ፡
አንዱም ፡ አንዱ ፡ በየዘመናቸውና ፡ በየሥልጣ
ናቸው ፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ በየመውጫቸ
ውና ፡ በየስማቸው ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ መሪያቸው ፡
የሚሆን ፡ የከበረ ፡ መልአኩ ፡ ዑርኤል ፡ ባሳ
የኝ ፡ በየወራታቸውም ፡ ጸንተው ፡ እንዲኖሩ ፡
የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ።
፫፤ ሰሌዳቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ይህም ፡ ዓለም ፡ እስከ ፡
ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖርበት ፡ ዘመን
ንም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ ጸንቶ ፡ የሚ
ኖር ፡ ሐዲስ ፡ ሥራ ፡ እስኪሠራም ፡ ድረስ ፡ እሱ ፡
እንዳሳየኝ ፡ የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ።
፬፤ የብርሃኖችን ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ መጀመሪያው ፡
ሥራት ፡ ይህ ፡ ነው ።
፭፤ የበራ ፡ የፀሐይ ፡ መውጫ ፡ በምሥራቅ ፡ ባሉ ፡
በሰማይ ፡ መስኮቶች ፡ ነው ፡ መግቢያውም ፡
በምዕራብ ፡ ባሉ ፡ በሰማይ ፡ መስኮቶች ፡ ነው ።
፮፤ ፀሐይ ፡ የሚወጣባቸው ፡ ስድስት ፡ መስኮቶ
ችን ፡ አየሁ ፡ ፀሐይም ፡ የሚገባባቸው ፡ በታ
ዎች ፡ ስድስት ፡ መስኮቶችንም ፡ አየሁ ።
፯፤ ጨረቃም ፡ በነዚያ ፡ መስኮቶች ፡ ይወጣል ፡
ይገባል ።
፰፤ ከሰማይ ፡ ከክቦችን ፡ የሚመሩ ፡ ከክቦችም ፡ ከሚ
መሯቸው ፡ ከክቦች ፡ ጋራ ፡ በነዚያ ፡ ደጃፎች ፡
ይወጣሉ ፡ ይገባሉ ፡ እኒህም ፡ መስኮቶች ፡ ስድ
ስቱ ፡ በምሥራቅ ፡ ስድስቱ ፡ ፀሐይ ፡ በሚገባ
በት ፡ በምዕራብ ፡ ናቸው ።
፱፤ አንዱም ፡ አንዱን ፡ ካየሁት ፡ በኋላ ፡ ያየሁት ፡
አንዱም ፡ አንዱም ፡ የቀና ፡ ነው ፡ በዚያም ፡
መስኮት ፡ በግራ ፡ በቀኝ ፡ ብዙ ፡ መስኮቶች ፡
አሉ ። ( ሚያዝያ ፡ ነው ፡ )
፲፤ መጀመሪያ ፡ ስሙ ፡ ፀሐይ ፡ የሚባል ፡ ታላቁ ፡
ብርሃን ፡ ይወጣል ፡ ዙሪያውም ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡
ዙሪያ ፡ ነው ፡ ሁለመናው ፡ የሚያቃጥልና ፡ የሚ
ያበራ ፡ እሳትን ፡ የተመላ ፡ ነው ።
ወደሚሄድባቸውም ፡ ሠረገላዎች ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ፲፩፤
ሠረገላዎችን ፡ የሚነዳ ፡ ነፋስ ፡ ይነፍሳል ።
ፀሐይም ፡ ከምሥራቅ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ይገባል ፡ ፲፪፤
ወደ ፡ ምሥራቅም ፡ ለመሄድ ፡ ከምዕራብ ፡ ወደ ፡
መስዕ ፡ ይመለሳል ፡ ወደዚህም ፡ መስኮት ፡ ሊገባ ፡
ይመራል ፡ በሰማይም ፡ ሁኖ ፡ ያበራል ።
አሁን ፡ እንደ ፡ ተናገርሁት ፡ በመጀመሪያው ፡ ፲፫፤
ወር ፡ በታላቁ ፡ መስኮት ፡ ይወጣል ፡ በአራተኛ
ይቱም ፡ ደጃፍ ፡ ይወጣል ፡ ይችውም ፡ አራተኛ
ይቱ ፡ ደጃፍ ፡ ፀሐይ ፡ በምሥራቅ ፡ ከሚወጣባ
ቸው ፡ ስለዚህ ፡ ከስድስቱ ፡ ደጃፎች ፡ አንዲቱ ፡
ናት ።
በመጀመሪያው ፡ ወር ፡ ፀሐይ ፡ ከሷ ፡ ከሚወጣ ፲፬፤
ባት ፡ በዚያችም ፡ በአራተኛይቱ ፡ ደጃፍ ፡ በዘ
መናቸው ፡ በሚከፈቱበት ፡ ጊዜ ፡ ከነሱ ፡ዋዕይ ፡
የሚወጣባቸው ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ደጃፎች ፡
አሉባት ።
ፀሐይ ፡ ከምሥራቅ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ በዚች ፡ በአ ፲፭፤
ራተኛይቱ ፡ ደጃፍ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ይወጣል ።
በሰማይ ፡ ካለው ፡ መግቢያ ፡ በአራተኛይቱ ፡ ፲፮፤
ደጃፍ ፡ አቅንቶ ፡ ይወርዳል ።
በነዚያም ፡ ወራት ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ፲፯፤
ቀኒቱ ፡ ከቀን ፡ ትረዝማለች ፡ ሌሊቱም ፡ ከሌ
ሊት ፡ ታጥራለች ።
በዚችም ፡ ቀን ፡ ቀኒቱ ፡ ከሌሊቱ ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ ፲፰፤
ትበልጣለች ።
ጠንቅቀው ፡ ቢቈጥሯት ፡ ቀኒቱ ፡ አሥር ፡ ክፍል ፡ ፲፱፤
ትሆናለች ፡ ሌሊቱም ፡ ስምንት ፡ ክፍል ፡ ትሆ
ናለች ።
ፀሐይም ፡ ከዚች ፡ ከአራተኛይቱ ፡ ደጃፍ ፡ ይወ ፳፤
ጣል ፡ በአራተኛይቱም ፡ ደጃፍ ፡ ይገባል ።
ሠላሳ ፡ ቀን ፡ በምሥራቅ ፡ ወዳለችው ፡ ወዳም ፳፩፤
ስተኛይቱ ፡ ይመለሳል ፡ ከሷም ፡ ወጥቶ ፡ ባምስ
ተኛይቱ ፡ ደጃፍ ፡ ይገባል ።
ያን ፡ ጊዜም ፡ ቀኒቱ ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ ትበልጣ ፳፪፤
ለች ፡ ቀኒቱም ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ክፍልን ፡ ትሆ
ናለች ፡ ሌቲቱም ፡ ታጥራለች ፡ ሰባት ፡ ክፍል
ንም ፡ ትሆናለች ።
ፀሐይም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመለሳል ፡ ወደ ፡ ፳፫፤
ስድስተኛይቱም ፡ ደጃፍ ፡ ይገባል ፡ የጳጉሜ ፡
ቀን ፡ ከሷ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ኖረች ፡ በስድስተኛይቱ ፡
ደጃፍ ፡ ሠላሳ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ይወጣል ፡ ይገባል ።
በዚያችም ፡ ቀን ፡ ቀኒቱ ፡ ከሌሊቱ ፡ ትረዝማ ፳፬፤
ለች ፡ ቀኒቱም ፡ የሌሊቱ ፡ እጥፍ ፡ ትሆናለች ፡
ቀኒቱም ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ክፍልን ፡ ትሆናለች ።
ሌቲቱም ፡ አጥራ ፡ ስድስት ፡ ክፍልን ፡ ትሆና
ለች ። ( ሰኔ ፡ )
ቀኒቱ ፡ ታጥር ፡ ዘንድ ፡ ሌቲቱም ፡ ትረዝም ፡ ፳፭፤
ዘንድ ፡ ፀሐይ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዳርቻም ፡ ይመ
ለሳል ።
ፀሐይም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ፳፮፤
ስድስተኛው ፡ መስኮት ፡ ይገባል ፡ ከሷ ፡ ይወ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



ጣል ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ በምዕራብ ፡ ይገባል ።
፳፯ ሠላሳውም ፡ ቀን ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ጠንቅቆ ፡
ቢቈጥሩ ፡ ቀኒቱ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ትጐድላለች ፡
ቀኒቱ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ትሆናለች ፡
ሌሊቱም ፡ ሰባት ፡ ክፍል ።
፳፰ ፀሐይም ፡ ከስድስተኛይቱ ፡ መስኮት ፡ ከምዕራብ ፡
ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይሄዳል ፡ ሠላሳም ፡
ቀን ፡ በምስተኛይቱ ፡ መስኮት ፡ ይወጣል ፡ በሚ
ገባበት ፡ በምስተኛይቱ ፡ መስኮት ፡ ዳግመኛ ፡
በመግቢያው ፡ ይገባል ።
፳፱ በዚያችም ፡ ቀን ፡ ቀኒቱ ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ታን
ሳለች ፡ ቀኒቱም ፡ አሥር ፡ ክፍል ፡ ትሆናለች ፡
ሌሊቱም ፡ ስምንት ፡ ክፍል ፡ ትሆናለች ።
፴ ፀሐይም ፡ ከዚያች ፡ ካምስተኛይቱ ፡ መስኮት ፡
ይወጣል ፡ በሚገባበት ፡ በምስተኛይቱ ፡ መስ
ኮት ፡ ይገባል ።
፴፩ የጳጉሜ ፡ ቀኗ ፡ ገብታ ፡ ስለ ፡ ተቈጠረች ፡ ባራ
ተኛይቱ ፡ መስኮት ፡ ሠላሳ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ይወ
ጣል ፡ በመግቢያዋም ፡ ይገባል ።
፴፪ በዚያችም ፡ ቀን ፡ ቀኑ ፡ ከሌሊቱ ፡ ጋራ ፡ ይተካ
ከላል ፡ የተካከለም ፡ ይሆናል ፡ ሌሊቱ ፡ ዘጠኝ ፡
ክፍል ፡ ትሆናለች ።
፴፫ ፀሐይም ፡ ከዚያች ፡ ከራተኛይቱ ፡ መስኮት ፡
ይወጣል ፡ በመግቢያውም ፡ ገብቶ ፡ ወደ ፡ ምሥ
ራቅ ፡ ይመለሳል ።
፴፬ በሦስተኛውም ፡ መስኮት ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ይወ
ጣል ፡ በሦስተኛውም ፡ መስኮት ፡ በምዕራብ ፡
ይገባል ።
፴፭ በዚችም ፡ ቀን ፡ አንዲቱ ፡ ሌሊት ፡ ካንዲቱ ፡
ሌሊት ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ትበልጣለች ፡ አን
ዲቱም ፡ ቀን ፡ ካንዲቱ ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡
ቀን ፡ ታጥራለች ፡ ጠንቅቆ ፡ ቢቈጥሩት ፡ ሌሊ
ቱም ፡ አሥር ፡ ክፍል ፡ ይሆናል ፡ ቀኑም ፡ ስም
ንት ፡ ክፍል ፡ ይሆናል ።
፴፮ ፀሐይም ፡ ከዚያች ፡ ከሦስተኛይቱ ፡ መስኮት ፡
ወጥቶ ፡ በምዕራብ ፡ ባለ ፡ በሦስተኛይቱ ፡ መስ
ኮት ፡ ይገባል ፡ ወደ ፡ ምሥራቅም ፡ ይመለሳል ።
፴፯ ፀሐይም ፡ በሁለተኛው ፡ መስኮት ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡
ከምሥራቅ ፡ ይወጣል ።
፴፰ እንደዚህም ፡ በሁለተኛው ፡ መስኮት ፡ በሰማይ ፡
ባለ ፡ መግቢያው ፡ ይገባል ፡ በዚያችም ፡ ቀን ፡
ሌሊቲቱ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ክፍልን ፡ ቀኒቱም ፡
ሰባት ፡ ክፍልን ፡ ትሆናለች ።
፴፱ ፀሐይም ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ከዚች ፡ ከሁለተኛይቱ ፡
መስኮት ፡ ወጥቶ ፡ በሁለተኛይቱ ፡ መስኮት ፡
መግቢያ ፡ ይገባል ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመለሳል ።
፵ የጳጉሜ ፡ ቀኗ ፡ ገብታ ፡ ስለ ፡ ተቈጠረች ፡ ፀሐ
ይም ፡ በንዲቱ ፡ በዚች ፡ (ጥር ፡) ሠላሳ ፡ አንድ ፡
ቀን ፡ ወጥቶ ፡ በዚች ፡ በንዲቱ ፡ መስኮት ፡ መግ
ቢያ ፡ ይገባል ።
፵፩ በዚያችም ፡ ቀን ፡ ሌሊቲቱ ፡ ከቀኒቱ ፡ ትረዝማ
ለች ፡ ቀኒቱም ፡ ሁለት ፡ እጥፍን ፡ ትሆናለች ፡
ጠንቅቀው ፡ ቢቈጥሩ ፡ ሌሊቲቱ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡
ክፍል ፡ ቀኒቱም ፡ ስድስት ፡ ክፍልን ፡ ትሆና
ለች ።
ፀሐይም ፡ መስኮቶችን ፡ ጨረሰ ፡ ዳግመኛም ፡ ፵፪
በኒህ ፡ መስኮቶች ፡ ላይ ፡ ዙሮ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡
በዚያ ፡ መስኮት ፡ ይገባል ፡ በመግቢያውም ፡
በትክክል ፡ ይገባል ።
በዚያችም ፡ ቀን ፡ ሌሊቲቱ ፡ ከርዝመቷ ፡ አንድ ፡ ፵፫
እጅ ፡ ታጥራለች ፡ ይኸውም ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡
ነው ፡ ሌሊቲቱ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ቀኒ
ቱም ፡ ሰባት ፡ ክፍል ፡ ትሆናለች ።
ፀሐይም ፡ ተመልሶ ፡ በምሥራቅ ፡ ወደሚወጣ ፵፬
በት ፡ ወደ ፡ ሁለተኛው ፡ መስኮት ፡ ገባ ፡ በዚ
ህም ፡ መስኮት ፡ ተመልሶ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ይወ
ጣል ፡ ይገባል ።
በዚያችም ፡ ቀን ፡ ሌሊቲቱ ፡ ከርዝመቷ ፡ ታጥ ፵፭
ራለች ፡ ሌሊቲቱ ፡ አሥር ፡ ክፍል ፡ ቀኒቱም ፡
ስምንት ፡ ክፍል ፡ ትሆናለች ።
በዚያችም ፡ ቀን ፡ ፀሐይ ፡ ከዚያች ፡ ከሁለተኛ ፵፮
ይቱ ፡ መስኮት ፡ ይወጣል ፡ በመግቢያውም ፡
ገብቶ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመለሳል ።
ፀሐይም ፡ የጳጉሜ ፡ ቀን ፡ ገብታ ፡ ስለ ፡ ተቈጠ ፵፯
ረች ፡ በሦስተኛይቱ ፡ መስኮት ፡ ሠላሳ ፡ አንድ ፡
ቀን ፡ ወጥቶ ፡ በሰማይ ፡ ባለ ፡ መግቢያው ፡ ይገባል ።
በዚያችም ፡ ቀን ፡ ሌሊቲቱም ፡ ታንሳለች ፡ ሌሊ ፵፰
ቲቱም ፡ ዘጠኝ ፡ ቀኒቱም ፡ ዘጠኝ ፡ ክፍል ፡ ትሆ
ናለች ።
ሌሊቱም ፡ ከቀኑ ፡ ጋራ ፡ ይተካከላል ፡ ዓመቱም ፡ ፵፱
ጠንቅቆ ፡ ቢቈጥሩት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስሳ ፡ አራት ፡
ቀን ፡ ይሆናል ።
የሌሊትና ፡ የቀን ፡ ርዝመቷ ፡ የሌሊትና ፡ የቀ ፶
ንም ፡ ማጠሯ ፡ በፀሐይ ፡ መንገድ ፡ ይለያል ።
ስለዚህም ፡ ጎዳናው ፡ ይረዝማል ፡ አንዱ ፡ ቀን ፡ ፶፩
ካንዱ ፡ ቀን ፡ አንዱም ፡ ሌሊት ፡ ካንዱ ፡ ሌሊት ፡
ያጥራል ።
የፀሐይ ፡ ሥራት ፡ መንገዱም ፡ መመለሱም ፡ ፶፪
ይህ ፡ ነው ።
በተመለሰም ፡ ጊዜ ፡ ስሳውን ፡ ከንትሮስ ፡ ሊፈ ፶፫
ጽም ፡ ይመለሳል ፡ ተመልሶም ፡ በምሥራቅ ፡
ይወጣል ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚኖር ፡ ታላቅ ፡ ብር
ሃንም ፡ ይህ ፡ ነው ።
ጌታ ፡ እንዳዘዘ ፡ በሱ ፡ አምሳል ፡ የሚጠራ ፡ ከም ፶፬
ሥራቅ ፡ የሚወጣ ፡ ደገኛ ፡ ብርሃን ፡ ይህ ፡ ነው ።
እንዲህ ፡ ሆኖ ፡ ይወጣል ፡ ይገባል ፡ መጕደልም ፡ ፶፭
የለበት ፡ በሠረገላ ፡ ሆኖ ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊ
ትም ፡ ይሮጣል ፡ እንጂ ፡ አያርፍም ።
ብርሃኑም ፡ ከጨረቃ ፡ ሰባት ፡ እጅ ፡ በልጦ ፡ ያበ ፶፮
ራል ።
የሁለቱ ፡ ሁሉ ፡ የፀሐይና ፡ የጨረቃ ፡ መጠና ፶፯
ቸው ፡ የተካከለ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

የዚህን ፡ የፀሐይ ፡ ሥራት ፡ ካየሁ ፡ በኋላ ፡ ፩
ስሙ ፡ ጨረቃ ፡ የሚባል ፡ የታናሹን ፡ ብርሃን ፡
ሌላ ፡ ሥራት ፡ አየሁ ።
ክብነቱም ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ክብ ፡ ነው ፡ በሚቀ ፪

www.ethiopianorthodox.org

መጥበት ፡ በሠረገላውም ፡ ነፋስ ፡ ይነፍሳል ።
፫ ብርሃንም ፡ በመጠን ፡ ይሰጠዋል ።
፬ በወሩም ፡ ሁሉ ፡ ጨረቃ ፡ መውጫው ፡ መግቢያው ፡ ይለወጣል ፡ ቀኑም ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ቀን ፡ ነው ።
፭ ነገ ፡ ከሚቀበለው ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ጋራ ፡ ዛሬ ፡ የሚቀበለው ፡ ብርሃን ፡ በተካከለ ፡ ጊዜ ፡ ከፀሐይ ፡ ሰባት ፡ እጅ ፡ ብርሃን ፡ ተቀብሎ ፡ የሚያበራ ፡ ይሆናል ።
፮ እንዲህ ፡ ሆኖ ፡ ይወጣል ፡ በሠላሰኛው ፡ ቀን ፡ ማጭድነቱ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ሆኖ ፡ ይወጣል ።
፯ በዚያችም ፡ ቀን ፡ ይታያል ፡ ለናንተም ፡ ወሠርቀ ፡ ወርኅ ፡ ይባላል ።
፰ በሠላሰኛው ፡ ቀን ፡ ሠርቅ ፡ ሊያደርግ ፡ በሀያ ፡ ዘጠኝኛ ፡ ቀን ፡ ፀሐይ ፡ በሚወጣበት ፡ ደጃፍ ፡ ከፀሐይ ፡ ጋራ ፡ ያድራል ።
፱ ሰባት ፡ ሰባት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ የሚሣልበት ፡ እኩሌታው ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ከብርሃን ፡ የራቀ ፡ ነው ፡ ከአሥራ ፡ አራት ፡ እጅ ፡ ብርሃን ፡ ተለይታ ፡ ሰባት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ከተሣለበት ፡ ከሰባተኛይቱ ፡ እጅ ፡ በቀር ፡ ሰሌዳው ፡ ሁሉ ፡ ብርሃን ፡ የሌለበት ፡ ብላሽ ፡ ነው ።
፲ ነገ ፡ በሚቀበለው ፡ መጠን ፡ ዛሬ ፡ ፯ት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ በተቀበለበት ፡ ቀን ፡ ሰባት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ተቀብሎ ፡ የሚበራ ፡ ይሆናል ፡ ሰባት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ከተሣለበት ፡ ከኩሌታው ፡ በቀር ፡ ስድስቱ ፡ እጅ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የሚሆን ፡ ሰባቱም ፡ እጅ ፡ ከብርሃን ፡ የራቀ ፡ ነው ።
፲፩ ነገ ፡ ሠርቅ ፡ ሊያደርግ ፡ ከፀሐይ ፡ ጋራ ፡ ያድራል ፡ ፀሐይም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ጨረቃ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ይወጣል ፡ ነገ ፡ በሚቀበለው ፡ ብርሃን ፡ እኩሌታ ፡ ዛሬም ፡ ይቀበላል ።
፲፪ ጨረቃ ፡ ሠርቅ ፡ ከሚያደርግበት ፡ ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ጨረቃ ፡ ከፀሐይ ፡ ጋራ ፡ ያድራል ።
፲፫ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ ሰባቱ ፡ ስድስቱ ፡ እጅ ፡ እኩሌታይቱ ፡ አሥራ ፡ አራተኛይቱም ፡ እጅ ፡ ጨለማ ፡ ይሆናል ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ ፈጽሞ ፡ ሰባት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ተቀብሎ ፡ ይወጣል ።
፲፬ ወጥቶም ፡ ከፀሐይ ፡ መውጫ ፡ ከምሥራቅ ፡ ይርቃል ፡ በቀረው ፡ ቀን ፡ ሰባት ፡ ሰባት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ እየተቀበለ ፡ ያበራል ።

## ምዕራፍ ፡ ፸፫ ።

፩ በወሮቹ ፡ መንገድ ፡ በሚያደርግበት ፡ በዚያ ፡ ትእዛዝ ፡ ሁለተኛ ፡ መሔጃውን ፡ ሁለተኛ ፡ ትእዛዙን ፡ አየሁለት ።
፪ የከበረ ፡ መልአክ ፡ ዑርኤል ፡ ሁሉን ፡ አሳየኝ ፡ ይኸውም ፡ ሁሉንም ፡ የሚመራቸው ፡ ነው ።
፫ እንዳሳየኝ ፡ በታቸውንም ፡ ጻፍኩ ።
፬ ጽንተው ፡ እንደሚኖሩ ፡ መጠን ፡ ወራታቸውን ፡ ጻፍኩ ፡ የብርሃናቸውን ፡ መልክ ፡ ጻፍኩ ።
፭ አሥራ ፡ አምስቱ ፡ ቀን ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ባንዱ ፡ ቀን ፡ ሰባት ፡ ብርሃን ፡ ባንዱ ፡ ሰባት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ እየተቀበለ ፡ ብርሃኑን ፡ ሁሉ ፡ በምሥራቅ ፡ ፈጽሞ ፡ ያገኛል ፡ ሰባት ፡ ሰባት ፡ እጅ ፡ ክፍለ ፡ ብርሃንም ፡ እየተነሣው ፡ ጨለማውን ፡ ሁሉ ፡ በምዕራብ ፡ ፈጽሞ ፡ ያገኛል ።
፮ በታወቁም ፡ ወራቶች ፡ መግቢያዎቹን ፡ ይለውጣል ፡ በታወቁም ፡ ወራቶች ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ እየተሰጠው ፡ መንገዱን ፡ ይሄዳል ።
፯ በሕፀፁ ፡ በምስትም ፡ ጨረቃ ፡ ከፀሐይ ፡ ጋራ ፡ ይገባል ፡ በመካከል ፡ ባሉ ፡ በነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ መስኮቶች ፡ በራተኛይቱና ፡ በሦስተኛይቱ ፡ መስኮት ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይወጣል ።
፰ ዳግመኛም ፡ ዙሮ ፡ ተመልሶ ፡ ፀሐይ ፡ በሚወጣበት ፡ መስኮት ፡ ይወጣል ፡ በዚያም ፡ መስኮት ፡ ብርሃኑን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ያገኛል ።
፱ ከፀሐይ ፡ ይርቃል ፡ ፀሐይ ፡ ከሷ ፡ በሚወጣበት ፡ በስድስተኛይቱ ፡ መስኮት ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ይገባል ።
፲ ፀሐይም ፡ ከራተኛይቱ ፡ መስኮት ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ካምስተኛይቱ ፡ መስኮት ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ ባራተኛይቱ ፡ መስኮት ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይወጣል ።
፲፩ ዳግመኛም ፡ ተመልሶ ፡ ባራተኛይቱ ፡ መስኮት ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይወጣል ፡ ብርሃኑንም ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ያገኛል ።
፲፪ ይርቃል ፡ በመጀመሪያይቱም ፡ መስኮት ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ይገባል ፡ ዳግመኛም ፡ ተመልሶ ፡ ፀሐይ ፡ ከሷ ፡ በሚወጣበት ፡ ባራተኛይቱ ፡ መስኮት ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይወጣል ።
፲፫ በየወራታቸው ፡ ሥራት ፡ ፀሐይ ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲወጣ ፡ እንዲገባ ፡ አናኗራቸውን ፡ እንደዚህ ፡ አየሁ ፡ አለ ።
፲፬ በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ አምስቱ ፡ ዓመት ፡ ይጨመራል ፡ ለፀሐይም ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ይደርሰዋል ።
፲፭ ላንዱ ፡ ዓመት ፡ ቀኖች ፡ ሁሉ ፡ ይደርሱታል ፡ ከነዚህም ፡ ካምስቱ ፡ ዘመኖች ፡ ተወጣጥተው ፡ ቀኖቹ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስሳ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ይሆናሉ ።
፲፮ ለከከቦችና ፡ ለፀሐይ ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ይደርሳቸዋል ፡ ካምስቱ ፡ ዓመት ፡ ስድስት ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ሆኖ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ይደርሳቸዋል ።
፲፯ ጨረቃም ፡ ከከከቦችና ፡ ከፀሐይ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ይጐላል ።
፲፰ ጨረቃም ፡ ዘመኖችን ፡ ጠንቅቆ ፡ ያስቈጥራቸዋል ።
፲፱ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስሳ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ እየሆነ ፡ ጠንቀቀው ፡ በውነት ፡ ዓመቱን ፡ ይለውጣሉ ፡ እንጂ ፡ ሁሉም ፡ ለዘላለሙ ፡ እንደሚኖሩት ፡ መጠን ፡ አንዲት ፡ ቀን ፡ አያተርፉም ፡ አንዲትም ፡ ቀን ፡ አያጐሉም ፡ አለ ።
፳ የሦስቱ ፡ ዓመት ፡ ቀን ፡ ሺህ ፡ ዘጠና ፡ ሁለት ፡ ነው ፡ የስምንቱ ፡ ዓመት ፡ ቀኑ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ያምስቱ ፡ ዓመት ፡ ቀኑ ፡ ሺህ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ሀያ ፡ ቀን ፡ ነው ።

፴፩፡ ለጨረቃም ፡ ለብቻው ፡ ይደርሰዋል ፡ የሦስቱም ፡ ዓመት ፡ ቀኑ ፡ ሺህ ፡ ስሳ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ነው ።
፴፪፡ በስሳ ፡ ሁለቱ ፡ ቀን ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ በመውጣቱ ፡ ለፀሐይ ፡ ቀን ፡ ይጨመርለታልና ፡ ጨረቃ ፡ ላምስቱ ፡ ዓመት ፡ አምሳ ፡ ቀን ፡ ይጐላል ።
፴፫፡ ለጨረቃ ፡ የስምንቱ ፡ ዓመት ፡ ቀኑ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ያምስቱ ፡ ዓመት ፡ ቀኑ ፡ ሺህ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ቀን ፡ ይሆናል ።
፴፬፡ በስምንቱ ፡ ዓመት ፡ የሚያንሰው ፡ ቀኑ ፡ ሰማንያ ፡ ቀን ፡ ነውና ፡ ከስምንቱም ፡ ዓመት ፡ የጐደለባቸው ፡ ቀኖች ፡ ሰማንያ ፡ ቀን ፡ ናቸው ።
፴፭፡ እነሱ ፡ እንደሚኖሩበት ፡ ፀሐይም ፡ እንደሚኖርበት ፡ መጠን ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡ በውነት ፡ ይጨረሳል ።
፴፮፡ ከከቦች ፡ ከሚወጡባቸው ፡ መስኮቶች ፡ ፀሐይ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ይወጣል ፡ ይገባል ።

## ምዕራፍ ፡ ፸፬ ።

፩፡ በፍጥረቶቹ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በከከቦችም ፡ ሁሉ ፡ የተሾሙ ፡ የሻለቆች ፡ የሚመሯቸው ፡ የወር ፡ መጋቢዎችን ፡ የሚመሩ ፡ የ፲፩ ፡ መጋቢዎች ፡ በዚያ ፡ ይወጣሉ ፡ ይገባሉ ።
፪፡ ከሚጨመሩባቸው ፡ የዘመኑ ፡ ቍጥር ፡ ሁሉ ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ ከመኖሪያቸውም ፡ ከማይለዩ ፡ ከ፬ ፡ ከከቦች ፡ ጋራ ፡ ይወጣሉ ፡ ይገባሉ ።
፫፡ በዘመኑ ፡ ቍጥር ፡ የማይቈጠሩ ፡ እነዚህ ፡ ከከቦች ፡ አራቱን ፡ ጳጉሜን ፡ ይመግባሉ ።
፬፡ እነዚያ ፡ ከከቦች ፡ ዓለሙ ፡ ጸንቶበት ፡ በሚኖረው ፡ ዘመን ፡ በውነት ፡ ይገዛሉና ፡ በነሳቸው ፡ ሰዎች ፡ ይበድሉባቸዋል ።
፭፡ አንዱ ፡ በመጀመሪያው ፡ መስኮት ፡ ( ጥር ፡ ) አንዱ ፡ በሦስተኛው ፡ መስኮት ፡ (መጋቢት ፡) አንዱ ፡ በራተኛው ፡ መስኮት ፡ (ሚያዝያ ፡) አንዱ ፡ በስድስተኛው ፡ መስኮት ፡ (ሰኔ ፡) ይወጣል ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ጸንቶበት ፡ የሚኖርበትን ፡ ቀን ፡ ጠንቅቆ ፡ ቢቈጥሩት ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ጸንቶበት ፡ በሚኖረው ፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ ስሳ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ይጨረሳል ።
፮፡ ባራቱ ፡ ጳጉሜ ፡ ላራቱ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ላመቱም ፡ ለሰባቱም ፡ ቀን ፡ ተሾሟልና ፡ የዘለዓለም ፡ ምስጋና ፡ ያለው ፡ ጌታ ፡ በሰማይ ፡ ብርሃናት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የሾመው ፡ መልአኩ ፡ ዑርኤል ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አሳየኝ ።
፯፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሰማይ ፡ ያበሩ ፡ ዘንድ ፡ ወደዚህም ፡ ዓለም ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ።
፰፡ ጨረቃና ፡ ፀሐይ ፡ ከዋክብትም ፡ በሰማይ ፡ ሠረገላዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚዞሩ ፡ ቅንየታት ፡ የሚባሉ ፡ ከከቦችም ፡ ሁሉ ፡ ለሌሊትና ፡ ለቀንም ፡ መሪዎች ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ በነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሾሞታልና ፡ አሳየኝ ።
፱፡ ዑርኤል ፡ በሰማይ ፡ ያለ ፡ ፀሐይ ፡ በሚመላለስባቸው ፡ በሠረገላዎች ፡ ዙሪያ ፡ የፀሐይ ፡ እግሮች ፡ ከነሱ ፡ የሚወጡባቸው ፡ የተከፈቱ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ መስኮቶችን ፡ እንዲህ ፡ አሳየኝ ።
፲፡ በታወቁባቸው ፡ ዘመኖች ፡ በተከፈቱ ፡ ጊዜ ፡ ከነሳቸው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ድርቅ ፡ ይወጣል ።
፲፩፡ ለነፋሶች ፡ ጠልንም ፡ ለሚያመጣ ፡ ነፋስ ፡ በዘመኖች ፡ በተከፈቱ ፡ ጊዜ ፡ በምድር ፡ ዳርቻ ፡ ሆኜ ፡ ጨረቃና ፡ ፀሐይ ፡ ከከቦችም ፡ የሰማይ ፡ ፍጥረቶችም ፡ ሁሉ ፡ በምዕራብና ፡ በምሥራቅ ፡ ከነሳቸው ፡ የሚወጡባቸው ፡ የተከፈቱ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ መስኮቶችን ፡ በምድር ፡ ዳርቻ ፡ ባለ ፡ በሰማይ ፡ አየሁ ።
፲፪፡ ብዙ ፡ የሆኑ ፡ የተከፈቱ ፡ መስኮቶችም ፡ በግራና ፡ በቀኙ ፡ አሉ ።
፲፫፡ ጌታ ፡ እንዳዘዛቸው ፡ ከከቦቹ ፡ ከነሳቸው ፡ እንደሚወጡባቸው ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸውም ፡ መጠን ፡ እንደሚገቡባቸው ፡ እንደነዚያ ፡ መስኮቶች ፡ አንዲቱ ፡ መስኮት ፡ በዘመኗ ፡ ሙቀትን ፡ ታስገኛለች ።
፲፬፡ የማይገቡ ፡ ከከቦች ፡ በሚመላለሱባቸው ፡ በነዚያ ፡ መስኮቶች ፡ በበታቻቸውና ፡ በበላያቸው ፡ ሠረገላዎችን ፡ ለዘላለሙ ፡ በሰማይ ፡ሲሮጡ ፡ አየሁ ።
፲፭፡ ሁሉንም ፡ አንዱ ፡ ፀሐይ ፡ ይበልጣቸዋል ፡ እሱም ፡ በዓለም ፡ ሁሉ ፡ ይዞራል ።

## ምዕራፍ ፡ ፸፭ ።

፩፡ ለነፋሶች ፡ ሁሉ ፡ መውጫ ፡ መግቢያ ፡ የሚሆኑ ፡ ነፋሶች ፡ ከነሱ ፡ የሚወጡባቸው ፡ የተከፈቱ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ መስኮቶችንም ፡ በምድር ፡ ዳርቻ ፡ አየሁ ።
፪፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ ይነፍሳሉ ፡ ተከፍተው ፡ ካየኋቸው ፡ በነዚያ ፡ መስኮቶች ፡ ሦስቱ ፡ በምሥራቅ ፡ ሦስቱ ፡ በምዕራብ ፡ ሦስቱ ፡ በሰሜን ፡ ሦስቱ ፡ በደቡብ ፡ ናቸው ።
፫፡ መጀመሪያ ፡ ያየኋቸው ፡ ሦስቱ ፡ በምሥራቅ ፡ ሦስቱም ፡ በመስዕ ፡ በኋላ ፡ ያየኋቸው ፡ ሦስቱ ፡ በአዜብ ፡ ሦስቱ ፡ በምዕራብ ፡ ናቸው ።
፬፡ ከነዚያም ፡ መስኮቶች ፡ በራቱ ፡ የፍቅርና ፡ የበረከት ፡ ነፋሶች ፡ ይወጣሉ ፡ ከነዚያም ፡ ከስምንቱ ፡ መስኮቶች ፡ መቅሠፍት ፡ የሚያወጡ ፡ ነፋሶች ፡ ይወጣሉ ።
፭፡ ወደዚህም ፡ ዓለም ፡ በተላኩ ፡ ጊዜ ፡ ምድርን ፡ ሁሉ ፡ ያጠፏታል ፡ በሷ ፡ ላይ ፡ ውኃንም ፡ ያጠፏታል ፡ በሷ ፡ ላይ ፡ የሚኖሩትንም ፡ ሁሉ ፡ በየብስና ፡ በውኃው ፡ ላይ ፡ ያለውንም ፡ ሁሉ ፡ ያጠፏቸዋል ።
፮፡ ለአዜብ ፡ በምትቀርብ ፡ በምሥራቅ ፡ በኵል ፡ ባለች ፡ ስሙ ፡ ስባሕይ ፡ የሚባል ፡ መጀመሪያው ፡ ነፋስ ፡ ይወጣል ፡ ለአዜብ ፡ በምትቀርብ ፡ በምሥራቅ ፡ በኵል ፡ ባለች ፡ በመጀመሪያይቱ ፡ መስኮት ፡ ከሷ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ የሚያጠፋ ፡ ድርቅ ፡ ጥፋትም ፡ ይወጣል ።
፯፡ በመከከል ፡ ባለች ፡ በሁለተኛይቱም ፡ መስኮት ፡ ቅንነት ፡ ይወጣል ፡ ከሷም ፡ በጎ ፡ ዝናብ ፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



በኀ፡ ፍሬ ፡ በኀ፡ ፍቅር ፡ በኀ ፡ ጠል ፡ ይወጣል ።

፰ በመስዕ ፡ በኩል ፡ ባለች ፡ በሦስተኛይቱም ፡ መስኮት ፡ ውርጭ ፡ ድርቅ ፡ በአዜብ ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ እነዚህን ፡ ነፋሶች ፡ ካየሁ ፡ በኋላ ፡ በመጀመሪያ ፡ በየኋቸው ፡ በሦስቱ ፡ መስኮቶች ፡ ነፋሶች ፡ ይወጣሉ ።

፱ እነሱም ፡ ለምሥራቅ ፡ በምትቀርብ ፡ በመጀመሪያይቱ ፡ መስኮት ፡ የድርቅ ፡ ነፋስ ፡ ይወጣል ።

፲ በሷ ፡ አጠገብ ፡ ባለች ፡ በመካከለኛይቱ ፡ መስኮት ፡ ከሷ ፡ በኀ ፡ ሽቱ ፡ በኀ ፡ ጠል ፡ በኀ ፡ ዝናም ፡ ፍቅር ፡ ድኅነት ፡ ይወጣል ።

፲፩ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ባለች ፡ በሦስተኛይቱ ፡ መስኮት ፡ ከሷ ፡ ክፉ ፡ ጠል ፡ ይወጣል ፡ ክፉ ፡ ዝናብ ፡ ኩብኩብ ፡ ጥፋት ፡ ይወጣል ።

፲፪ ስሙ ፡ ባሕር ፡ በሚባል ፡ በመስዕ ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ እኒህን ፡ ነፋሶች ፡ ካየሁ ፡ በኋላ ፡ ካየኋቸው ፡ ከሦስቱ ፡ መስኮቶች ፡ ለአዜብ ፡ በምትቀርብ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ባለች ፡ በሰባተኛይቱ ፡ መስኮት ፡ ከሷ ፡ ክፉ ፡ ጠል ፡ ክፉ ፡ ዝናብ ፡ ኩብኩብና ፡ ጥፋትም ፡ ይወጣል ።

፲፫ በቀኖች ፡ በመካከለኛይቱም ፡ መስኮት ፡ ከሷ ፡ በኀ ፡ ዝናም ፡ በኀ ፡ ጠል ፡ ድኅነት ፡ ፍቅርም ፡ ይወጣል ።

፲፬ ለመስዕ ፡ በምትቀርብ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ባለች ፡ በሦስተኛይቱም ፡ መስኮት ፡ ከሷ ፡ ጉም ፡ ውርጭ ፡ ዋግ ፡ ክፉ ፡ ጠል ፡ ክፉ ፡ ዝናም ፡ ኩብኩብም ፡ ይወጣል ።

፲፭ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ የነዚህን ፡ አራቱን ፡ ነፋሶች ፡ ካየሁ ፡ በኋላ ፡ ለመስዕ ፡ በቀረበች ፡ በመጀመሪያይቱ ፡ መስኮት ፡ ከሷ ፡ ክፉ ፡ ጠል ፡ ክፉ ፡ ዝናም ፡ የረጋው ፡ የተበተነው ፡ ውርጭ ፡ ዋግ ፡ ቀቅ ፡ ይወጣል ።

፲፮ ከመካከለኛይቱም ፡ መስኮት ፡ በኀ ፡ ጠል ፡ በኀ ፡ ዝናም ፡ ፍቅር ፡ በረከትም ፡ ይወጣል ።

፲፯ በአዜብ ፡ በኩል ፡ ባለች ፡ በኋለኛይቱም ፡ መስኮት ፡ ከሷ ፡ ድርቅ ፡ ጥፋት ፡ ዋዕይ ፡ ጥፋት ፡ ይወጣል ።

፲፰ ባራቱ ፡ በሰማይ ፡ ማዕዘን ፡ ያሉ ፡ አሥራ ፡ ሁለቱ ፡ መስኮቶች ፡ ተጨረሱ ፡ ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡ ትእዛዛቸውን ፡ ሁሉ ፡ መቅሠፍታቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ተድላ ፡ ደስታቸውንም ፡ ሁሉ ፡ አሳየሁህ ፡ አለ ።

፲፱ መጀመሪያ ፡ የወጣ ፡ ነውና ፡ መጀመሪያ ፡ የወጣውን ፡ ነፋስ ፡ ስሙን ፡ ጽባሕዊ ፡ ይሉታል ።

፳ ገናና ፡ ፀሐይ ፡ በዚያ ፡ ይወርዳልና ፡ ይልቁንም ፡ ለዘላለሙ ፡ የከበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ ይወርዳልና ፡ ሁለተኛውንም ፡ ነፋስ ፡ ስሙን ፡ አዜብ ፡ ይሉታል ። (ውዐይ ፡)

፳፩ የሰማይ ፡ ብርሃኖች ፡ ሁሉ ፡ በዚያ ፡ ይጎድላሉና ፡ ወደዚያም ፡ ይገባሉና ፡ ከምዕራብ ፡ የሚነፍሰውንም ፡ ነፋስ ፡ ስሙን ፡ የጎደለ ፡ ይሉታል ።

፳፪ ስሙ ፡ መስዕ ፡ የሚባል ፡ አራተኛውም ፡ ነፍስ ፡ ከሦስት ፡ ይከፈላል ፡ ከሦስቱ ፡ አንዱ ፡ ለሰው ፡ ማደሪያ ፡ የሚያፀና ፡ ነው ፡ ሁለተኛውም ፡ በውሀ ፡ ባሉ ፡ ባሕሮች ፡ በጥልቀቶችም ፡ በዛፍም ፡ በወንዞችም ፡ በጨለማም ፡ በጉምም ፡ የተሸመ ፡ ነው ፡ ሦስተኛውም ፡ ክፍል ፡ በቸርነቱ ፡ በምትወረስ ፡ ከገነት ፡ የተሸመ ፡ ነው ።

፳፫ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ካሉ ፡ ተራሮች ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጡ ፡ ሰባት ፡ ተራሮች ፡ ረጃጅሞች ፡ አየሁ ።

፳፬ ከነሱም ፡ ውርጭ ፡ ይወጣል ፡ ቀኑም ፡ ዘመኑም ፡ ዓመቱም ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ያልፋል ፡ ይሄዳል ።

፳፭ ከፈሳሾች ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጡ ፡ ሰባት ፡ ፈሳሾችን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አየሁ ፡ ከነሱ ፡ አንዱ ፡ ከምዕራብ ፡ መጥቶ ፡ ሰፊ ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ውቅያኖስ ፡ ውሀውን ፡ ያፈሳል ።

፳፮ እነዚያ ፡ ሁለቱ ፡ ከመስዕ ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ ውሀቸውን ፡ ከወደምሥራቅ ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ያፈሳሉ ።

፳፯ የቀሩቱም ፡ አራቱ ፡ የነሳቸው ፡ ባሕር ፡ እስከሚሆን ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ደርሰው ፡ በመስዕ ፡ አጠገብ ፡ ይፈሳሉ ።

፳፰ ሁለቱ ፡ ፈሳሾች ፡ ግን ፡ ሰፊ ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ውቅያኖስ ፡ ይመለሳሉ ፡ በዚያም ፡ ጉባዔ ፡ ያደርጋሉ ።

፳፱ በየብስና ፡ በባሕር ፡ ታላላቆች ፡ ሰባት ፡ ደሴቶችን ፡ አየሁ ፡ ከነዚህም ፡ ሁለቱ ፡ በየብስ ፡ አምስቱ ፡ በሰፊ ፡ ባሕር ፡ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፸፪ ።

፩ የፀሐይ ፡ ስም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ አንዱ ፡ አርያሬስ ፡ ይባላል ፡ ሁለተኛውም ፡ ቶማስስ ፡ ይባላል ።

፪ ለጨረቃም ፡ አራት ፡ ስሞች ፡ አሉት ፡ አንዱ ፡ ስሙ ፡ አሰንያ ፡ ይባላል ፡ ሁለተኛውም ፡ ዕብላዕ ፡ ይባላል ፡ ሦስተኛው ፡ ብናሴ ፡ ይባላል ፡ አራተኛው ፡ ኢራዕ ፡ ይባላል ።

፫ ታላላቆች ፡ ብርሃኖች ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ናቸው ፡ ክበባቸውም ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ክበብ ፡ ነው ፡ የሁለቱ ፡ ሁሉ ፡ መጠኖቻቸው ፡ የተካከሉ ፡ ናቸው ።

፬ በፀሐይም ፡ ሰሌዳ ፡ ከጨረቃ ፡ ሰባት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ይጨመርበታል ፡ የፀሐይ ፡ ሰባተኛው ፡ ክፍል ፡ እስቲጨረስ ፡ ድረስ ፡ በልክ ፡ ይቀበላል ።

፭ በምዕራብ ፡ መስኮት ፡ ይገባሉ ፡ ወደ ፡ መስዕ ፡ ይዞራሉ ፡ በሰማይ ፡ ሁነው ፡ እያበሩ ፡ በምሥራቅ ፡ መስኮት ፡ ይወጣሉ ።

፮ ጨረቃም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ በሰማይ ፡ ይታያል ፡ ነገ ፡ በሚቀበለው ፡ ሰባት ፡ በሰባት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ልክ ፡ ዛሬ ፡ ሰባት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ይቀበላል ።

፯ ባሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ ብርሃኑን ፡ ፈጽሞ ፡ ያገኛል ፡ ሦስት ፡ አምስት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃንም ፡ ይጨመርለታል ።

፰ ለዘመን ፡ ምልክት ፡ ሊሆን ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ብርሃኑን ፡ ፈጽሞ ፡ ያገኛል ፡ ሦስት ፡ አምስት ፡ ክፍለ ፡ ብርሃንም ፡ ይሰጠዋል ፡ ጨረቃም ፡ በፀሐይ ፡ ሰባተኛ ፡ ክፍለ ፡ ብርሃን ፡ ያበራል ።

፱፡ ሕፀፅ ፡ በሚያደርግበትም ፡ ጊዜ ፡ በመጀመሪያ
ይቱ ፡ ቀን ፡ አሥራ ፡ አራተኛውን ፡ እጅ ፡ ክፍለ ፡
ብርሃን ፡ ያጣል ፡ በሁለተኛይቱም ፡ ቀን ፡ አሥራ ፡
ሦስተኛይቱን ፡ ያጣል ።
፲፡ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ አሥራ ፡ ሁለተኛውን ፡
ክፍል ፡ ያጣል ፡ በራተኛውም ፡ ቀን ፡ አሥራ ፡
አንደኛውን ፡ ክፍል ፡ ያጣል ።
፲፩፡ በምስተኛውም ፡ ቀን ፡ አሥረኛውን ፡ ክፍል ፡
ያጣል ፡ በስድስተኛውም ፡ ዘጠኝኛውን ፡ ክፍል ፡
ያጣል ።
፲፪፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ስምንተኛውን ፡ ክፍል ፡
ያጣል ፡ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ሰባተኛውን ፡
ክፍል ፡ ያጣል ።
፲፫፡ በዘጠኝኛውም ፡ ቀን ፡ ስድስተኛውን ፡ ክፍል ፡
ያጣል ፡ በሥረኛውም ፡ ቀን ፡ አምስተኛውን ፡
ክፍል ፡ ያጣል ።
፲፬፡ በሥራ ፡ አንደኛውም ፡ ቀን ፡ አራተኛውን ፡
እጅ ፡ ያጣል ፡ በሥራ ፡ ሁለተኛውም ፡ ቀን ፡ ሦስ
ተኛውን ፡ እጅ ፡ ያጣል ።
፲፭፡ በሥራ ፡ ሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ሁለተኛውን ፡
እጅ ፡ ያጣል ፡ በሥራ ፡ አራተኛውም ፡ ቀን ፡
ሰባተኛውን ፡ እጅ ፡ ያጣል ።
፲፮፡ በሥራ ፡ አምስተኛውም ፡ ቀን ፡ ከብርሃን ፡ የቀረ ፡
ብርሃኑ ፡ ሁሉ ፡ ይጨረሳል ።
፲፯፡ በታወቁም ፡ ወራቶች ፡ በሀያ ፡ ዘጠኝ ፡ በሀያ ፡
ዘጠኝ ፡ ቀን ፡ ለጨረቃ ፡ ምላት ፡ ይሆንላታል ፡
በሀያ ፡ ስምንት ፡ በሀያ ፡ ስምንት ፡ ቀንም ፡ ምላት ፡
የሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ።
፲፰፡ ብርሃን ፡ በጨረቃ ፡ በተሣለ ፡ ጊዜ ፡ መልአኩ ፡
ዑርኤልም ፡ ሌላ ፡ ሥራቱን ፡ አሳየኝ ።
፲፱፡ ከፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ከሚጨመርላት ፡ ቀን ፡
ጀምሮ ፡ ጨረቃ ፡ በምትሄድበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡
ብርሃኗን ፡ በፀሐይ ፡ ፊት ፡ ታገኛለች ፡ እስከ ፡
አሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ብርሃኗ ፡ በሰ
ማይ ፡ ይጨረሳል ።
፳፡ ሰሌዳውም ፡ ሁሉ ፡ በተቃጠለ ፡ ጊዜ ፡ ብርሃኗ ፡
በሰማይ ፡ ይፈጸማል ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ በፊ ፡
ብርሃን ፡ ይሳልባታልና ፡ መጀመሪያይቱም ፡
ጨረቃ ፡ የተወለደችበት ፡ ቀን ፡ ትባላለች ፡
፳፩፡ ፀሐይ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ በሚገባበትም ፡ ብር
ሃኑ ፡ ፈጽሞ ፡ ይጨረሳል ፡ በሌሊትም ፡ ከምሥ
ራቅ ፡ ይወጣል ።
፳፪፡ ፀሐይ ፡ በፊቱ ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ ጨረቃ ፡
መላ ፡ ሌሊቱን ፡ ያበራል ፡ ጨረቃ ፡ ከፀሐይ ፡
ጋራ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይተያያል ።
፳፫፡ የጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ ከወጣበት ፡ ጀምሮ ፡ ብርሃኑ ፡
ሁሉ ፡ እስኪጨረስ ፡ ድረስ ፡ ከዚያ ፡ ዳግመኛ ፡
ብርሃኑ ፡ ያንሳል ።
፳፬፡ ጨረቃም ፡ የሚያበራበት ፡ ወራት ፡ ያልፋል ፡
ሰሌዳው ፡ ብርሃን ፡ የሌለው ፡ ብላሽ ፡ ይሆናል ።
፳፭፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ምላት ፡ በሚደረግበት ፡ ዘመን ፡
በሠላሳኛው ፡ ቀን ፡ ሕፀፅ ፡ ያደርጋል ፡ ሦስቱንም ፡
ወር ፡ ሕፀፅ ፡ በሚደረግባቸው ፡ ወራቶች ፡ በሀያ ፡
ዘጠኝኛውም ፡ ቀን ፡ ሕፀፅ ፡ ያደርጋል ።

በመጀመሪያው ፡ ዘመን ፡ በመጀመሪያው ፡ መስ ፳፮፡
ከት ፡ በመቶ ፡ ሰባ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በመወለጃ
ውም ፡ ዘመን ፡ ሦስቱን ፡ ወር ፡ በሠላሳ ፡ በሠላሳ ፡
ቀን ፡ ይታያል ፡ ሦስቱንም ፡ ወር ፡ በሀያ ፡ ዘጠኝ ፡
በሀያ ፡ ዘጠኝ ፡ ቀን ፡ ይታያል ። (ይወለዳል ፡)
ያለ ፡ ፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ብርሃን ፳፯፡
ምንም ፡ ምን ፡ የላትምና ፡ በሀያ ፡ በሀያ ፡ ቀን ፡
ሌሊት ፡ ሰው ፡ መስሎ ፡ ቀን ፡ ሰማይ ፡ መስሎ ፡
ይታያል ።
አሁንም ፡ ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡ ሁሉን ፡ አሳየሁህ ፡ ፳፰፡
በሰማይ ፡ ያሉ ፡ የከከቦችም ፡ ሥራት ፡ ሁሉ ፡
ተጨረሰ ።
በየቀኑ ፡ ሁሉ ፡ በየዘመኑም ፡ ሁሉ ፡ በየሹመታ ፳፱፡
ቸውም ፡ ሁሉ ፡ በያመቱም ፡ ሁሉ ፡ በመግቢያ
ውም ፡ በታዘዘበትም ፡ ሁሉ ፡ በወሩም ፡ ሁሉ ፡
በሱባዔውም ፡ ሁሉ ፡ የሚሆነውን ፡ የነዚህን ፡
ሥራት ፡ አሳየኝ ።
በዚች ፡ በስድስተኛይቱ ፡ መስኮት ፡ ብርሃኑ ፡ ፴፡
ጨርሶ ፡ ይጠፋልና ፡ በስድስተኛይቱ ፡ መስኮት ፡
የሚደረግ ፡ የጨረቃንም ፡ ሕፀፅ ፡ አሳየኝ ፡
አለ ።
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የወር ፡ መባቻ ፡ ይሆናል ፡ ፴፩፡
ሕፀፅ ፡ በሚያደርግበት ፡ ዘመን ፡ በመጀመሪያ
ይቱ ፡ መስኮት ፡ የሚደረገውን ፡ ሕፀፁንም ፡
አሳየኝ ።
መቶ ፡ ሰባ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ እስኪጨረስ ፡ ድረስ ፡ ፴፪፡
በሱባዔው ፡ ቊጥር ፡ ቢቈጠሩት ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡
ሱባዔ ፡ ከሁለት ፡ ቀን ፡ ይሆናል ።
ጨረቃ ፡ በንዱ ፡ ዘመን ፡ ከከከቦች ፡ ሥራትና ፡ ፴፫፡
ከፀሐይ ፡ የሚያንሰው ፡ ጠንቀቆ ፡ ቢቈጥሩት ፡
አምስት ፡ ቀን ፡ ይሆናል ።
የምታየው ፡ ይህም ፡ አንቀጽ ፡ በተጨረሰ ፡ ፴፬፡
ጊዜ ፡ መሪያቸው ፡ የሚሆን ፡ ገናና ፡ መልአክ ፡
ዑርኤል ፡ ካሳየኝ ፡ ከብርሃን ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡
እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ምሳሌ ፡
ታያለህ ።
በዚያም ፡ ወራት ፡ መልአኩ ፡ ዑርኤል ፡ ሄኖክ ፡ ፴፭፡
ሆይ ፡ እነሆ ፡ ሁሉን ፡ አሳየሁህ ፡ ብሎ ፡ መለሰ
ልኝ ።
ይኸንን ፡ ፀሐይ ፡ ይህንን ፡ ጨረቃ ፡ ታየው ፡ ፴፮፡
ዘንድ ፡ በሰማይ ፡ ያሉ ፡ ከከቦችን ፡ የሚመራ
ቸው ፡ ከዋክብትንም ።
ሥራቸውን ፡ ዘመናቸውንም ፡ መውጫቸው ፴፯፡
ንም ፡ የሚለውጡ ፡ ከዋክብትንም ፡ ሁሉ ፡ ታያ
ቸው ፡ ዘንድ ፡ ገለጥሁልህ ።

## ምዕራፍ ፡ ፸፫ ።

በኋላንም ፡ ወራት ፡ ዘመናች ፡ ያጥራሉ ፡ ፩፡
በመዝምሪያቸውና ፡ በርሻቸው ፡ ያለ ፡ ከዝመራ
ቸው ፡ በኋላ ፡ ይደርሳል ።
በምድር ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ይለወጣል ፡ ፪፡
በዘመኑም ፡ አፍርቶ ፡ አይታይም ፡ ዝናምም ፡
ይከለከላል ፡ ሰማይም ፡ ዝናምን ፡ አታዘንምም ።
በነዚያም ፡ ዘመናች ፡ ፊት ፡ የሚደርሰው ፡ የም ፫፡

ድሩ ፡ ፍሬ ፡ በኋላ ፡ የሚደርስ ፡ ይሆናል ፡ በዘ
መኑም ፡ አይበቅልም ፡ የንጨቱም ፡ ፍሬ ፡ ከማ
ፍራት ፡ ይከለከላል ።
፬፡ ጨረቃም ፡ ሥራቱን ፡ ይለውጣል ፡ በዘመኑም ፡
ሲያበራ ፡ አይታይም ።
፭፡ በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ ሰማይ ፡ ጠርቶ ፡ ይታያል ፡
በምዕራብ ፡ በኵል ፡ በታላቅ ፡ ሠረገላ ፡ ዳርቻ ፡
ሁኖ ፡ ድርቅ ፡ ይደርሳል ፡ ሰማይም ፡ ከብርሃን ፡
ሥራት ፡ ይልቅ ፡ ፈጽሞ ፡ ያበራል ።
፮፡ ብዙዎችም ፡ ሰዎች ፡ የታዘዙ ፡ የከዋክብትን ፡
አለቆች ፡ ይስታሉ ፡ እሊህም ፡ ግብራቸውንና ፡
ሥራቸውን ፡ ይለውጣሉ ፡ በታዘዙላቸው ፡ ዘመ
ኖቻቸውም ፡ አይታዩም ።
፯፡ የከከቦችም ፡ ሥራት ፡ ሁሉ ፡ በኃጢአተኞች ፡
ይለወጥባቸዋል ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡
ሰዎች ፡ በነሳቸው ፡ አእምሮዋቸውን ፡ ይለው
ጣሉ ።
፰፡ ሥራቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ይለውጣሉ ፡ ይስታሉ ፡
አምላኮችንም ፡ ያስመስላቸዋል ።
፱፡ መከራ ፡ ይበዛበቸዋል ፡ ሁሉንም ፡ ያጠፋቸው ፡
ዘንድ ፡ መቅሠፍት ፡ ይመጣባቸዋል ፡ ሄኖክ ፡
በሰማይ ፡ ሰሌዳ ፡ የተጻፈውን ፡ መጽሐፍ ፡ እይ ፡
ተመልከት ፡ በነሱ ፡ የተጻፈውንም ፡ አንብበው ፡
አንዱንም ፡ አንዱንም ፡ ሁሉ ፡ መርምረህ ፡ እወቅ ፡
አለኝ ፡ አለ ።
፲፡ በሰማይ ፡ ዳርቻ ፡ የተጻፈውን ፡ አይቼ ፡ የተጻፈ
ውን ፡ ሁሉ ፡ አነበብኩት ፡ ሁሉንም ፡ መርምሬ ፡
አወቅሁ ።
፲፩፡ መጽሐፊቱን ፡ አነበብኋት ፡ በሷም ፡ የተጻፈው
ንም ፡ ሁሉ ፡ አነበብሁ ፡ የሰዎችንም ፡ ሥራ ፡
ሁሉ ፡ ተመለከትሁት ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ዘመን ፡
እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለ ፡ ከሥ
ጋዊ ፡ ከደማዊ ፡ የተወለደውን ፡ ሁሉ ፡ አየሁ ።
፲፪፡ የዓለሙን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አከናውኖ ፡ እንደ ፡
ፈጠረ ፡ መጠን ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ገናና ፡ የሆነ ፡
የዘላለም ፡ ክብር ፡ ያለው ፡ ንጉሥ ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አመሰገንሁት ።
፲፫፡ ስለ ፡ መታገሡም ፡ ጌታን ፡ ፈጽሜ ፡ አመሰገን
ሁት ፡ ይህነንም ፡ ሁሉ ፡ አይቼ ፡ በአዳም ፡ ልጆች ፡
ላይ ፡ አለቀስሁ ።
፲፬፡ ደግ ፡ ቸር ፡ ሆኖ ፡ የሚሞት ፡ ሰው ፡ በደልም ፡
ከሱ ፡ ያልተጻፈበት ፡ ፍርድ ፡ በሚፈረድበትም ፡
ቀን ፡ በሱ ፡ የበደል ፡ ሥራ ፡ ያልተገኘበት ፡
ሰው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ደግ ፡ ነው ።
፲፭፡ የከበሩ ፡ እነዚያም ፡ ሦስቱ ፡ መላእክት ፡ ወደ ፡
ቤቱ ፡ አቀረቡኝ ፡ በቤቱ ፡ ደጃፍ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡
ባለውም ፡ ምድር ፡ አኖሩኝ ።
፲፮፡ ለልጅህ ፡ ለማቱሳላ ፡ ይኽንን ፡ ሁሉ ፡ ንገር ፡ እሱ ፡
በደካማ ፡ በሕርይ ፡ ፈጥሯቸዋልና ፡ በጌታ ፡
ፊት ፡ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዳይከ
ብር ፡ ለልጆችህም ፡ ሁሉ ፡ ይህንን ፡ ገልጠህ ፡
አስተምር ፡ አሉኝ ።
፲፯፡ ልጆችህን ፡ ታስተምራቸው ፡ ዘንድ ፡ ትጽፍላ
ቸውም ፡ ዘንድ ፡ ለልጆችህም ፡ ሁሉ ፡ ታዳኝ
ባቸው ፡ ዘንድ ፡ ዳግመኛም ፡ እስክታገዝላቸው ፡
ድረስ ፡ በልጆችህም ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡
እንተውልሃለን ፡ አሉኝ ።
በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ግን ፡ ከነሱ ፡ መካከል ፡ ፲፰፡
ይወስዱሃል ፡ ደጎች ፡ ሰዎች ፡ ለደጎች ፡ ሰዎች ፡
እውነት ፡ ነገርን ፡ ያስተምራሉና ፡ ለማስተማር ፡
ልቡናህ ፡ ይጽና ።
ደግ ፡ ሰው ፡ ከደግ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ ፲፱፡
እስበሳቸውም ፡ ይዋደዳሉ ፡ ኃጥእም ፡ ሰው ፡
ከኃጥእ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ይሞታል ፡ ወደ ፡ ኃጢአ
ትም ፡ የተመለሰ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ኃጢአት ፡ ከተ
መለሰው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በባሕረ ፡ ገሃነም ፡ ይሰጥ
ማል ።
በጎ ፡ ሥራም ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ የክፉ ፡ ሰዎ ፡ ፳፡
ችን ፡ ሥራ ፡ አንሠራም ፡ ስላሉ ፡ ይሞታሉ ፡ እግ
ዚአብሔርን ፡ የዘነጉ ፡ የክፉ ፡ ሰዎችንም ፡ ሥራ ፡
ስለ ፡ ሠሩ ፡ በሚጠፉበት ፡ በታ ፡ ይሰበሰባሉ ።
በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ መላእክት ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ፳፩፡
ተነጋግረው ፡ ጨረሱ ፡ አራቱን ፡ ማዕዘነ ፡ ዓለም ፡
የፈጠረ ፡ ጌታን ፡ እያመሰገንሁት ፡ ወደ ፡ ዘመ
ዶቼ ፡ ገባሁ ፡ አለ ።

## ምዕራፍ ፡ ፹፪ ።

አሁንም ፡ ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ ፩፡
ላንተ ፡ እነግራለሁ ፡ ላንተም ፡ እጽፍልሃለሁ ፡
ሁሉንም ፡ ገለጥሁልህ ፡ አለው ።
የነዚህንም ፡ ሁሉ ፡ መጣፎቻቸውን ፡ ሰጠሁህ ፡ ፪፡
(አስተማርኩህ ፡) ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡ በኔ ፡ ባባትህ ፡
እጅ ፡ የተጻፈውን ፡ መጻፍ ፡ ተመልከት ፡ ለልጅ ፡
ልጅ ፡ ዘመን ፡ አስተምር ።
ላንተ ፡ ጥበብን ፡ አስተማርኩህ ፡ ካንተም ፡ በኋላ ፡ ፫፡
ለልጆችህ ፡ አስተማርኩ ፡ በልቡናቸው ፡ ጸንታ ፡
ልትኖር ፡ ይችንም ፡ ጥበብ ፡ ለዘላለሙ ፡ እስከ ፡
ልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ለልጆቻቸው ፡
ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ ላንተ ፡ ልጆች ፡ ለሚሆኑ
ህም ፡ ሰዎች ፡ አስተማርሁ ።
ይችን ፡ ጥበብ ፡ ይማሯት ፡ ዘንድ ፡ የሚያው ፡ ፬፡
ቋት ፡ በጆሯቸውም ፡ የሚሰሟት ፡ ሰዎች ፡ በኃ
ጢአት ፡ አይያዙም ፡ ካማሩ ፡ ከተወደዱ ፡ ምግ
ቦች ፡ ይልቅ ፡ ለሚማሯት ፡ ሰዎች ፡ ትስማማቸ
ዋለች ።
ጻድቃንም ፡ ሁሉ ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ፡ ፭፡
በእውነት ፡ ሥራ ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡
ባለ ፡ ዘመናቸውም ፡ ሁሉ ፡ ቍጥር ፡ እንደ ፡
ኃጥአን ፡ ኃጢአት ፡ የሌለባቸውም ፡ ሰዎች ፡
ሁሉ ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።
በሰማይ ፡ በሚሔድ ፡ ፀሐይ ፡ በመስኮቱ ፡ ከሺ ፡ ፮፡
አለቆች ፡ ጋራ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ይገባል ፡ ይወጣል ።
ከሚጨመሩላቸው ፡ አራቱን ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ፯፡
ከሚለዩ ፡ ከሚመሯቸው ፡ ካራቱ ፡ ከዋክብት ፡
ጋራ ፡ የከዋክብት ፡ ሥራታቸው ፡ ይህ ፡ ነው ።
ከነሱም ፡ ጋራ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ይገባሉ ፡ እነሱን ፡ ፰፡
ሰዎች ፡ ይስቷቸዋል ፡ ይስቷቸዋልና ፡ በዓለሙ ፡
ሁሉ ፡ በቍጥር ፡ አይቈጥሯቸውም ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



፱ በዘመኑ ፡ ቍጥር ፡ አሉና ፡ ምንም ፡ ቢኖሩ ፡ እነሱ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ በውነት ፡ የተጻፉ ፡ ናቸውና ፡ ምንም ፡ በጻፉ ፡ ሰዎች ፡ ጠንቅቀው ፡ አያውቋቸውም ።

፲ አንዱ ፡ በመጀመሪያይቱ ፡ መስከት ፡ ይገባል ፡ አንዱ ፡ በሦስተኛይቱ ፡ መስከት ፡ አንዱ ፡ በራተኛይቱ ፡ መስከት ፡ አንዱ ፡ በስድስተኛው ፡ መስከት ፡ ይገባል ።

፲፩ ዓመቱም ፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ ስልሳ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ይፈጸማል ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ የተጻፈውም ፡ ቍጥሩ ፡ የተጠነቀቀ ፡ ነው ።

፲፪ ለብርሃኖች ፡ ለወሮችም ፡ ላራቱም ፡ ክፍለ ፡ ዘመኖች ፡ ለሦስት ፡ መቶ ፡ ስሳ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ለሰበቱም ፡ ቀን ፡ የተሾመ ፡ ነውና ፡ ይኽን ፡ ሁሉ ፡ አሳየኝ ።

፲፫ የፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ገዥ ፡ ጌታ ፡ በሰማይ ፡ ሠራዊት ፡ የሾመው ፡ መልአኩ ፡ ዑርኤልም ፡ በኔ ፡ እውቀትን ፡ አሳደረብኝ ።

፲፬ በሰዎች ፡ ላይ ፡ በሰማይ ፡ የፀሐይን ፡ የጨረቃን ፡ የከዋክብትን ፡ በሠረገላ ፡ ሁነው ፡ የሚመላለሱ ፡ የሰማይ ፡ ሠራዊትን ፡ ሁሉ ፡ ብርሃን ፡ ያሳይ ፡ ዘንድ ፡ በመዓልትና ፡ በሌሊት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ መልአኩ ፡ ዑርኤል ፡ አሳየኝ ።

፲፭ በቦታቸው ፡ በዘመኖቻቸውም ፡ በሱባዔያቸውም ፡ በወሮቻቸውም ፡ የሚወጡ ፡ የሚገቡ ፡ የከከቦች ፡ ሥራትም ፡ ይቺ ፡ ናት ።

፲፮ ምግብናቸውን ፡ የሚጠብቁ ፡ ከዋክብትን ፡ የሚመሩ ፡ የከዋክብት ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ በዘመናቸውም ፡ በሥራታቸውም ፡ በየጊዜያታቸውም ፡ በወሮቻቸውም ፡ በሹመታቸው ፡ በመቋሚያቸውም ፡ ሁነው ፡ ይገባሉ ።

፲፯ አራቱን ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የሚለዩ ፡ አራቱ ፡ መሪዎቻቸው ፡ አስቀድመው ፡ ይገባሉ ።

፲፰ ከነሱም ፡ ቀጥሎ ፡ ሠላሳውን ፡ ቀን ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስልሳ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ የሚሆን ፡ ዓመቱንም ፡ የሚለዩ ፡ ሥራታት ፡ የሚባሉ ፡ ከከቦችን ፡ የሚመሩ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ የወር ፡ መጋቦች ፡ ሰባቱን ፡ ዕለታት ፡ አራቱን ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በሚለዩ ፡ በዘጠና ፡ አንድ ፡ መጋቢዎች ፡ ላይ ፡ በሚጨመሩ ፡ አራቱንም ፡ ጳጉሜን ፡ ከሚለዩ ፡ ከሺ ፡ አለቆች ፡ ጋራ ፡ ይገባሉ ።

፲፱ እነዚያም ፡ የሺ ፡ አለቆቹ ፡ በመሪና ፡ በተመሪ ፡ መካከል ፡ ናቸው ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ መቋሚያ ፡ በኋላ ፡ ይጨመራል ፡ መሪዎቻቸውም ፡ ሠላሳውን ፡ ቀን ፡ ይለያሉ ።

፳ የተሠሩ ፡ አራቱን ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የሚለዩ ፡ የነዚህ ፡ የዘጠና ፡ አንድ ፡ መጋቢዎች ፡ ስማቸው ፡
፳፩ ሕልመልመሌክና ፡ ምልክኤል ፡ ናሬልና ፡ ሚልኤል ፡ ናቸው ።

፳፪ የሺ ፡ አለቆችን ፡ የሚመሯቸው ፡ የወር ፡ መጋቦች ፡ ስማቸው ፡ አንድርናኤል ፡ ኢየሱሳኤል ፡ ኢይሉማኤል ፡ ናቸው ።

፳፫ ሥራታት ፡ የሚባሉ ፡ የሻለቆችን ፡ የሚመሩ ፡ የዘጠና ፡ አንድ ፡ መጋቢዎችን ፡ የሚከተሉ ፡ እኒህ ፡ ሦስቱ ፡ ናቸው ።

፳፬ አንዱ ፡ አራቱን ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የሚለዩ ፡ ምቅዋማት ፡ የሚባሉ ፡ የወር ፡ መጋቢዎችን ፡ የሚመሩ ፡ እነዚያን ፡ የዘጠና ፡ አንድ ፡ መጋቢዎች ፡ የሚከተሉ ፡ ሥራታት ፡ የሚባሉ ፡ የሻለቆችን ፡ የሚመሩ ፡ ሦስቱን ፡ የወር ፡ መጋቢዎች ፡ የሚከተል ፡ ነው ።

፳፭ ስሙ ፡ ተመዓኒ ፡ ( ውሁይ ፡ ) ፀሐይንም ፡ የሚባል ፡ ምልክኤል ፡ የሚባል ፡ ከከብ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዘመን ፡ ወጥቶ ፡ ይመግባል ።

፳፮ በሹመቱ ፡ የሚመግባቸው ፡ ቀኖችም ፡ ሁሉ ፡ ዘጠና ፡ አንድ ፡ ቀኖች ፡ ናቸው ።

፳፯ በሱ ፡ ሹመት ፡ ወራት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይታዩ ፡ ዘንድ ፡ ያላቸው ፡ እኒህ ፡ የቀኖቹ ፡ ምልክቶች ፡ ወዝዋዕይ ፡ ኀዘንም ፡ ናቸው ።

፳፰ እንጨቶችም ፡ ሁሉ ፡ ያፈራሉ ፡ በእንጨቶችም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቅጠል ፡ ይወጣል ፡ የስንዴውም ፡ መከር ፡ ጽጌ ፡ ረዳውም ፡ ሌሎች ፡ አበባዎችም ፡ ሁሉ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ያብባሉ ፡ በክረምት ፡ የሚለመልሙ ፡ እንጨቶችም ፡ ይደርቃሉ ።

፳፱ በበታቾቻቸው ፡ ያሉ ፡ የሺ ፡ አለቆችና ፡ የሚመሩ ፡ የነዚህ ፡ የወር ፡ መጋቦች ፡ ስማቸው ፡ ብርክኤል ፡ ዘልብሳኤል ፡ ናቸው ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ የሚጨመር ፡ ስሙ ፡ ሄሉያሲፍ ፡ የሚባል ፡ የሺ ፡ አለቆች ፡ አለቃ ፡ ሌላ ፡ ከከብ ፡ አለ ።

፴ ይህ ፡ ምልክኤል ፡ የሚመግብበት ፡ ወራት ፡ አለቀ ፡ ከከቦችን ፡ የሚመራ ፡ ሁለተኛው ፡ መጋቢ ፡ ስሙን ፡ የበራ ፡ ፀሐይ ፡ ብለው ፡ የሚጠሩት ፡ ሕልመልመሌክ ፡ ነው ።

፴፩ የሚያበራበትም ፡ ቀን ፡ ሁሉ ፡ ዘጠና ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ የሚመግብባቸው ፡ የነዚህ ፡ ወራቶች ፡ ምልክቶች ፡ ድርቅና ፡ ዋዕይ ፡ ናቸው ።

፴፪ እንጨቶችም ፡ ፈጽሞ ፡ የበሰለ ፡ ፍሬያቸውን ፡ ያወጣሉ ፡ የደረቀ ፡ ፍሬያቸውንም ፡ ያሰጣሉ ፡ በጎችም ፡ ይንጠላጠላሉ ፡ ይፀንሳ ።

፴፫ ሰዎችም ፡ በዱር ፡ ያለ ፡ የንጨቱን ፡ ፍሬ ፡ በርሻውም ፡ ያለ ፡ ፍሬውን ፡ ሁሉ ፡ በወይኑ ፡ አውድማ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ይሰበስባሉ ፡ በተሾመበትም ፡ ወራት ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ይደረጋል ።

፴፬ ስማቸውም ፡ ሥራቶቻቸውም ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፡ በበታቻቸው ፡ ያሉ ፡ የለት ፡ መጋቢዎችን ፡ የሚመሩ ፡ የሻለቆች ፡ ስማቸው ፡ ጊዳኤል ፡ ኪኤልም ፡ ሂኤል ፡ ናቸው ፡ ከነሳቸው ፡ ጋራ ፡ የሚጨመር ፡ የሺ ፡ አለቆች ፡ አለቃ ፡ ስሙ ፡ ለስፋኤል ፡ ነው ፡ የተሾመበትም ፡ ወራት ፡ ተፈጸመ ።

ምዕራፍ ፡ ፵፱ ።

፩ ዛሬም ፡ ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡ ያየሁትን ፡ ራዕይ ፡ ሁሉ ፡ ገለጥሁልህ ፡ ይህንንም ፡ በፊትህ ፡ እናገራለሁ ።

፪ ሚስት ፡ ሳላገባ ፡ ሁለት ፡ ራዕዮችን ፡ አየሁ ፡ ከነሱ ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ጋራ ፡ አይመሳሰልም ።

፫፡ መጀመሪያውን ፡ ራዕይ ፡ መጽሐፈ ፡ አበውን ፡
በምማርበት ፡ ጊዜ ፡ አየሁ ፡ ሁለተኛውን ፡ ራዕይ ፡
ግን ፡ እናትህን ፡ ሳላገባ ፡ አየሁ ፡ የጸና ፡ ራዕይን ፡
አየሁ ።
፬፡ ስለነዚህም ፡ ነገሮች ፡ ጌታን ፡ ለመንሁት ፡ በያቴ ፡
በመላልኤልም ፡ ቤት ፡ ተኝቼ ፡ ሳለሁ ፡ በራዕይ ፡
ሰማይ ፡ ሲወድቅ ፡ አየሁ ፡ አውታሩ ፡ ነፋስን ፡
ሲቀማ ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ ሲወድቅ ፡ አየሁ ።
፭፡ ወደ ፡ ምድርም ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ ምድርን ፡ በታ
ላቅ ፡ ጥልቅ ፡ ውሀ ፡ ሰጥማ ፡ አየኋት ።
፮፡ ተራሮች ፡ በተራሮች ፡ ላይ ፡ ሲሰቀሉ ፡ ኮረብታ
ዎችም ፡ በኮረብታዎች ፡ ላይ ፡ ሲሰጥሙ ፡ ረጃ
ጅሞች ፡ እንጨቶችም ፡ ከግንዳቸው ፡ እየተነ
ቀሉ ፡ ሲወድቁ ፡ በጥልቅ ፡ ወንዝም ፡ ሲሰጥሙ ፡
አየኋቸው ፡ አለ ።
፯፡ ከሱም ፡ የተነሣ ፡ ባንደበቴ ፡ ነገር ፡ ተነገረ ፡ ምድ
ርም ፡ ጠፋች ፡ ብዬ ፡ እጮህ ፡ ጀመር ።
፰፡ አያቴ ፡ መላልኤልም ፡ እኔ ፡ በሱ ፡ ዘንድ ፡ ተኝቼ ፡
ሳለሁ ፡ አነሣኝ ፡ ልጄ ፡ እንደዚህ ፡ አድርገህ ፡
ለምን ፡ ትጮሀለህ ፡ እንደዚህስ ፡ አድርገህ ፡
ለምን ፡ ታለቅሳለህ ፡ አለኝ ፡ አለ ።
፱፡ እኔም ፡ ያየሁትን ፡ ራዕይ ፡ ሁሉ ፡ ነገርሁት ።
፲፡ ልጄ ፡ በአእምሮ ፡ የጸና ፡ እንደ ፡ መሆንህ ፡ አየህ ፡
በምድር ፡ የተሠወረውን ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ በሕ
ልም ፡ ማየትህ ፡ በረታ ፡ ምድርም ፡ በጥልቅ ፡
ውሀ ፡ ትሰጥም ፡ ዘንድ ፡ አላት ፡ ጽኑ ፡ ጥፋትንም ፡
ትጠፋለች ፡ አለኝ ።
፲፩፡ አሁንም ፡ ልጄ ፡ አንተ ፡ የታመንህ ፡ ነህና ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ እንዲቀር ፡ የክብር ፡ ባለ
ቤት ፡ ጌታን ፡ ለምነው ።
፲፪፡ ምድርን ፡ ሁሉ ፡ ያጠፋታል ፡ ልጄ ፡ ከሰማይም ፡
ወርዶ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይኖራል ፡
በዚህም ፡ ዓለም ፡ ጽኑ ፡ ጥፋት ፡ ያደርጋል ።
፲፫፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ተነሥቼ ፡ ፈጽሜ ፡ ለመንኩ ፡
ልመናዬንም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ ሊሆን ፡
ጻፍኩት ፡ አለ ።
፲፬፡ ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡ ሁሉን ፡ አሳየሁህ ፡ አንገቴን ፡
ደፍቼ ፡ በወጣሁ ፡ ጊዜ ፡ ሰማይን ፡ አየሁት ፡ ፀሐ
ይንም ፡ ከምሥራቅ ፡ ሲወጣ ፡ አየሁት ።
፲፭፡ ጨረቃም ፡ በምዕራብ ፡ ሲገባ ፡ አየሁ ፡ ጥቂቶች ፡
ከዋክብቶችም ፡ ነበሩ ፡ ቀድሞ ፡ በመፍጠር ፡
ያወቀውን ፡ ሁሉ ፡ አይቼ ፡ የፍርድ ፡ ባለቤት ፡
እግዚአብሔርን ፡ አመሰገንሁት ።
፲፮፡ ፀሐይን ፡ ከምሥራቅ ፡ መስኮት ፡ አውጥቷልና ፡
ምስጋናን ፡ አቀረብሁለት ፡ ፀሐይም ፡ ወጥቶ ፡
በሰማይ ፡ ላይ ፡ አበራ ፡ ተነሥቶም ፡ እኔ ፡ በየሁ
ለት ፡ ጎዳና ፡ ይሄዳል ።
፲፯፡ በውነትም ፡ ቃሎች ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርጌ ፡ ልዩ ፡
ገናና ፡ የሆነ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገንሁት ።
፲፰፡ ፈጣሪ ፡ ለሰዎች ፡ ልጆች ፡ ሊናገሩበት ፡ አንደ
በትን ፡ ሊያውቁበት ፡ ልቡናን ፡ ፈጥሮ ፡ እንደ ፡
ሰጠ ፡ ለኔም ፡ ልናገርበት ፡ አንደበት ፡ ላውቅ
በት ፡ ልቡናን ፡ ፈጥሮ ፡ ሰጥቶኛልና ፡ በሥጋዊ ፡
በደማዊ ፡ አንደበቴ ፡ ገናንነቱን ፡ ተናገርኩ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ የተመሰገንህ ፡ ነህ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፱፡
ገናና ፡ ኃይለኛ ፡ በገናንነትህም ፡ ኃይለኛ ፡ ነህ ፡
በሰማይ ፡ ያለ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ አንተ ፡
ነህ ፡ ከነገሥታቱ ፡ በላይ ፡ ያለህ ፡ ንጉሥ ፡ አንተ ፡
ነህ ፡ አራቱ ፡ ማዕዝነ ፡ ዓለምንም ፡ የፈጠርህ ፡
አንተ ፡ ነህ ።
አገዛዝህ ፡ መንግሥትህም ፡ ገናንነትህም ፡ ለዘላ ፳፡
ለሙ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ ሥልጣንህም ፡ ለልጅ ፡
ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።
ሰማዎችም ፡ ሁሉ ፡ ለዘላለሙ ፡ መኖሪያህ ፡ ፳፩፡
ናቸው ፡ ምድርም ፡ ሁሉ ፡ ለዘላለሙ ፡ የግሮችህ ፡
መዘርጊያ ፡ ናት ።
አንተ ፡ ሁሉን ፡ ፈጥረሃልና ፡ አንተ ፡ ሁሉን ፡ ፳፪፡
ትገዛለህ ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ ሥራ ፡ አይሳንህም ፡
አንዲትም ፡ ጥበብ ፡ አትሠወርህም ፡ ዙፋንህም ፡
ከናኗሯ ፡ አትለወጥም ፡ አንተም ፡ ከባሕርይህ ፡
አትለወጥም ።
አንተም ፡ ሁሉን ፡ መርምረህ ፡ ፈጽመህ ፡ ታው ፳፫፡
ቃለህ ፡ ሁሉንም ፡ ትሰማለህ ፡ ሁሉን ፡ መርም
ረህ ፡ ታውቃለህና ፡ ካንተ ፡ የሚሠወር ፡ ነገር ፡
የለም ።
አሁንም ፡ በልዑል ፡ ማዕርግ ፡ ያሉ ፡ ደቂቀ ፡ ፳፬፡
ሴት ፡ አንተን ፡ ይበድላሉና ፡ ጽኑ ፡ ፍርድ ፡
እስከሚደረግበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በሥጋዊ ፡
በደማዊ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ቍጣህ ፡ ትታዘዛለች ።
አሁንም ፡ ፈጣሪ ፡ ጌታ ፡ ገናና ፡ ንጉሥ ፡ የምት ፳፭፡
ሆን ፡ አቤቱ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡
ታስቀርልኝ ፡ ዘንድ ፡ ልመናዬን ፡ እንድትሰማኝ ፡
ፈጽሜ ፡ እለምናለሁ ።
አቤቱ ፡ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ አጥፍ ፳፮፡
ተህ ፡ ምድርን ፡ ባዶዋን ፡ አታስቀራት ፡ ለዘላ
ለሙም ፡ ጥፋት ፡ አይሁን ።
አሁንም ፡ ጌታዬ ፡ አንተን ፡ ያሳዘነችህ ፡ ሰውነ ፳፯፡
ትን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አጥፋ ።
እውነትን ፡ የቀና ፡ ሥራንም ፡ የሚሠሩ ፡ የኖ ፳፰፡
ኅን ፡ ወገኖች ፡ ግን ፡ ለዘላለሙ ፡ ሕግ ፡ ሊጠብቁ ፡
አታጥፋ ፡ ከኔ ፡ ከባሪያህም ፡ ልመና ፡ አቤቱ ፡
ፊትህን ፡ አትመልስ ፡ እልኩት ፡ አለ ።

ምዕራፍ ፡ ፴ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ሕልምን ፡ አየሁ ፡ ልጄ ፡ ፩፡
ሁሉንም ፡ አሳየሁህ ።
ሄኖክ ፡ መለሰለት ፡ ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡ ልጄ ፡ ነገሬን ፡ ፪፡
ስማኝ ፡ እልሃለሁ ፡ አለው ።
የኔን ፡ ያባትህን ፡ ሕልም ፡ ለመስማት ፡ ጆሮህን ፡ ፫፡
አቅርብ ፡ እናትህ ፡ አድናንም ፡ ሳላገባት ፡ መጥቼ ፡
ራዕይ ፡ አየሁ ።
እነሆ ፡ አዳም ፡ ከምድር ፡ ተፈጠረ ፡ ያም ፡ ፬፡
አዳም ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ሆነ ፡ ከሱም ፡ በኋላ ፡
አንዲት ፡ ሔዋን ፡ ተፈጠረች ።
ከሷም ፡ ሁለት ፡ ጥጆች ፡ ተወለዱ ፡ ከሁለቱ ፡ ፭፡
አንዱ ፡ ጥቁር ፡ ሆነ ፡ (ቃየል ፡) አንዱም ፡ ቀይ ፡
ሆነ ፡ (አቤል ፡) ይህ ፡ ጥቁሩ ፡ ጥጃ ፡ ይህን ፡ ቀይ ፡
ጥጃ ፡ ወጋው ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ ተከትሎ ፡ ገደ

ለው ።
፮፡ ከዚያም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ቀዩን ፡ ጥጃ ፡ ማየት ፡
አልተቻለኝም ፡ ያም ፡ ጥቁሩ ፡ ጥጃ ፡ አደገ ።
፯፡ ከሱም ፡ ጋር ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ጥጃ ፡ መጣች ።
( ሉድ ፡ ) እሱን ፡ መስለው ፡ ከሱ ፡ የሚወጡ ፡
ብዙ ፡ ላሞችንም ፡ አየሁ ፡ እሱንም ፡ ይከተላሉ ።
፰፡ መጀመሪያ ፡ የወጣችው ፡ ሴቲቱ ፡ ያቺ ፡ ጊደ
ርም ፡ ( ሔዋን ፡ ) መጀመሪያ ፡ ከወጣው ፡ ከዚያ ፡
ላም ፡ ( አዳም ፡ ) ፊት ፡ ወጣች ።
፱፡ ያንንም ፡ ቀይ ፡ ጥጃ ፡ ፈለገችው ፡ አላገኘች
ውም ፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ ታላቅ ፡ ጩኸትን ፡ ጮኸች ፡
ፈለገችው ።
፲፡ ያ ፡ መጀመሪያ ፡ የወጣው ፡ በሬ ፡ ወደሷ ፡ እስቲ
መጣ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ፡ ዝምም ፡ አሰኛት ፡
ከዚያችም ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ አላለቀሰችም ።
፲፩፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ነጭ ፡ ላምን ፡ ወለደች ፡
( ሴት ፡ ) ከሱም ፡ ቀጥሎ ፡ ብዙ ፡ ላሞችን ፡ ጥቋ
ቁሮች ፡ ጊደሮችን ፡ ወለደች ።
፲፪፡ በተኛሁበትም ፡ ይህ ፡ በለአእምሮ ፡ የሆነ ፡ ሴትን ፡
የከበረ ፡ የገነነ ፡ ሁኖ ፡ አየሁት ፡ አሁንም ፡ እንደ
ዚህም ፡ አደገ ፡ በዕውቀትም ፡ የከበረ ፡ የገነነ ፡
ሆነ ፡ ከሱም ፡ ብዙ ፡ ነጫጮች ፡ ላሞች ፡ ተወ
ለዱ ፡ በመልክም ፡ ይመስሉታል ።
፲፫፡ ብዙ ፡ በለአእምሮ ፡ የሆኑ ፡ በመልክም ፡ የሚመ
ስሏቸው ፡ ልጆችን ፡ ይወልዱ ፡ ጀመር ፡ አን
ዱም ፡ አንዱን ፡ በግብር ፡ ተከተለው ።
፲፬፡ ተኝቼ ፡ ዳግመኛም ፡ በይኖቼ ፡ አየሁ ፡ ከም
ድር ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ሰማይንም ፡ አየሁ ።
፲፭፡ እነሆ ፡ ከሰማይ ፡ አንድ ፡ ኮከብ ፡ ወደቀ ፡ ( ስማ
ዝያ ፡ ) ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፡ የሰውንም ፡ ገንዘብ ፡
ሁሉ ፡ ይበላል ፡ በነዚያም ፡ ላሞች ፡ መካከል ፡
( ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ) ይሰመራል ፡ አለ ።
፲፮፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ጥቋቁሮችንና ፡ ታላላቆችን ፡
ላሞች ፡ አየሁ ፡ እነሆ ፡ ሁሉም ፡ ምስጋናቸውን ፡
መሰምሪያቸውንም ፡ ( ግብራቸው ፡ ) ለወጡ ፡
ጥጃም ፡ አስወለዱዋቸው ።
፲፯፡ አንዱ ፡ ከአንዱም ፡ ጋር ፡ ይሬሁ ፡ ጀመር ፡ ዳግ
መኛም ፡ በራዕይ ፡ ሰማይን ፡ አየሁት ።
፲፰፡ ብዙ ፡ ከከቦችንም ፡ እነሆ ፡ አየሁ ፡ ከሰማይም ፡
( ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ) ወደዚያ ፡ ወደ ፡ መጀመሪያው ፡
ኮከብ ፡ ወረዱ ፡ ወደነዚያም ፡ ጥጆች ፡ መካከል ፡
ወደቁ ።
፲፱፡ ላሞችም ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ በመካከላቸው ፡ የሚሠ
ማሩ ፡ ሆኑ ፡ እነሱንም ፡ ፈጽሚ ፡ አየኋቸው ።
፳፡ እነሆ ፡ ሁሉንም ፡ እንደ ፡ ፈረሶች ፡ ኃፍረታቸ
ውን ፡ አውጥተው ፡ በላሞች ፡ ጊደሮች ፡ ላይ ፡
ይንጠላጠሉ ፡ ጀመር ።
፳፩፡ ሁሉም ፡ ጸንሰው ፡ ግመሎችንና ፡ ዝሆኖችን ፡
አህዮችንም ፡ ወለዱ ፡ ላሞችም ፡ ሁሉ ፡ እነሱን ፡
ፈሩዋቸው ፡ ከነሱም ፡ የተነሣ ፡ ደነገጡ ።
፳፪፡ በጥርሳቸውም ፡ እየበታተኑ ፡ ይጥሏቸው ፡ ይው
ጧቸው ፡ ጀመር ፡ በቀንዶቻቸውም ፡ እየወጓ
ቸው ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እነዚያን ፡ ላሞች ፡ ይበ
ሏቸው ፡ ጀመር ። ( እኩሉ ፡ እኩሉን ። )

ከዚህ ፡ ዓለም ፡ የተወለዱ ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ ፳፫፡
እነሆ ፡ ከነሱ ፡ የተነሣ ፡ ይንቀጠቀጡ ፡ ይነቀ
ወጡ ፡ ጀመር ፡ ከነሱም ፡ ይሸሹ ፡ ጀመር ፡ አለ ።

ምዕራፍ ፡ ፹፩ ።

ዳግመኛም ፡ አየኋቸው ፡ አንዱን ፡ አንዱ ፡ ፩፡
ይወጋው ፡ ጀመር ፡ አንዱንም ፡ አንዱ ፡ ይው
ጠው ፡ ጀመር ፡ ያጠፋው ፡ ጀመር ።
ምድርም ፡ ( ትሑታኑ ፡ ) ትጮህ ፡ ጀመር ፡ ዳግ ፪፡
መኛም ፡ ዓይኖቼን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አቅንቼ ፡ በራ
ዕይ ፡ አየሁ ።
የሸበቱ ፡ ሰዎችን ፡ የመሰሉ ፡ መላእክት ፡ እነሆ ፡ ፫፡
ከሰማይ ፡ ወጡ ፡ አንዱ ፡ ከዚያ ፡ በታ ፡ ወጣ ፡
ሦስቱም ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ወጡ ።
ኋላ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ የወጡ ፡ እኒህም ፡ ሦስቱ ፡ እጄን ፡ ፬፡
ያዙኝ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ካሉ ፡ ሰዎች ፡ ለይተው ፡
ወሰዱኝ ።
በረጅምም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ፭፡
ከዚህ ፡ ዓለም ፡ የምትበልጥ ፡ ገነትን ፡ አሳዩኝ ፡
ኮረብታውም ፡ ሁሉ ፡ ከሱ ፡ ያነሰ ፡ ሆነ ።
በነዚያ ፡ ግመሎችና ፡ ዝሆኖች ፡ ላይ ፡ ባህዮ ፮፡
ችም ፡ ላይ ፡ በኮከቦቹም ፡ ላይ ፡ በላሞቹም ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ የሚመጣውን ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ እስ
ክታይ ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ተቀመጥ ፡ አሉኝ ፡
( ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ናቸው ፡ )
ቀድመው ፡ ከወጡ ፡ ከነዚያ ፡ ከራቱ ፡ አንዱን ፡ ፯፡
አየሁት ፡ ( ሩፋኤል ፡ ) ከሰማይ ፡ የወደቀ ፡ ያንን ፡
መጀመሪያውን ፡ ኮከብ ፡ ያዘው ።
እጁን ፡ እግሩን ፡ አሥሮ ፡ በጥልቅ ፡ ጉድጓድ ፡ ፰፡
ጣለው ፡ ያም ፡ ጉድጓድ ፡ ጠበብ ፡ ነው ፡ ጥልቅ ፡
ነው ፡ ጭንቅ ፡ ነው ፡ ጨለማም ፡ ነው ።
ከነዚያም ፡ አንዱ ፡ ( ገብርኤል ፡ ) ሰይፉን ፡ ፱፡
መዞ ፡ ለነዚያ ፡ ዝሆኖች ፡ ለነዚያም ፡ ግመሎ
ችና ፡ አህዮች ፡ ሰጣቸው ።
አንዱ ፡ አንዱን ፡ ይወጋው ፡ ጀመር ፡ ትሑታ ፲፡
ኑም ፡ ሁሉ ፡ በነሱ ፡ ተነዋወጡ ።
በሕልሜም ፡ ባየሁ ፡ ጊዜ ፡ ከነዚያ ፡ ከወጡት ፡ ፲፩፡
ከራቱ ፡ አንዱ ፡ እነሆ ፡ ከሰማይ ፡ መረቡን ፡ ጣለ ።
( ሚካኤል ፡ ነው ፡ )
ኃፍረታቸው ፡ እንዳስሊ ፡ ፈረስ ፡ ኃፍረት ፡ ፲፪፡
የሆነ ፡ ታላላቅ ፡ ከከቦችንም ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡
ያዘ ።
እግራቸውንና ፡ እጃቸውንም ፡ ሁሉ ፡ አሥሮ ፡ ፲፫፡
በምድር ፡ ጉድጓድ ፡ ጣላቸው ።
ከነዚህም ፡ ከራቱ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡ ሱርያል ፡ ፲፬፡
አእምሮ ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ኖኅ ፡ ሄደ ፡ ኖኅም ፡
እየራደ ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ የማየ ፡ አይህን ፡ ምሥ
ጢር ፡ አስተማረ ።
ታደሰ ፡ በለ ፡ አእምሮም ፡ ሆነ ፡ ታላቃ ፡ መርከ ፲፭፡
ብንም ፡ ሠርቶ ፡ በሷ ፡ ተቀመጠ ።
ሦስቱም ፡ ልጆቹ ፡ በዚያች ፡ መርከብ ፡ ከሱ ፡ ፲፮፡
ጋር ፡ ተቀመጡ ፡ በነሱም ፡ ላይ ፡ የሱርያል ፡
ክንፉ ፡ ቀጋረደ ።
ዳግመኛም ፡ ዓይኖቼን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አቅንቼ ፡ ፲፯፡

ከፍ ፡ ያለ ፡ ጠፈርን ፡ አየሁ ፡ በሱም ፡ ሰባት ፡ የውሀ ፡ ሻሻቴዎች ፡ አሉ ፡ እነዚህ ፡ ሻሻቴዎች ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ብዙ ፡ ውሀን ፡ ያፈሳሉ ።
፲፰ ዳግመኛም ፡ አየሁ ፡ እነሆ ፡ ደገኛ ፡ በሚሆን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከምድር ፡ ምንጮች ፡ ተከፈቱ ።
፲፱ ይህም ፡ ውሀ ፡ ከምድር ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ይፈላ ፡ ይነሣም ፡ ጀመር ፡ ምድሩ ፡ ሁሉ ፡ በውሀ ፡ እስኪሸፈን ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ አያሳየውም ፡ ነበር ።
፳ ሁሉም ፡ ላይ ፡ ውሀው ፡ በዛ ፡ ጨለማ ፡ ጉም ፡ ሆነ ፡ የዚህንም ፡ ውሀ ፡ ላውን ፡ አየሁ ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ውሀው ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ።
፳፩ በዚህም ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ውሀውን ፡ አፍሶ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ጸና ።
፳፪ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ እስኪሰጥሙ ፡ ተሰጥመውም ፡ በዚያ ፡ ውሀ ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ።
፳፫ ያም ፡ መርከብ ፡ በውሀው ፡ ላይ ፡ ይዋኝ ፡ ነበር ፡ ገዞሆኖችና ፡ ላሞች ፡ አህዮችና ፡ ግመሎች ፡ ከብቶችም ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ተሰጠሙ ።
፳፬ እኔም ፡ እነሱን ፡ ማየት ፡ አልተቻለኝም ፡ እነሱም ፡ መውጣት ፡ ተሳናቸው ፡ በጥልቅም ፡ ባሕር ፡ ተሰጥመው ፡ ጠፉ ።
፳፭ ዳግመኛም ፡ ከዚህ ፡ ከታላቁ ፡ ጠፈር ፡ እኒህ ፡ ሻሻቴዎች ፡ እስቲጠፉ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ በራዕይ ፡ አየሁ ፡ ከምድርም ፡ የወጣው ፡ ምንጩ ፡ ተደፈነ ።
፳፮ ሌሎች ፡ ጕድጓዶችም ፡ ተከፈቱ ፡ ምድር ፡ እስቲገለጥ ፡ ድረስ ፡ ውሀው ፡ ወደነሱ ፡ ይወርድ ፡ ጀመር ።
፳፯ መርከብም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ። (አራራት ፡) ጨለማይቱ ፡ ራቀች ፡ ብርሃን ፡ ሆነ ።
፳፰ ባለ ፡ አእምሮ ፡ የሆነ ፡ ያም ፡ ኖኅ ፡ ከዚያ ፡ ከመርከቡ ፡ ወጣ ፡ ሦስቱም ፡ ልጆቹ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ወጡ ።
፳፱ ከነሆም ፡ ከሦስቱ ፡ ልጆቹ ፡ ባለአእምሮ ፡ የሆነ ፡ የአንዱ ፡ ሴም ፡ በመልክም ፡ በግብርም ፡ ኖኅን ፡ ይመስለዋል ፡ ከነሳቸው ፡ አንዱ ፡ ያፌትም ፡ እንደ ፡ ደም ፡ ቀይ ፡ ነው ፡ ከሦስቱ ፡ አንዱ ፡ ካም ፡ ግን ፡ ጥቁር ፡ ነው ፡ ባለአእምሮ ፡ የነበረ ፡ ኖኅም ፡ ከነሱ ፡ ተለይቶ ፡ ሞተ ።

ምዕራፍ ፡ ፴፪ ።

፩ የምድረ ፡ በዳ ፡ አውሬዎችን ፡ ወፎችንም ፡ ይወልዱ ፡ ጀመር ፡ ከነሱም ፡ የአሕዛብ ፡ ቅመምነት ፡ ተገኘ ።
፪ አናብስት ፡ የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ አናምርት ፡ የፋርስ ፡ ሰዎች ፡ አዝዕብት ፡ የግብጽ ፡ ሰዎች ፡ አክልብት ፡ የኢሎፍሊ ፡ ሰዎች ፡ አፅዕብት ፡ የሶርያ ፡ ሰዎች ፡ ሐራውያ ፡ የኤዶምያስ ፡ ሰዎች ፡ ቄናጽል ፡ አማሌቃውያን ፡ ሽኮኮዎች ።
፫ አነር ፡ ጥምብ ፡ አሞራ ፡ ያልታወቁ ፡ አሕዛብ ፡ ሞዓብ ፡ አሞን ፡ ተገኙ ፡ ዘማች ፡ አሞራ ፡ አንጭት ፡ አሞራ ፡ ጕሬዛ ፡ ያልታወቁ ፡ አሕዛብ ፡ ተገኙ ፡ (ሮማውያን ፡ ናቸው) ።
በነሱም ፡ መካከል ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ አብርሃም ፡ ፬
ተወለደ ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ጋር ፡ እስበሳቸው ፡ ይጣሉ ፡ ጀመር ።
በመካከላቸውም ፡ የተወለደ ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ፭
የሚሆን ፡ ይህም ፡ አብርሃም ፡ ይስማኤልን ፡ ወለደ ፡ እንደሱም ፡ ያለ ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ይስሐቅን ፡ ወለደ ።
የይስማኤል ፡ ልጆች ፡ በዙ ፡ ከአብርሃምም ፡ የተ ፮
ወለደ ፡ ይስሐቅ ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ያዕቆብንና ፡ አእምሮ ፡ የሌለው ፡ ዔሳውን ፡ ወለደ ።
ያም ፡ ዔሳው ፡ ብዙ ፡ የኤዶምያስን ፡ ሰዎች ፡ ፯
ወለደ ፡ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ያዕቆብ ፡ አሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ነገደ ፡ እስራኤልን ፡ ወለደ ።
እነዚህ ፡ አሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡ እስራኤልም ፡ ፰
ካደጉ ፡ በኋላ ፡ ከነሱ ፡ አንዱ ፡ ዮሴፍን ፡ ለይስማኤላውያን ፡ ሸጡት ።
እነዚህም ፡ ይስማኤላውያን ፡ ዳግመኛ ፡ ዮፍሴን ፡ ፱
ለግብፃውያን ፡ ሸጡት ፡ ያም ፡ ዮሴፍ ፡ ከግብፃውያን ፡ መካከል ፡ አደገ ።
ከሱ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ በግብፃ ፲
ውያንም ፡ መካከል ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ ይሰመሩ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ዮሴፍ ፡ አመጣቸው ።
እነዚህም ፡ የያዕቆብ ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ ብዙ ፡ ፲፩
ሆኑ ፡ ግብፃውያንም ፡ ልጆቻቸውን ፡ እስኪገሉባቸው ፡ ድረስ ፡ ያስፈሯቸው ፡ ያስጨንቋቸው ፡ ጀመር ።
የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ በብዙ ፡ ውሀ ፡ ፈሳሽ ፡ ፲፪
ጣሏቸው ፡ እኒህ ፡ እስራኤልም ፡ በልጆቻቸው ፡ ጥፋት ፡ ይጮሁ ፡ ወደ ፡ ጌታቸውም ፡ ይከሱ ፡ ያጣሉ ፡ ጀመር ።
ከግብፃውያን ፡ የዳነ ፡ ሙሴም ፡ ወደ ፡ ምድያም ፡ ፲፫
ሰዎች ፡ ሸሽቶ ፡ ሄደ ።
ያ ፡ የእስራኤል ፡ ጌታ ፡ የእስራኤልን ፡ ልመና ፡ ፲፬
ሰምቶ ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ከጽርሐ ፡ አርያም ፡ እስቲወርድ ፡ ድረስ ፡ እስራኤል ፡ ፈጽመው ፡ ወደሱ ፡ ሲጮሁ ፡ በፍጹምም ፡ አእምሯቸው ፡ ጌታቸውን ፡ ሲለምኑት ፡ አየኋቸው ።
ወደነሱ ፡ መጥቶ ፡ አያቸው ፡ ከግብፃውያን ፡ ፲፭
ኰብሎ ፡ የሄደ ፡ ያንን ፡ ሙሴን ፡ ጠርቶ ፡ እስራኤልን ፡ እንዳይነኳቸው ፡ ያዳኙባቸው ፡ ዘንድ ፡ የግብፃውያንን ፡ ነገር ፡ ነገረው ።
ያም ፡ ሙሴ ፡ በጌታ ፡ ቃል ፡ ታዞ ፡ ወደ ፡ ግብፃ ፲፮
ውያን ፡ ሄደ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ አሮንም ፡ ያንን ፡ ሙሴን ፡ ተገናኘው ፡ አብሮት ፡ ሄደ ።
ሁለቱም ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ ወደነዚህ ፡ ፲፯
ግብፃውያን ፡ አደባባይ ፡ ገቡ ፡ ተናገሯቸው ።
እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እስራኤልን ፡ እንዳይነኳ ፲፰
ቸው ፡ አዳኙባቸው ።
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ግብፃውያን ፡ በኃይላቸው ፡ ፲፱
ሁሉ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ፈጽመው ፡ እንደ ፡ ጸኑባቸው ፡ አየኋቸው ።
እስራኤልም ፡ ፊጮሁ ፡ ጌታቸውም ፡ ወደ ፡ እስራ ፳

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



ኤል ፡ መጥቶ ፡ እነዚህ ፡ ግብፃውያንን ፡ ያጠፋ
ቸው ፡ ጀመር ።
፳፩፡ ግብፃውያንም ፡ ይጮሁ ፡ ጀመር ፡ እስራኤል ፡
ግን ፡ ዝም ፡ አሉ ፡ ከዚያም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ አል
ጮሁም ፡ ከግብፃውያንም ፡ ተለይተው ፡ እስቲ
ወጡ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ እስራኤልን ፡ አየኋቸው ።
፳፪፡ የግብፃውያንም ፡ ዓይነ ፡ ልቡናቸው ፡ በድንቁ
ርና ፡ ተሸፈነ ፡ እነሆም ፡ ግብፃውያን ፡ ከሠራዊ
ቶቻቸው ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ እስራኤልን ፡ ተከተ
ሏቸው ።
፳፫፡ የእስራኤልም ፡ ጌታ ፡ እየመራቸው ፡ ከነሱ ፡
ጋር ፡ ሄደ ፡ እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ እሱን ፡ ተከተ
ሉት ፡ ፊቱም ፡ የበራ ፡ የከበረ ፡ ነው ፡ መልኩም ፡
የሚያስፈራ ፡ ነው ።
፳፬፡ ግብፃውያን ፡ ግን ፡ በተጠራቀመች ፡ አንዲት ፡
ውኃ ፡ እስኪገናኟቸው ፡ ድረስ ፡ እነሆ ፡ እስራ
ኤልን ፡ ይከተሏቸው ፡ ጀመር ። (ኤርትራ ፡)
፳፭፡ ያም ፡ የተጠራቀመው ፡ ውኃ ፡ ከሦስት ፡ ከራት ፡
ተከፈለ ፡ ውኃውም ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ተከፍሎ ፡
በፊታቸው ፡ ጸና ፡ የእስራኤልም ፡ ጌታ ፡ ይመ
ራቸው ፡ ነበር ፡ በግብፃውያንና ፡ በእስራኤልም ፡
መካከል ፡ ቁሞ ፡ ነበር ።
፳፮፡ እነሆም ፡ ግብፃውያን ፡ እስራኤልን ፡ ገና ፡ አላ
ይዋቸውም ፡ ነበር ፡ በዚህ ፡ በተጠራቀመውም ፡
ውኃ ፡ መካከል ፡ ሄዱ ።
፳፯፡ ግብፃውያንም ፡ እስራኤልን ፡ ተከተሏቸው ፡
እነሆም ፡ ግብፃውያን ፡ በተጠራቀመው ፡ ውኃ ፡
ላይ ፡ እነሱን ፡ ተከትለው ፡ ሮጡ ።
፳፰፡ የእስራኤልንም ፡ ጌታ ፡ በዩት ፡ ጊዜ ፡ ከፊቱ ፡
ይሸሹ ፡ ዘንድ ፡ ተመለሱ ።
፳፱፡ ያም ፡ የተጠራቀመው ፡ ውኃ ፡ ተሰበሰበ ፡ ፈጥ
ኖም ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ፍጥረቱ ፡ ሆነ ፡ እነሆ ፡ ግብ
ፃውያንን ፡ እስኪ ፡ አሰጥማቸው ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፡
መልቶ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ።
፴፡ እስራኤልን ፡ የተከተሏቸው ፡ ግብፃውያን ፡
ሁሉ ፡ እስቲጠፉ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ እስቲሰጥ
ሙም ፡ ድረስ ፡ አየሁ ።
፴፩፡ እስራኤል ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ከውኃው ፡ ወጥተው ፡
ሣርና ፡ ውኃ ፡ ወደሌለበት ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡
ሄዱ ።
፴፪፡ ዓይነ ፡ ልቡናቸውም ፡ ፈጽሞ ፡ ምሥጢርን ፡
ይመረምር ፡ ጀመር ፡ የእስራኤልም ፡ ጌታቸው ፡
ሲጠብቃቸው ፡ እህል ፡ ውኃ ፡ ሲሰጣቸው ፡
አየሁ ።
፴፫፡ ያም ፡ ሙሴ ፡ በፊት ፡ በፊት ፡ እየሄደ ፡ ይመራ
ቸው ፡ ነበር ፡ ያም ፡ ሙሴ ፡ ረጅም ፡ ወደሆነ ፡
ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ራስ ፡ ወጣ ።
፴፬፡ የእስራኤልም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡
ወደነሱ ፡ ላከው ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በፊታቸው ፡
የቆመ ፡ የእስራኤልን ፡ ጌታ ፡ አየሁት ።
፴፭፡ መልኩም ፡ ያማረ ፡ ነው ፡ የሚያስፈራም ፡
ነው ፡ ኃይለኛም ፡ ነው ፡ እነሆም ፡ እስራኤል ፡
ሁሉ ፡ እሱን ፡ አይተው ፡ ፊቱ ፡ ከመገለጡ ፡
የተነሣ ፡ ፈሩ ።

እነዚህም ፡ ሁሉ ፡ ከሱ ፡ የተነሣ ፡ ፈርተው ፡ ፴፮፡
ይርዱ ፡ ይንቀጠቀጡ ፡ ነበር ፡ በመካከላቸው ፡
ከነበረ ፡ ሁለተኛ ፡ ከሆነ ፡ ከአሮን ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡
ያንን ፡ ሙሴን ፡ ተከትለው ፡ ጮሁ ።
በጌታችን ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ ፊትንም ፡ ማየት ፡ ፴፯፡
አይቻለንምና ፡ አይናገረን ፡ አሉ ፡ የሚመራቸ
ውም ፡ ይህ ፡ ሙሴ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡
ሲና ፡ ራስ ፡ ወጣ ።
የእስራኤልም ፡ ዓይነ ፡ ልቡናዎቻቸው ፡ በድን ፴፰፡
ቍርና ፡ ይያዙ ፡ ከአስተማራቸውም ፡ ሕግ ፡ ወጥ
ተው ፡ ይስቱ ፡ ጀመር ።
ይህም ፡ ሙሴ ፡ በደላቸውን ፡ አላወቀም ፡ ነበር ፡ ፴፱፡
የእስራኤል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በነ
ርሱ ፡ ታላቅ ፡ ቍጣን ፡ ተቈጣባቸው ።
ይህም ፡ ሙሴ ፡ በደላቸውን ፡ አውቆ ፡ ከደብረ ፡ ፵፡
ሲና ፡ ራስ ፡ ወረደ ።
ወደ ፡ እስራኤልም ፡ መጣ ፡ ዓይነ ፡ ልቡናዎቻ ፵፩፡
ቸው ፡ በድንቍርና ፡ የተያዙ ፡ ከሕጉም ፡ ወጥ
ተው ፡ የበደሉ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ አገኘ ።
እስራኤልም ፡ ሙሴን ፡ በዩት ፡ ጊዜ ፡ ፈሩ ፡ ከፊቱ ፡ ፵፪፡
መገለጥ ፡ የተነሣ ፡ ተንቀጠቀጡ ፡ ወደ ፡ ሕጋቸ
ውም ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ወደዱ ።
ይህም ፡ ሙሴ ፡ ከነሱ ፡ የተለዩ ፡ ሌዋውያንን ፡ ፵፫፡
ይዞ ፡ ወደ ፡ በደሉ ፡ ወደነዚህ ፡ ወደ ፡ እስራ
ኤል ፡ ገባ ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይገሏቸው ፡ ጀመር ፡ እስራኤ ፵፬፡
ልም ፡ ከፊቱ ፡ መገለጥ ፡ የተነሣ ፡ ፈሩ ፡ ይህም ፡
ሙሴ ፡ የበደሉ ፡ እነሆ ፡ እስራኤልን ፡ ወደ ፡
አምልኮት ፡ መለሳቸው ፡ ወደ ፡ ሕጎቻቸውም ፡
ተመለሱ ።
ያም ፡ ሙሴ ፡ በለ ፡ አእምሮ ፡ እስቲሆን ፡ ድረስ ፡ ፵፭፡
ለእስራኤል ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ማደ
ሪያ ፡ ደብተራ ፡ ኦሪትን ፡ እስኪሠራ ፡ ድረስ ፡ እስ
ራኤልንም ፡ ሁሉ ፡ በዚያ ፡ በደብተራ ፡ ኦሪት ፡
ሥራት ፡ እስኪያቆማቸው ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡
በዚያ ፡ ቦታ ፡ ራዕይ ፡ አየሁ ።
እስራኤልን ፡ የመራቸው ፡ ይኸን ፡ ሙሴን ፡ የተ ፵፮፡
ገናኘው ፡ ያ ፡ አሮን ፡ እስቲሞት ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡
አየሁ ።
ስልሳው ፡ እልፍ ፡ አጋር ፡ ሁሉ ፡ እስቲጠፉ ፡ ፵፯፡
ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ፡ ስለነሳቸውም ፡ ፈንታ ፡
ውሉድ ፡ ተነሡ ፡ ብዙ ፡ ወገን ፡ ወደሚሆንም ፡
ገቡ ።
ወደ ፡ ውሀው ፡ ፈሳሽ ፡ (ዮርዳ ፡) ቀረቡ ፡ የሚ ፵፰፡
መራቸው ፡ በለ ፡ አእምሮ ፡ የሆነው ፡ ይህ ፡
ሙሴ ፡ ከነሱ ፡ ተለይቶ ፡ ሞተ ።
እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ ፈልገው ፡ አጡት ፡ በሱም ፡ ፵፱፡
ሞት ፡ ታላቅ ፡ ጩኸትን ፡ ጮሁ ፡ ለዚህም ፡
ለሙሴ ፡ በሚጮሁት ፡ ጩኸት ፡ ዝም ፡ እስ
ቲሉ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ።
የዚያንም ፡ ውሀ ፡ ፈሳሽነት ፡ አልፈውት ፡ ሄዱ ፡ ፶፡
ስለ ፡ ሞቱት ፡ ሰዎች ፡ ምትክ ፡ እስራኤልን ፡
የሚመሯቸው ፡ ሹማምንት ፡ ሁሉ ፡ ተሾሙ ፡
ተሾመውም ፡ መሯቸው ።

፺፩፡ እስራኤልም ፡ ወዳማረ ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ተወደ
ደች ፡ ወደ ፡ ከበረች ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡
እስኪገቡ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ።
፺፪፡ እነዚህም ፡ እስራኤል ፡ እስቲጠግቡ ፡ ድረስ ፡
ደርሼ ፡ አየሁ ፡ ያም ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ በማ
ረች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በመካከላቸው ፡ ጸንቶ ፡
ይኖር ፡ ነበር ።
፺፫፡ ዓይነ ፡ ልቡናዎቻቸው ፡ የሚገለጡበት ፡ ወራት ፡
አለ ፡ ከአሮን ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ሳሙኤል ፡ ተነሥቶ ፡
እስቲሾምላቸው ፡ ድረስ ፡ በድንቊርና ፡ የተያዙ
በት ፡ ወራት ፡ አለ ።
፺፬፡ ሳሙኤልም ፡ ወደ ፡ አምልኮቱ ፡ መለሳቸው ፡
የልቡናቸውም ፡ ዓይኖች ፡ በሩላቸው ።
፺፭፡ ከሳሙኤል ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ከነሱ ፡ አንዱ ፡ ሳኦል ፡
ተነሥቶ ፡ እስቲነግሥላቸው ፡ ድረስ ፡ እኒህ ፡
እስራኤልን ፡ ኢሎፍላውያን ፡ አማሌቃውያን ፡
የኤዶምያስም ፡ ሰዎች ፡ ያጠፏቸው ፡ ጀመር ።
፺፮፡ ይህም ፡ ሳኦል ፡ ከወዲያና ፡ ከወዲህ ፡ እያለ ፡
ሁሉንም ፡ ጨርሶ ፡ እስቲያጠፋቸው ፡ ድረስ ፡
እነዚህን ፡ ኢሎፍላውያንን ፡ አማሌቃውያን
ንም ፡ የኤዶምያስንም ፡ ሰዎች ፡ ይወጋ ፡ ጀመር ።
፺፯፡ የዚያ ፡ የሳሙኤልም ፡ ዓይነ ፡ ልቡናዎቹ ፡ በሩ
ለት ፡ እስራኤልን ፡ የሚጠብቅ ፡ ጌትነቱን ፡ የተወ ፡
የዚያን ፡ የሳኦልን ፡ ዕዳውን ፡ አወቀበት ።
፺፰፡ እነዚህ ፡ እስራኤልንም ፡ ይጐዳቸው ፡ ይረግጣ
ቸውም ፡ ጀመር ፡ እሱም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ሳያ
ገኝ ፡ ኖረ ።
፺፱፡ የእስራኤል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሳሙኤ
ልን ፡ ከሳኦል ፡ ልዩ ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡
ላከው ፡ ንጉሥ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ጌትነቱን ፡ ስለ ፡
ተወ ፡ ስለ ፡ ሳኦል ፡ ፈንታ ፡ እስራኤልን ፡ ይገዛ
ቸው ፡ ዘንድ ፡ ቀብቶ ፡ አነገሠው ።
፻፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ሄዶ ፡ ለብቻው ፡ ተናገረው ፡ ያንን ፡
ዳዊትንም ፡ ቀብቶ ፡ አነገሠው ፡ ለእስራኤልም ፡
ገዥ ፡ አደረገው ።
፻፩፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ እኒህ ፡ ኢሎፍላውያን ፡ እስራኤ
ልን ፡ እየመጡ ፡ ያስጨንቋቸው ፡ ነበር ።
፻፪፡ መጀመሪያ ፡ የነገሠ ፡ ሳኦልም ፡ በኋላ ፡ የሚነ
ግሥ ፡ ዳዊትን ፡ አስወጥቶ ፡ ሰደደው ፡ በኋላ ፡
የሚነግሥ ፡ ዳዊትም ፡ ከፊቱ ፡ ተነሥቶ ፡ ሸሸ ።
፻፫፡ መጀመሪያ ፡ የነገሠ ፡ ሳኦልን ፡ ኢሎፍላውያን ፡
እስቲያጠፉት ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ።
፻፬፡ ከሱ ፡ በኋላ ፡ የነገሠ ፡ ዳዊትም ፡ ተነሥቶ ፡ በአ
እምሮ ፡ ያነሱ ፡ እስራኤልን ፡ ጠበቃቸው ።
፻፭፡ ከሱም ፡ በኋላ ፡ የነገሠ ፡ ዳዊት ፡ ብዙ ፡ ልጆችን ፡
ወልዶ ፡ ሞተ ።
፻፮፡ ሰሎሞንንም ፡ ስለሱ ፡ ፈንታ ፡ ነገሠ ፡ ለኒህም ፡
ለእስራኤል ፡ ፍጹም ፡ ገዥ ፡ ሆነ ፡ በሱም ፡ ዘመን ፡
እስራኤል ፡ በውቀት ፡ ጐለመሱ ።
፻፯፡ እኒህም ፡ እስራኤል ፡ በሱ ፡ ዘመን ፡ በዙ ፡ እኒ
ህም ፡ ሁሉ ፡ ኢሎፍላውያን ፡ አማሌቃውያን ፡
የኤዶምያስ ፡ ሰዎች ፡ ከሱ ፡ የተነሣ ፡ ፈርተው ፡
ሸሹ ።
፻፰፡ ያም ፡ ሰሎሞን ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ ወጋ ፡ እነዚ
ያም ፡ አሕዛብ ፡ ዳግመኛ ፡ በእስራኤል ፡ መካ
ከል ፡ አልገቡም ፡ ከነሳቸው ፡ ፈጽመው ፡ ምንም ፡
ምን ፡ ገንዘብ ፡ አልነጠቁም ።
ይህም ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ ታላቅ ፡ ሰፊም ፡ ሆነ ፡ ፻፱፡
ለእስራኤል ፡ ገዥ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ በዚህ ፡
ደብተራ ፡ አሪት ፡ ላይ ፡ ለኒህ ፡ ለእስራኤል ፡
ጌታ ፡ ታላቅ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ተሠራ ።
ይህም ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ ተዋረደ ፡ ቤተ ፡ መቅ ፻፲፡
ደስ ፡ ግን ፡ ከበረ ፡ ታላቅ ፡ ሆነ ፡ የእስራኤል ፡
ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በዚያ ፡ በቤተ ፡ መቅ
ደስ ፡ ላይ ፡ በረድኤት ፡ አደረበት ፡ ብዙ ፡ የሆ
ነች ፡ መሥዋዕትንም ፡ በፊቱ ፡ አቀረቡ ።
ዳግመኛም ፡ እኒህን ፡ እስራኤልን ፡ እንደ ፡ በደሉ ፡ ፻፲፩፡
በብዙ ፡ ሥራዎችም ፡ ጸንተው ፡ እንደ ፡ ኖሩ ፡
አየኋቸው ፡ ያንም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንደ ፡
ተዉ ።
የእስራኤል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እስራ ፻፲፪፡
ኤል ፡ ዓበይት ፡ ነቢያትን ፡ ጠርቶ ፡ አስተምሩ ፡
ብሎ ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ላካቸው ፡ እስራኤ
ልም ፡ ይገድሏቸው ፡ ጀመር ።
ከነቢያትም ፡ አንዱ ፡ ኤልያስ ፡ ከሞት ፡ ዳነ ፡ ፻፲፫፡
አልሞተም ፡ ፈጥኖ ፡ ሄዶ ፡ በእስራኤል ፡ ከተማ ፡
አስተማረ ።
እስራኤልም ፡ ሊገሉት ፡ ወደዱ ፡ የእስራኤል ፡ ፻፲፬፡
ገዥ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከእስራኤል ፡ እጅ ፡
አዳነው ፡ ወደኔም ፡ አውጥቶ ፡ አኖረው ።
ያዳኑበቸው ፡ ዘንድ ፡ በነሱም ፡ ዘንድ ፡ ጮኸው ፡ ፻፲፭፡
ያስተምሩዋቸው ፡ ዘንድ ፡ ከዓበይት ፡ ነቢያት ፡
ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ደቂቀ ፡ ነቢያትን ፡ ወደነዚህ ፡ ወደ ፡
እስራኤል ፡ አስተምሩ ፡ ብሎ ፡ ሰደዳቸው ።
የእስራኤል ፡ ገዥ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪ ፻፲፮፡
ያው ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ በተዉ ፡ ጊዜ ፡ ከነሱ ፡
የተነሣ ፡ የመጣባቸውን ፡ መከራ ፡ አየሁ ፡
ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሥራት ፡ ወጥተው ፡ ዓይነ ፡ ልቡ
ናቸውም ፡ በድንቊርና ፡ ተያዘ ።
የእስራኤል ፡ ገዥ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ብዙ ፡ ፻፲፯፡
ሰልፍን ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ እንዳደረገ ፡ በየወገ
ናቸውም ፡ እነዚህ ፡ እስራኤል ፡ ያንን ፡ ሰልፍ ፡
እስኪጠፉት ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ።
ማደሪያው ፡ ቤተ ፡ መቅደስንም ፡ ለአሕዛብ ፡ ፻፲፰፡
ሰጡ ፡ እሱም ፡ በፋርስና ፡ በባቢሎን ፡ ሰዎች ፡
በሶርያና ፡ በግብፅ ፡ ሰዎች ፡ በሌሎች ፡ አሕዛብ ፡
እጅና ፡ በማሌቅ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ ጣላቸው ።
እኒህም ፡ አሕዛብ ፡ እኒህ ፡ እስራኤልን ፡ በሞት ፡ ፻፲፱፡
ይነጥቋቸው ፡ ጀመር ፡ እነሱም ፡ ይህንን ፡ ቤተ ፡
መቅደሳቸውን ፡ ማደሪያቸውንም ፡ እንደ ፡ ተዉ ፡
አየሁ ።
በሞት ፡ ይነጥቋቸውም ፡ ዘንድ ፡ በባቢሎን ፡ ፻፳፡
ሰዎች ፡ እጅ ፡ ከብታቸውንም ፡ ይበሉባቸው ፡
ዘንድ ፡ በሌሎች ፡ አሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ ጣላ
ቸው ።
ከአሕዛብ ፡ የተነሣ ፡ ከብታቸው ፡ ተበልቶባቸ ፻፳፩፡
ዋልና ፡ እኔም ፡ በፍጹም ፡ ኃይሌ ፡ እጮህ ፡ የእ
ስራኤል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እለምነው ፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



የእስራኤልንም ፡ ግፍ ፡ አሳየው ፡ ጀመርኩ ።
፹፪ እሱም ፡ እያየ ፡ ዝም ፡ አለ ፡ ከብቶቻቸው ፡ ፈጽሞ ፡
ተበልቶባቸዋልና ፡ አገራቸውንም ፡ ተቀምተዋ
ልና ፡ እሱም ፡ ገንዘባቸውን ፡ ሊያጠፉባቸው ፡
በሌሎች ፡ አሕዛብ ፡ እጅ ፡ ጥሏቸዋልና ፡ ደስ ፡
አለው ።

ምዕራፍ ፡ ፴፫ ።

፩ ሰባውን ፡ ነገሥታት ፡ ጠራ ፡ ይጠብቋቸውም ፡
ዘንድ ፡ እኒህ ፡ እስራኤልን ፡ ጠብቁ ፡ ብሎ ፡ በነ
ዚህ ፡ እጅ ፡ ጣላቸው ።
፪ ነገሥታቱን ፡ ሠራዊቶቻቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ከና
ንተ ፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስ
ራኤልን ፡ ይጠብቋቸው ፡ ዘንድ ፡ ጠብቁ ፡ አለ ፡
እኔም ፡ የማዝችሁን ፡ ሁሉ ፡ አድርጉ ፡ አላቸው ።
፫ እኔም ፡ በቍጥር ፡ እሰጣችኋለሁ ፡ ከነሱም ፡ የሚ
ጠፋውን ፡ እኔ ፡ እነግራችኋለሁ ፡ እነሱንም ፡
አጥፉ ፡ እነዚህ ፡ እስራኤልንም ፡ ጠብቁ ፡ ብሎ ፡
ሰጣቸው ።
፬ ከሰው ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ሚካኤልንም ፡ ጠራው ፡
ከዘገኋቸው ፡ ፈጽመው ፡ ወጥተው ፡ ከነሱ ፡ ያጠ
ፉሉና ፡ በኒህ ፡ እስራኤል ፡ ላይ ፡ መምራኑ ፡ የሚ
ያደርጉትን ፡ ጥፋት ፡ ሁሉ ፡ አይተህ ፡ ልብ ፡ አድ
ርገው ፡ አለው ።
፭ በኔ ፡ ትእዛዝ ፡ የሚያጠፏቸው ፡ ምን ፡ ያህልም ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ በነሱም ፡ ፈቃድ ፡ የሚያጠፉት ፡
ምን ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥጋባቸውን ፡ በነገ
ሥታቱም ፡ የሚደረገውን ፡ ጥፋት ፡ ሁሉ ፡ ጻፍ ፡
አለው ።
፮ አንዱም ፡ አንዱም ፡ ንጉሥ ፡ የሚያጠፋትን ፡
ጥፋት ፡ ሁሉ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ጣፈው ፡ በፊቴም ፡
በቍጥር ፡ አንብብ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ያጠፏቸው ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ለጥፋት ፡ ያሰጧ
ቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ።
፯ የነገሥታቱን ፡ ሥራቸውን ፡ ሁሉ ፡ መርምሬ ፡
አውቅ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ምስክር ፡ ሊሆነኝ ፡ ጻፍ ።
፰ በዘገኋቸው ፡ ትእዛዝ ፡ ጸንተው ፡ ይኖሩ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ አይኖሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚያደርጉትንም ፡
አይቼ ፡ እሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ጻፍ ፡ አለው ።
፱ በየጊዜው ፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ የሚያጠፋ
ትን ፡ የነገሥታቱን ፡ ጥፋት ፡ ሁሉ ፡ ጽፈሕ ፡
ሁሉንም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አምጣው ፡ እንጂ ፡ እነሱ ፡
ግን ፡ አይወቁ ፡ አንተም ፡ አታሳያቸው ፡ ዳግመ
ኛም ፡ አታስተምራቸው ፡ አለው ።
፲ እኒህም ፡ ነገሥታቱ ፡ በየሹመታቸው ፡ እስኪ
ጠብቋቸው ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ፡ ይገሉ ፡
ጀመር ፡ ከዘገኋቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ ወጥተው ፡
ብዙ ፡ ያጠፉ ፡ ጀመር ።
፲፩ ነገሥታቱም ፡ እኒህን ፡ እስራኤልን ፡ በባቢሎን ፡
ሰዎች ፡ እጅ ፡ ጣሏቸው ፡ የፋርስና ፡ የባቢሎን ፡
ሰዎችም ፡ ከእስራኤል ፡ ብዙዎችን ፡ ፈጽመው ፡
አጠፏቸው ።
፲፪ የኤዶምያስም ፡ ሰዎች ፡ ከነሱም ፡ ጋር ፡ የእስራ
ኤልን ፡ ከብት ፡ አጠፉ ፡ ቤተ ፡ መቅደስንም ፡
አቃጠሉት ፡ እስራኤል ፡ የሚጠበቁበት ፡ ይህ
ንንም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ቈፈሩት ።
እስራኤል ፡ የሚጠበቁበት ፡ ያ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ፲፫
ተቈፍሯልና ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ስለ ፡ ፈረሰ ፡
ፈጽሚ ፡ እጅግ ፡ አዘንኩ ።
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እኒህ ፡ እስራኤል ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ፲፬
መቅደስ ፡ ይገቡም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይገቡም ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ እነሱን ፡ ማየት ፡ አልተቻለኝም ።
መምራኑ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ እኒህን ፡ እስራ ፲፭
ኤልን ፡ ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ በኃጢአት ፡ ለሚ
ኖሩ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ አሳልፈው ፡ ሰጧቸው ።
ከነሱ ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ሁሉ ፡ በየሹመቱ ፡ በቍ ፲፮
ጥር ፡ ይቀበላል ፡ ከነሱ ፡ የሚያጠፋው ፡ ምንም ፡
ያህል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንዱ ፡ ለሁለተኛው ፡ በመ
ጽሐፍ ፡ ይጽፍለታል ፡ ይልቁንም ፡ ከሥራታ
ቸው ፡ ወጥተው ፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ ይገላል ፡
ዳግመኛም ፡ ያጠፋል ።
እኔም ፡ ስለነዚህ ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፲፯
ፈጽሚ ፡ አለቅስ ፡ ጀመር ።
እንደዚህም ፡ በራዕይ ፡ ይኸን ፡ ነገር ፡ የሚጽፍ ፡ ፲፰
ቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ በቀኑ ፡ ሁሉ ፡ ከኒህ ፡ ከመ
ምራኑ ፡ ለሚጠፋው ፡ ላንዱም ፡ ላንዱ ፡ እንዲ
ጥፍለት ፡ አየሁ ።
አውጥቶም ፡ እንዲያኖረው ፡ አየሁ ፡ ለእስራ ፲፱
ኤል ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ያንን ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ሁሉ ፡ የሚሠሩትንም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡
ከነሱ ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ በሞት ፡ ያራቁንም ፡
ሁሉ ፡ ለጥፋት ፡ አሳልፈው ፡ የሰጡትንም ፡
ሁሉ ፡ ያሳያል ።
መጽሐፉም ፡ በእስራኤል ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ ተነበበ ፡ ፳
ጌታም ፡ መጽሐፉን ፡ በጁ ፡ አንሥቶ ፡ አንብቦ ፡
አጥሮ ፡ አኖራት ።
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ነገሥታቱ ፡ እስራኤልን ፡ ፳፩
አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰባዒ ፡ ሲጠብቋቸው ፡ አየሁ ፡
ከነዚህም ፡ ከእስራኤል ፡ ሦስቱ ፡ ተመልሰው ፡
መጡ ፡ ወዳገራቸውም ፡ ገቡ ።
ከዚያም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የፈረሰውን ፡ ሁሉ ፡ ፳፪
ይሠሩ ፡ ጀመር ፡ የኤዶምያስም ፡ ሰዎች ፡ ከለከ
ሏቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከልክለው ፡ ማስቀረት ፡
አልተቻላቸውም ።
ዳግመኛም ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ይሠሩ ፡ ጀመር ፡ ፳፫
ቤተ ፡ መቅደስንም ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ አደሱት ፡
ታላቅ ፡ ግንብም ፡ ሆነ ።
ዳግመኛም ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ፊት ፡ ማዕድን ፡ ፳፬
ሲያኖሩ ፡ ንጹሕ ፡ ያይደለውን ፡ ርኩሱን ፡ ዳቦ ፡
ሁሉ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ሲሠሩ ፡ አየሁ ።
በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የእስራኤል ፡ ዓይነ ፡ ልቡና ፳፭
ቸው ፡ (ዕውቀት ፡) በድንቍርና ፡ ተይዘዋል ፡
ምሥጢርም ፡ አያዩም ፡ መምሮቻቸውም ፡ እን
ደዚሁ ፡ ናቸው ።
ለጥፋትም ፡ ፈጽመው ፡ ይሰጧቸዋል ፡ እስራኤ ፳፮
ልንም ፡ በእግራቸው ፡ ይረግጧቸዋል ፡ (ይሠለ
ጥኑባቸዋል ፡) ገንዘባቸውንም ፡ ይበሉባቸዋል ።
የእስራኤልንም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስራ ፳፯

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



ኤል ፡ ሁሉ ፡ ዳግመኛ ፡ እስኪ.በተኑ ፡ ድረስ ፡
ዝም ፡ አለ ፡ ከአሕዛብም ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሆኑ ፡ ከአ
ሕዛብም ፡ እጅ ፡ አላዳናቸውም ።
፳፰ መጽሐፉን ፡ የሚጽፍ ፡ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ሚካ
ኤል ፡ አውጥቶ ፡ ለጌታ ፡ አሳየው ፡ በእስራኤል ፡
ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ አነበበው ፡
ስለነሱም ፡ ይለምነዋል ።
፳፱ የመምራትንም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ እያሳየው ፡ ይለም
ነዋል ፡ በመምራትም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በፊቱ ፡ ያዳ
ኘል ፡ ይህንንም ፡ መጽሐፍ ፡ አንሥቶ ፡ በሱ ፡
ዘንድ ፡ አኑሮ ፡ ወጣ ።
፴ ነገሥታቱም ፡ እስከ ፡ ነገሡበት ፡ ዘመን ፡ ድርሺ ፡
አየሁ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ነገሥታትም ፡ እንደዚህ ፡
አድርገው ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ።
፴፩ ሁሉም ፡ በየሹመታቸው ፡ እንደ ፡ ቀድሞዎቹ ፡
ነገሥታት ፡ ጠብቀው ፡ ጨረሱ ።
፴፪ ሌሎች ፡ ነገሥታትም ፡ በየሹመታቸው ፡ ይጠ
ብቋቸው ፡ ዘንድ ፡ ከጻቸው ፡ ተቀበሏቸው ፡ አን
ዱም ፡ አንዱ ፡ ንጉሥ ፡ ሁሉ ፡ በየሹመቱ ፡ ይጠ
ብቃል ።
፴፫ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በከፍታ ፡ የሚኖሩ ፡ አሕዛብን ፡
ሁሉ ፡ በራዕይ ፡ አየሁ ፡ መጡ ፡ የሞዓብና ፡ የአ
ሞን ፡ ሰዎች ፡ ያልታወቁ ፡ አሕዛብ ፡ ሮማውያ
ንም ፡ የሞዓብና ፡ የአሞን ፡ ሰዎች ፡ ያልታወቁ ፡
አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ እየመሩ ፡ ሲያመጧቸው ፡
አየሁ ።
፴፬ እነዚህንም ፡ እስራኤልን ፡ ያጠፏቸው ፡ ጀመር ፡
ዓይናቸውንም ፡ ያጠፏቸው ፡ ጀመር ፡ ከብታቸ
ውንም ፡ ይበሉባቸው ፡ ጀመር ።
፴፭ እስራኤልም ፡ ከአሕዛብ ፡ የተነሣ ፡ ከብታቸው ፡
ተበልቶባቸዋልና ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ጮኸው ፡ ለመኑ ።
፴፮ እኔም ፡ ተኝቼ ፡ ሳለሁ ፡ ጮኩ ፡ እስራኤልንም ፡
በሚጠብቃቸው ፡ በንጉሡም ፡ ጮኩ ።
፴፯ እስራኤልም ፡ ከኢሎፍላውያን ፡ የተነሣ ፡ ከሞ
ዓብ ፡ ከአሞንም ፡ የተነሣ ፡ ካልታወቁም ፡ አሕ
ዛብ ፡ የተነሣ ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ ደርሺ ፡
አየሁ ።
፴፰ ገንዘባቸውን ፡ ልብሳቸውን ፡ ልጃቸውንም ፡
ወገኖቻቸው ፡ ብቻቸውን ፡ እስቲቀሩ ፡ ድረስ ፡
ፈጽመው ፡ አልተዉላቸውም ፡ ወገኖቻቸውም ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ጠፉ ፡ እስራኤልም ፡ ከብዛታ
ቸው ፡ አነሱ ።
፴፱ ሀያ ፡ ሦስትም ፡ ነገሥታት ፡ እስከ ፡ ተሾሙበት ፡
ዘመን ፡ ድረስ ፡ ደርሺ ፡ አየሁ ፡ አምሳ ፡ ስምንት ፡
ሱባኤን ፡ በየሹመቻቸው ፡ ተሾመው ፡ ጨረሱ ።
፵ አእምሮ ፡ ካለቸው ፡ ከኒህ ፡ ከዓበይት ፡ ነቢያት ፡
ንዑሳን ፡ ሐዋርያት ፡ ከእስራኤል ፡ ተወለዱ ፡
የእስራኤል ፡ ዓይነ ፡ ልቡናቸውንም ፡ ይገልጡ ፡
ጀመር ፡ ይጠብቃሉ ፡ እስራኤልንም ፡ ጮኸው ፡
ያስተምሩ ፡ ጀመር ።
፵፩ ፈጽመው ፡ ቸል ፡ አሉ ፡ እንደ ፡ ዓይነ ፡ ልቡናዎ
ቻቸውም ፡ ፈጽመው ፡ በድንቍርና ፡ ቈያዙ ፡
እንጂ ፡ ድንቍርናውም ፡ በነሱ ፡ የበረታ ፡ ሆነ ፡
እንጂ ፡ እስራኤል ፡ አልሰሟቸውም ፡ የነገሯቸ
ውንም ፡ ነገር ፡ አላዳመጧቸውም ።
በራዕይም ፡ ሮማውያን ፡ ወደነዚህ ፡ ወደ ፡ ሐዋ ፵፪
ርያት ፡ ፈጥነው ፡ ሲሄዱባቸው ፡ አየሁ ፡ ከኒህም ፡
ከሐዋርያት ፡ ለይተው ፡ አንዱን ፡ ዮሐንስን ፡
ይዘው ፡ ገደሉት ።
ሐዋርያትንም ፡ ፈጽመው ፡ ገደሏቸው ፡ ለኒ ፵፫
ህም ፡ ለሐዋርያት ፡ ሥልጣን ፡ እስቲሰጣቸው ፡
ድረስ ፡ ደርሺ ፡ አየሁ ፡ ሮማውያንም ፡ ሥልጣ
ናቸውን ፡ እናጠፋለን ፡ አሉ ።
ከኒህም ፡ ከእስራኤል ፡ አንዱ ፡ ገናና ፡ ክርስቶስ ፡ ፵፬
እስኪወለድ ፡ ድረስ ፡ ደርሺ ፡ አየሁ ፡ ዓይነ ፡ ልቡ
ናቸውም ፡ ተገለጠላቸው ።
በነሱም ፡ ምሥጢር ፡ አየባቸው ፡ ዓይነ ፡ ልቡና ፵፭
ቸውም ፡ ተገለጠላቸው ፡ ሐዋርያትንም ፡ ተከ
ተሉኝ ፡ አላቸው ፡ ሐዋርያትም ፡ ሁሉ ፡ አይተ
ውት ፡ ወደሱ ፡ ሄዱ ።
ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ እኒህ ፡ የሞዓብ ፡ የአ ፵፮
ሞን ፡ ሰዎች ፡ ያልታወቁ ፡ አሕዛብ ፡ ሮማውያን ፡
ሌሎች ፡ አሕዛብ ፡ ሐዋርያትን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡
ድረስ ፡ ያጠፏቸው ፡ ነበር ፡ ፈጥነው ፡ ወደሳ
ቸው ፡ ሄደው ፡ ያጠፏቸው ፡ ነበር ።
ሐዋርያት ፡ ግን ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ነበር ፡ ኋላ ፡ ፵፯
ግን ፡ ለእስራኤል ፡ ጮኸው ፡ አስተማሩ ፡ እነዚ
ህም ፡ ሮማውያን ፡ ከጌታ ፡ ጋራ ፡ ይጋደሉ ፡ ይጣ
ሉም ፡ ነበር ።
የጌታንም ፡ ሥልጣን ፡ ሊያጠፉ ፡ ወደዱ ፡ ነገር ፡ ፵፰
ግን ፡ አልቻሉትም ፡ (አንስርት ፡) ሌሎቹ ፡ ነገሥ
ታት ፡ የሞዓብ ፡ የአሞንም ፡ ሰዎች ፡ እነዚህ ፡
ሌሎች ፡ አሕዛብም ፡ እስኪመጡ ፡ ድረስ ፡ ደርሺ ፡
አየሁ ።
የዚህን ፡ የጌታን ፡ ሥልጣን ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ፵፱
ለሮማውያን ፡ እርዱን ፡ ብለው ፡ ጮሁ ።
ሮማውያንም ፡ ከጌታ ፡ ጋር ፡ ተጣልተው ፡ ተጋ ፶
ደሉ ፡ እሱም ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ተጣላ ፡ ረዳኤ ፡ አም
ላክነቱን ፡ የሚመሰክርለት ፡ መላክ ፡ ይመጣ ፡
ዘንድ ፡ ጮኸ ።
የነገሥታቱን ፡ ስም ፡ የጻፈ ፡ ይህ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካ ፶፩
ኤል ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ ደርሺ ፡ አየሁ ።
ወደ ፡ እስራኤል ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ ይዞ ፡ ይወጣል ፡ ፶፪
እሱም ፡ ረዳኤ ፡ አምላክ ፡ ነህ ፡ አለው ፡ ሁሉ
ንም ፡ ገልጦ ፡ አሳየው ፡ ይህንንም ፡ ክርስቶስን ፡
ረዳኤ ፡ አምላክ ፡ ነህ ፡ የሚለው ፡ መልአክ ፡
ወረደ ፡ ይህም ፡ የእስራኤል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ወደነሱ ፡ በመዓት ፡ እስኪመጣባቸው ፡
ድረስ ፡ ደርሺ ፡ አየሁ ።
ያዩትም ፡ አይሁድ ፡ ሁሉ ፡ ሸሹ ፡ ሁሉም ፡ ከገጸ ፡ ፶፫
መዓቱ ፡ የተነሣ ፡ በሥልጣኑ ፡ ጠፉ ፡ የሞዓብ ፡
የአሞን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ሌሎች ፡ አሕዛብም ፡
ሁሉ ፡ ሮማውያንም ፡ ሁሉ ፡ ሌሎች ፡ አሕዛብም ፡
ተሰበሰቡ ።
እስራኤልንም ፡ ለማጥፋት ፡ የሮምን ፡ ሰዎች ፡ ፶፬
ከነሱ ፡ ጋር ፡ አመጧቸው ፡ ሁሉም ፡ አንድ ፡
ሁነው ፡ መጡ ፡ የዚህን ፡ የክርስቶስን ፡ ሥል

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



ጣን ፡ ሊያጠፉ ፡ ተራዱ ።
፷፭፡ በጌታ ፡ ቃል ፡ መጽሐፉን ፡ የሚጽፍ ፡ ይህንን ፡
ቅዱስ ፡ ሚካኤልንም ፡ በኋላ ፡ የተነሡ ፡ እኒህ ፡
አሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገሥታት ፡ ሰውን ፡ ያጠፉበት ፡
ይህንን ፡ መጽሐፍ ፡ እስቲገልጠው ፡ ድረስ ፡
ደርሼ ፡ አየሁ ።
፷፮፡ ከነሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ከነበሩት ፡ ይልቅ ፡ እነሱ ፡
አብልጠው ፡ ሰውን ፡ እንዳጠፉ ፡ በእስራኤል ፡
ገዥ ፡ ፊት ፡ አሳየ ፡ የእስራኤልም ፡ ገዥ ፡ እግ
ዚአብሔርም ፡ ወደነሱ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡
ደርሼ ፡ አየሁ ።
፷፯፡ ቍጣውን ፡ የሚጨርስበት ፡ በትሩን ፡ በጁ ፡ አን
ሥቶ ፡ ምድርን ፡ መታት ፡ ምድርም ፡ ተሰነጠ
ቀች ፡ አሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡
ከኒህም ፡ ከአይሁድ ፡ ወገኖች ፡ ከዚያ ፡ ወድቀው ፡
በምድር ፡ ሰጠሙ ፡ ምድርም ፡ ተጫነቻቸው ።
፷፰፡ ለሐዋርያትም ፡ ታላቅ ፡ ሥልጣን ፡ እስኪሰጣ
ቸው ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ፡ ሐዋርያትም ፡ ከው
ቀት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወደ ፡ ሆኑ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡
ሁሉ ፡ ሊያጠፏቸው ፡ ወጡ ።
፷፱፡ በከፍታ ፡ የሚኖሩ ፡ አሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ ከፊታ
ቸው ፡ ሸሹ ።

ምዕራፍ ፡ ፺፬ ።

፩፡ ባማረች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡
እስቲሠራ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ፡ የእስራኤ
ልም ፡ ጌታ ፡ በሱ ፡ በረድኤት ፡ አደረበት ።
፪፡ የተጣሉትንም ፡ መጣሮች ፡ አንሥቶ ፡ በእስራ
ኤል ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ እነዚህን ፡ የተጣሉ ፡ መጣ
ሮች ፡ ገለጣቸው ።
፫፡ የቀደሙ ፡ አእምሮ ፡ ያደረባቸው ፡ እኒህን ፡ ሰባ
ቱን ፡ መላእክት ፡ ጠሯቸው ፡ አፍረታቸው ፡
እንደ ፡ ፈረስ ፡ አፍረት ፡ የሆነ ፡ ከኒህ ፡ ከደቂቀ ፡
ሴት ፡ የሚቀድም ፡ መጀመሪያ ፡ የተሾመ ፡ ስማ
ዝያ ፡ ወደሱ ፡ ያመጡት ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ።
፬፡ አስቀድሞ ፡ የወደቀ ፡ መጀመሪያ ፡ የተሾመ ፡
ዲያብሎስን ፡ አመጡት ፡ ሌሎችንም ፡ ሁሉ ፡
ወደሱ ፡ አመጡቸው ።
፭፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ከሆኑ ፡ ከሰባቱ ፡ ሊቃነ ፡ መላእ
ክት ፡ አንድ ፡ የሚሆን ፡ በሱ ፡ ፊት ፡ የነገሥታ
ቱን ፡ ግፍ ፡ የሚጽፍ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤልን ።
፮፡ እስራኤልን ፡ ጠብቁ ፡ ብዬ ፡ የሰጠኋቸውን ፡
ተቀብለውም ፡ ከዘገኋቸው ፡ ወጥተው ፡ ብዙዎ
ችን ፡ ያጠፉ ፡ እነዚህን ፡ ሰባውን ፡ ነገሥታት ፡
ወስደህ ፡ አግዛቸው ፡ አለው ።
፯፡ ሁሉንም ፡ እነሆ ፡ ታስረው ፡ አየኋቸው ፡ ሁሉም ፡
በፊቱ ፡ ቆሙ ፡ አስቀድሞ ፡ ፍርድ ፡ በደቂቀ ፡
ሴት ፡ ተጀመረ ፡ ተወቀሱ ፡ ኃጢአተኞች ፡
ሁነው ፡ ተገኙ ፡ ፍጹም ፡ መቻያም ፡ ወደሚደረ
ግበት ፡ ቦታ ፡ ተፈርዶባቸው ፡ ሄዱ ።
፰፡ መላእክትም ፡ ወደ ፡ ጥልቅ ፡ ገሃነም ፡ ጣሏቸው ፡
ያም ፡ ቦታ ፡ ፈጽሞ ፡ የሚያላልብ ፡ እሳትን ፡
ምሰሶ ፡ የተመላ ፡ ነው ።
፱፡ እነዚያም ፡ ሰባው ፡ ነገሥታት ፡ መምራኑ ፡ ተወ
ቀሱ ፡ ኃጢአተኞችም ፡ ሆኑ ፡ እነሱም ፡ ወደዚህ ፡
ጥልቅ ፡ ገሃነም ፡ ወደቁ ።
እንደዚሁ ፡ እሳትን ፡ በተመላ ፡ ምድር ፡ መከ ፲፡
ከል ፡ አንድ ፡ ገሃነምን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተከፍቶ ፡
አየሁት ።
በድንቍርና ፡ የተያዙ ፡ እነዚህም ፡ አይሁድን ፡ ፲፩፡
ወደዚያ ፡ ቦታ ፡ አመጡቸው ፡ ሁሉም ፡ ተወ
ቀሱ ፡ ኃጢአተኞች ፡ ሁነው ፡ ተገኙ ፡ እሳት ፡
ባለበት ፡ በዚህ ፡ በገሃነም ፡ ወድቀው ፡ ተቃጠሉ ።
ይህም ፡ ጥልቅ ፡ ገሃነም ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ (መንግ ፲፪፡
ሥተ ፡ ሰማያት ፡) በቀኙ ፡ ሆነ ፡ እነዚህንም ፡
አይሁድን ፡ በገሃነም ፡ ሲቃጠሉ ፡ ወገናቸውም ፡
ሲቃጠል ፡ አየሁ ።
ይህንን ፡ ያረጀውን ፡ ቤት ፡ (ሕገ ፡ ኦሪት ፡) እስ ፲፫፡
ኪያፈርሰው ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ ለማየት ፡ ቆምኩ ፡
ምሰሶዎችንም ፡ ሁሉ ፡ አወጡቸው ። (ነቢያት ፡
ካህናት ፡)
የዚያም ፡ ቤት ፡ ጌጡና ፡ ተክሉ ፡ ሁሉ ፡ (ሥር ፲፬፡
ዓተ ፡ ኦሪት ፡) ከሱ ፡ ጋር ፡ ፈረሰ ፡ መላእክትም ፡
አውጥተውም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ቀኝ ፡ ባለ ፡
በንድ ፡ ቦታ ፡ (፩ ፡ ያዕቆብ ፡) ጣሉት ።
የእስራኤል ፡ ገዥ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከዚህም ፡ ፲፭፡
ከቀደመው ፡ ቤት ፡ ፈጽሞ ፡ (ወንጌል ፡) የሚበ
ልጥ ፡ አዲስ ፡ የሆነ ፡ ቤትን ፡ አምጥቶ ፡ እስኪ
ሠራ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ፡ ያንንም ፡ ቤት ፡
አምጥቶ ፡ አስቀድማ ፡ በፈረሰችው ፡ ቤት ፡ ቦታ ፡
አጸናው ።
ምሰሶዎቿም ፡ ሁሉ ፡ አዲሶች ፡ ናቸው ፡ ጌጡም ፡ ፲፮፡
ሁሉ ፡ አዲስ ፡ ነው ፡ ቀድሞ ፡ አርጅታ ፡ ከፈረሳ
ትም ፡ ቤት ፡ ይልቅ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡ ሐዋርያትም ፡
ሁሉ ፡ በመካከሏ ፡ ናቸው ።
ከሞት ፡ የቀሩ ፡ እስራኤልንም ፡ ሁሉ ፡ አየኋ ፲፯፡
ቸው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የቀሩም ፡ ሁሉ ፡ ከሰማይ ፡
በታች ፡ ያሉ ፡ አሕዛብም ፡ ሁሉ ።
እኒህ ፡ ለሐዋርያት ፡ ወድቀው ፡ ይሰግዳሉ ፡ ይለ ፲፰፡
ምኗቸዋል ፡ የነገሯቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ቃል ፡ ይሰ
ሙዋቸዋል ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡ አስቀ ፲፱፡
ድመውም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ያወጡኝ ፡ እነዚህም ፡
ሦስቱ ፡ መላእክት ፡ እጄን ፡ ያዙኝ ።
የዚያም ፡ የክርስቶስ ፡ ሥልጣኑ ፡ ይዛኝ ፡ ሳለች ፡ ፳፡
ፍርድ ፡ ሳትደረግ ፡ አውጥተው ፡ በኒህ ፡ በሐዋ
ርያት ፡ መካከል ፡ አኖሩኝ ።
እነዚያም ፡ ሐዋርያት ፡ ሁሉ ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ፳፩፡
ሆኑ ፡ ጺጋ ፡ ክብራቸውም ፡ ታላቅ ፡ ሆነ ፡ ከነቀ
ፋም ፡ የነፃ ፡ ሆነ ።
የጠፉ ፡ የተበተኑ ፡ ሁሉ ፡ በሩቅ ፡ ያሉ ፡ አሕዛ ፳፪፡
ብም ፡ ሁሉ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የነበሩ ፡ እስራኤ
ልም ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ተሰበሰቡ ።
ሁሉም ፡ ደጋግ ፡ ሁነዋልና ፡ ወደ ፡ ማደሪያው ፡ ፳፫፡
ቤተ ፡ መቅደስም ፡ ተመልሰዋልና ፡ የእስራኤል ፡
ገዥ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡
አለው ።
ለሐዋርያት ፡ የተሰጣቸው ፡ ይህንንም ፡ ሥልጣን ፡ ፳፬፡

www.ethiopianorthodox.org

እስኪያጠፉት ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ፡ ወደ ፡
ቤቱም ፡ መለሱት ፡ በጌታም ፡ ፊት ፡ ጠቅሎ ፡
አኖሩት ፡ (ጠበቃት ።)
፸፭ እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ በዝተው ፡ በዚያ ፡ በቤተ ፡
መቅደስ ፡ ሥራት ፡ ጸኑ ፡ አልቻላቸውም ፡ የሁ
ሉም ፡ ዓይን ፡ ልቡናዎቻቸው ፡ ተገልጠው ፡ በጎ ፡
በጎ ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ፡ ከነሱ ፡ አንዱም ፡ በመ
ካከላቸው ፡ ምሥጢር ፡ የሚያይ ፡ አልነበረም ።
፸፮ ያም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ታላቅ ፡ ሰፊም ፡ ምስጋ
ናውንም ፡ ፈጽሞ ፡ የተመላ ፡ ሆኖ ፡ አየሁት ፡
አንድ ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ክርስቶስን ፡ ተወልዶ ፡
አየሁት ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቶቹ ፡ ሐዋርያትም ፡
ታላላቆች ፡ ናቸው ።
፸፯ እስራኤልና ፡ አሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ ፈርተው ፡ በየ
ጊዜው ፡ ይለምኑታል ።
፸፰ ዘመዶቻቸውም ፡ ሁሉ ፡ በአእምሮ ፡ እስቲለ
ወጡ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ፡ ወገኖቻቸውም ፡
ሁሉ ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ሆኑ ።
፸፱ መጀመሪያ ፡ የተናገርኩት ፡ ሐሳዊ ፡ መሲሕም ፡
በመካከላቸው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ሆነ ፡ ይኸውም ፡
ሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ ታላቅ ፡ አጥፊን ፡ ሆነ ፡ በሱም ፡
ዘንድ ፡ ታላላቅ ፡ በድንቁርናም ፡ የተያዙ ፡ ሐሳዊ ፡
ሄኖክ ፡ ሐሳዊ ፡ ኤልያስ ፡ አሉት ።
፹ የእስራኤል ፡ ገዥ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በነሱ ፡
በወገኖቻቸውም ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አለው ።
፹፩ እኔም ፡ በመካከላቸው ፡ ተኝቼ ፡ ተነሥቼ ፡ ሁሉን ፡
አየሁ ፡ ተኝቼም ፡ ያየሁት ፡ ራዕይ ፡ ይህ ፡ ነው ፡
ተመኝታዬም ፡ ተነሥቼ ፡ የቸርነት ፡ ባለቤት ፡
ጌታን ፡ አመሰገንሁት ፡ ለሱም ፡ ምስጋናን ፡ አቀ
ረብሁለት ።
፹፪ ከሱም ፡ የተነሣ ፡ ታላቅ ፡ ልቅሶን ፡ አለቀስኩ ፡
ወዳየሁት ፡ ወደዚህ ፡ ገሃነም ፡ ሲወርዱ ፡ በየሁ ፡
ጊዜ ፡ መታገሡን ፡ አልቻልኩምና ፡ እንባዬ ፡
አልተገታም ።
፹፫ ሁሉ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ መጥቶ ፡ ይጨርሳልና ፡
የሰው ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ በየወገን ፡ በየወገኑ ፡ ተገ
ለጠልኝ ።
፹፬ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ የቀደመውን ፡ ሕልሜን ፡
አሰብኩት ፡ ይህንን ፡ ራዕይ ፡ አይቻለሁና ፡ ስለዚ
ህም ፡ ነገር ፡ አለቀስኩ ፡ ታወክሁ ።
፹፭ አሁንም ፡ ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡ አስተምራቸው ፡
የሚል ፡ ቃል ፡ ጠርቶኛል ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡
ድረስ ፡ የሚደርስበችሁን ፡ ሁሉ ፡ ገልጬ ፡ አስ
ተምራችሁ ፡ ዘንድ ፡ ዕውቀትም ፡ ተሰጥቶኛ
ልና ፡ ወንድሞችህን ፡ ሁሉ ፡ ጥራልኝ ፡ የናትህ
ንም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ሰብስብልኝ ።
፹፮ ገልጬ ፡ አስተምራችሁ ፡ ዘንድ ፡ ዕውቀቱ ፡ በኔ ፡
ላይ ፡ በዝቶ ፡ ተሰጠኝ ።
፹፯ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ከኔ ፡ ተለይቶ ፡ ሄደ ፡ ወንድሞ
ቹን ፡ ሁሉ ፡ ወደሱ ፡ ጠራቸው ፡ ዘመዶቹንም ፡
ሰበሰባቸው ፡ ለልጆቹም ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ ነገ
ርን ፡ ነገራቸው ።
፹፰ ልጆቼ ፡ የኔ ፡ ያባታችሁን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ስሙ ፡
በናንተ ፡ አዳኝባችኋለሁና ፡ ወዳጆቼ ፡ የሚያገ
ኛችሁንም ፡ መከራ ፡ እነግራችኋለሁና ፡ ከንደ
በቴ ፡ የወጣውንም ፡ ነገር ፡ በሚገባ ፡ ስሙ ፡
አላቸው ።
የቀናች ፡ ሕግንም ፡ ውደዷት ፡ በሷም ፡ ጸንታ ፹፱
ችሁ ፡ ኑሩ ፡ ሁለት ፡ ልብም ፡ ሁናችሁ ፡ ወደ ፡
ቀናች ፡ ሕግ ፡ አትቅረቡ ፡ ልጆቼ ፡ በውነት ፡
ሥራ ፡ ዘንታችሁ ፡ ኑሩ ፡ እንጂ ፡ ሁለት ፡ ልብ ፡
ሆነው ፡ ከሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አት
ሁኑ ።
ያችም ፡ ወደ ፡ በጎ ፡ ሥራዎች ፡ ትመራችኋለች ፡ ፺
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የግፍ ፡ አካል ፡ እንዳጸና ፡ አው
ቃለሁና ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ከፈጣሪያችሁ ፡ ጋር ፡
አንድ ፡ ያደርጋችኋል ።
በዚህም ፡ ዓለም ፡ ጽኑ ፡ መቅሠፍት ፡ ይጨረ ፺፩
ሳል ፡ ግፍም ፡ ሁሉ ፡ ትጨረሳለች ፡ (ታልፋ
ለች ፡ ) ሠሪዎቿም ፡ ፤ ጠፉሉ ።
ሥራውም ፡ ሁሉ ፡ የልፋል ፡ ዳግመኛም ፡ ፺፪
(ጥቅመ ፡ ሰናዖር ፡ ) ግፍ ፡ ሁሉ ፡ ተሠርታ ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ትጨረሳለች ፡ የግፍ ፡ ሥራና ፡
የበደል ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ትጀመራለች ፡ በደልም ፡
ሁለት ፡ እጥፍ ፡ ሆና ፡ ትሠራለች ።
ኃጢአትና ፡ ሐሰት ፡ በደልና ፡ ስድብ ፡ ክፉውም ፡ ፺፫
ሥራ ፡ ሁሉ ፡ እየበዛ ፡ ወንጀልና ፡ በደልም ፡
እየበዛ ፡ ጣዖትም ፡ እየተመለከ ፡ ጽኑ ፡ መቅሠ
ፍት ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ በነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ይደረጋል ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ፍርድን ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ የከ ፺፬
በረ ፡ ጌታ ፡ በመቅሠፍትና ፡ በመዓት ፡ ይመ
ጣል ።
በነዚያ ፡ ወራቶች ፡ ግፍ ፡ ከሠሪዎቿ ፡ ጋራ ፡ ትጠ ፺፭
ፋለች ፡ ከክዳትም ፡ ጋራ ፡ በሐሠት ፡ ጸንተው ፡
የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ይጠፋሉ ፡
ይኸም ፡ ሁሉ ፡ ለአሕዛብ ፡ ይሰጣል ።
አዳራሽ ፡ በእሳት ፡ ትጠፋለች ፡ (ሰዶም ፡ ገሞራ ፡ ) ፺፮
ከዚህም ፡ ከዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ያወጧቸዋል ፡ በተ
ፈረደባቸው ፡ በእሳት ፡ ይጠፋሉ ፡ በቀኑጣ ፡ ዘለ
ዓለም ፡ ጸንቶ ፡ ለሚኖር ፡ በጽኑም ፡ ፍርድ ፡
ይጠፋሉ ።
ደግ ፡ ሰው ፡ አብርሃም ፡ ከንዋመ ፡ ሐኬት ፡ ይለ ፺፯
ያል ፡ ኢታምልክ ፡ ይሠራል ፡ ይሰጣቸዋል ፡
ከዚያም ፡ ቀጥሎ ፡ የበደል ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡
ይጠፋሉ ።
የከነዓንም ፡ ሰዎች ፡ በኢያሱ ፡ ሰይፍ ፡ ይጠፋሉ ፡ ፺፰
እግዚአብሔርንም ፡ የሚሳደቡ ፡ ወገኖች ፡ በበ
ታው ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋሉ ።
ግፍን ፡ የሚያስቧት ፡ ስድብንም ፡ የሚሠሯት ፡ ፺፱
ሰዎች ፡ በጦር ፡ ይጠፋሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፹፭ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሁለተኛ ፡ እውነት ፡ ነገር ፡ ፩
የሚደረግበት ፡ ስምንተኛይቱ ፡ ሱባዔ ፡ ትደረ
ጋለች ፡ ሰውን ፡ ከሚበድሉ ፡ ሰዎች ፡ የተነሣ ፡
እውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ ይደረግበት ፡ ዘንድ ፡ ለሷ ፡
ሥልጣን ፡ ይሰጣል ፡ ኃጥአንም ፡ በጻድቃን ፡

እጅ ፡ ይወድቃሉ ።
፪ ፡ በመጨረሻዋም ፡ ከበጎ ፡ ሥራቸው ፡ የተነሣ ፡
ቤት ፡ ንብረት ፡ ያደርጋሉ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡
ሊመሰገንበት ፡ ለገናና ፡ ንጉሥ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ደብተራ ፡ ኦሪት ፡ ይሠራል ።
፫ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በዘጠኘኛይቱ ፡ ሱባዔ ፡ ለሰው ፡
ሁሉ ፡ እውነተኛይቱ ፡ ሕግ ፡ ትገለጣለች ።
፬ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የዘነጉ ፡ ሰዎችም ፡ ሥራ ፡
ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ይጠፋል ፡ ሰውም ፡ ለጥ
ፋት ፡ ይቈጠራል ፡ ይህንንም ፡ አይተው ፡ ሌሎች ፡
ሰዎች ፡ የቀናች ፡ ሥራን ፡ ይመለከታሉ ።
፭ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሥረኛይቱ ፡ ሱባዔ ፡ ሰባት ፡
እጅ ፡ የሚሆን ፡ የዘላለም ፡ ፍርድ ፡ ይደረግበታል ።
፮ ፡ በደቂቀ ፡ ሴትም ፡ ፍርድ ፡ ትደረጋለች ፡ በመላ
እክት ፡ መካከል ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ደገኛ ፡ መን
ግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ይሰጣል ፡
ይባላል ።
፯ ፡ የቀድሞ ፡ ሰማይ ፡ ፈጽሞ ፡ ያልፋል ፡ ይባላል ፡
አዲስ ፡ (ጠፈር ፡) መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይሰ
ጣል ፡ ይባላል ፡ የሰማይ ፡ ሠራዊት ፡ ጸድቃንም ፡
ሁሉ ፡ ሰባት ፡ እጥፍ ፡ ብርሃንን ፡ ለዘላለሙ ፡
ያበራሉ ።
፰ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸው ፡
ብዙ ፡ ሱባዔዎች ፡ በቸርነቱና ፡ በይቅርታ ፡ ለዘ
ላለሙ ፡ ይደረጋሉ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ኃጢ
አት ፡ እስተዘላለሙ ፡ ትሠራለች ፡ አትሠራም ።
፱ ፡ አሁንም ፡ ልጆቼ ፡ እነግራችኋለሁ ፡ የግፍ ፡ ሥራ
ዎችንና ፡ የበጎ ፡ ሥራዎችን ፡ ገልጬ ፡ አስተም
ራችኋለሁ ።
፲ ፡ ዳግመኛ ፡ የሚመጣባችሁን ፡ መከራ ፡ ታውቁ ፡
ዘንድ ፡ ገልጬ ፡ አስተምራችኋለሁ ፡ አሁንም ፡
ልጆቼ ፡ ስሙኝ ፡ በበጎ ፡ ሥራዎች ፡ ጸንታችሁ ፡
ኑሩ ።
፲፩ ፡ በግፍ ፡ ሥራ ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡
ሁሉ ፡ ለዘላለሙ ፡ ይጠፋሉ ፡ ልጄ ፡ በግፍ ፡
ሥራዎች ፡ ጸንታችሁ ፡ አትኑሩ ፡ እላችኋለሁ ።
፲፪ ፡ ሕግን ፡ በሰው ፡ ልቡና ፡ ከምጽፍ ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡
ክቡር ፡ የዓለሙም ፡ ሁሉ ፡ መምህር ፡ ከምሆን ፡
ከኔ ፡ ከሄኖክ ፡ የተጻፈ ።
፲፫ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የጥበብ ፡ ትምህርት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
ለሚኖሩ ፡ ለልጆቼ ፡ ሁሉ ፡ ፍቅርንና ፡ የቀና ፡
ነገርን ፡ ለሚሠሩ ፡ ኋላ ፡ ለሚወለዱ ፡ ልጆችም ፡
ትድረስ ።
፲፬ ፡ ንጹሕ ፡ ክቡር ፡ ገናናም ፡ የሚሆን ፡ ጌታ ፡ ለሰው ፡
ሁሉ ፡ መዋዕለ ፡ ንስሐን ፡ ሰጥቷልና ፡ ሰውነታ
ችሁ ፡ በአዝማን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ እንዳ
ታዝን ፡ ትሁን ።
፲፭ ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ከንዋመ ፡ ሐኬት ፡ ይለያል ፡ ወደ ፡
እውነት ፡ ሥራዎችም ፡ ይሔዳል ።
፲፮ ፡ ሥራውም ፡ ሁሉ ፡ አኗኗሩም ፡ በይቅርታና ፡
በቸርነት ፡ ነው ፡ ደጉንም ፡ ሰው ፡ ለዘላለሙ ፡
ይቅር ፡ ይለዋል ፡ በሱም ፡ ለዘለዓለሙ ፡ የቀና ፡
ሥራን ፡ ይሰጠዋል ፡ ሥልጣንንም ፡ ይሰጠዋል ።
፲፯ ፡ ቸርነቱ ፡ በእውነትም ፡ ሥራ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡
ዕውቀትም ፡ ለዘላለሙ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ በለ
ማወቅ ፡ የተሠራች ፡ ኃጢአትም ፡ እስተዘላ
ለሙ ፡ ትጠፋለች ፡ ከዚያችም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡
እስተዘላለሙ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ትወራለች ፡
አትባልም ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሄኖክ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፡ ከመጻሕ ፲፰ ፡
ፍት ፡ እየተጠቀሰ ፡ ይናገር ፡ ጀመረ ።
ሄኖክ ፡ የሕጋውያንን ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ፲፱ ፡
ያሉ ፡ የደናግልንም ፡ ነገር ፡ ሕግን ፡ የሚጠብቅ ፡
የቀና ፡ ሥራንም ፡ የሚሠራ ፡ የአብርሃምንም ፡
ነገር ፡ ተናገረ ፡ ልጆቼ ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡
ፈጽሜ ፡ እነግራችኋለሁ ፡ አለ ።
በሰማይ ፡ የታየኝን ፡ ራዕይ ፡ የከበሩ ፡ ከሆኑ ፡ ፳ ፡
ከመላእክት ፡ ቃል ፡ ሰምቼ ፡ ያወቅሁትን ፡ በሰ
ማይ ፡ ሰሌዳነትም ፡ አይቼ ፡ ልብ ፡ ያደረግሁትን ፡
እኔ ፡ ሄኖክ ፡ እነግራችኋለሁ ።
ሄኖክም ፡ ከመጻሕፍት ፡ እየጠቀሰ ፡ ይናገር ፡ ፳፩ ፡
ጀመረ ፡ በለአእምሮ ፡ የምሆን ፡ እኔ ፡ ሄኖክ ፡
በመጀመሪያይቱ ፡ ሱባዔ ፡ ተወለድሁ ።
እውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ እስኪደረግ ፡ ድረስ ፡ ጌታ ፡ ፳፪ ፡
የሰውን ፡ ኃጢአት ፡ ታገሠ ፡ ከኔም ፡ በኋላ ፡
በሁለተኛይቱ ፡ ሰባዔ ፡ ጽኑ ፡ ኃጢአት ፡ ትሠ
ራለች ።
ተንኰልም ፡ ጸናች ፡ በሷም ፡ የመጀመሪያይቱ ፡ ፳፫ ፡
መከራ ፡ መጨረሻ ፡ ትደረጋለች ። (ማየ ፡ አይኅ ፡
ነው ፡)
ኖኅም ፡ በሷ ፡ ከማየ ፡ አይህ ፡ ይድናል ፡ ዘመ ፳፬ ፡
ኑም ፡ ከተጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ግፍ ፡ ትሠራለች ፡
እሱንም ፡ ለበደሉ ፡ ሰዎች ፡ የልሳን ፡ መለያየ
ትን ፡ ያደርጋል ። ( በቋንቋ ፡ )
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሦስተኛይቱ ፡ ሱባዔ ፡ በመ ፳፭ ፡
ጨረሻዋ ፡ እውነተኛ ፡ ሕግን ፡ ለመጠበቅ ፡ አብ
ርሃም ፡ ይመረጣል ፡ ከሱም ፡ ለዘላለሙ ፡ ሕግን ፡
የሚጠብቅ ፡ ይስሐቅ ፡ ይወለዳል ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ባራተኛይቱ ፡ ሱባዔ ፡ በመጨ ፳፮
ረሻዋ ፡ ነቢያትና ፡ ካህናት ፡ ራዕይ ፡ ያያሉ ፡
ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ ጸንታ ፡ የምትኖር ፡ ሕገ ፡
ኦሪትም ፡ ትሠራለች ፡ ደብተራ ፡ ኦሪትም ፡ ትሠ
ራላቸዋለች ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ባምስተኛይቱ ፡ ሱባዔ ፡ በመ ፳፯ ፡
ጨረሻዋ ፡ መንግሥትና ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እስ
ተዘላለሙ ፡ ሊኖር ፡ ይሠራል ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በስድስተኛይቱ ፡ ሱባዔ ፡ በሷ ፡ ፳፰ ፡
የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ደንቆሮዎች ፡ ናቸው ፡
የሁሉም ፡ ልቡናቸው ፡ ከጥበብ ፡ ይለያል ፡
በሷም ፡ ኤልያስ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ያርጋል ።
በመጨረሻዋም ፡ የመንግሥቱ ፡ ቤት ፡ በእሳት ፡ ፳፱ ፡
ይቃጠላል ፡ የተመረጡ ፡ የመንግሥትም ፡ ዘመ
ዶች ፡ ሁሉ ፡ በሷ ፡ ይበተናሉ ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሰባተኛይቱ ፡ ሱባዔ ፡ ወንጀ ፴ ፡
ለኛ ፡ ኃጢአቷ ፡ ብዙ ፡ የሆነ ፡ ሥራዋም ፡ ሁሉ ፡
ወንጀል ፡ የሚሆን ፡ ልጅ ፡ ትነሣለች ።
በመጨረሻዋ ፡ ዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ሕግን ፡ ፴፩ ፡
ከጠበቀ ፡ ከአብርሃም ፡ የተወለዱ ፡ የትምርታ

ቸው ፡ ዋጋ ፡ ሰባት ፡ እጥፍ ፡ ሆኖ ፡ የሚሰጣ
ቸው ፡ ነቢያት ፡ ፍጥረቱን ፡ ሁሉ ፡ ለማስተማር ፡
ይመረጣሉ ።
፹፪ ከሰው ፡ ከተወለደ ፡ ሁሉ ፡ የከበረ ፡ የጌታ ፡
ቃሉን ፡ ሰምቶ ፡ የማይተዋወክ ፡ ማነው ፡ አሳቡ
ንስ ፡ ያስብ ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ ማነው ።
፹፫ ሰማይን ፡ ሥራዋንም ፡ ሁሉ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡
ማየት ፡ የሚችል ፡ ማነው ።
፹፬ የሰማይን ፡ ሥራ ፡ መርምሮ ፡ ማወቅ ፡ የሚቻ
ለው ፡ ከሥጋውም ፡ ለይቶ ፡ ነፍሱን ፡ ከነፍ
ሱም ፡ ለይቶ ፡ ሥጋውን ፡ ማየት ፡ የሚቻለው ፡
ይህ ፡ ነፍሴ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡
መናገር ፡ የሚቻለው ፡ ማነው ፡ ይህም ፡ ባይ
ሆን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ መውጣት ፡ የመላእክትን ፡
ክንፍ ፡ አይቶ ፡ የሚያስባቸው ፡ ይህም ፡ ባይ
ሆን ፡ እንደነሳቸው ፡ ማድረግ ፡ የሚቻለው ፡
ማነው ።
፹፭ የምድርን ፡ አቈልቋይዋን ፡ ወርዷን ፡ ምንም ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ማወቅ ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
ማነው ።
፹፮ የነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ልክቸው ፡ ለማን ፡ ተገለጠ ፡ የሰ
ማይን ፡ ምጥቀቷን ፡ ርዝመቷን ፡ ምንም ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ የፀናችበትም ፡ በምንም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
መርምሮ ፡ ማወቅ ፡ የሚችል ፡ የከከቦችም ፡
ቍጥራቸው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፀሐይ ፡
ጨረቃም ፡ ሁሉ ፡ በየትም ፡ እንዲያርፉ ፡ ማወቅ ፡
የሚቻለው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ቢኖር ፡ በሱ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፹፮ ።

፩ አሁንም ፡ ልጆቼ ፡ እውነተኛይቱን ፡ ሕግ ፡
ውደዷት ፡ የውነት ፡ ሥራዎችን ፡ ይቀበሏቸው ፡
ዘንድ ፡ ይገባልና ፡ በሷም ፡ ጸንታችሁ ፡ ኑሩ ፡
እላችኋለሁ ።
፪ የግፍ ፡ ሥራዎች ፡ ግን ፡ ፈጥነው ፡ ይጠፋሉ ፡
ያንሳሉ ፡ በደግነት ፡ ለታወቁ ፡ ሰዎችም ፡ ከልጅ ፡
ልጅ ፡ ጀምሮ ፡ የሞትና ፡ የግፍ ፡ ሥራዎች ፡ ይገ
ለጣሉ ፡ ሰዎችም ፡ ከነሳቸው ፡ ይርቃሉ ፡ እነ
ሱንም ፡ አይከተሏቸውም ።
፫ አሁንም ፡ ለናንተ ፡ ለወዳጆቼ ፡ በግፍና ፡ በክፉ ፡
ሥራዎች ፡ ሞትን ፡ በሚያመጡ ፡ ሥራዎች ፡
ጸንታችሁ ፡ አትኑሩ ፡ እውነት ፡ ነገርን ፡ የተመ
ረጣች ፡ ድኅነታችሁንም ፡ ለናንተ ፡ ፈጽማችሁ ፡
ውደዱ ፡ እንጂ ፡ እንዳትጠፉ ፡ ወደነሱ ፡ አትቅ
ረቡ ፡ እላችኋለሁ ።
፬ በፍቅር ፡ ሥራዎችም ፡ ጸንታችሁ ፡ ኑሩ ፡ ትድ
ናላችሁ ፡ በተድላ ፡ ደስታውም ፡ ትዘጋጃላችሁ ፡
በልቡናችሁም ፡ አሳብ ፡ ሕጉን ፡ ትይዛላችሁ ።
፭ ክፉ ፡ ጥበብን ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ደጋጎች ፡ ሰዎ
ችን ፡ ክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ እንዲፈትኗቸው ፡ አው
ቃለሁና ፡ ነገሬ ፡ ከልቡናችሁ ፡ አይጥፋ ፡ ለኃ
ጢአትም ፡ ልቡና ፡ ሁሉ ፡ አይገኝላት ፡ ሕግ ፡
ቢያፈርሱ ፡ የሚመጣው ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ አያን
ስም ።
፮ እነሱ ፡ ፈጥነው ፡ ይጠፋሉና ፡ ፍቅር ፡ አንድነ
ትም ፡ የላቸውምና ፡ ሐሰት ፡ ነገርን ፡ ግፍንም ፡
ተንኰልንም ፡ አጥንተው ፡ ለሚሠሯት ፡ ሰዎች ፡
ወዮላቸው ።
ከሥር ፡ ከመሠረታቸው ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋሉና ፡ ፯
በሰይፍም ፡ ተቀራደው ፡ ያልቃሉና ፡ ወርቅን ፡
ብርንም ፡ የሚሰበስቧት ፡ ሰዎች ፡ ፍርዱ ፡ ፈጥ
ነው ፡ ይጠፋሉና ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ ቀምተው ፡
ቤታቸውን ፡ ለሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ወዮላቸው ።
በባለጠግነታችሁ ፡ ላይ ፡ ታምናችኋልና ፡ ከባ ፰
ለጠግነታችሁም ፡ ትለያላችሁና ፡ እናንተ ፡ ባለ
ጠጎች ፡ ወዮላችሁ ።
እግዚአብሔርን ፡ በባለጠግነታችሁ ፡ ወራት ፡ ፱
አላሰባችሁትምና ፡ እናንተስ ፡ ስድብን ፡ በደል
ንም ፡ ሠራችኋት ፡ ደም ፡ ለሚፈስበት ፡ ጨለ
ማም ፡ ለሚደረግባት ፡ ጽኑ ፡ ፍርድም ፡ ለሚፈ
ረድባት ፡ ዕለተ ፡ ምጽአትም ፡ የተዘጋጃችሁ ፡
ሆናችሁ ።
የፈጠራችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲያጠፋችሁ ፡ ፲
በናንተም ፡ ጥፋት ፡ ላይ ፡ ይቅርታው ፡ እንዳይ
ደረግላችሁ ፡ እኔም ፡ እንደዚህ ፡ ብዬ ፡ እነግራ
ችኋለሁ ።
እናንተንም ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በናንተ ፡ ፲፩
ጥፋት ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ የናንተም ፡ መምሮቻ
ችሁም ፡ በነዚያ ፡ ወራት ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔ
ርን ፡ ለዘነጉ ፡ ሰዎችና ፡ ለኃጥአን ፡ ስድብ ፡ ይሆ
ናሉ ።
ዓይኖቼ ፡ ውሀን ፡ የቋጠሩ ፡ ደመናዎችን ፡ ይሆኑ ፡ ፲፪
ዘንድ ፡ በናንተም ፡ ላይ ፡ አለቅስ ፡ ዘንድ ፡ ውሀ
ንም ፡ እንደ ፡ ቋጠረ ፡ ደመና ፡ እንባዬን ፡ አፈስ ፡
ዘንድ ፡ ከልቡናዬም ፡ ኀዘን ፡ አርፍ ፡ ዘንድ ፡ ላይ
ኖቼ ፡ ማን ፡ በሰጠኝ ፡ ነበር ።
ክፋትንና ፡ ስድብን ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አድርጉ ፡ ፲፫
ብሎ ፡ ማን ፡ አስተማራችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡
ኃጥአን ፡ እናንተን ፡ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ ያገኛች
ኋል ።
እንደ ፡ ወደዳችሁ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ፍርድን ፡ ታደ ፲፬
ርጉባቸው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዳግመኛ ፡
በጃችሁ ፡ ይጥሏቸዋልና ፡ ወዳጆቼ ፡ ጻድቃን ፡
ከኃጥአን ፡ የተነሣ ፡ አትፍሩ ።
እንዳትፈቱ ፡ ሁናችሁ ፡ የማይገባ ፡ ግዝትን ፡ ፲፭
ለምትገዝቱ ፡ ለናንተ ፡ ወዮላችሁ ፡ ስለ ፡ ኃጢ
አታችሁም ፡ ድኅነት ፡ ከናንተ ፡ ራቀ ።
እንደ ፡ ሥራችሁ ፡ መጠን ፡ ፍዳውን ፡ ትቀበላላ ፲፮
ችሁና ፡ ለባልንጀራችሁ ፡ ክፉ ፡ ምላሽ ፡ ለምት
መልሱ ፡ ለናንተ ፡ ወዮላችሁ ።
በሠራችሁት ፡ ሥራ ፡ ፈጥናችሁ ፡ ትጠፋላች ፲፯
ሁና ፡ ሐሰት ፡ ለምትመሰክሩ ፡ ለበደልም ፡ ለም
ትገቧት ፡ ለናንተ ፡ ወዮላችሁ ።
ደጋግ ፡ ሰዎችን ፡ አስወጥታችሁ ፡ ትሰዷቸዋላ ፲፰
ችሁና ፡ እናንተም ፡ በነሱ ፡ እጅ ፡ ትወድቃላች
ሁና ፡ ከሠራችሁትም ፡ ግፍ ፡ የተነሣ ፡ ትሰደዳ
ላችሁና ፡ የነሱም ፡ ፍዳ ፡ በናንተ ፡ ይጸናልና ፡
ለናንተ ፡ ለኃጥአን ፡ ወዮላችሁ ።
ጠላቶቻችሁ ፡ ኃጥአን ፡ ከፊታችሁ ፡ ፈጥነው ፡ ፲፱

እንዲጠፉ ፡ እንደ ፡ ወደዳችሁ ፡ ሥልጣንም ፡
በነሳቸው ፡ እንዲደረግ ፡ ወዳጆቼ ፡ ጻድቃን ፡
ይህንን ፡ ተስፋ ፡ አደረጉ ።
፳ ኃጥአን ፡ መከራ ፡ በሚቀበሉበትም ፡ ቀን ፡ የና
ንተ ፡ ልጆች ፡ እንዳሞሮች ፡ ተነሥተው ፡ ከፍ ፡
ከፍ ፡ ይላሉ ።
፳፩ በታችሁም ፡ ከጥንብ ፡ አሞራ ፡ በታ ፡ ይልቅ ፡
ይርቃል ፡ ወጥታችሁም ፡ ወደ ፡ ቀበሮ ፡ ጉድ
ጓድ ፡ ከመዐኞችም ፡ ፊት ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡
ሽኮኮ ፡ ለዘላለሙም ፡ ወደ ፡ ገደል ፡ ጥግ ፡ ትገበ
ለች ።
፳፪ በናንተም ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ሥራቸውን ፡ ይሠራሉ ፡
ይህ ፡ ኃጢአታችሁ ፡ በናንተ ፡ ምስክር ፡ ይሆን
ብችኋል ፡ እንጂ ፡ እናንተ ፡ እንደነሱ ፡ አትሆ
ኑም ፡ ለወንድሞቻችሁም ፡ ከኃጥአንም ፡ ጋራ ፡
አንድ ፡ ሆናችሁ ፡ እንደ ፡ ሄለይም ፡ ቃላቸውን ፡
አቅጥነው ፡ ያለቅሳሉ ።
፳፫ ይህ ፡ መከራው ፡ ለናንተ ፡ ድኅነት ፡ ይሆንላች
ኋልና ፡ የበራም ፡ ብርሃን ፡ ለናንተ ፡ ያበራላች
ኋልና ፡ ከሰማይም ፡ ዕረፍት ፡ የሚደረግበትን ፡
ቃል ፡ ትሰማላችሁና ፡ መከራ ፡ የምትቀበሉ ፡
ጻድቃን ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ አትፍሩ ።
፳፬ ባለጸግነታችሁ ፡ ደጋግ ፡ ሰዎችን ፡ ያስመስላች
ኋልና ፡ እናንተ ፡ ክፉዎች ፡ ኃጥአን ፡ ወዮላችሁ ፡
ልቡናችሁ ፡ ግን ፡ እናንተ ፡ በደለኞች ፡ እንደ ፡
ሆናችሁ ፡ ይዘልፋችኋል ። (ያውቅባችኋል ፡)
፳፭ ይህም ፡ ነገር ፡ በናንተ ፡ ለክፋታችሁ ፡ መታሰ
ቢያ ፡ ምስክር ፡ ይሆናል ፡ አለ ።
፳፮ ያፈራውን ፡ ስንዴ ፡ የምትበሉ ፡ ከላምም ፡ ጡት ፡
የተገኘ ፡ ወተቱንም ፡ የምትጠጡ ፡ የተዋረዱ
ትንም ፡ ሰዎች ፡ በኃይላችሁ ፡ የምትረገግጧ
ቸው ፡ ለናንተ ፡ ወዮላችሁ ።
፳፯ የኃጢአታችሁን ፡ ፍዳ ፡ ፈጥናችሁ ፡ ትቀበላላ
ችሁና ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ውኃን ፡ ለምትጠጡ ፡ ሰዎች ፡
ወዮላችሁ ፡ የሕይወት ፡ መገኛ ፡ ሕጉን ፡ ትታ
ችኋልና ፡ ፈጽማችሁ ፡ ትጠፋላችሁ ።
፳፰ በደልን ፡ ተንኰልን ፡ ስድብን ፡ ለምትሠሩ ፡
ለናንተ ፡ ወዮላችሁ ፡ ይህም ፡ በናንተ ፡ የክፋታ
ችሁ ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆናል ።
፳፱ የምትጠፉበት ፡ ቀን ፡ ትመጣለችና ፡ ደጉን ፡
ሰው ፡ በኃይላችሁ ፡ ራስ ፡ ራሱን ፡ ለምትቀጠ
ቅጡት ፡ ለናንተ ፡ ለኃይለኞች ፡ ወዮላችሁ ።
፴ በነዚያ ፡ ወራቶች ፡ ለደጋግ ፡ ሰዎች ፡ በናንተ ፡
በተፈረደባችሁ ፡ ቀን ፡ ደጋጎችና ፡ ብዙዎች ፡
ወራቶች ፡ ይመጣሉ ፡ አለ ።

## ምዕራፍ ፡ ፻፯ ።

፩ ኃጥአን ፡ ለስድብ ፡ እንዲሆኑ ፡ ግፍም ፡ በሠ
ሩበት ፡ ቀን ፡ እንዲጠፉ ፡ ወዳጆቼ ፡ ጻድቃን ፡
እመኑ ።
፪ እግዚአብሔር ፡ የናንተን ፡ ጥፋት ፡ ያስባልና ፡
በሰማይም ፡ ያሉ ፡ መላእክት ፡ በናንተ ፡ ጥፋት ፡
ላይ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋልና ፡ ይህ ፡ በደግነታችሁ ፡
የታወቀ ፡ ይሆንላችኋል ።

ኃጥአን ፡ ምን ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አላችሁ ፡ የጻ ፫
ድቃን ፡ ጸሎታቸው ፡ ዋጋ ፡ ሊያሰጥ ፡ በሰማ
ችሁ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ በሚፈረድብት ፡ በዚያች ፡
ቀንስ ፡ ወዴት ፡ ትሸሻላችሁ ።
በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ የቅዱሳን ፡ ልመናቸው ፡ ፬
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትደርሳለች ፡ በናንተ ፡
ግን ፡ የሚፈረድባችሁ ፡ ወራት ፡ ይደርስባችኋል ።
በግፋችሁ ፡ የሠራችሁትም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በከ ፭
በረና ፡ በገነነ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይነበ
በል ፡ ፊታችሁም ፡ በመከራው ፡ ያፍራል ፡ በግፍ ፡
የጸና ፡ ሥራችሁም ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋል ።
በየብስና ፡ በባሕር ፡ መካከል ፡ ያላችሁ ፡ የክፉ ፮
ዎች ፡ ሰዎችም ፡ ስም ፡ አጠራራቸው ፡ በናንተ ፡
የተጠራብችሁ ፡ ኃጥአን ፡ ለናንተ ፡ ወዮላችሁ ።
በውነት ፡ ያይደለ ፡ ወርቅና ፡ ብርን ፡ የምትሰበ ፯
ስቡ ፡ ባለጸግነትን ፡ አገኘን ፡ ገንዘቡም ፡ በዛልን ፡
የወደድነውንም ፡ ሁሉ ፡ ገዛን ፡ የምትሉ ፡ ሰዎች ፡
ለናንተ ፡ ወዮላችሁ ።
ብሩን ፡ ሰብስበናልና ፡ በሳጥኖቻችንም ፡ መልተ ፰
ናልና ፡ በቤታችንም ፡ ያሉ ፡ አራሾች ፡ እንደ ፡
ውሀ ፡ በዝተውልናልና ፡ አሁንም ፡ ያሰብነውን ፡
ሁሉ ፡ እናድርግ ፡ ለምትሉ ፡ ለናንተ ፡ ወዮላ
ችሁ ።
ከናንተ ፡ ፈጥኖ ፡ ይጠፋል ፡ እንጂ ፡ ባለጠግነት ፡ ፱
አይኖርላችሁምና ፡ አሰታችሁ ፡ እንደ ፡ ውሀ ፡
ይበዛል ።
ይህን ፡ ሁሉ ፡ በግፍ ፡ ሰብስባችሁታልና ፡ እና ፲
ንተ ፡ ግን ፡ ለጽኑ ፡ ጥፋት ፡ ትሰጣላችሁ ።
በዚህም ፡ ዓለም ፡ ብዙ ፡ ነገርን ፡ ታያላችሁና ፡ ፲፩
ዛሬም ፡ ሰነፎችና ፡ ብልሆች ፡ ለምትሆኑ ፡ ለና
ንተ ፡ እነግራችኋለሁ ።
እናንተ ፡ ወንዶቹ ፡ ከሴቶች ፡ ይልቅ ፡ እናንተ ፡ ፲፪
ጌጡን ፡ ታጌጣላችሁና ፡ ይልቁን ፡ ከድንግሊቱ ፡
ይልቅ ፡ ብዙ ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ ጌጥን ፡ ታደርጋ
ላችሁና ።
በመንግሥት ፡ በገናንነት ፡ በሥልጣን ፡ ያለን ፡ ፲፫
ይመስላችኋል ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ በነጭ ፡
ሐርም ፡ የከበርን ፡ ይመስላችኋል ።
መብሎችም ፡ እንደ ፡ ውሀ ፡ በዝተው ፡ በፊታ ፲፬
ቸው ፡ ይቀርባሉ ፡ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ጥበብና ፡
ትምህርት ፡ የላቸውም ።
በዚህም ፡ በመብሉና ፡ በመጠጡ ፡ ገንዘቦቻቸው ፡ ፲፭
ከክብራቸውና ፡ ከጌትነታቸውም ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡
አንድ ፡ ሆነው ፡ ይጠፋሉ ።
በስድብ ፡ በችጋር ፡ በጽኑ ፡ በቀልም ፡ ሁነው ፡ ፲፮
ሊኖሩ ፡ ነፍሳቸው ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ጉድጓድ ፡
ትወድቃለች ፡ (ገሃነም ፡ ነው ) ።
ኃጥአን ፡ ተራራው ፡ በባሕርዩ ፡ ተገኘ ፡ እንዳል ፲፯
ነበረ ፡ እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ እንዳይሆን ፡ ኮረብ
ታይቱም ፡ ለሴት ፡ ሴት ፡ በሪያ ፡ እንዳይደሉ ፡
ለናንተ ፡ ነገርኋችሁ ።
እዳምና ፡ ሐዋን ፡ ከራሳቸው ፡ አንቅተው ፡ ፲፰
ሠሯት ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ እንደ ፡ ተናገርሁት ፡
ኃጢአትም ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ የባሕርይ ፡ ሁና ፡

አልተላከችም ፡ እኗንም ፡ የሠሯት ፡ ሰዎች ፡
ለጽኑ ፡ መርገም ፡ ይሆናሉ ፡ (ሐሩሩ ፡ ይበላሉ) ።
፲፱ በድዋ ፡ በሠራችው ፡ ሥራ ፡ ልጅ ፡ ሳትወልድ ፡
ትሞታለች ፡ እንጂ ፡ ለሴትም ፡ መምከን ፡ አል
ተሰጣትም ፡ ነበር ።
፳ ኃጥአን ፡ ክፉ ፡ ሠራችሁ ፡ ሁሉ ፡ በሰማይ ፡ እንደ ፡
ተገለጠ ፡ ፈጽሞም ፡ የተሠወረ ፡ የግፍ ፡ ሥራም ፡
እንደሌላችሁ ፡ በገናናና ፡ በከበረ ፡ ስሙ ፡ ምዬ ፡
ነገርኋችሁ ።
፳፩ በሰውነታችሁ ፡ በልቡናችሁም ፡ የሚሠወርላ
ችሁ ፡ አታስመስሉት ፡ በሰማይ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ ይጻፍ ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ በየቀኑ ፡
የሠራችሁትን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽማችሁ ፡ አታውቁ
ምና ፡ በልቡናችሁ ፡ ይሠወርልናል ፡ አትበሉ ።
፳፪ ፍርድ ፡ እስከሚፈረድበት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽ
አት ፡ ድረስ ፡ የበደላችሁት ፡ በደል ፡ በየቀኑ ፡
ሁሉ ፡ እንዲጻፍባችሁ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ታው
ቃላችሁ ።
፳፫ በስንፍናችሁ ፡ ትጠፋላችሁና ፡ መምራንንም ፡
አትሰሟቸውምና ፡ በጎ ፡ ነገርም ፡ አታገኞችሁ
ምና ፡ እናንተ ፡ ሰነፎች ፡ ወዮላችሁ ።
፳፬ አሁንም ፡ ጥፋት ፡ ለታዘዘበት ፡ ቀን ፡ እናንተ ፡
የተዘጋጃችሁ ፡ እንደሆናችሁ ፡ እወቁ ፡ ተፈር
ዶባችሁ ፡ ወደገሃነም ፡ ትሄዳላችሁ ፡ እንጂ ፡ ኃጥ
አን ፡ እንድናለን ፡ ብላችሁ ፡ ተስፋ ፡ አታድርጉ ።
፳፭ ጽኑ ፡ ፍርድ ፡ ለሚፈረድበት ፡ ቀን ፡ መከራም ፡
በታዘዘበት ፡ በሰውነታችሁም ፡ ታላቅ ፡ ጉስቊ
ልና ፡ በታዘዘበት ፡ ቀን ፡ ለጥፋት ፡ ተዘጋጅታ
ችኋልና ፡ ምግባርን ፡ ስላላወቃችሁ ፡ በነፍስ ፡
ትሞታላች ።
፳፮ ክፉ ፡ ሥራን ፡ የምትሠሩ ፡ ብርንዶንም ፡ የም
ትበሉት ፡ እናንት ፡ ልበ ፡ ድንጋዎች ፡ ወዮላ
ችሁ ፡ ገናና ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
አብዝቶ ፡ የፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ያመረ ፡
ነው ፡ እያላችሁ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ትበላላ
ችሁ ፡ ትጠጣላችሁ ፡ ትጠግባላችሁ ፡ እናንተ ፡
ከወዴት ፡ አግኝታችሁት ፡ ነው ፡ አንድነትም ፡
የላችሁም ።
፳፯ የበደልን ፡ ሥራ ፡ ለምትወዱት ፡ ለናንተ ፡ ወዮ
ላችሁ ፡ በጎይቱንስ ፡ ለምን ፡ ትመኟታላችሁ ።
፳፰ በጻድቃንም ፡ እጆች ፡ አልፋችሁ ፡ ትያዙ ፡
ዘንድ ፡ አደላችሁ ፡ እወቁ ፡ አንገቶቻችሁንም ፡
ቆርጠው ፡ ይገሏችኋል ፡ ከዚያም ፡ አስቀድ
መው ፡ አይራሩላችሁም ።
፳፱ ለናንተ ፡ መቃብር ፡ አይቆፍሩላችሁምና ፡ በጻ
ድቃን ፡ መከራ ፡ ደስ ፡ ለሚላችሁ ፡ ለናንተ ፡
ወዮላችሁ ።
፴ የድኅነት ፡ አለኝታ ፡ አይደረግላችሁምና ፡ የመ
ምህራንን ፡ ነገር ፡ ለምትንቁ ፡ ለናንት ፡ ወዮላ
ችሁ ።
፴፩ ሐሰት ፡ ነገራቸውን ፡ ይሰሟት ፡ ዘንድ ፡ ስንፍና
ቸውንም ፡ እንዳይዘነጓት ፡ እነሱ ፡ አሰታቸውን ፡
ይጽፋሉና ፡ ሕጉን ፡ የዘነጉ ፡ ሰዎች ፡ ነገርንና ፡
የአሰትን ፡ ነገር ፡ ለምትጽፉ ፡ ለናንት ፡ ወዮላ
ችሁ ።
አይዘገዩም ፡ ፈጥነው ፡ ይሞታሉ ፡ እንጂ ፡ ፍቅር ፡ ፴፪
አንድነት ፡ አይደረግላቸውም ።
ክፉ ፡ እርጂና ፡ ለምታረጁ ፡ ሰዎች ፡ ወዮላችሁ ፡ ፴፫
የሐሰቱንም ፡ ነገር ፡ ፈጽመው ፡ ያከብራሉ ፡
በዚህም ፡ ሥራችሁ ፡ ጠፋችሁ ፡ ድኅነት ፡ በጎም ፡
ነገር ፡ የላችሁም ።
የቀኑ ፡ ነገሮችንም ፡ ለምትለዋውጡቸው ፡ ለና ፴፬
ንተ ፡ ወዮላችሁ ፡ ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖረው
ንም ፡ ሥርዓት ፡ ይለውጣሉ ፡ ራሳቸውንም ፡ ኃጢ
አተኞች ፡ ያስደረጉ ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
ይጠፉ ፡ ዘንድ ፡ አላቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፺፰ ።

በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ ጻድቃን ፡ ለበጐነታ ፩
ችሁ ፡ መታሰቢያ ፡ ሊሆን ፡ የለመናችሁትን ፡
ዋጋ ፡ ትቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ ተዘጋጁ ።
በልዑል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለክፋታቸው ፡ ፪
መታሰቢያ ፡ አድርገው ፡ ኃጥአን ፡ ኃጢአታቸ
ውን ፡ እንዲያኖሩት ፡ እናንተም ፡ በመላእክት ፡
ፊት ፡ ለበጐነታቸው ፡ ምስክር ፡ አድርጋችሁ ፡
ክብሮቻችሁን ፡ አኖራችኋቸው ።
በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ አሕዛብ ፡ ይተዋወካሉ ፡ ፫
ጥፋትም ፡ በታዘዘበት ፡ ቀን ፡ የአሕዛብ ፡ ዘመ
ዶች ፡ ይነሣሉ ።
በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ የተቸገሩ ፡ ሰዎች ፡ ተሰ ፬
ደው ፡ ይወጣሉ ፡ ልጆቻቸውንም ፡ አሕዛብ ፡
ይነጥቋቸዋል ፡ ልጆቻቸውንም ፡ እየወጉ ፡ ይጥ
ሏቸዋል ።
ከነሱም ፡ የተነሣ ፡ ልጆቻቸው ፡ ውራጅ ፡ ይሆ ፭
ናሉ ፡ የናታቸውንም ፡ ጡት ፡ ሲጠቡ ፡ ልጆቻ
ቸውን ፡ እየወጉ ፡ ይጥሏቸዋል ።
ወደነሱም ፡ በፍቅር ፡ አይመለሱም ፡ ለሚወዷ ፮
ቸው ፡ ልጆቻቸው ፡ አይራሩላቸውም ።
የማይገታ ፡ ደም ፡ ለሚፈስበት ፡ ቀን ፡ ኃጢአት ፡ ፯
ተዘጋጅታለችና ፡ ለኃጥአን ፡ እኔ ፡ ዳግመኛ ፡ እነ
ግራችኋለሁ ።
ለድንጋይም ፡ ይሰግዳሉ ፡ የብሩና ፡ የወርቁን ፡ ፰
የሸክላውንና ፡ የንጨቱንም ፡ ምስል ፡ የሚሠሩ ፡
ናቸው ።
ለረከሱ ፡ ለረቂቃን ፡ ለክፉዎችም ፡ ለግዙፋን ፡ ፱
አጋንንት ፡ ለጣዖቱም ፡ ሁሉ ፡ ለመስጊድም ፡
ሁሉ ፡ ይሰግዳሉ ።
ከነሳቸውም ፡ ረድኤት ፡ ሁሉ ፡ አይገኝም ፡ ስለ ፡ ፲
ልቡናቸውም ፡ ድንቊርና ፡ ከሥላሴ ፡ ልቡና ፡
ይዘነጋሉ ፡ በልቡናቸው ፡ ፍርሃት ፡ የልቡና
ቸው ፡ ዓይኖች ፡ በድንቊርና ፡ ይያዛሉ ።
ሥራቸውን ፡ ሁሉ ፡ ባሰት ፡ ሠርተዋልና ፡ ለድን ፲፩
ጋዩም ፡ ሰግደዋልና ፡ ፈጥነውም ፡ ይጠፋሉና ፡
ሕልማቸውን ፡ አየን ፡ በማለታቸው ፡ ሕጉን ፡
ይዘነጋሉ ፡ መከራውንም ፡ ይፈራሉ ።
በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ የጥበብን ፡ ነገር ፡ የሚቀ ፲፪
በሉ ፡ የሚወዷትም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የተደነቁ ፡
ሰዎች ፡ ናቸው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



፲፫፤ የልዑል ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ሥራዎች ፡ ይሠ
ሯቸዋል ፡ በውነተኛም ፡ ሥራዎች ፡ ጸንተው ፡
ይኖራሉ ፡ እነሱ ፡ ይድናሉና ፡ ሕጉን ፡ እንደ ፡
ዘነጉ ፡ ሰዎች ፡ ሕጉን ፡ አይዘነጉም ።
፲፬፤ በሲኦል ፡ ትጠፋላችሁና ፡ ለወንድማችሁ ፡ ክፉ
ውን ፡ ነገር ፡ አብዝታችሁ ፡ የምትሠሩ ፡ ለእና
ንተ ፡ ወዮላችሁ ።
፲፭፤ በሱ ፡ ትጠፋላችሁና ፡ ተንኮልንና ፡ ኃጢአትን ፡
መሠረት ፡ ንፍገትን ፡ የምትሠሩ ፡ በዚህም ፡
ዓለም ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምትአሳዝኑ ፡ ሰዎች ፡
ወዮላችሁ ።
፲፮፤ በድኃ ፡ ገንዘብ ፡ ቤታችሁን ፡ የምትሠሩ ፡ እናንተ ፡
ወዮላችሁ ፡ ሥራቸውም ፡ ሁሉ ፡ ውብ ፡ ነው ፡
የኃጢአትም ፡ የሚሠራበት ፡ ደንጋይ ፡ ነው ፡
አንድነትም ፡ እንደሌላችሁ ፡ እኔ ፡ እነግራችኋ
ለሁ ።
፲፯፤ ለዘለዓለሙ ፡ የሚኖር ፡ የአባቶቻቸው ፡ ርስትና ፡
ድንበርን ፡ ለሚያፈርሱ ፡ ሰዎች ፡ ወዮላቸው ፡
ለነሱ ፡ ዕረፍት ፡ ነፍስ ፡ አይደረግምና ፡ ልቡና
ቸውንም ፡ ወደ ፡ ጣዖቱ ፡ ይወስዱታል ።
፲፰፤ በደልን ፡ የምትሠሪት ፡ ግፍንም ፡ ለምትረ
ዱት ፡ ለናንተ ፡ ወዮላችሁ ፡ ጌትነታችሁን ፡ ያጠ
ፉዋልና ፡ በልቡናችሁም ፡ ክፋትን ፡ ያሳድርብ
ችኋልና ፡ ጽኑ ፡ ፍርድ እስከሚፈረድባት ፡ እስከ ፡
ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ ባልንጀሮቻችሁን ፡
ለምትገሉ ፡ ሰዎች ፡ ወዮላችሁ ።
፲፱፤ ሁላችሁንም ፡ በሰይፍ ፡ ያጠፋችሁ ፡ ዘንድ ፡
ረቂቅ ፡ ቍጣን ፡ አመጣባችሁ ፡ ደናግልና ፡ ሕጋ
ውያንም ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአታችሁን ፡ ያስባሉ ።
፳፤ በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ አባቶች ፡ ከልጆቻቸው ፡
ጋር ፡ በንድ ፡ በታ ፡ ተቀራደው ፡ ያልቃሉ ።
፳፩፤ ሰው ፡ ልጁን ፡ ከመግደል ፡ የልጅ ፡ ልጁንም ፡
ከመግደል ፡ በመራራት ፡ እጁን ፡ አይከለክል
ምና ፡ ከነሱ ፡ ደም ፡ እንደ ፡ ፈሳሽ ፡ ውኃ ፡ እስኪ
ፈስ ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፡ ወንድሞች ፡ ከወንድሞቻ
ቸው ፡ ጋራ ፡ በሞት ፡ ይጠፋሉ ።
፳፪፤ ኃጢአተኛው ፡ የከበረ ፡ ታላቅ ፡ ወንድሙን ፡
ከመግደል ፡ እጁን ፡ አይከለክልም ፡ ጎሕም ፡
ከቀደደ ፡ ጀምሮ ፡ ፀሐይ ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ
ይዋጋሉ ።
፳፫፤ ፈረስ ፡ የኃጥአን ፡ ደም ፡ እስከ ፡ እቢያጉሱ ፡
ድረስ ፡ እያማታው ፡ ይሄዳል ፡ ሠረገላ ፡ ግን ፡
እስከ ፡ ራሷ ፡ ድረስ ፡ ትሰጥማለች ።
፳፬፤ በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ አለቆች ፡ ወደሚሠሩት ፡
በታ ፡ ይወርዳሉ ።
፳፭፤ ኃጢአትን ፡ የሚረዷት ፡ ሰዎችንም ፡ ሁሉ ፡
ወደ ፡ አንዱ ፡ በታ ፡ ይመልሷቸዋል ።(ገሃነም ፡)
፳፮፤ በኃጥአን ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ይፈረድ ፡ ዘንድ ፡ በዚ
ያች ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ በመዓት ፡ ይነሣል ።
፳፯፤ ከከበሩ ፡ መላእክትም ፡ በደናግልና ፡ በሕጋው
ያን ፡ ላይ ፡ ጠባቂዎችን ፡ ይሰጣል ፡ እነሱም ፡
ክፋት ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአትም ፡ ሁሉ ፡ ጨርሶ ፡ እስ
ኪጠፋ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ዓይን ፡ ብሌኔ ፡ ይጠብቋ
ቸዋል ።

ቢተኙም ፡ ብዙ ፡ እንቅልፍን ፡ ይተኛሉ ፡ የሚ ፳፰፤
ፈሩትም ፡ ነገር ፡ የላቸውም ።
በዚያም ፡ ወራት ፡ ብልሆች ፡ ሰዎች ፡ እውነተኛ ፡ ፳፱፤
ነገርን ፡ ያያሉ ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡
በዚች ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
ልብ ፡ ያደርጋሉ ፡ ባለጸግነታቸውም ፡ ኃጢአት ፡
ሠርተው ፡ በሚጠፉበት ፡ ጊዜ ፡ ማዳናቸውን ፡
እንዳይችል ፡ ያውቃል ።
ጽኑ ፡ መከራ ፡ በምታደርጉበት ፡ ቀን ፡ ጻድቃ ፴፤
ንን ፡ በስጨንቃችኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ኃጥአን ፡ ወዮ
ላችሁ ፡ በእሳትም ፡ ታቃጥሏቸዋላችሁ ፡ እናን
ተም ፡ እንደ ፡ ሥራችሁ ፡ ፍዳውን ፡ ትቀበላላ
ችሁ ።
ክፉውን ፡ ነገር ፡ ልብ ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ የም ፴፩፤
ትተጉ ፡ ልባችሁ ፡ ግልብጥብጥ ፡ ላለ ፡ ለናንተ ፡
ወዮላችሁ ፡ ፍራት ፡ ያገኛችሁ ፡ ዘንድ ፡ አላችሁ ፡
የሚራዳችሁም ፡ ወዳጅ ፡ የለም ።
በፋችሁ ፡ በተናገራችሁ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ሕግንም ፡ ፴፪፤
በዘነጋችሁበት ፡ በጃችሁም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በገሃ
ነም ፡ ትቃጠላላችሁና ፡ ኃጥአን ፡ ለናንተ ፡ ወዮ
ላችሁ ።
ጨረቃንና ፡ ፀሐይን ፡ ከከቦችንም ፡ ከማምለካ ፴፫፤
ቸው ፡ የተነሣ ፡ ስለ ፡ ኃጢአታችሁ ፡ መላእክት ፡
በሰማይ ፡ ሥራችሁን ፡ እንዲመረምሩ ፡ አሁ
ንም ፡ እወቁ ።
በወዳጆቼ ፡ በጻድቃን ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ፴፬፤
ጽኑ ፡ መቻያን ፡ ታደርጉባቸዋላችሁና ፡ ጉሙ
ንና ፡ ደመናውን ፡ ሁሉ ፡ ዝናቡንና ፡ ጠሉንም ፡
በናንተ ፡ ያዳኝባችኋል ፡ ወደናንተ ፡ እንዳይወ
ርዱ ፡ ከናንተ ፡ የተነሣ ፡ ሁሉ ፡ ይከለከላሉና ፡
በኃጢአታችሁም ፡ መውረድን ፡ አያስቡምና ።
አሁንም ፡ ዝናብ ፡ ወደናንተ ፡ መውረድን ፡ እን ፴፭፤
ዳይከለክል ፡ ጠልም ፡ ከናንተ ፡ ብርንና ፡ ወር
ቅን ፡ ተቀብሎ ፡ ይወርድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እጅ ፡
መንሻ ፡ ስጡ ።
ውርጭ ፡ ቀግም ፡ በናንተ ፡ ቢወድቅባችሁ ፡ የነ ፴፮፤
ሱም ፡ ቅዝቃዜ ፡ ቢደረግባችሁ ፡ ዋጉን ፡ የሚ
ያመጡ ፡ ነፋሶች ፡ ሁሉ ፡ ቢታዘዙባችሁ ፡ የነ
ዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጭንቅነትም ፡ ያገኛችሁ ፡ በነዚያ ፡
ወራት ፡ በነሱ ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ አይቻላችሁም ።

## ምዕራፍ ፡ ፻፱ ።

በደብር ፡ ቅዱስ ፡ የነበራችሁ ፡ እናንተ ፡ ሁሉ ፡ ፩፤
ሰማያዊ ፡ ሕግን ፡ ተረዷት ፡ የእግዚአብሔር
ንም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ መርምሩ ፡ በፊቱ ፡ ክፉ ፡
ነገርን ፡ እንዳትሠሩ ፡ ከሱ ፡ የተነሣ ፡ ፍሩ ።
የሰማይ ፡ ደጃፍን ፡ ቢዘጋ ፡ ዝናቡን ፡ ጠሉንም ፡ ፪፤
ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ እንዳይወርድ ፡ በናንተ ፡ ምክ
ንያት ፡ ቢከለክለው ፡ ምን ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡
አላችሁ ።
መዓቱን ፡ በናንተ ፡ በሥራችሁም ፡ ሁሉ ፡ ቢያ ፫፤
መጣባችሁ ፡ እናንተ ፡ እሱን ፡ የምትለምኑት ፡
አይደለምን ፡ አለ ።
በቸርነቱ ፡ ላይ ፡ ታላላቅ ፡ የጸኑ ፡ ነገሮችንም ፡ ፬፤

ትናገራላችሁና ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ የላችሁም ።
፭ ከማዕበል ፡ ከሞገዱ ፡ የተነሣ ፡ እንዲተዋወኩ ፡ መርከበኞቻቸውም ፡ ከነፋሶች ፡ የተነሣ ፡ እንዲነ
ዋወጡ ፡ እንዲጨነቁ ፡ በመርከብ ፡ ተጭነው ፡ የሚሄዱ ፡ ነገሥታትን ፡ አታዋቸውምን ፡ አለ ። (ነጋድያን ።)
፮ ያማረ ፡ ገንዘባቸው ፡ ሁሉ ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ አብሯ ቸው ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ይወጣልና ፡ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ይፈራሉ ።
፯ ባሕር ፡ የምትውጣቸው ፡ በሷም ፡ የሚጠፉ ፡ መስሏቸዋልና ፡ በልቡናቸው ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ አያ
ስቡም ፡ ባሕር ፡ ሁሉ ፡ ውሀዎቿም ፡ ሁሉ ፡ መነዋ ወጧም ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ ነውና ።
፰ እሱ ፡ ሥራዋን ፡ ሁሉ ፡ ውሀዎቿንም ፡ ሁለመ ናዋን ፡ ሁሉ ፡ በሸዋ ፡ ወስኗልና ።
፱ ቍጣውን ፡ ፈርታ ፡ ትደርቃለች ፡ ዓሣዎቿም ፡ ሁሉ ፡ ይሞታሉ ፡ በሷም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ይሞታሉ ።
፲ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያላችሁ ፡ እናንተ ፡ ኃጥአን ፡ ግን ፡ አትፈሩም ፡ ምድርና ፡ ሰማይን ፡ በነሱ ፡ ያለውንም ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረ ፡ እሱ ፡ አይደለምን ፡ ለምን ፡ አትፈሩ ።
፲፩ በባሕርና ፡ በየብስ ፡ ለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ጥበብንና ፡ ትምህርትን ፡ የሰጠ ፡ ማነው ፡ በመ ርከብ ፡ ተጭነው ፡ የሚሄዱ ፡ እነዚያ ፡ ነጋድያን ፡ ባሕርን ፡ የሚፈሩ ፡ አይደለምን ፡ ኃጥአን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አይፈሩትም ።
፲፪ በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ ጭንቅ ፡ መከራ ፡ በናንተ ፡ ቢያመጣባችሁ ወዴት ፡ ትሸሻላችሁ ፡ ከየትስ ፡ ትድናላችሁ ።
፲፫ የተናገረውንም ፡ ነገር ፡ በናንተ ፡ ቢያመጣብ ችሁ ፡ የምትፈሩ ፡ የምትደነግጡ ፡ አይደለምን ፡ ብርሃኖችስ ፡ ሁሉ ፡ በጽኑ ፡ ፍራት ፡ ተይዘው ፡ የሚፈሩ ፡ የሚደነግጡ ፡ አይደለምን ።
፲፬ ምድርስ ፡ ሁሉ ፡ በጽኑ ፡ ፍራት ፡ ተይዛ ፡ የምት ንቀጠቀጥ ፡ ለኅልፈትስ ፡ የምትቸኩል ፡ አይደ ለምን ።
፲፭ መላእክትም ፡ ሁሉ ፡ የተያዙትን ፡ ይጨርሳሉ ፡ ከክብር ፡ ባለቤት ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ሊሠወሩ ፡ ይወዳሉ ።
፲፮ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ ሰዎችም ፡ ይርዳሉ ፡ ይተ ዋወካሉ ፡ እናንተ ፡ ኃጥአን ፡ ግን ፡ ለዘላለሙ ፡ የተረገማችሁ ፡ ናችሁ ፡ ፍቅር ፡ አንድነትም ፡ የላችሁም ።
፲፯ እናንተ ፡ የጻድቃን ፡ ሰውነቶች ፡ አትፍሩ ፡ በው ነት ፡ ነገርም ፡ የሞታችሁ ፡ ሰዎች ፡ ዋጋች ሁን ፡ እንድታገኙ ፡ ተስፋ ፡ አድርጉ ።
፲፰ ሰውነታችሁ ፡ በጽኑ ፡ መከራ ፡ በልቅሶ ፡ በት ልቅ ፡ መከራ ፡ ተይዛ ፡ በኀዘን ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ወርዳለችና ፡ አትዘኑ ።
፲፱ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ውሾ ፡ ውሾ ፡ በተባላችሁበት ፡ ቀን ፡ ጽኑ ፡ መከራና ፡ ስድብንም ፡ በተቀበላችሁ በት ፡ ቀን ፡ ሞታችሁ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ በጎነታ
ችሁ ፡ መጠን ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ባላችሁ ፡ ሰውነታችሁ ፡ ተድላ ፡ ደስታን ፡ አላገኘምና ፡ አትዘኑ ።
በሞታችሁም ፡ ጊዜ ፡ ኃጥአን ፡ ጻድቃን ፡ እኛ ፡ እንደሞትን ፡ ሞቱ ፡ በሥራቸውስ ፡ ጥቅማቸው ፡ ምንድነው ፡ ይላሉ ። ፳
በመከራና ፡ በኀዘን ፡ ሳሉ ፡ እነሆ ፡ እንደኛ ፡ ሞቱ ፡ ከኛ ፡ ብልጫቸው ፡ ምንድነው ፡ ከዛሬ ፡ ፳፩
ጀምሮ ፡ በሞት ፡ ተካከልን ፡ ምንን ፡ ያገኛሉ ፡ እነሱ ፡ እንደኛ ፡ እነሆ ፡ ሙተዋልና ፡ ከዛሬም ፡ ጀምሮ ፡ ለዘላለሙም ፡ ብርሃንን ፡ አያውምና ፡ ለዘላለሙ ፡ ምን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ያያሉ ።
እናንተ ፡ ኃጥአን ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ ኃጢአትና ፡ ቅሚያ ፡ ገንዘብ ፡ ማጠራቀምና ፡ ሰውን ፡ መግ ፈፍ ፡ በማረ ፡ ዘመንም ፡ ተድላ ፡ ደስታውን ፡ ማየት ፡ በቃችሁ ፡ እላችኋለሁ ። ፳፪
ሞተው ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ ግፉ ፡ ሁሉ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ አልተገኘምና ፡ መጨረሻቸው ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ እንደሆነ ፡ ጻድቃንን ፡ አያችኋቸ ውን ። ፳፫
ተፈጥረውም ፡ እንዳልተፈጠሩ ፡ የሆኑ ፡ ሰውነ ቶታቸውም ፡ በመከራ ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡ መቃ ብር ፡ ወረዱ ። ፳፬

## ምዕራፍ ፡ ፵ ።

በክብሩና ፡ በገናና ፡ ጌትነቱ ፡ በገናንነቱና ፡ ፩
በከበረ ፡ መንግሥቱም ፡ ጻድቃን ፡ ለናንተ ፡ ዛሬ ፡ እነግራችኋለሁ ።
ይህንንም ፡ ምሥጢር ፡ እኔ ፡ አውቄአለሁና ፡ ፪
በሰማይ ፡ ሰሌዳነትም ፡ ያለውን ፡ አንብቤአለ ሁና ፡ ቅዱሳን ፡ የጻፉትንም ፡ አይቻለሁና ፡ እነግራችኋለሁ ።
በጎው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተድላ ፡ ደስታውም ፡ ክብ ፫
ሩም ፡ ተዘጋጅቶላቸዋልና ፡ የነሱ ፡ ነገር ፡ በው ስጣቸው ፡ ፈጽሞ ፡ ተጽፎላቸው ፡ አገኘሁ ።
በቀናና ፡ በውነት ፡ ነገር ፡ በብዙም ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ፬
ለሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ሰውነት ፡ ተጻፈላቸው ፡ የድካ ማችሁም ፡ ዋጋ ፡ ይሰጣችኋል ፡ የናንተም ፡ እድ ላችሁም ፡ ከልሞቱ ፡ ሰዎች ፡ እድል ፡ ይበልጣል ።
በሃይማኖት ፡ የሞታችሁ ፡ የናንተ ፡ ሰውነት ፡ ፭
አርፋ ፡ ትኖራለች ፡ ሰውነቶቻቸውም ፡ ፈጽ መው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።
መታሰቢያቸውም ፡ በገናና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፮
ፊት ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ አሁንም ፡ መከራቸውን ፡ አትፍሩት ።
የሞታችሁ ፡ ኃጥአን ፡ በኃጢአታችሁ ፡ በሞታ ፯
ችሁ ፡ ጊዜ ፡ ወዮላችሁ ።
እንደናንተ ፡ ያሉ ፡ ኃጥአንም ፡ ስለናንተ ፡ ኃጥ ፰
አን ፡ እናንተ ፡ ንዑዳን ፡ ክቡራን ፡ ናችሁ ፡ ባለ ዘመናቸውም ፡ ሁሉ ፡ ተድላ ፡ ደስታውን ፡ አዩ ።
ዛሬም ፡ በባለጠግነትና ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ሳሉ ፡ ፱
ሞቱ ፡ ሰልፉንና ፡ መከራውንም ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳሉ ፡ አላዩም ፡ በጌትነትም ፡ ሳሉ ፡ ሞቱ ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋም ፡ ሳሉም ፡ መቻያም ፡ አል

ተደረገባቸውም ፡፡
፲፡ ነፍሶቻቸውን ፡ መላእክት ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ እንዲ
ያወርዷቸው ፡ ጽኑ ፡ መከራቸውስ ፡ ክፉ ፡ ነገሮ
ችን ፡ እንዲሆኑባቸው ፡ አታውቋቸውምን ፡፡
፲፩፡ ሰውነታችሁ ፡ በጽኑ ፡ መከራና ፡ በጨለማ ፡ በሚ
ነድ ፡ በሚያላልብ ፡ መከራም ፡ ወደ ፡ ጽኑ ፡
መቻያ ፡ ትገባለች ፡ ጽኑ ፡ መቻያም ፡ ለልጅ ፡
ልጅ ፡ ዘመን ፡ ትደረጋለች ፡፡
፲፪፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ የላችሁምና ፡ ወዮላችሁ ፡
በሕይወተ ፡ ነፍስ ፡ ያሉ ፡ ደናግልና ፡ ለሕጋው
ያን ፡ በደከምንበት ፡ ወራት ፡ ለናንተ ፡ ድከምን ፡
ደከምን ፡ አትበሏቸው ፡፡
፲፫፡ መከራውን ፡ ሁሉ ፡ አየን ፡ ብዙ ፡ መከራዎች
ንም ፡ ተቀበልን ፡ ጨርሰን ፡ ጠፋን ፡ ከዚያ ፡ አስ
ቀድሞም ፡ አነስን ፡ ሰውነታችንም ፡ አነሰች ፡
በዚሁም ፡ ጠፋን ፡፡
፲፬፡ በነገር ፡ የሚረዳን ፡ የለም ፡ በነሱ ፡ ሥራ ፡ ደከ
ምን ፡ በነሱ ፡ ሥራ ፡ ስንደክም ፡ ምንምን ፡
ተስፋ ፡ አላገኘንም ፡ በመከራውም ፡ ተጨንቀን ፡
ጠፋን ፡ አትበሏቸው ፡፡
፲፭፡ ከዛሬ ፡ ነገ ፡ ድኅነትን ፡ እናያ ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡
አደረግን ፡ ገዥ ፡ ልንሆን ፡ ተስፋ ፡ አደረግን ፡
ተገዥ ፡ ሆን ፡ ሥራውን ፡ ስንሠራ ፡ ደከምን ፡፡
፲፮፡ በደከምንበትም ፡ ድካም ፡ ላይ ፡ ግዳጃችንን ፡
አልጨረስንም ፡ ለኃጥአንም ፡ መብሎችን ፡ ሆን ፡
በደለኞች ፡ ሰዎችም ፡ አገዛዛቸውን ፡ አጸኑብን ፡፡
፲፯፡ እኛን ፡ የሚጠሉን ፡ እኛንም ፡ የሚወጉን ፡
ሰዎች ፡ በኛ ፡ ሠለጠኑብን ፡ ለሚጠሉንም ለጠ
ላቶቻችን ፡ አንገታችን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አደረግን ፡
እነሱ ፡ ግን ፡ አልራሩልንም ፡፡
፲፰፡ ከነሱ ፡ ሸሽተን ፡ ከመከራው ፡ ልናርፍ ፡ ወደ
ድን ፡ ከነሱም ፡ ሸሽተን ፡ የምንድንበት ፡ ቦታ ፡
አላገኘንም ፡፡
፲፱፡ በመከራውም ፡ ተይዘን ፡ በመላእክት ፡ ዘንድ ፡
ጠላቶቻችንን ፡ ከሠሥናቸው ፡ በሚጠሉን ፡ ጠላ
ቶቻችንም ፡ ላይ ፡ ጮህን ፡ ጩኸታችንን ፡
ግን ፡ አልሰሙንም ፡ ቃላችንንም ፡ ሊሰሙን ፡
አይወዱም ፡፡
፳፡ ለሚቀሙን ፡ ገንዘባችንንም ፡ የሚበሉብን ፡
ያሳነሱንን ጠላቶቻችንን ፡ ይረዷቸዋል ፡ ግፋ
ቸውንም ፡ ይሠውሩላቸዋል ፡ እንጂ ፡ ገንዘባች
ንን ፡ የሚበሉብን ፡ ሰዎች ፡ አገዛዛቸውን ፡ ከኛ ፡
አያጠፉልንም ፡፡
፳፩፡ በየሀገሩ ፡ ይበትኑናል ፡ ይገሉናል ፡ ሞታቸው
ንም ፡ ይሠውሩብናል ፡ እንጂ ፡ እጃቸውን ፡ እን
ዲያነሡ ፡ አላሰቡም ፡ አትበሏቸው ፡፡
፳፪፡ ጻድቃን ፡ የእናንተን ፡ ነገር ፡ በገናና ፡ ፈጣሪ ፡
በጌትነቱ ፡ ፊት ፡ ለበጎ ፡ ነገር ፡ መላእክት ፡ በሰ
ማይ ፡ እንዲያስቡት ፡ እነግራችኋለሁ ፡፡
፳፫፡ በገናና ፡ ፈጣሪ ፡ ጌትነቱ ፡ ፊት ፡ ስማችሁ ፡ ይጻ
ፋል ፡ በቀድሞው ፡ ዘመን ፡ በክፉ ፡ ነገር ፡ በድ
ካሙም ፡ ሁሉ ፡ ጉስቁላችኋልና ፡ ዋጋችሁን ፡
እንድታገኙ ፡ ተስፋ ፡ አድርጉ ፡፡
፳፬፡ አሁንም ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ብርሃን ፡ አብርታችሁ ፡
ትታያላችሁ ፡ የሰማይም ፡ ደጃፍ ፡ ይከፈትላች
ኋል ፡፡
ምስጋናችሁንም ፡ በሚገባ ፡ አመስግኑ ፡ መላእ ፳፭፡
ክት ፡ መከራችሁን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘባችሁን ፡ የሚ
ቀሟቸውን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይመራሉና ፡ ተድ
ላችሁ ፡ ደስታችሁ ፡ ይገለጣል ፡፡
እንደ ፡ መላእክት ፡ በሰማይ ፡ ታደርጓት ፡ ዘንድ ፡ ፳፮፡
ያላችሁ ፡ ብዙ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ እንድታደርጉ ፡
ተስፋ ፡ አድርጉ ፡ አለኝታችሁንም ፡ አትተው ፡
ጽኑ ፡ ፍርድ ፡ በሚደረግበት ፡ ቀን ፡ ትሠወሩ ፡
ዘንድ ፡ ይላችሁ ፡ አይደለም ፡፡
እንደ ፡ ኃጥአንም ፡ ሁናችሁ ፡ አትገኙ ፡ ከናን ፳፯፡
ተም ፡ የተነሣ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡
የዘላለም ፡ መቻያ ፡ ትደረጋለች ፡፡
አሁንም ፡ ጻድቃን ፡ ኃጥአንን ፡ ጸንተው ፡ በፈ ፳፰፡
ቃዳቸው ፡ ተዘጋጅተው ፡ ባያችኋቸው ፡ ጊዜ ፡
አትፍሩ ፡፡
ከሰማይ ፡ መላእክት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ትሆኑ ፡ ፳፱፡
ዘንድ ፡ አላችሁና ፡ እነሱ ፡ ከሚሠሩት ፡ ግፍ ፡
እራቁ ፡ እንጂ ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ የተባበራችሁን ፡
አትሁኑ ፡፡
እናንተ ፡ ኃጥአን ፡ መላእክት ፡ አይመረምሩ ፴፡
ንም ፡ ኃጢአታችንም ፡ ሁሉ ፡ አይጻፍብንም ፡
ትላላችሁና ፡ በየቀኑ ፡ የሠራችሁትንና ፡ ኃጢ
አታችሁን ፡ ሁሉ ፡ ይጽፉ ፡ ዘንድ ፡ አላቸው ፡፡
ጨለማና ፡ ብርሃን ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ ኃጢአታ ፴፩፡
ችሁን ፡ ሁሉ ፡ እንዲገልጡባችሁ ፡ አሁንም ፡
እኔ ፡ ገልጬ ፡ እነግራችኋለሁ ፡ ይህንንም ፡
በልቡናችሁ ፡ አትዘንጉ ፡ ሐሰትም ፡ አታድርጉ ፡፡
የቀናውን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ጥመት ፡ አትመልሱት ፡ ፴፪፡
የገነነ ፡ የከበረ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ነገር ፡
ሐሰት ፡ አታድርጉት ፡ ለጽኑ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ ሐሰታችሁም ፡ ሁሉ ፡ ዝንጋታችሁም ፡
ሁሉ ፡ እውነት ፡ አይደለችምና ፡ ጣዖታችሁን ፡
አታመስግኑት ፡፡
ብዙዎች ፡ ኃጥአን ፡ የቀናውን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ፴፫፡
ጥመት ፡ ፈጽመው ፡ እንዲመልሱት ፡ ዛሬም ፡
እኔ ፡ ይህንን ፡ ምሥጢር ፡ መርምሬ ፡ አውቀዋ
ለሁ ፡፡
ክፉዎችንም ፡ ነገሮችን ፡ ይናገራሉ ፡ ጽኑ ፡ ጽኑ ፡ ፴፬፡
ነገሮችንም ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ በሐሰት ፡ ይናገ
ራሉ ፡ በነገራቸውም ፡ ላይ ፡ የሐሰት ፡ መጻሮ
ችን ፡ ይጽፋሉ ፡፡
ነገር ፡ ግን ፡ ነገሮቼን ፡ ሁሉ ፡ በቀና ፡ ነገር ፡ በንደ ፴፭፡
በቶቻቸው ፡ ሊጽፉ ፡ ላይለውጡ ፡ አስቀድሚ ፡
ስለነሳቸው ፡ ያዳኝሁባቸውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
በቀና ፡ ነገር ፡ ይጽፉት ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ፡ ነገሮቼ
ንም ፡ ባያሳንሱ ፡ በተገባ ፡ ነበር ፡፡
ለደጋግ ፡ ሰዎች ፡ ላዋቆችም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ፴፮፡
ብዙ ፡ ጥበብና ፡ የቀና ፡ ነገርም ፡ ሊሆናቸው ፡
መጻሕፍት ፡ ይሰጧቸዋልና ፡ ለኃጥአንም ፡ ይገለ
ጡላቸዋልና ፡ ሌላ ፡ ምሥጢርንም ፡ አውቃለሁ ፡፡
እነሱ ፡ ያምኑባቸዋል ፡ በነሱም ፡ ደስ ፡ ይላቸ ፴፯፡
ዋል ፡ ከነሱ ፡ ይልቅ ፡ የቀና ፡ ነገር ፡ ያለባቸው ፡

ሕጎችን ፡ ሁሉ ፡ ያወቁ ፡ ጻድቃንም ፡ ሁሉ ፡
ዋጋቸውን ፡ ያገኛሉ ።
፴፫ በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላሉ ፡
ሰዎች ፡ ጥበባቸውን ፡ ያስተምሩዋቸው ፡ ዘንድ ፡
ጌታ ፡ አሰሟቸው ፡ አለ ።
፴፬ እናንተ ፡ መምሮቻቸው ፡ ናችሁና ፡ የመምርነ
ታችሁንም ፡ ዋጋ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ታገኛላች
ሁና ፡ አስተምሯቸው ፡ አለ ።
፵ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳሉ ፡ በቀና ፡ ሥራዎች ፡
ልጄና ፡ እኔ ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ለዘላለሙ ፡ አንድ ፡
እንሆናለንና ፡ አስተምሯቸው ፡ ፍቅር ፡ አንድ
ነትም ፡ ይደረግላችኋልና ፡ በውነት ፡ የቀና ፡
ሕጉንም ፡ የምትጠብቁ ፡ ሰዎች ፡ ደስ ፡ ይበላ
ችሁ ፡ አለ ።

ምዕራፍ ፡ ፵፩ ።

፩ ከብዙ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ልጁ ፡ ማቱሳላ ፡ ልጁ ፡
ላሜህን ፡ ሚስት ፡ አጋባው ፡ ከሱም ፡ ፀንሳ ፡
ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ።
፪ ሰውነቱም ፡ እንደ ፡ ዕንቍ ፡ ነጭ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡
ጽጌ ፡ ረዳም ፡ ቀይ ፡ ነው ፡ የራሱም ፡ ጠጕር ፡
እንደ ፡ ነጭ ፡ ብዝት ፡ ነው ፡ የተሸራሺ ፡ ነው ፡
ዓይኖቹም ፡ ያማሩ ፡ ናቸው ።
፫ ዓይኖቹንም ፡ በገለጠ ፡ ጊዜ ፡ ቤቱን ፡ ሁሉ ፡
እንደ ፡ ፀሐይ ፡ አበራ ፡ ቤቱም ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡
በራ ፡ ከዋላጂቱም ፡ እጅ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ነገር ፡
ጀመረ ፡ የቸርነት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስ
ጋናን ፡ ተናገረ ።
፬ ከሱም ፡ የተነሣ ፡ አባቱ ፡ ላሜህ ፡ ፈርቶ ፡ ሸሸ ፡
ወዳባቱ ፡ ወደ ፡ ማቱሳላም ፡ መጣ ፡ እኔ ፡ ልውጥ ፡
ልጅ ፡ ወለድሁ ፡ እንደ ፡ ሰውም ፡ አይደለም ።
፭ የሰማይ ፡ መላእክት ፡ ልጆቹንም ፡ ይመስላል ፡
ፍጥረቱም ፡ ልዩ ፡ ናት ፡ እንደኛም ፡ አይደለም ፡
ዓይኖቹም ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ እግሮች ፡ ናቸው ፡
ፊቱም ፡ የበራ ፡ ነው ፡ አለ ።
፮ ከመላእክት ፡ የተወለደ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከኔስ ፡
ያልተወለደ ፡ ይመስለኛል ፡ እኔስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
በሱ ፡ ዘመን ፡ ድንቅ ፡ ሥራ ፡ እንዳይሠራ ፡ ብዬ ፡
እፈራለሁ ።
፯ መኖሪያው ፡ ከመላእክት ፡ ጋራ ፡ ነውና ፡ ወዳባ
ታችን ፡ ወደ ፡ ሄኖክ ፡ ትሔድ ፡ ዘንድ ፡ ከሱም ፡
እውነቱን ፡ ነገር ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ አሁንም ፡
አባቴ ፡ ፈጽሜ ፡ እለምንሀ ፡ ዘንድ ፡ አለሁ ፡
፰ ማቱሳላም ፡ የልጁን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡
በዚያ ፡ እንዳለሁ ፡ ሰምቷልና ፡ ጮኸ ፡ እኔም ፡
ቃሉን ፡ ሰማሁት ፡ አለ ።
፱ ወደሱም ፡ መጣሁ ፡ ወደኔ ፡ መጥተሃልና ፡ ልጄ ፡
እነሆ ፡ አለሁ ፡ አልኩት ።
፲ ስለ ፡ ታላቁ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ቀረብሁበት ፡ ስለ ፡
ጭንቅ ፡ ራእይም ፡ ወዳንተ ፡ መጣሁ ፡ ብሎ ፡
መለሰልኝ ።
፲፩ መልኩ ፡ ፍጥረቱም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ፍጥረት ፡
ያልሆነ ፡ መልኩም ፡ ከዕንቍ ፡ ይልቅ ፡ የሚነጣ ፡
ከጽጌ ፡ ረዳም ፡ የሚቀላ ፡ የራሱም ፡ ጠጕር ፡
ከብዝት ፡ ይልቅ ፡ የሚነጣ ፡ ዓይኖቹም ፡ እንደ ፡
ፀሐይ ፡ እግር ፡ የሚያበሩ ፡ ልጅ ፡ ለልጄ ፡ ለላ
ሜህ ፡ ተወልዷልና ፡ አባቴ ፡ አሁንም ፡ ስማኝ ።
ዓይኖቹንም ፡ በገለጠ ፡ ጊዜ ፡ ቤቱን ፡ ሁሉ ፡ አበራ ፡ ፲፪
ከዋላጅቱም ፡ እጅ ፡ ተነሥቶ ፡ አፉንም ፡ ከፍቶ ፡
የሰማይ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገነው ።
አባቱ ፡ ልጄ ፡ ላሜህም ፡ ፈርቶ ፡ ወደኔ ፡ ሸሸ ፡ ፲፫
ከሰማይ ፡ መላእክት ፡ የተወለደ ፡ አስመሰለው ፡
እንጂ ፡ እሱ ፡ ከሱ ፡ እንደተወለደ ፡ አላመነም ።
እውነቱን ፡ ትነግረኝ ፡ ዘንድ ፡ እነሆ ፡ እኔ ፡ ወዳ ፲፬
ንተ ፡ መጣሁ ።
እኔም ፡ ሄኖክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ፲፭
ይሠራል ፡ ብዬ ፡ የሱን ፡ ነገር ፡ ተናገርሁ ፡ ያባቴ ፡
የያሬድ ፡ የልጁ ፡ ወገኖች ፡ ከሰማይ ፡ በላይ ፡
ያለ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕጉን ፡ አፍርሰዋልና ፡
ይህንን ፡ በራዕይ ፡ ፈጽሜ ፡ አይቼ ፡ ነገርሁህ ፡
አለው ።
እነሆ ፡ ኃጢአትንም ፡ ይሠራሉ ፡ ሥራቱንም ፡ ፲፮
ያፈርሳሉ ፡ ከሴቶችም ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆኑ ፡
ከነሱም ፡ ጋር ፡ ኃጢአትን ፡ ይሠራሉ ፡ ከነሱም ፡
ሚስቶችን ፡ አግብተው ፡ ከነሱ ፡ ልጆችን ፡
ወለዱ ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ጽኑ ፡ ጥፋት ፡
ይደረጋል ።
ጥፋት ፡ ያለበት ፡ ውሀ ፡ ይወርዳል ፡ ታላቁም ፡ ፲፯
ጥፋት ፡ በንዱ ፡ ዓመት ፡ ይደረጋል ፡ ለናንተ ፡
የተወለደ ፡ ልጅ ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
እሱ ፡ ብቻ ፡ ይቀራል ፡ ሦስቱም ፡ ልጆቹ ፡ ከሱ ፡
ጋራ ፡ ከማየ ፡ አይህ ፡ ይድናሉ ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሞተ ፡ ፲፰
ጊዜ ፡ እሱ ፡ ይድናል ፡ ልጆቹም ፡ አርበኞች ፡
ሰዎችን ፡ ይወልዳሉ ፡ እነዚህም ፡ ሥጋውያን ፡
ናቸው ፡ እንጂ ፡ መንፈሳውያን ፡ አይደሉም ።
ጽኑ ፡ መቅሠፍትም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይደረጋል ፡ ፲፱
ምድርም ፡ ከኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ትነጻለች ።
አሁንም ፡ ይህ ፡ የተወለደ ፡ ልጅ ፡ በእውነት ፡ ፳
የሱ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለልጅህ ፡ ለላሜህ ፡
ንገረው ፡ እሱ ፡ ከጥፋት ፡ የቀረ ፡ ይሆንላችኋ
ልና ፡ ስሙንም ፡ ኖኅ ፡ ብለህ ፡ ጥራው ፡ በሱ ፡
ዘመን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ትጨረስ ፡ ዘንድ ፡ ካላት ፡
በደል ፡ ሁሉና ፡ ከኃጢአትም ፡ ሁሉ ፡ የተነሣ ፡
ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ከምትመጣ ፡ ጥፋት ፡ ልጆ
ቹና ፡ እሱ ፡ ይድናሉ ፡ መላእክት ፡ ያወቋቸውን ፡
ምሥጢሮች ፡ አውቃለሁና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ አስቀድማ ፡ ከተጨረሰችው ፡
ኃጢአት ፡ ይልቅ ፡ ፈጽማ ፡ የምትበልጥ ፡ ግፍ ፡
ትደረጋለች ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገልጦልኛ
ልና ፡ ነግሮኛልና ፡ በሰማይ ፡ ሰሌዳነት ፡ የተጻፈ
ውን ፡ አወቅሁ ፡ አነበብሁ ።
ሕጉን ፡ የምትጠብቅ ፡ ልጅ ፡ (አብርሃም ፡ ) እስክ ፳፩
ትነሣ ፡ ድረስ ፡ አንዲቱ ፡ ልጅ ፡ ካንዲቱ ፡ ልጅ ፡
ይልቅ ፡ አብልጣ ፡ ትበድላለችና ፡ በነሱ ፡ የተጻ
ፈውን ፡ አየሁ ፡ በደል ፡ ትጠፋለች ፡ ኃጢአ
ትም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከሰው ፡ ትርቃለች ፡ በጎ
ውም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በሷ ፡ ይመጣል ፡ ይህ ፡ የተ

ወለደ ፡ ልጅ ፡ በውነት ፡ የሱ ፡ ልጅ ፡ ነውና ፡
ሐሰትም ፡ አይደለምና ፡ አሁንም ፡ ልጄ ፡ ሂደህ ፡
ለልጅህ ፡ ለላሜህ ፡ ንገረው ፡ ማቱሳላም ፡ ያባቱ ፡
የሄኖክን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡
በስውር ፡ ገልጦለታልና ፡ ነገሩን ፡ ሰምቶ ፡ ተመ
ለሰ ።
፳፱ ከጥፋቷ ፡ ሁሉ ፡ አድኖ ፡ ምድርን ፡ ደስ ፡ ያሰኘ
ታልና ፡ የዚያን ፡ የልጅ ፡ ስሙን ፡ ኖኅ ፡ አለው ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፪ ።

፩ ለልጄ ፡ ለማቱሳላ ፡ ከሱም ፡ በኋላ ፡ ለሚ
መጡ ፡ ሰዎች ፡ በኋላ ፡ ዘመንም ፡ ሥራቱን ፡
ለሚጠብቁ ፡ ሰዎች ፡ ሄኖክ ፡ የጻፈው ፡ ሁለተኛ ፡
መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ።
፪ ክፉውን ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ እስቲጨ
ረሱ ፡ ድረስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የበደሉ ፡ ሰዎ
ችም ፡ ሥራዊት ፡ እስቲጨረስ ፡ ይህንን ፡ የሥራ
ችሁ ፡ እናንተ ፡ በነዚህ ፡ ወራቶች ፡ ትቆያላችሁ ።
፫ ስማቸው ፡ ከጻድቃን ፡ ቍጥር ፡ ይፋቅ ፡ ዘንድ ፡
አለውና ፡ ልጃቸውም ፡ ለዘላለሙ ፡ ይጠፋልና ፡
እናንተ ፡ ግን ፡ በኃጢአት ፡ የመጣው ፡ መከራ ፡
እስቲያልፍ ፡ ድረስ ፡ ደጅ ፡ ጥኑ ፡ ልጆቻቸውም ፡
ይሞታሉ ፡ በማይታይም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ቦታ ፡
ሁነው ፡ ጩኸው ፡ ያለቅሳሉ ፡ በዚያም ፡ ቦታ ፡
ምድር ፡ የለምና ፡ በገሃነም ፡ ይቃጠላሉ ። ከጥ
ልቅነቱ ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ማየትን ፡ አልቻ
ልሁምና ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ እንደማይታይ ፡ ደመና ፡
ያለ ፡ አየሁ ።
፬ የእሳቱንም ፡ ዋዕዩ ፡ ሲነድ ፡ አየሁት ፡ ይኸውም ፡
የሚያስፈራ ፡ ነው ፡ እንደሚያስፈሩ ፡ ተራሮ
ችም ፡ በእሳት ፡ ተከበዋል ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡
እያሉ ፡ ይተዋወካሉ ።
፭ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ካሉ ፡ ከሰባቱ ፡ ሊቃነ ፡ መላእክት ፡
አንዱን ፡ መልአክ ፡ ብቻውን ፡ የሚነድ ፡ የእሳት ፡
ዋዕይ ፡ የልቅሶም ፡ ቃል ፡ የፍጹም ፡ ጩኸት ፡
የጽኑ ፡ መከራ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰማይ ፡ አይ
ደለምና ፡ ይህ ፡ የሚያስፈራ ፡ ቦታ ፡ ምንድነው ፡
ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።
፮ ይህ ፡ የምታየው ፡ ቦታ ፡ የተነቀፉ ፡ ሰዎችና ፡
የኃጥአን ፡ ልጆች ፡ ኃጢአትንም ፡ የሚሠሩ ፡
ሰዎች ።
፯ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ያላቸው ፡ በነቢ
ያት ፡ አንደበት ፡ እግዚአብሔር ፡ ያናገረውን ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ ወዳለመሆን ፡ የሚመልሱ ፡ ሰዎ
ችም ፡ በዚያ ፡ ይወድቃሉ ፡ አለኝ ።
፰ መላእክት ፡ ያነበቹው ፡ ዘንድ ፡ ለተዋረዱ ፡ ልጆ
ችና ፡ ለኃጥአን ፡ ይደርስባቸው ፡ ዘንድ ፡ ያለው
ንም ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ከነሳቸው ፡ ወገን ፡ በሰ
ማይ ፡ የተጻፉ ፡ አሉና ፡ በዚያ ፡ ይወድቃሉ ፡
አለኝ ።
ሥጋቸውን ፡ መከራ ፡ ያስቻሉ ፡ በፈጣሪያቸ ፱
ውም ፡ አምነው ፡ መከራ ፡ የተቀበሉ ፡ በክፉ ፡
ሰዎችም ፡ የተነሣ ፡ የጐሰቈሉ ፡ ፈጣሪያቸው
ንም ፡ የወደዱ ፡ ሰዎች ፡ ብርና ፡ ወርቅን ፡ አይ
ወዱም ። ሥጋቸውን ፡ ለመከራ ፡ የሰጡ ፡ ራሳቸ
ውን ፡ እንደ ፡ ሞተች ፡ ሰውነት ፡ አደረጉ ፡ እንጂ ፡
ከተፈጠሩ ፡ ጀምሮ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ መብ
ሎችንም ፡ ያልወደዱ ፡ ሰዎች ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡
ሹመት ፡ ሽልማት ፡ አልወደዱም ። ይህንንም ፡
አስተዋሉ ፡ ጌታም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስሙን ፡ ያመ
ሰግኑ ፡ ዘንድ ፡ ፈተናቸው ፡ ሰውነቶቻቸውም ፡
በንጽሕና ፡ ተገኙ ።
የቀረውንም ፡ ሥጋቸውን ፡ ሁሉ ፡ በመጻፎች ፡ ፲
ተናገርኩ ፡ እሊህ ፡ ከሕፃንነታቸው ፡ ጀምሮ ፡
ዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ሰማያዊ ፡ ሕጉን ፡
ሲወዱት ።
ለክፉፉ ፡ ሰዎችም ፡ መከራ ፡ ሲቀበሉ ፡ ከነሳቸ ፲፩
ውም ፡ ተግዳሮትን ፡ ስድብንም ፡ ሲሰሙ ፡ እኔ
ንም ፡ ሊያመሰግኑኝ ፡ ጐስቍለዋልና ፡ ለየራሳ
ቸው ፡ ዋጋቸውን ፡ ስጣቸው ።
አሁንም ፡ እውቀት ፡ ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ የተወ ፲፪
ለዱ ፡ ደጎች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ነፍሳቸውን ፡ እጠ
ራለሁ ፡ ለሃይማኖታቸው ፡ እንደሚገባቸው ፡
መጠን ፡ በሥጋቸው ፡ ክብርን ፡ ያላገኙ ፡ በመ
ከራ ፡ ከክርስቶስ ፡ ለተወለዱ ፡ ለጻድቃን ፡ መከ
ራቸውን ፡ እለውጥላቸዋለሁ ።
የከበረ ፡ ስሜን ፡ የወደዱትን ፡ ሰዎችንም ፡ በበራ ፡ ፲፫
ብርሃን ፡ ከገሃነም ፡ አወጣቸዋለሁ ። አንዱንም ፡
አንዱንም ፡ በከበረ ፡ በክብር ፡ ዙፋን ፡ አኖረ
ዋለሁ ፡ የፈጣሪ ፡ ፍርዱ ፡ እውነት ፡ ነውና ፡
ቍጥር ፡ በሌላቸው ፡ ዘመኖችም ፡ ያበራሉ ።
በቀኑ ፡ ሥራዎች ፡ በሚገኝ ፡ በመንግሥተ ፡ ፲፬
ሰማይ ፡ ለታመኑ ፡ ሰዎች ፡ የሃይማኖታቸውን ፡
ዋጋ ፡ ይሰጣቸዋልና ።
በብርሃን ፡ ሲያበሩ ፡ ሲያመሰግኑም ፡ ጻድቃን ፡ ፲፭
በድንቁርና ፡ ከዲያብሎስ ፡ የተወለዱ ፡ ኃጥአ
ንን ፡ በገሃነም ፡ ሲወድቁ ፡ ያይዋቸዋል ፡ ኃጥአ
ንም ፡ ጻድቃንን ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ሲያ
በሩ ፡ ያይዋቸዋል ።
እነሱም ፡ በተጻፈላቸው ፡ ዘመኖችና ፡ ቀኖች ፡ ፲፮
ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለዘለዓ
ለሙ ፡ በውነት ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡
ሄኖክ ፡ ተሠውሮ ፡ ያየው ፡ በዚህ ፡ መላ ፡ ተፈ
ጸመ ።